# የደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር

# የአሥር ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ




## (ከ2013-2022 በጀት ዓመት)

ፕላንና ልማት ቡድን

ታህሳስ /2015

ደሴ

# Contents

1.መግቢያ ....5

3. የኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ እንደ መነሻ....11

4. የማህበራዊ ልማት ዘርፍ እንደ መነሻ....23

5. መሰረተ ልማት ዘርፍ እንደ መነሻ....29

6. መልካም አስተዳደር ዘርፍ እንደ መነሻ....32

7. የነበሩ ጥቅል ተግዳሮቶች ....36

8. የ10 አመቱ እቅድ....38

8.1 የልማት እቅዱ መነሻ ሀሳቦች....38

8.2. የልማት መሪ እቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች ....39

8.2.1. ጥራት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥ ....39

8.2.2. የሴቶችንና የወጣቶችን ተሳትፎ፣ ተጠቃሚነትና ብቃት ማሳደግ ....41

8.2.3. ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት ....41

8.2.4. የዞኑን አቅም መሠረት ያደረገ ቀልጣፋ ኢኮኖሚ መገንባት ....42

9. የ10 ዓመቱ መሪ የልማት እቅድ የትኩረት መስኮች....43

9.1. ብዝሃ ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮች ልማት ላይ ማተኮር....43

9.2. የዘመናዊ ግብርና ልማት ....43

9.3. የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ....44

9.4. የማዕድን ሀብት ልማት ....44

9.5. የቱሪዝም ልማት....44

9.6. የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ....45

9.7. ዘላቂ የከተማ ልማት ....45

9.8. መሠረተ ልማት....45

9.9. የሰው ኃብት ልማትና የስነ ህዝብ ትሩፋት ....46
9.10. ስነ-ህዝብ ልማት ....47
9.11. ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ ....47
10. የኢኮኖሚ ልማት አርፍ ....48
10.1. ግብርና ልማት....48
10.2. እንስሳትና አሳ ሃብት ....65
10.3. አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና....72
10.4. ህብረት ስራ ማህበራት....74
10.5. መሬት....81
10.6. ስራና ስልጠና ....87
10.7. ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት....99
10.9. ባህል ቱሪዝም....111
11. ማህበራዊ ልማት ዘርፍ....114
11.1. ትምህርት....114
11.3. ሴቶች ህጻናት ....120
11.4. ወጣትና ስፖርት ....123
12. መሰረተ ልማት ዘርፍ....125
12.1. መንገድ ....125
12.2. ዉሃና ኢነርጂ ልማት ....126
12.3. ከተማና መሰረተ ልማት ....130
13. መልካም አስተዳደር ዘርፍ....132
13.1. ሲቪል ሰርቪስ....132
13.2. ዐቃቢ ህግ ....134
13.3.ህዝብ ቅሬታ ....140

13.5. ሰለምና ደህንነት ....................................................................................................141

13.5. መንግስት ኮሙኒኬሽን ..........................................................................................143

13.1. ገንዘብ መምሪያ.................................................................................................145

13.ገቢ አሰባሰብ........................................................................................................146


# 1.መግቢያ

ደቡብ ወሎ ያለውን ዕምቅ አቅም መሠረት በማድረግ የሚታዩ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን በመቅረፍ ወደ ሚፈለገው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥና የዕድገት ከፍታ ለመድረስ የሚያስችል ከ2013-2022 በጀት ዓመት የሚዘልቅ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ረቂቅ በመዘጋጀት ላይ የነበረ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ሳይጠናቀቅ ቀርቷል፡፡ ባለፉት ሁለት ዓመታት የኮቪድ ወረርሽኝና በአሸባሪው የትግራይ ወራሪ ሀይል ምክንያት በዞናችን ከፍተኛ የሰብዓዊ፣ ቁሳዊና ስነልቦናዊ ቀውስ አስከትሏል፡፡ ይህም በጥናቱ መሠረት ወደ 128 ቢሊየን ብር የሚደርስ ውድመት አድርሷል፡፡ ድምር ውጤቱም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን በከፍተኛ ደረጃ ጉዳት ያደረሰና ኢኮኖሚው የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅሙም ዝቅ እንዳደረገው የሚታወቅ ነው፡፡ በሌላ በኩል በተለይ ከጦርነቱ በኋላ በህዝቡና በአመራሩ ከፍተኛ ቁጭትና መነሳሳት መፈጠሩ፣ የፌደራል መንግስቱም ሆነ ክልሉ ዞኑን በተለያየ መንገድ ድጋፍየማድረግ እንቅስቃሴ የሚጠናከር መሆኑ፣ እንዲሁም ዲያስፖራውም የሚያደርገውን ድጋፍ በከፍተኛ ሁኔታ የሚያሳድግ መሆኑ ታሳቢ ከተደረገ የወደሙ ተቋማት ወደነበሩበት እንዲመለሱ ከማድረግና ወደኋላ የቀረውን የልማት እንቅስቃሴ ከማካካስ ባሻገር በመሪ ዕቅዱ ከተቀመጡ ግቦች በላይ ስኬት ለማስመዝገብ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ነው፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት 2 ዓመታት የነበሩ ነባራዊ ሁኔታዎችን በመተንተንና የአጠቃላይ ዕቅዱ የግምገማ አካል በማድረግ እና ያላሳካናቸውን እና ወደ ኋላ ያስቀሩን ጉዳዮችን በመለየት በቀጣይ 8 ዓመታት ለማካካስና ከዚያ በላይ ውጤት ማስመዝገብን ታሳቢ ያደረገ ዕቅድ ለማዘጋጀት ተሞክሯል፡፡
በአጠቃላይ ይህ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ሰነድ በውስጡ የዞኑን የልማት እምቅ አቅሞች ትንተና፣ በኢኮኖሚው ፣ በማህበራዊ ፣ በመሰረተ-ልማትና በመልካም አስተዳደር ዘርፍ የነበረው አፈጻጸም፣ዞናዊ ርዕይ፣ የዕቅዱን መነሻዎች፣ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የትኩረት መስኮች እና የዕቅዱን ልዩ ባህሪያት እንዲያካትት ተደርጎ ጠቅለል ባለ መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. የዞኑ የመልማት አቅሞች

ደቡብ ወሎ ለሁሉም አይነት የኢኮኖሚ ዘርፎች ልማት ምቹ የሆነ ከሞላ ጎደል ሁሉም አይነት መሠረታዊ የተፈጥሮ ሀብት አቅሞች ያሉት ነው፡፡ በመሆኑም በዞኑ ያሉትን እምቅ የልማት አቅሞች ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ በመለየትና በማልማት በብዛት ያለውን ሀብት በስፋት ተጠቅሞ የዞኑን ኢኮኖሚ ማሳደግ ያስችላል፡፡ ከዚህ አኳያ ዞኑ በብዙ እምቅ ሀብቶች ተነጻጻሪ ጠቀሜታ/Comparative Advantage/ ያለው በመሆኑ ያሉትን ጸጋዎች በአግባቡ በማወቅ ለልማት ማዋልና ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትና የህዝቡን የልማት ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ እምቅ አቅሞች በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡


**የአየር ንብረት፡-** በቀጠናው 87 ከመቶው አካባቢ የሚሆነው ከ900 -2000 ሚ.ሜ ዝናብ የሚያገኝ ሲሆን የሁለት የርጥበት ወቅቶች የመህርና በልግ አብቃያ ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ በመሆኑ በአብዛሀኛው አካባቢ በአመት ሁለት ጊዜ ሰብል ማምረት ይችላል፡፡ የዞኑ ዝቅተኛው የሙቀት መጠን 11.2 ዲግሪ ሴሊሺየስ ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 22.2 ዲግሪ ሴሊሺየስ ነው፡፡ ዞኑ በ 5 አይነት የአየር ንብረት ቀጠናዎች የተከፋፈለ ሲሆን እነሱም ውርጭ (1.2 በመቶ)፣ ደጋ (35.2 በመቶ)፣ ወይና ደጋ (54.4 በመቶ) ቆላ (9.2 በመቶ) ናቸው፡፡ በመሆኑም ዞኑ ከበርሃ የአየር ንብረት ባሻገር ሁሉንም የአየር ንብረቶች የያዘ መሆኑ በግብርና ምርት እና በእንስሳት ሃብት ልማት ብልጫ ማምጣት የሚችል እንደሆነ ያመላክታል፡፡




ምስል 1. የደቡብ ወሎ ዞን የአየር ንብረት የሚያሳይ ካርታ

**የእንስሳት ሀብት፡-** እንደሚታወቀዉ ሀገራችን ኢትዩጲያ በእንስሳት ሃብት ብዛት ከአለም 10ኛ ከአፍሪካ ደግሞ 1ኛ ደረጃን ትይዛለች፡፡ አማራ ክልል ከፍተኛ የእንስሳት ሃብት ካላቸዉ ክልሎች ዉስጥ አንዱ ሲሆን፣ በክልሉ ዉስጥ በጥቀሉ 53,514,348 የሚሆኑ እንስሳት ይገኛሉ፣ ከዚህ ዉስጥ በደቡብ ወሎ የሚገኙት ጠቅላላ የእንስሳት ብዛት 5,672,521 ሲሆኑ የክልሉን (10.6%) ነዉ፡፡ ሆኖም በዞኑ ካለዉ ሰፊ የእንስሳት ሃብት አንጻር ዘርፉ ገና ያልተነካ እና ብዙ መስራት እንሰሚጠበቅ ሳያል፡፡

**የማዕድን ሀብት፡-** በዞኑ ያለ የማዕድን ሀብት ላይምስቶን፣ ጂፕሰም፣ድንጋይ ከሰል፣ ሲልካ ሳንድ፣ ክሌይ፣ ኦፓል፣ነዳጅ፣ አምበር እና ጃስፐር ያሉ የከበሩ ማዕድናት ይገኛሉ፡፡ የድንጋይ ከሠል በውጫሌ 3.3 ሚሊየን ቶን እና በላይ የክምችት መጠን እንዳለ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ይህ ደግሞ ኢኮኖሚውን በማሳደግም ሆነ ሰፊውን ስራ ፈላጊ ወጣት በከፍተኛ ደረጃ ችግሩን ሊቀርፍ የሚችል ዘርፍ ነው፡፡





ምስል 2. በደቡብ ወሎ ዞን የማዕድን ሃብት የሚያሳይ የናሙና ምስል

**የመሬት ሀብት፡-** የዞኑ የመሬት አቀማመጥ በአብዛኛው ተራራማና ሸለቋማ እንድሁም ወጣ ገባ የበዛበት መሆኑ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ስለሆነም ተራራማና ሸለቋማ አካባቢዎችን አትክልትና ፍራፍሬ እና ደን በማልማት የስራ ዕድል ከመፍጠርና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም

ከማግኘትና የአካባቢውን የአየር ንብረት ከመጠበቅ ባለፈ ከተራራው በታች የሚገኙ አካባቢዎችን ከአፈር መሸርሸር ለመጠበቅ እና የወሃ መገኛ ዕድሎችን ለማስፋት ያስችላል፡፡ በተጨማሪም ሜዳማ አካባቢዎችን ለእርሻ አገልግሎት ለማዋል እድል ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል ሰንሰለታማ ተራሮች የብዝሃ ሀብታቸውን በመጠበቅ የቱሪስት መስህብ ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉበት ሠፊ ዕድል ያለ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ዞኑ 1,855,890 ሄ/ር የቆዳ ስፋት ውስጥ ለእርሻ አገልግሎት መስጠት የሚችለው 543,728ሄ/ር፡፡

አካባቢውም እንደ ጤፍ፣ ገብስና ስንዴ የብርዕ ሰብሎችን፣ ማሽላ ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ምስር እና ሽንብራ ያሉትን ሰብሎች በስፋት የማምረት አቅም አለው፡፡ በሌላ በኩል ግን እስካሁን የተሠራው የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራ በቂ ባለመሆኑ ይልቁንም በደን መመንጠርና ያልተገባ የመሬት አያያዝ ምክንያት ሠፊ የአፈር መሸርሸር በዞናችን እየታየ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በሚቀንስ ምርታማነት እንደ አገርም ሆነ እንደ አካባቢያችን ከሚገኘው ጥቅል ምርት ቀላል የማይባል ድርሻ በየዓመቱ እየታጣ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በአርሶ አደር ደረጃም የመሬት ምርታማነት መቀነስ ለገቢ ዝቅ ማለትና ለምግብ ዋስትና መታጣት ችግር የሚዳርግ ሆኗል፡፡ ከዚህም አልፎ ለብዝሃ ህይወት መመናመን፣ በውሃ ሚዛን መዛባት ምክንያት የከርሰምድር ውሃ መቀነስና በዚህም ለመጠጥና ለመስኖ የሚሆን ውሃ እጥረት መከሰት፣ በደለል ምክንያት በየወረዳዎች ያሉ አነስተኛ ግድቦችና በዞናችን ውስጥበሚገኙ ሀይቆች የአገልግሎት ጊዜ ማጠር፣ የመሳሰሉት ዘርፈ ብዙ ችግሮች የሚያስከትል ስለሆነ ተራሮችን አረንጓዴ በማልበስ እና በመሳሰሉት የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ ዘዴዎች መሬትን ዘላቂ ጥቅም ሊሰጥ በሚያስችል መልኩ መጠበቅና ማልማት የግድ ይላል፡፡



ምስል 3. የደቡብ ወሎ ዞን የምርት ወቅቶችን እና የመሬት አቀማመጥን የሚያሳይ ካርታ

## የቱሪዝም ሃብት


ደቡብ ወሎ ዓይነተ ብዙ የታሪክ፣ የባህልና የተፈጥሮ መዳረሻዎች (የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ሃብቶች) ያሉት አካባቢ ነው፡፡ የወሎ ተቻችሎ በጋራ የመኖር እሴትና ጥበብ ለሃገረ-መንግስት ግንባታ ከፍተኛ ድርሻ ሊያበረክት እንደሚችል ይገመታል፡፡ ምንም እንኳን ዞናችን በርካታ የቱሪዝም ሃብቶች ቢኖሩትም ከዘርፉ የሚፈለገውን ያህል ጥቅም እያገኘ አይደለም፡፡ ስለሆነም በዘርፉ በእውቀት፣ በክህሎት እና በአደረጃጀት የተቃኘ አገልግሎት ስርዓት መዘርጋትና ማሻሻል ይገባል፡፡

## የዉሃ ሃብት፡-

በደቡብ ወሎ በርካታ የዉሃ ሃብቶች ያሉ ሲሆን በዞኑ አብዘሃኛዉን የዉሃ ተፋሰስ ወይም ወንዞችን የሚሸፍነዉ የአባይ ተፋሰስ ነዉ፡፡ በተጨማሪም በምስራቁ የዞኑ ክፍል የአዋሽ ተፋሰስ ወንዞች በብዛት ይገኛሉ፡፡ በዞኑ 3 ሰፋፊ ሃይቆች የሚገኙ ሲሆን እነርሱም ሎጎ ሃይቅ፣አርርዲቦ ሃይቅና ማይባር ሃይቅ ናቸዉ፡፡ በዞኑ የሚገኙ ወንዞች አብዘሃኞቹ አመቱን ሙሉ የሚፈሱና ሰፊ የከርሰ-ምድር ውኃ እንደሚገኝ ጥናቶች የሚያመላክቱ ሲሆን ካለዉ የዉሃ ሃብት አንጻር የንጹህ መጠጥ ዉሃ አቅርቦት እና የመስኖ እርሻ እንቅስቃሴ በጣም አናሳ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡



ምስል 4. የደቡብ ወሎ ዞን የዉሃ ተፋሰስን የሚያሳይ ካርታ





ምስል 5. የደቡብ ወሎ ዞን የንጹህ መጠጥ ዉሃ አቅርቦትን የሚያሳይ ግራፍ

**አምራች ሰብዓዊ ሀብት፡-** የዞኑ ህዝብ ቁጥር ሲታይ ትልቅ የልማት አቅም ሊሆን የሚችል ሀይል ነው፡፡ ዞኑ ወጣት የሚበዛበት 50 በመቶ የሚሆነውን ይይዛል፡፡ ይህ ሀይል ትኩስ ሀይልና የልማት አልፋና ኦሜጋ የኢኮኖሚው ወሳኝ አካል ሊሆን የሚችል ነው፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን ዞኑ የቀጣይ የስነ ህዝብ ትሩፋት ተጋሪ በመሆኑ ይህም እንደ አንድ የእድገት አቅም ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ከዚህ አንፃር ሰብዓዊ ሀብት ልማት በአንድ በኩል የልማት ጥረት ውጤት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለልማት ወሳኝ ግብዓት ነው፡፡

በትምህርትና በጤና ዙሪያ እስከአሁን የተገነቡ አቅሞች ለተሻለ የሰብዓዊ ካፒታል ትልቅ አቅሞች ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ የህዝብ ቁጥር ብቻውን ለዕድገት ዋስትና ሊሆን እንደማይችል ተገንዝቦ ይልቁንም የህዝቡን እውቀት በማሳደግ፣ ክህሎቱን በማሻሻል እና አመለካከቱን በማስተካከል የማምረት አቅሙን ማሳደግ ለልማት መረጋገጥ ወሳኝ ጉዳይ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በሌላ በኩል በአምራች የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ከአጠቃላዩ ህዝብ ጋር ሲነጻፀር ሠፊ ስለሆነ ይህን ዕድል ወይም ትሩፋት በአግባቡ መጠቀምና ልማትን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡

በአጠቃላይ በትምህርትና በጤና ሴክተር የተጀመሩትን ስራዎች አጠናክሮ በማስቀጠል ተወዳዳሪና የማምረት አቅሙ ያደገ ሰብዓዊ ሀብት የመገንባት ስራውን በቀጣይ የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡




ምስል 6. የደቡብ ወሎ ዞን የህዝብ እድገት የሚያሳይ ግራፍ

## 3. የኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ እንደ መነሻ

### ግብርና

በዞናችን በኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ ግብርና ዋናዉ የኢኮኖሚችን ምንጭ እንደመሆኑ መጠን ባለፉት አስር አመታት በግብርናዉ ዘርፍ በርካታ ለዉጦች የተመዘገቡ ሲሆን በአንጻሩ ብዙም ለዉጥ ያልታየባቸዉ የግብርና ዘርፎችም እንደነበሩ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በመኽር ሊለማ የሚችል መሬት በሄክታር ሲታይ መጠነኛ መሻሻል የታየበት ሲሆን ባለፉት 10 አመታት በአማካይ 4,392,021 ሄ/ር መሬት በመኽር ለማልማት ታቅዶ 3,080,098 ሄ/ር (70.1%) ማድረስ ተችሏል ይህም በመጀመሪያዉ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ማለትም ከ2003 ዓ.ም- 2007 ዓ.ም በአማካይ ከነበረበት 62.4% በሁለተኛዉ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን ማለትም ከ2008ዓ.ም-2012ዓ.ም በአማካይ 78.88% ማደረስ ተችሏል፡፡ በመኽር በዋና ዋና ሰብሎች የተሸፈነን መሬት 373,230ሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 101,662.75ሄ/ር (27.2%) ብቻ ለማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ገና ብዙ መስራት እንደሚጠበቅ ያሳያል፡፡ በብእርና አገዳ ሰብሎች የተሸፈነ መሬት በ2007ዓ.ም ከነበረዉ 51.9% በ2012ዓ.ም ወደ 32.5% ዝቅ ያለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ከፍተኛ ጥረት እንደሚያስፈልግ ያሳያል፡፡ በጥራጥሬ የተሸፈነ መሬት ሲታይ በመጀመሪያዉ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን የእቅድ ዘመን የተሰራ ስራ ባይኖርም በሁለተኛዉ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ እስከ 2012ዓ.ም ድርስ 78,552.3ሄ/ር መሬት ለመሸፈን ታቅዶ 12,690.5 ሄ/ር(16.1%) የተሰራ ሲሆን ዘርፍ ለወደፊት ከፍተኛ መሻሻልን የሚጠይቅ


እንደሆነ ያሳያል፡፡ በቅባት ሰብሎች የተሸፈነ መሬት ሲታይ እስከ 2012ዓ.ም ድረስ በአማካይ 20.64% ማሳካት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በመኸር በዋና ዋና ሰብሎች የተገኜ ምርት ሲታይ ከ2008 - 2012ዓ.ም ድረስ 7,333,240.6 ኩ/ል ለማምረት ታቅዶ 3,916,523.6 ኩ/ል (53.4%) ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍም ቢሆን ብዙ መሻሻል የሚያስፈልግ መሆኑን ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል በበልግ በዋና ዋና ሰብሎች የለማ መሬት ሲታይ ባለፉት 10 አመታት ዉስጥ 104,348.8 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 87732.9 ሄ/ር በአማካይ 84% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ የተሻለ ለዉጥ ማምጣት ተችሏል፡፡ በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬትን ስንመለከት ምንም እንኳ ቀደም ሲል በነበሩት አመታት የመረጃ ግብዐት እጥረት የታየበት እና በክልሉ ጥናት ተደርጎ ማስተካከያ ቢደረግበትም ባለፉት አስር አመታት 84,895.8 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 72370.1 ሄ/ር (85.24%) ማድረስ የተቻለ ቢሆንም ዞኑ ካለዉ እምቅ የዉሃ ሃብት አንጻር ሲታይ ግን ገና ብዙ የሚቀር ስራ እንዳለ መዘንጋት የለበትም፡፡ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ብዛትን ስንመለከት እስከ 2012ዓ.ም መጨረሻ ድረስ 78.4% ገበሬዎችን ያካተተ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ጥሩ ስራ መሰራቱን ያሳያል፡፡ በኤክስቴንሽን አገልግሎት የሰለጠኑ አርሶ አደሮች ብዛት እስከ 2012ዓ.ም መጨረሻ ድረስ 54.7% ሲሆን ሙሉ ፓኬጅ የተጠቀሙ አርሶ አደሮች ብዛት ደግሞ እስከ 2012ዓ.ም ድረስ 102.66% ማድረስ ተችሏል፡፡ በዚህ ዘርፍ የተሻለ ስራ መሰራቱን ያሳያል፡፡ በመስመር የተዘራ መሬት መጠንን በምናይበት ጊዜ ከ2006ዓ.ም ጀምሮ በአማካይ 227021ሄ/ር መሬት ለመዝራት ታቅዶ 12752.8ሄ/ር (5.6%) ብቻ ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ገና ብዙ መሻሻል እንደሚያስፈልግ ግልጽ ነዉ፡፡ የተንጣፋፊ የኩትቻ መሬት መጠንን ስናይ በ2007ዓ.ም ከነበረበት 25% በአማካይ በ2012ዓ.ም ወደ 0.14% ዝቅ ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል በኖራ የታከመ አሲዳማ መሬትን ስንመለከት በ2003 ዓ.ም ብቻ ከታቀደዉ እቅድ አንጻር 100% ማሳካት ቢቻልም ከ2003ዓ.ም በኋላ ለተከታታይ 9 አመታተት ምንም የተሰራ ስራ የለም ስለዚህ በዚህ ዘርፍ ለወደፊት በትኩረት መስራት አማራጭ የሌለዉ መፍትሄ ይሆናል፡፡

የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ እና ልማትን በተመለከተ የአፈርና ዉሃ ጥበቃ ቴክኖሎጂ የተሰራበት መሬት ባለፉት አስር አመታት ዘርፉ የተሰሩ ስራዎች በዉጤት ሲመዘን እዚህ ግባ የማይባል ስለሆነ ዘርፉ ላይ ቀጣይ ትልቅ ስራ መስራት ይጠበቃል፡፡ በዞናችን ያገገመ መሬትን በምንመለከትበት ጊዜ በሁለተኛዉ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በ2008 እና

2012ዓ.ም በአማካይ 28076 ሄ/ር ለማገገም ታቅዶ 16,197 ሄ/ር (57.7%) ማሳካት ተችሏል፡፡ ባለፉት አስር አመታት በዞናችን የተተከሉ ችግኞች ብዛት ስንመለከት የ2012ዓ.ም ሳይጨምር የእቅዳችንን 91.47% መትከል ተችሏል፡፡ የዞናችንን የደን ሽፋን በምንመለከትበት ጊዜ በአስር አመታት ዉስጥ የተሰራ ጥናት ባይኖርም ለወደፊት ይህ ተግባር ትልቅ የቤት ስራ ሆኖ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

የግብርና ግበዓት አቅርቦትን በተመለከተ የቀረበ የአፈር ማዳበሪያን ባለፉት አስር አመታት በአማካይ 263,370.3ኩ/ል ታቅዶ 214,408.3ኩ/ል 81.4% ማሳካት ተቻለ ሲሆን በዚህ ረገድ የተሰራዉ ስራ የተሻለ ነዉ፡፡ የተሰራጨ የአፈር ማዳበሪያ እስከ 2007ዓ.ም 16.5% የነበረ ሲሆን በ2012 ዓ.ም 84% ማድረስ የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ፈጣን ለዉጥ ማምጣት ተችሏል፡፡ ባለፉት አስር አመታት የቀረበን ምርጥ ዘርን ስንመለከት ከ2004-2012ዓ.ም ባለዉ ጊዜ በአማካይ 27,528.9ኩ/ል ታቅዶ 8,846 ኩ/ል 32.1% ማድረስ የተቻለ ቢሆንም በዘርፉ ከዚህ በላይ አፈጻጸም መመዝገብ የነበረበትና ለወደፊት ትኩረት የሚሻ ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በዞናችን የተሰራጨን ምርጥ ዘር ስንመለከት እስከ 2007ዓ.ም ድረስ በአማካይ 15.92% ምርጥ ዘር የተሰራጨ ሲሆን እስከ 2012ዓ.ም ድረስ ወደ 16.4% ብቻ ማሰራጨት የተቻለ ሲሆን ይህ ዘርፍ አሁንም ማነቆ ሆኖ የቀጠለ ተግባር ሲሆን ለወደፊት ትልቅ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡



ምስል 7. የዞኑን የምርት እድገት የሚያሳይ ግራፍ

## ህብርት ስራ

ለሁለንተናዊ የኢኮኖሚ እድገት የህብረት ስራ ማህበራትን ማጠናከር አይነተኛ መፍተሄ እንደሆን ይታመናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ዘርፍ ከሚከናወኑ ተግባራት ወስጥ ባለፉት አስር አመታት የተቋቋሙ መሰ/ኅ/ሥ/ማህበራት ቁጥርን ከ764 መሰ/ኅ/ስ/ማ ለማቋቋም ታቅዶ 685 (89.66%) ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ የተሻለ አፈጻጸም ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ የተጠናከረ ዩኒየንን ስንመለከት ባለፉት አስር አመታት 62 ዩኒየኖችን ማጠናከር ታቅዶ ክንዉን 62 ሲሆን 100% ማሳካት ተችሏል፡፡ በዚህ ዘርፍ ከፍተኛ ዉጤት ማስመዝገብ ቢቻልም ዞኑ ካለዉ እምቅ ሃብት እና የሰዉ ሃይል አንጻር ሲታይ ግን ብዙ መስራትን እንደሚጠይቅ አያጠራጥርም፡፡ አጠቃላይ የመሰ/ኅ/ሥ/ማኅበራት ብዛት ሲታይ ባለፉት አስር አመታት 16,796 ማህበራትን ለማድረስ ታቅዶ 16,783 መሰ/ህ/ስ/ ማህበራትን በማቋቋም 99.9% ማሳደግ ተችሏል፡፡ አጠቃላይ የዩኒየኖችን ብዛት ስናይ ባለፉት አስር አመታት 77 ለማድረስ ታቅዶ ክንዉን 77 ሲሆን በተከታታይ 100% ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ በዚህ ዘርፍ ላይ ጥሩ ዉጤት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ የኅ/ሥ/ማህበራት የቁጠባ መጠን በብር ስንመለከት ባለፉት አስር አመታት በአማካይ 435,207,942 ብር ለማስቆጠብ ታቅዶ 366,586,599 ብር (84.2%) ማሳካት የተቻለ ሲሆን የኅ/ሥ/ማኅበራት የካፒታል መጠን ሲታይ ባለፉት አስር አመታት በአማካይ ብር 2,284,085,120 ክንዉን 2,184,701,936 (95.6%) ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ የታየዉ ለዉጥ የሚያበረታታ ነዉ፡፡ በአግሮ ፕሮሰሲንግ የተሳተፉ ዩኒዩኖች ብዛት በምናይበት ጊዜ በ2007ዓ.ም ከነበረበት 95.5% በ2012ዓ.ም ወደ 70% ዝቅ ያለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ የታየዉ የአፈጻጸም መቀነስ ለወደፊት መሻሻል ሚገባዉ ተግባር ይሆናል፡፡

## እንስሳት ሃብት ልማት፡-

አካባቢያችን ለእንስሳት ሃብት ልማት ያለውን አመችነት ያህል ህብረተሰቡን የተጠቃሚነት ሳያረጋግጥ በባህላዊ የአመራረት ዘይቤ ሲከወን ቆይቷል፡፡ ከዘርፉ በዞኑ ድርቆ መኖ ለማምረት የሚያስችል አቅም እንዳለ የተለያዩ ምንጮች ያሉ ሲሆን የመኖ ችግኝን በመትከል አሁን ላይ አፈጻጸሙ በአማካይ 90.8% መሆኑን ያሣያል፡፡ይህም የመኖ የምርት መሻሻል የታየበት ምክንያት አረንጓዴ የመኖ ምንጮች በተፋሰስ ላይ በስፋት በመልማታቸው፣ በሰብል ምርት ማዳበሪያና ምርጥ ዘር እና አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን

በመጠቀም በርካታ የሰብል ተረፈ ምርት መገኘት መቻሉ፣ የግጦሽ መሬትን በተለያዩ ስልቶች ለማምረት መሞከሩ /በተፈጥሮ ማዳበሪያና በበልግ፣ በመስኖ ማልማት፣የአግሮ ኢንዱስትሪ ውጤቶች እና ግለሰቦችና ዩኒየኖች መኖ በማቀነባበር በሰፊው ማምረታቸው ነው ፡፡

የእንስሣት ጤና ጥበቃ አገልግሎት አሰጣጥ ባለፉት 10 አመታ የክትባት ሽፋን እቅድ 34,008,393 ክንውን 32,352,867/95% የክትባት ሽፋን ያገኙ ሲሆን 17,876,769 እንስሣቶች የህክምና አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ በዚህም ከ2009 ወድህ በተደረገው የበጎችና ፍየሎች የውጭ ጥገኛ በሽታ ቁጥጥር 18,204,250 በማቀድ 8,099,820 አፈጻጸም 44.5% መሆኑን ያሣያል፡፡

የእንስሣት ጤና አገልግሎት ተደራሽነት በሁለቱ ስትራቴጅክ ዓመት የክሊኒክ ብዛት በእቅድ ከተያዘው 279 ውስጥ 162/58%/ የተገነቡ መሆኑን ያሣያል፡፡ በባለፉት 2003፣ 2007፣2010 አመታት በሰው ሰራሽ ዘዴና በተሸሻለ ኮርማ  የዳልጋ ከብቶችን ዝርያ ከማሻሻል ጋር በተያያዘ እቅድ 76136 ሲሆን ክንውኑ 41153 /54%/ መሆኑን እና የዳልጋ ከብት ዝርያን ለማሻሻል የተደረገው ጥረት አበረታች ቢሆንም የተፈለገውን ያህል ውጤት ለማግኘት አልተቻለም፡፡ በዞናችን በ2005፣2007 እና 2010 ዓ.ም በእቅድ ከተያዘው በቁጥር 2271 ውስጥ 1177 /51.80%/ የተዳቀሉ መሆኑን ያሣያል፡፡ ባለፉት 10 አመታት የወተት ምርት በየአመቱ አማካይ እቅድ 961,694 ክንውን 766,509.4/79.7%/ ቶን መሆኑን ያሣያል፡፡ የዳልጋ ከብት በማድለብ ባለፉት 10አመታ በእቅድ ከታያዘው 288,942.57 ቶን ሲሆን ክንውኑ 372,621.41 /100%/ ማምረት ተችሏል፡፡ በዞናችን የዓሣ ምርት ከሎጐና ከአርዲቦ ፣ከማይባር እና ከአንዳንድ ትላልቅ ወንዞች ይገኛል፡፡ የዓሣ ምርት ከ2005 ጀምሮ ባሉት መረጃዎች መሰረት በእቅድ ከተያዘው 16,505.5 ውስጥ 9,409.5 /57%/የተከናወነ መሆኑን ያሣያል፡፡ ለዚህም ዋነኛ ምክንያት የሎጐ ሐይቅ የዓሣ ማምረት አቅም በየጊዜው እየቀነሰ መምጣትና የሕገ-ወጥ አሥጋሪዎች መበራከት ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሐይቁ የውኃ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣት ሌላው እጅግ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት የሐይቁ አካባቢዎች የደን ሽፋን እየተመናመነ በመምጣቱ ደለል በሐይቁ ውስጥ በመግባቱ ነው፡፡ **የማር ምርት** በዞናችን የባለፉት 10 ከታቀደው 47487 ቶን ውስጥ 12622 /26.6%/ መሆኑን ያሣያል፡፡ **የእንቁላል ምርት** 2003/3፣5፣7፣9/2011-12/ በጀት አመት በእቅድ ከተያዘው 1547 በሚ/ቁጥር ሲሆን

አፈጻጸሙ ሲታይ 411.98/26.63%/ ሚ/ቁ መሆኑን ያሣያል፡፡ የቆዳና ሌጦ ምርት ባለፉት ከ2005 አምስት ጀምሮ ባሉት አመታት በእቅድ ከተያዘው በቁጥር 8766861 ክንውኑ 31708991 የተመረተ መሆኑን ያሣያል፡፡ይህም ስለቆዳና ሌጦ አያያዝና አጠባበቅ የሚሰጠው ኤክስቴንሽን ጠንካራ መሆኑን ያሣያል፡፡

## አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና

የማህበረሰባችንን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ በአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ዘርፍ የሚሰሩ ተግባራትን በተገቢዉ መልኩ መስራት አስፈላጊ ነዉ፡፡ የተካሄዱ አስቸኳይ የአደጋ ስጋት ጥናትን ስንመለከት ከ2003-2012ዓ.ም ባሉት ተከታታ 10 አመታት 20 ትናቶችን ለማድረግ ታቅዶ ክንዉን 18 በአማካይ 90% ማሳካት የተቻለ ሲሆን ፤የተካሄደ የስነ-ምግብ ጥናትን ስንመለከት ከ2003-2007ዓ.ም በአማካይ 90% ማሳካት የተቻለ ሲሆን ከ2008-2012ዓ.ም በአማካይ ወደ 30% ዝቅ ያለ ሲሆን በዚህ ተግባር ላይ የታየዉ የአፈጻጸም መቀነስ ወደፊት እንዳይደገም ትኩረት አድረጎ መስራትን ይጠይቃል፡፡ በዞናችን ድጋፍ የሚሹ ህዝቦችን ስንመለከት ከ2003-2012ዓ.ም ባሉት ተከታታይ አመታት 1822094 ሰዎችን ለመለየትና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ክንዉን 1822094 (100%) በዚህ ዘርፍ የታየዉ ስኬት በዚሁ ሊቀጥል የሚገባ ይሆናል፡፡ በልማታዊ ሴፍቲኔት የተመረቁ ተጠቃሚዎች ብዛትን በምንመለከትበት ጊዜ ከ2003-2012 ዓ.ም በነበሩት አስር አመታት 1145162 ሰዎችን ለማስመረቅ ታቅዶ ክንዉን 315358 (27.5%) ብቻ ማሳካት ተችሏል፡፡

## ስራና ስልጠና


በዞናችን በየጊዜዉ እየጨመረ የመጣዉን የስራ አጥ ወጣቶች ቁጥር ለመቀነስ እና ከኢኮኖሚ እድገቱ ጋር የሚጣጣም የህዝብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በቴክኒክ ሙያ እና ኢንተርፕራይዝ የሚሰሩ ተግባራትን በሚገባ ወደ ተግባር መቀየር እጅግ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በመሆኑም ባለፉት አስር አመታት በርካታ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን ከ2003-2012ዓ.ም የቴክኒክ ሙያ ኮሌጆች በቁጥር ሲታይ 14 ማድረስ ተችሏለው፡፡ ከመጀመሪያዉ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ክንዉን አንጻር ሲታይ ጥሩ መሻሻል የታየበት ተግባር ነዉ፡፡ የመንግስት ቴክኒክ ሙያ ኮሌጆች መደበኛ ቅበላ ስልጠናን በተመለከተ ከ2003-2005ዓ.ም ያለዉ አፈጻጸም ሪፖረቱ ዉስጥ ባይካተትም በ2006ዓ.ም 6178 ተማሪዎችን ለመቀበል ታቅዶ 4588(74.3%) ማሳካት የተቻለ ሲሆን በ2007ዓ.ም ከታቀደዉ 5118 ተማሪዎች ዉስጥ 5115(99.9%) ተማሪዎችን መቀበል

የተቻለ ሲሆን ከ2007-2012ዓ.ም በአማካይ 80% ተማሪዎችን መቀበል ተችሏል፡፡ የግል ቴክኒክ ሙያ ኮሌጅ ሰልጣኝ ቅበላን ስንመለከት ከ2006-2012ዓ.ም 67,430 ተማሪዎችን ለመቀበል ታቅዶ 55,129 (81.7%) ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ወደፊት በተሻለ ሁኔታ መስራት እንደሚያስፈልግ ያሳያል፣ኢንተርፕሪነርሺፕ ስልጠና የወሰዱ ሰልጣኞችን በተመለከተ ከ2006-2012ዓ.ም 501,645 ሰልጠኞችን ለማሰልጠን ታቅዶ ክንዉን 383,349 (76.4%) ማሳካት ተችሏል፡፡ በዚህ ዘርፍ የተሻለ አፈጻጸም ቢታይም ስልጠናዉን ከሚፈልጉ ሰወች ብዛት አንጻር ሲታይ አሁንም ብዙ መስራት እንደሚያስፈልግ ያሳያል፡፡ የክህሎት ስልጠና የወሰዱ ሰልጣኞችን ስንመለከት እስከ 2012ዓ.ም መጨረሻ ድረስ 69.66% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ወደፊት የተሻለ ስራ መስራት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

የተሸጋገረ ቴክኖሎጂ ብዛትን ስንመለከት ከ2008-2012ዓ.ም 2163 በእቅድ ተይዞ 1920 (88.76%) ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ የተሻለ ዉጤት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ የደረጃ ሽግግር ያደረጉ ኢንተርፕራይዞች ብዛት ከ2005-2012ዓ.ም ባለዉ ጊዜ 19097 ታቅዶ ክንዉን 11904 በአማካይ 62.3% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ከዚህ የተሻለ ዉጤት ለማስመዝገብ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አዲስ የተቋቋሙ የጥ/አ/ኢንተርፕራይዞች ብዛት ከ2003ዓ.ም-2012ዓ.ም 71854 ኢንተርፕራዞችን ለማቋቋም ታቅዶ ክንዉን 65020 በአማካይ 90.5% ማሳካት የተቻለ ሲሆን የመምሪያዉ ዋነኛ ተግባር የሆነዉን የስራ እድል የተፈጠረላቸዉን ስራ ፈላጊዎች ስንመለከት ከ2003-2012ዓ.ም በ10 አመቱ በከተማና በገጠር ለ805,502 ስራ ፈላጊዎች ስራ ለመፍጠር ታቅዶ ቋሚ 420,539 ጊዜዊ 255,352 በድምሩ 675,891 (83.9%) በዞናችን የስራ ፈላጊዎች ቁጥር ከፍተኛ ከመሆኑ አንጻር ገና ብዙ መስራት እንደሚጠበቅ ያሳያል ፡፡

ከገበያ ትስስር የተገኘን ገቢ ስንመለከት ከ2003-2007ዓ.ም ድረስ 495,586,182ብር ገቢ ለማድረግ ታቅዶ ክንዉን 666,398,940 በአማካይ 134.4% ማሳካት የተቻለ ሲሆን ከ2008-2012ዓ.ም ድረስ 1222436131 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ ክንዉኑ 1,966,296,086 ወደ 160.8% ከፍ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ የተሰራዉ ስራ አበረታች ዉጤት የተመዘገበበት ነዉ፡፡አዲስ የተገነቡ ክላስተር ሸዶችን በተመለከተ በ2007ዓ.ም 174.3% ማሳካት የተቻለ ሲሆን ከ2008-2012ዓ.ም በአማካይ 96.7% ማሳካት ተችሏል፡፡ አዲስ የተገነቡ ክላስተር ሸዶች ተጠቃሚ ጥ/አ/ኢንተርፕራይዞች ብዛትን ስንመለከት በ2007ዓ.ም 86.17% ማሳካት

የተቻለ ሲሆን ከ2008-2012ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በአማካይ 74.45% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ከዚህ የተሻለ ዉጤት ማስመዝገብ ይቻል ዘንድ ጥረቱን በተቻለ መልኩ አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡ በአዲስ ስራ የጀመሩ የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን ብዛት በተመለከተ በተከታታይ በ2010ዓ.ም 80% በ2011ዓ.ም 85% እና በ2012ዓ.ም 100% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ የተደረገዉ ጥረት አበረታች ዉጤት የታየበት ነዉ፡፡




መስል 8. የደ/ወሎ ዞን የስራ እድል በዘረፍ ሲተነተን የሚያሳይ በግራፍ

## መሬት ልማት

የመጀመሪያ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በመስጠትን ለ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ መስጠት ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር ጋር በተያያዘ ከ2003-2010 ዓ.ም ድረስ ባሉት አመታት እስካሁን በዞናችን ስር በሚገኙ 20 የገጠር ወረዳዎች እቅድ 103,309 ክንውን 88,219 አፈጻጸም 85.39% ሲሆን ከ2011 ዓ.ም ወድህ የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያገኙ እቅድ 81,669 ክንውን 98,555 /100%/ የተሰጡ መሆኑንያሣያል፡፡ በዞኑ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት አመታት የ635504 ባለይዞታወች ማሳ ወደ ኮምፒውተር ለማስገባት ታቅዶ 258,242 (40.63%) በማከናወን መረጃቸው ወደ ኮምፒዩተር ማስገባት ተችሏል፡፡ በዞናችን በሚገኙ በሁሉም ቀበሌዎች የምዝገባና የትቸታ ስራ በከፍተኛ ደረጃ የተሰራ ቢሆንም በስራ እንቅስቃሴ ወቅት በየጊዜው በየወረዳው በአንዳንድ ቀበሌዎች በመሬት ዙሪያ አቤቱታና ቅሬታዎች ስለሚታዩና እነኚህን ማጥፋት ባይቻል በእጅጉ ለመቀነስ የሁሉንም ቀበሌወች የመሬት መዝገባና ልኬታ የመዳሰስ ስራን አጠናክሮ በመቀጠል ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ እቅድ

148 ክንውን 133/89.86%/ ቀበሌዎች ፕላን ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ ይህም የተሸለ አፈጻጸም መሆኑን ያመላክታል፡፡

በዞናችን በግብርናው ኢንቨስትመንት ዘርፍ መሳተፍ የሚፈልጉ ግለሰቦችን እንቅስቃሴ በአግባቡና ለውጥ ሊያመጣ በሚችል መልኩ ለማስተናገድ በሚደረገው ፕሮግራም እስካሁን ከ2009 ጀምሮ በተሰበሰበ መረጃ በጥናት የተለየ እና ለኢንቨስትመንት የተሰጠ የመሬት ስፋት በሄክታር እቅድ 2641.8 ሄ/ር ክንውን 2870.92 /ከ100%/ በማዘጋጀት የኢንቨስትመንቱን ዘርፍ ማጠናከር ይቻላል፡፡ ለህዝብ ጥቅም ሲባል መሬታቸውን የሚለቁ ባለይታወችን ንብረት በመገመትና በማስከፈል በኩል በ2011 እና 2012 ዓ.ም እቅድ 18445 ክንውን 8083 /43.8%/ ይህም ዝቅተኛ አፈጻጸም ላይ መሆኑን ያሣያል፡፡

የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም በማጠናከር የዞኑን የደን ሽፋን እና የተፈጥሮ ሀብት ስራውን አጋዥ እንድሆን ማድረግ ከዘርፉ የሚጠበቅ ነው ፡፡ባለፉት 10 አመታት የአካባቢ ተጽዕኖ በመገምገም የይሁንታ ፈቃድ የተሰጠ ሰነድ ብዛት በቁጥር እቅድ 2863 ክንውን 2779/97%/ ይህም አፈጻጸሙ የተሻለ መሆኑን ያሣያል፡፡የአካባቢ ፣ክትትል ምርመራና ቁጥጥር የተደረገላቸው ፕሮጀክቶች ብዛት በቁጥር እቅድ6763 ክንውን 7314 ይህም ከ100% በላይ መሆኑን ያሣያል፡፡ከ2007 ጀምሮ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ለመከላከል የተዘረጋ የአሰራር ስርዓት ብዛት እቅድ 56 ክንውን 50/89%/ መሆኑን ያሣያል፡፡

## ንግድና ገበያ ልማት

ባለፉት 10 አመታት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅን ተግባራዊ በማድረግ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት አዋጆችን የማስተዋወቅና የማስፈፀም፣ በዞኑ የንግድ ፈቃድ መስጫ መደቦች በሥራ ላይ ማዋል፣ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶችን ዝግጅት በማስተባበር ተግባራዊ ማድረግ፣ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥን በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የማድረግ ተግባራት በዕቅድ ተይዘው ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

በዞናችንችን ከ2006 ጀምሮ ባለ መረጃ በዕቅድ ዘመኑ መጀመሪያ የነበረውን የንግድ ማህበረሰብ ቁጥር በየአመቱ 10% በማሳደግ ተደርሶበት ከነበረው አዳዲስ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ፤ ነባር ምዝገባና ፈቃድ የማደስ አገልግሎት በመስጠት 80414 አድስ ንግድ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 75596/74%/ የተሰጠ ሲሆን ከህጋዊ ንግድ ፈቃድ እድሣት ጋር በተያያዘ 296383 ለማደስ ታቅዶ 261008/88%/፣ህጋዊ ንግድ ሽፋን እቅድ 159744 ክንውን 81% መድረሱን ያሣያል፡

የገበያ መሰረተ ልማት አድስ መደበኛ ገበያ ከማቋቋም አንጻር ባለፉት 7አመታት በእቅድ ከተያዘው 85 አፈጻጸሙ ሲታይ 110/ከ100% በላይ/ ማቋቋም ተችሏል፡፡ ወደ መረጃ ቋት /Excel/ የገባ የግብርና ምርት በኩንታል እቅድ 1702130 ኩ/ል ክንውን 1288949/75.72%/ ኩ/ል የግብና ምርት መመዝገቡን ያመላታል፡፡ ከ2009 ወድህ ባሉ አመታት የተገኘ የውጭ ምንዛሬ እቅድ በዶላር 145,272,911 ክንውን 167,490,056.65 ዶላር ይህም ከ100% በላይ አፈጻጸም እንዳለውና የተሸለ መሆኑን ያመላክታል፡

## ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት

እንደሚታወቀዉ ሀገራችን እየተመራችበት ያለዉን ግብርና መር የሆን የኢኮኖሚ አማራጭ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሻገር ከፍተኛ ጥረት ላይ መሆኗ ይታወቃል ሆኖም ይህን ለዉጥ ለማረጋገጥ በኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ዘርፍ የሚገኙ ተግባራትን በስኬት ማከናወን አማራጭ የሌለዉ መፍትሄ ነዉ፣ ስለሆነም ባለፉት አስር አመታት በዞናችን ዉስጥ በዘርፉ የተከናወኑ ተግባራትን ስንመለከት በዞናችን በማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ መስጠትን በተመለከተ ባለፉት አስር አመታት ለ4543 ሰዎች ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ3231 (71.1%) ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ የተሻለ አፈጻጸም ታይቷል ፣በማዕድን ማምረት ዘርፍ የስራ እድል መፍጠርን በተመለከተ ከ2003-2012ዓ.ም ባለዉ ጊዜ ለ49696 ሰወች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ45487(91.5%) ማሳካት የተቻለ ቢሆንም ዞናችን ሰፊ ስራ አጥ ቁጥር የሚታይበት ዞን እንደመሆኑ መጠን በመጀመሪያዉ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን የእቅድ ጊዜ የተሰራዉን ስራ ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡ ገቢ መሰብሰብን በምንመለከትበት ጊዜ ከ2003-2012ዓ.ም በነበረዉ ጊዜ 24,409,325.2 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 27141916.87 በአማካይ የእቅዱን 111% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ረገድ የታየዉ ስኬት እጂግ አበረታች ነዉ፡፡ ለባለሃብቶች የተሰጠን የኢንቨስትምንት ፈቃድን ስንመለከት ከ2004-2012ዓ.ም ድረስ ባሉት ዘጠኝ አመታት ለ1301 ባለሃብቶች ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 1350 በአማካይ የእቅዱን 103.7% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ በዚህ ዘርፍ የተሰራዉ ስራ እጂግ አበረታች ሲሆን ለወደፊትም በዚሁ መቀጠል ያለበት ተግባር መሆን ይገባዋል፡፡ የተመዘገበ ካፒታልን ስናይ ከ2003-2012 ዓ.ም በነበሩት አመታት 24,308,000,000 ብር ካፒታል ማስመዝገብ ታቅዶ 25,840,000,000 ብር 106.3% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ በዚህ ዘርፍ በተለይም በሁለተኛዉ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን የተሰራዉ ስራ እጂግ አመርቂ ዉጤት የተመዘገበበት ነበር፡፡

በባልሃብቶች የተፈጠርን የስራ እድል ስናይ ከ2003-2012ዓ.ም በነበሩት አስር አመታት ለ93202 ሰዎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ347050(372.36%) ሰዎች የስራ እድል መፍጠር ተችሏል ተግባሩን በዚሁ ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡ ወደ ተግባር የገቡ ፕሮጀክቶችን ስንመለከት በመጀመሪያዉ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዘመን በ2004ዓ.ም የእቅዱን 25% እና በ2007ዓ፣ም የእቅዱን 56.82% ብቻ ማሳካት የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ ከ2008-2012ዓ.ም በነበረዉ ጊዜ በአማካይ 51.8% ሲሆን ይህ ዘርፍ መሻሻል ያላሳየ በመሆኑ ወደፊት ትኩረት ሊሰጣቸዉ ከሚገቡ ተግባሮች መካከል አንዱ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ ወደ ስራ የገቡ ፕሮጀክሮችን የካፒታል መጠን ስንመለከት ከ2008-2012ዓ.ም በነበሩት አምስት አመታት 5,003,000,000 ብር ካፒታል ማስመዝገብ ታቅዶ 1,822,660,000 በአማካይ 36.4% ማሳካት የተቻለ ሲሆን ይህ ተግባር የዘርፉ ዋነኛ ተግባር እንደመሆኑ መጠን ዉጤቱ አናሳ በመሆኑ ወደፊት ትኩረት ሊሰጠዉ የሚገባ ተግባር ሆኖ ይቀጥላል፡፡ በፕሮጀክቶች የተፈጠሩ የስራ እድሎችን ስንመለከት በ2007-2012 ዓ.ም በነበሩት አስር አመታት ለ22766 ሰዎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ12386 (54.4%) ይህ የሚያሳየዉ ለዚህ ዘርፍ የተሰጠዉ ትኩረት አናሳ መሆኑን ሲሆን ለወደፊት ተግባሩን ለማሳካት ጠንካራ ስራ እንደሚያስፈልግ ያሳያል፡፡

የተገኜን የዉጭ ምንዛሬን ስንመለከት ከ2008-2012ዓ.ም በነበረዉ ጊዜ160,000,000 ብር ለማገኘት ታቅዶ ክንዉን 177,916,833 በአማካይ የእቅዱን 111.2% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ካለዉ የዉጭ ምንዛሬ እጥረት አንጻር እቅዳችንን በመለጠጥ ለወደፊት የበለጠ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በዞናችን የተቋቋሙን መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን ስንመለከት ከ2008-2012ዓ.ም ባሉት አመታት በአማካይ የእቅዱን 66.29% ማሳካት የተቻለ ሲሆን ዘርፉን ለማሻሻል ለወደፊት ከዚህ የተሻለ ጥረት እንደሚያስፈልግ ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ የኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅምን ስንመለከት ከ2008-2012ዓ.ም በነበሩት አመታት በአማካይ የእቅዱን 66፣29% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህም ዘርፍ ከዚህ የተሸለ ዉጤት ለማስመዝገብ ለወደፊት ከፍተኛ ጥረት እንደሚጠይቅ ያሳያል፡

## ባህል ቱሪዝም

እንደሚታወቀዉ ዞናችን የበረካታ ቱሪስት መስህቦች ባለቤት እንደሆነች ይታወቃል ሆኖም በኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ ዉስጥ የባህል እና ቱሪዝም ተግባራትን ማጠናከር ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ፋይዳ ያለዉ በመሆኑ ባለፉት አስር አመታት በዘርፉ ከተከናወኑ

ተግባራት መካከል የተደራጁ የባህል ማዕከላትን ስንመለከት ከ2003-2012ዓ.ም ባሉት አስር አመታት ዉስጥ ምንም የተከናወነ ተግባር የሌለ ሲሆን ይህ ዘርፍ ወደፊት ትኩረት ሊሰጠዉ የሚገባ ተግባር እንደሆነ ያሳያል፡፡ የተደራጁ የህዝብ ቤተ መጽሃፍትን ስንመለከት ከ2003-2012ዓ.ም ባሉት አመታት 16 ቤተ መጽሃፍትን ለማደራጀት ታቅዶ ክንዉን 7 (43.4%) ማሳካት የተቻለ ሲሆን ይህ ዘርፍ የተሰጠዉ ትኩረት አናሳ መሆኑ ያሳያል፡፡ የህዝብ ቤተ-መጽሃፍት ተጠቃሚዎች ብዛትን ስንመለከት ከ2003-2007ዓ.ም ባሉት አመታት በአማካይ 73.7% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ ከ2008-2012ዓ.ም ድረስ ወደ 88% ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

የኪነ-ጥበብ ፈጠራ ዉጤቶች ብዛትን ስንመለከት በ2004ዓ.ም 66% እንደዚሁም በ2007ዓ.ም 77% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ ከ2008-2012ዓ.ም በአማካይ ወደ 97.4% ከፍ ማድረግ ተችሏል በዚህ ዘርፍ የታየዉ መሻሻል አበረታች እንደነበር ያሳያል፡፡ የቅርስ ጥገና እና እንክብካቤን ስንመለከት ከ2008-2012ዓ.ም በአማካይ 80.9% ማሳካት ተችሏል፡፡ የቱሪዝም መዳረሻ ብዛትን ስንመለከት ከ2008-2012ዓ.ም ድረስ በአማካይ 50% ማሳካት ተችሏል፡፡ የቅርስ ምዝገባና መረጃ አደረጃጀትን ስንመለከት ከ2003-2007ዓ.ም በአማካይ በቋሚ 164.3% በተንቀሻቃሽ ደግሞ 58.2% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ ከ2008-2012ዓ.ም ድረስ በቋሚ ወደ 73.74% በተንቀሳቃሽ ደግሞ ወደ 89.27% ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህ ዘርፍ የተሻለ ስራ ተሰርቷል፣የሙዚየም ግንባታ ልማትን በተመለከተ ተግባሩ ስራ ላይ የዋለዉ ከ2010-2012ዓ.ም ብቻ ሲሆን በነዚህ አመታት በአማካይ 100% ማሳካት ተችሏል፡፡ የቱሪስት ፍሰት ገቢን ስንመለከት ከ2003-2012ዓ.ም ባሉት ተከታታይ አመታት 450,350,042 ብር ገቢ ለማድረግ ታቅዶ 371,224,922 (82%) ማሳካት የተቻለ ቢሆንም ካልፉት አስር አመታት ዉስጥ 4 አመታት ላይ እቅድና ክንዉን አልተቀመጠለትም፡፡

የቱሪስት ፍሰትን በቁጥር ስንመለከት ከ2003-2012ዓ.ም ባሉት አመታት 11,265,232 ታቅዶ ክንዉን 9,294,946 በአማካይ 82.5% ማሳካት የተቻለ ሲሆን፣በዘርፉ የስራ እድል ፈጠራን ስንመለከት ከ2007-2012ዓ.ም ባሉት ተከታታይ 5 አመታት ለ30745 ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ክንዉን ለ21691 ዜጎች በአማካይ 70.55% ማሳካት የተቻ ሲሆን በዚህ ዘርፍ የተሰራዉ ስራ አበታች ነዉ፡፡ የኮከብ ደረጃ የተሰጣቸዉን አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ብዛት ስንመለከት ከ2004 ዓ.ም 100% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በሌሎቹ አመታት ዉጤት ያልተመዘገበ ሲሆን በዚህ ዘርፍ የተፈጠረዉን መዘናጋት መቅረፍ ይገባል፡፡ የሙያ ብቃት

ማረጋገጫ የተሰጣቸዉ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብዛትን ስንመለከት ከ2004-2012ዓ.ም ባሉት አመታት ለ3458 ተቋማት ለመስጠት ታቅዶ ክንዉን 3511 በአማካይ ከ100% በላይ ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ የተመዘገበዉ ስኬት አበረታች ነበር፣ የተዘጋጁ የህትመት እና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ስራዎች ብዛትን ስናይ ከ2003-2012ዓ.ም ባሉት ተከታታይ አመታት በአማካይ 157.5% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ ከ2008-2012ዓ.ም በአማካይ ወደ 123.2% ዝቅ ቢልም በዚህ ዘርፍ ጥሩ ስራ ተሰርቷል፡፡ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ድጋፍና ክትትል ማድረግን በተመለከተ ከ2003-2012ዓ.ም ባሉት ተከታታይ አመታት በአማካይ 171% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ ከ2008-2012ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በአማካይ 104.2% ማሳካት ተችሏል፡፡

## ገቢን ማሳደግ

የገቢ አሰባሰብ ያለበት ሁኔታ የዞኑ ገቢ ባለፉት አሥር ዓመታት በከፍተኛ ደረጃ እያደገ ይገኛል፡፡ ወደቅርቡ ግን ዕድገት ቢኖረውም የእድገት መቶኛው ግን መቀነስ እየታየበት ነው፡፡ ይኸውም በ2005፣ 2006 ፣2007 ፣2008፣ 2009፣ 2010 እና 2011 በጀት ዓመት የገቢ አሰባሰብ እድገት በቅደም ተከተል 32.76% ፣17.57% ፣41.88% ፣18.93% ፣14.13%፣ 14.13%፣ 12.67% እና 20%ነው፡፡የገቢ አሰባሰቡ ዕድገት ሲታይ በብር ደረጃ እያደገ እነደመጣ ያሳያል፡፡ነገር ግን የክልሉ ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን ገቢ አሟጦ በመሰብሰብ በኩል ገና ብዙ መስራት ይጠይቃል፡፡


## 4. የማህበራዊ ልማት ዘርፍ እንደ መነሻ

## ትምህርት ልማት

የትምህርት ተሳትፎንና ፍትሀዊነትን ለማሳደግ በርካታ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን ባለፉት 10 አመታት እስከ 2012 የትምህርት ዘመን የተደረሰባቸው አበይት አፈፃፀሞች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ባልተዳረሰባቸው የገጠር አካባቢዎች ማህበረሰብ አቀፍ ቅድመ መደበኛ ትምህርትን በመዘርጋት ትምህርቱን በገጠር አካባቢዎች ተደራሽ በማድረግ 91,829 ተማሪዎች በማስተማር ጥቅል የትምህርት ተሳትፎውን 37.2% ማድረስ ተችሏል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የተማሪዎች ብዛት 496,598 እንዲደርስ በመደረጉ የትምህርት ተሳትፎው *70%* ደርሷል፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪዎች ቁጥር 87,875 እንዲደርስ በመደረጉ ተሳትፎው አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ 40.3 % እና ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ 16.7 % ሆኗል፡፡

እንዲሁም የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ተሳታፊዎች ቁጥር 41,140 በመድረሱ ማንበብና መፃፍ የሚችሉትን ጎልማሶች ዕቅድ አፈጻጸም 21.5% ማድረስ ተችሏል፡፡ እነዚህ ውጤቶች ሊገኙ የቻሉት በዋናነት 1,232 የመጀመሪያና 67 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በመኖራቸውና በ1,190 የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ጋር ተያይዘው የኦ ክፍል የቅድመ መደበኛ ትምህርት በመሰጠቱ ነው በተጨማሪም 2,196 የቅድመ መደበኛ፣ 19,023 የመጀመሪያና 4,702 የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምህራንና 1,232 የመጀመሪያና 67 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ር/መምህራን፣ 327 የመጀመሪያና 22 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሱፐርቫይዘሮች እንዲሁም 675 የተግባር ተኮር ጎልማሶች ትምህርት አመቻቾች እንዲኖሩ በመደረጉ ነው፡፡

የትምህርት ጥራትንና ተገቢነት ለማሻሻል የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ደግሞ የመምህራን ስልጠና ፕሮግራምን ማሻሻል፣ ስርዓተ ትምህርት ማቴሪያሎችን ማሻሻል፣ የመጽሀፍ ተማሪ ጥምርታን አንድ ለአንድ ማዳረስና ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መምህራንን ድርሻ ማሣደግ ናቸው፡፡ በአንዳንድ የገጠር አካባቢዎች ህፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶችን ለመድረስ አስቸጋሪ ሁኔታዎች የሚገጥማቸውን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ የሣተላይት ክፍሎችን በመክፈት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ የሳተላይት ክፍሎችን በመገንባትና ለትምህርት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ሂደት ላይ የህብረተሰቡ ተሳትፎ ከፍተኛ ነበር፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት አበረታች ውጤቶች ቢመዘገቡም የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሚፈለገው ደረጃ አለመስፋፋት፣ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ትኩረት ተሰጥቶት አለመተግበር፣ በየደረጃው የተማሪዎችን የማቋረጥና የመድገም ምጣኔ ከፍተኛ መሆን ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተመለከተ በዞናችን በፌዴራል የሚተዳደሩ 2 ዩኒቨርስቲዎች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ተቋማት ሠልጣኞችን ተቀብለው በማስተማር ላይ ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ በማህበራዊ ዘርፍ በትምህርት መስክ እድገት ቢኖርም ይህን ጅምር አጠናክሮ በጥራት ላይ አተኩሮ መስራት የሚጠይቅ መሆኑን ያሣያል፡፡



ምስል 9. የደ/ወሎ ዞን የትምህርት ሽፋን

## ጤና ልማት

በጤናዉ ዘርፍ ባለፉት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት በጤናው ዘርፍ ተግባራዊ የተደረገው በሽታን የመከላከል ስትራቴጂ የህብረተሰቡን የጤና ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት እንደሚያስችል በተጨባጭ ማየት ተችሏል፡፡ ከዚህ ስትራቴጂ በተጓዳኝ መሠረታዊ የጤና አገልግሎትን ተደራሽና ጥራት እና ፍትሃዊነት ያለው እንዲሆን ለማስቻል ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ይህም የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች አፈጻጸም የተሻለ ውጤት እንዲኖራቸው ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በዚህም የተላላፊ በሽታዎችን ስርጭት በመቆጣጠር የህጻናትን ሞት መቀነስ የተቻለ መሆኑን መጥቀስ ይቻላል፡፡


በተጨማሪም ወደ ጤና ተቋም ሄደው የማይወልዱ እናቶችን ቁጥር በመቀነስ በወሊድ ምክንያት የሚሞቱ እናቶችን ምጣኔ መቀነስ ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ የእናቶች ሞት ምጣኔ በ2003 ዓ.ም ከነበረበት 676 ከ100,000 እናቶች በ2009 ዓ.ም ወደ 401 ከ100,000 እናቶች፤ ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት እና ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ሞት ምጣኔን በቅደም ተከተል በ2008 ከነበረበት ከ85/1,000 ወደ 59/1,000 እና ከ67/1,000 እና 58/1,000 ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የጨቅላ ህፃናት ሞት ምጣኔ በ2008 ዓም ከነበረው 47 ከ1000 በህይወት ከተወለዱ ህፃናት በ2012 እ.ኤ.አ ወደ 46 መቀነስ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ወቅት የመቀንጨር እና መቀጨጭ ምጣኔን በቅደም ተከተል ከ46 በመቶ እና ከ10 በመቶ ወደ 41 በመቶና 8 በመቶ ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ በቲቢ በሽታ ምክንያት የሚከሰት የሞት መጠንን ከ32/100000 ህዝብ ወደ 22/100000 ህዝብ መቀነስ ተችሏል፡፡ ምንም እንኳ ወባ በሽታ ከዓመት ዓመት መቀነስ ይታይበት የነበረ ቢሆንም በ2012 ዓ.ም በታየው እንደገና የማገርሸት ሁኔታ የሞት መጠኑ ከስትራቴጂክ እቅድ ዘመኑ የመጀመርያ ዓመት ጋር ሲነጻጸር ተመሳሳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት በጤናው ዘርፍ በተሰሩ ዘርፈ ብዙ ተግባራት የዜጎች አማካይ በህይወት የመኖር የዕድሜ ጣሪያ በ2005 ከነበረበት 56 ዓመት በ2008 ወደ 65.5 ዓመት አድጓል፡፡ በጤና ዘርፍ በብዙ መልኩ እየተሸሻሉ ያሉ የፕሮግራም እና የአገልግሎት አሰጣጥ ቢታዩም በውሀ፣ በግል እና የአካባቢ ንፅህና ጉድለት ምክንያት (WasH)፣ የአልኮል መጠጥ፣ የስኳር እና ከአመጋገብ ስርአት ጋር ተያይዘው በሚመጡ ችግሮች ምክንያት የሚከሰት ሞት እና በሽታ አሁንም ችግር እንደሆኑ ቀጥለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በስራ ላይ የሚያጋጥም አደጋ እና ከፍተኛ የሆነ የደም ግፊት ካለፉት አስርት ዓመታት ወዲህ ጭማሪ እያሳየ የመጣ ሲሆን ኢትዮጵያ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ውስጥ እጅግ ከፍተኛ የሆነ አጣዳፊ እና ሥር የሰደደ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት እና ጠቃሚ የሆኑ ንጥረ ነገሮች እጥረት ካለባቸው ሀገራት ውስጥም በቀዳሚነት ትጠቀሳለች፡፡ ባጠቃላይ ጥራት ያለው አገልግሎት እና ፍትሀዊነትን ከማረጋገጥ አንጻር በተወሰኑ ፕሮግረሞች ላይ ሲታይ፡በ2012 ዓ.ም 50% ያገቡ ሴቶች የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ ሲሆኑ በ2007 ዓ.ም 47% ብቻ ነበር፡፡ በ2016 እ.ኤ.አ ወደ 17% የሚሆኑ ሴቶች ፍላጎታቸው ሳይሟላ የቀረ የቤተሰብ ዕቅድ ፍላጎት እንዳለ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

አራተኛው ዙር ቅድመ ወሊድ ክትትል ሽፋን በ2008 ከነበረበት 32% በ2012 ወደ 51% ያደገ ሲሆን የቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ጥራትን የበለጠ በማሻሻል የእናቶችን ጤና ለማረጋገጥና ከእርግዝና እና ወሊድ ጋር ታይዞ ሚመጣ ሞትን ለመቀነስ አሁንም ከፍተኛ ትኩረት ይሻል። እንደ እ.ኤ.አ. በ2019 በተደረገ መለስተኛ የስነ ህዝብ ጥናት መሰረት በክልሉ የፀረ አምስት ክትባት ለሶስተኛ ጊዜ የወሰዱ ሕፃናት (80%) እና ሁሉም ክትባቶች ያጠናቀቁ ህፃናት (69%) እንደሆነ ሳያል፡፡ አፍላ ወጣቶች እና ወጣቶች ወይም እድሜያቸው ከ10 እስከ 29 ዓመት እድሜ ክልል የሚገኙት 42% የሚሆነውን የህብረተሰብ ክፍል ይሸፍናሉ፡፡ በሃገር አቀፍ ደረጃ በተሰራ ጥናት ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 19 ዓመት የሚሆናቸው አፍላ ወጣት ሴቶች መካከል 20% የሚሆኑት የደም ማነስ እና 23% የሚሆኑት ደግሞ ዝቅተኛ ክብደት የሚታይባቸው እነደሆነ ሪፖርቱ ያሳያል፡፡

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከል እ.ኤ.አ በ2020 ከታቀዱት ሶስቱ 90ዎች የመጀመሪያው 90 ማለትም ቫይረሱ በደማቸው እንደሚገኝ ያውቁ ሰዎች ሽፋን 69%፣ የሁለተኛው ዘጠና ማለትም ቫይረሱ ለተገኘባቸው ሰዎች መድሀኒት ማስጀመር 68%፣ እና ሶስተኛው ዘጠና መድሀኒት ከሚወስዱት ሰዎች የቫይረሱን መጠን በደም ውስጥ በአንድ ሚሊ ሊትር ከ1000

የቫይረስ ኮፒ በታች ማውረድ የሚለው 47% በመሆኑ ዝቅተኛ አፈጻጸም እነደሆኑ ሪፖርቱ የሚያሳይ ሲሆን ይህም HIV ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ተግባራት ላይ ልዩ ትኩረት መስጠጥ እነደሚገባ አመላካች ነው፡፡ በሃገር አቀፍ ደረጃ እንደ እ.ኤ.አ በ2016 ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ምክንያት የአካል ጉዳቶች 43.5% እና ሞት 8.5% የሚከሰት ሲሆን ከጠቅላላው በአካል ጉዳት ምክንያት በህይወት ዘመን የመኖር እድል መቀነስ (DALYs lost) 46.1% አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡




ምስል 10. የደ/ወሎ ዞን የጤና ተቋማት ብዛት

## ሴቶች ህጻናት

የህብረተሰቡን 50 በመቶ የሚሆኑትን ሴቶች በተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃ ስራ በበቂ ሁኔታ ማሳተፍ ወሳኝ ጉዳይ ነዉ፡፡በመሆኑም በባለፉት ሁለት አምስት ዓመታት የዕ.ት.ዕ ዘመን 157,733 የሚሆኑ ሴቶች በድግግሞሽ የተሳተፉ ሲሆን በ2002 ከነበረው 20 በመቶ በ2012 ወደ  በመቶ አድጓል፡፡ በዚህ ተግባር የሴቶች ተሳትፎ እድገት ከቁጥርም ባለፈ በእምነትና በተነሳሽነት የተያዘ በአንዳንድ አካባቢም ጠንካራ አደረጃጀት የተፈጠረበት ተግባር እንደነበረ ታይቷል፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ስራ የባለትዳር ሴቶች ተሳትፎ በሚፈለገው ልክ አለመሆን፣ ሴቶች ባለሙት የተፋሰስ ልማት ስራዎች ላይ በመጠቀም በኩል ሰፊ ውስንነት መኖር፣ በተሰራው ተፋሰስ ልማት ዘላቂነት እንዲኖረው ከማድረግ አኳያ የባለቤትነት ስሜት አነስተኛ መሆንየሚሉት እንደችግር የታዩ ናቸው፡፡

ሴቶች በህብረት ስራ ማህበራት መደራጀታቸው የገቢ አቅማቸውን ለማሳደግ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ሲሰራ ቆይቷል፡፡በዚህም መሰረት በባለፉት ሁለት አምስት የዕ.ት.ዕ ዘመን ለ346,570 ሴቶች በህብረት ስራ ማህበራት ጠቀሜታና ፋይዳ ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር 81,346 ሴቶች በተለያዩ የህብረት ሥራ ማህበራት አባል እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ የሴቶች ድርሻም በ2002 ከነበረበት 14 በመቶ በ2012 ወደ 30 በመቶ ለማሳደግ ዕቅድ ተይዞ 26 በመቶ ደርሷል፡፡

በባለፉት ሁለት አምስት የዕ.ት.ዕ ዘመን ከተሰሩት ተግባራት መካከል የእናቶችን ጤና ለማሻሻል በሴቶች በራሳቸው አደረጃጀት መሰረት ነፍሰ ጡር እናቶች እንዲመዘገቡ፣ ወሊድ ክትትል እንዲያደርጉ፣ በሰለጠነ ባለሙያና በጤና ተቋማት እንዲወልዱ፣ 16ቱ የጤና ኤክስቴንሽ ፓኬጅ አሟልተው እንዲፈፅሙ በተለይም በወሊድ ምክንያት የሚደርሰዉን የእናቶች ሞት ለመቀነስወ.ዘ.ተ 1,675,839 ለሚሆኑ ሴቶች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ በዚህም የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት በ2007 ከነበረበት 49 በመቶ በ2012 ወደ 95.6 በመቶ፣ ቅድመ ወሊድ በ2007 ከነበረው 57.2 በመቶ በ2012 65.2 በመቶ ተፈፅሟል፡፡በጤና ተቋማት በሰለጠነ ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት በ2007 ከነበረበት 67.6 በመቶ በ2012 56.6 በመቶና፣ ድህረ ወሊድ በ2002 ከነበረበት 89 በመቶ በ2012 ወደ 30.7 በመቶ ብቻ መፈፀም ተችሏል፡፡

## ወጣትና ስፖርት ልማት

ልማት ዘርፍ አኳያ የሀገራችን የስፖርት ፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫ ከሆኑት መካከል የስፖርቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ አደረጃጀትና አመራር ህዝባዊ መሠረት እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡ ለዚሁ ተፈፃሚነት የፖሊሲው አስፈፃሚ አካላት ማለትም በየደረጃው የሚዋቀሩ የስፖርት ምክር ቤቶች ፣ በየደረጃው የሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራት (ፌዴሬሽኖችና የስፖርት የማህብረሰብ ኮሚቴዎች) እና ህዝባዊ ድርጅቶች ስፖርቱን ህዝባዊ መሠረት ለማስያዝ የበኩላቸውን እንቅስቃሴ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡

የስፖርት ምክር ቤቶችን ማቋቋሚያ አዋጅ መነሻ በማድረግ የስፖርት ምክር ቤቶች ከዞን እስከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ ተቋቁመው የስፖርት እና ህዝባዊ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ሰፊ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዞናችንም 24(ሃያ አራት) ወረዳዎችና ከተማ መስተዳድሮች የየወረዳቸው የስፖርት ምክር ቤቶች ያሏቸው ሲሆን 578(አምስት መቶ ሰባ ስምንት) የቀበሌ የስፖርት ምክር ቤቶች ተቋቁመው ወደ ስራ ገብተዋል፡፡ በዞን ደረጃ በስትራቴጂክ ዘመኑ

አምስት ጊዜ የምክር ቤት ጉባኤን ማካሄድ ይጠበቅበት የነበረ ሲሆን 100% መፈፀም ችሏል፡፡ በተለይ በ2010 በጀት ዓመት ከወሎ ዩንቨርሲቲ ጋር በመነጋገር ለሚመለከታቸው አካላት ጥናት ማቅረብ ችሏል፡፡

የወጣቶችን ማህበራዊ ጠንቆች ተጋላጭነት በመከላከል የተሟላ ስብዕና ያላቸውና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ ለማድረግ በባለፈውአንድ አምስት የዕ.ት.ዕ ዘመኑ መጨረሻ የወጣት ማዕከላት ቁጥርን በ2002 ከነበረበት 73 በ2012 212 ለማድረስ ታቅዶ 120 ማድረስ ተችሏል፡፡በዚህም 191,193 (ወንድ 95,597 ሴት 95,596) ወጣቶች በማዕከላት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ማዕከላት የተሟላ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በሙያ 211 በገንዘብ 100 እና በቁሳቁስ 138 ማዕከላትን በድግግሞሽ መደገፍና ማጠናከር ተችላል፡፡

የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የወጣቶችን አስተሳሰብ ለመገንባትና አመለካከት ለመቀየር፣ ማህበራዊ ኃላፊነት ስሜት እንዲያጎለብቱ፣የማህረሰቡን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ለመፍታት እንዲሁምበልማቱ የራሳቸውን ድርሻ ማበርከትእንዲችሉ በባለፈው አንድ አምስት የዕ.ት.ዕ ዘመን ትኩረት ተሰጥቶት ሲሰራ ቆይቷል፡፡በዚህም መሰረት በበጋ ወራት ወደ 257,029( ወንድ 138,247 ሴት 118,755) እንዲሁም በክረምት 1,740,775( ወንድ 939,847 ሴት 800,928) ወጣቶችን በድግግሞሽ በተለያዩ አገልግሎት መስኮች በማሳተፍ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲሰማሩ ተደርጓል፡

ወጣቶችን በሰፊው ተጋላጭ የሚያደርጋቸውን ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ለመከላከል እንዲቻል በባለፈውአንድ አምስት የዕ.ት.ዕ ዘመን ለ600,680 (ወንድ 330,069 ሴት 270,611) ወጣቶች በድግግሞሽ ህገወጥ ዝውውርን በመከላከል ዙሪያ ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ በተጨማሪም በህገወጥ መንገድ ከሀገር ወጥተው ከስደት የተመለሱ ወጣቶችን ግንዛቤ በመፍጠር በልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ዘርፎች 1,530(ወንድ 784 ሴት 747)እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል ወጣቱን ለማህበራዊ እና ለኢኮኖሚያዊ ቀውስ ከሚዳርጉት ማህበራዊ ችግሮች አንዱ አደንዛዥ ዕፆች እና መጤ ባህሎች ሲሆን ይህን ለመከላከል ለ600,680 (ወንድ 330,069 ሴት 270,611) ወጣቶች በድግግሞሽ ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡

## 5. መሰረተ ልማት ዘርፍ እንደ መነሻ

## የመንገድ ደህንነት ሥራዎች

ባለፉት 10 አመታት የዞኑን የገጠር መንገድ አውታር ይዞታ በማሻሻል እና ጥራቱን የጠበቀ በማድረግ የመንገድ መሰረተ ልማት ተደራሽ ከማድረግ አኳያ የተገነቡ መንገዶች በኪ.ሜ አጠቃላይ እቅድ 3495.77 ክንውን 3701.95 /ከ100% በላይ / ኪ.ሜ የተገነቡ ሲሆን የመንገድ ጥግግት ኪ/ሜ በ1000 ካሬ ኪ.ሜ እቅድ 1407.92 ክንውን 1407.92/100%/ መሆኑን ያሣያል፡፡ የተገናኙ ቀበሌዎች ብዛት በቁጥር 409 መሆናቸውን ያሣያል፡፡

የመንገዶችን የአገልግሎት አሰጣጥ ምቹትና ደህንነት በማሻሻል አማካይ የግር ጉዞን ከመቀነስ አኳያ እቅድ 21.667 አፈጻጸሙም 100% ሲሆን ከመጋቢ መንገድ የሚፈጅበት ጊዜ በደቂቃ እቅድ 1500 አፈጻጸሙም 100% መሆኑን ያሣያል፡፡ ከ2005 ዓ.ም ወድህ በተሰበሰበ መረጃ ህዝብ የማጓጓዝ አቅም ተሳፋሪ/ኪሎ ሜትር/ እቅድ 133663873 ክንውን 154774875 አፈጻጸሙ ሲታይ ከ100% በላይ መሆኑን ያሣያል፡፡

ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት አመታት የአሽከርካሪዎችንና የተሽከርካሪዎችን ብቃት ከማሳደግ አኳያ ቁጥጥር የተደረገባቸው ተሽከርካሪዎች ብዛት እቅድ 759364 ክንውን 705324 አፈጻጸም 92.88% ያሣያል፡፡

| ከ | ወደ | አስፋልት | ጠጠር | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|
| ሰዴ ዙሪያ | ኩታበር | 0 | 22 | 22 |
| ደሴ ዙሪያ | ወረኢሉ | 0 | 50 | 50 |
| ሳይንት | ለጋምቦ | 0 | 39 | 39 |
| መ/ሳይንት | ለጋምቦ | 0 | 38 | 38 |
| ተንታ | ወገል | 0 | 113 | 113 |
| ደሴ ዙሪያ | አልብኮ | 0 | 34 | 34 |
| ደሴ ዙሪያ | ለጋምቦ | 109 | 0 | 109 |
| ወግዲ | ለጋምቦ | 0 | 36 | 36 |
| ለጋምቦ | ቦረና | 82 | 0 | 82 |
| ተሁለደሬ | አምባሰል | 0 | 50 | 50 |
| ለጋምቦ | ከላላ | 0 | 57 | 57 |
| ተሁለደሬ | ቢስቲማ | 0 | 17 | 17 |
| ደሴ ዙሪያ | ቃሉ | 45 | 0 | 45 |
| ጃማ | ወረኢሉ | 0 | 30 | 30 |
| ወረኢሉ | ወ/አምባ | 0 | 40 | 40 |
| ተንታ | ማሻ | 0 | 44 | 44 |
| ኩታበር | ደላንታ | 0 | 76 | 76 |
| ቃሉ | አርጎባ | 0 | 36 | 36 |
| ወረባቦ | | ቃሉ | | 0 |

| | | |
|---|---|---|
| Total | 71 | 948 |

ሰንጠረዥ 1. የደ/ወሎ ዞን ወረዳወች የመንገድ መመጋገብ

## ከተማና መሰረተ ልማት

ከተሞች በፕላን የሚመሩ፣ ጽዱ፣ ውብና አረንጓዴ በማድረግ ለነዋሪዎቻቸውና ለጎብኝዎቻቸው የሚመቹ የምርትና የግብይት ማዕከላት ሁነው እንዲያድጉ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህም አንፃር ባለፉት 10 አመታት የዞናችን ከተሞች አሳታፊ ጥራት ያለውና ወጭ ቆጣቢ የሆነ የከተማ ፕላን ዝግጅት እንዲኖራቸው እና 100% በፕላን እንዲመሩ ማድረግ የሚሉ 2 ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠው ነበር፡፡

በለፉት 10 አመታት ከፕላን አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በከተሞች ፕላን ላይ የተቀመጡ መንገዶችን ከሶስተኛ ወገን ነጻ በማድረግና የመንገድ ወሰኖችን በማስከበር 804.13 ኪ.ሜ የተከፈተ ሲሆን ከተሞች ለሚጠየቁ የፕላን ምደባ ለውጥ ጥያቄዎች 100% ምላሽተሰጥቷል፡፡ በ4 ከተሞች የፕላን አፈፃፀም ኦዲት የተከናወነ ሲሆን በአብዛኞቹ ከተሞች የፕላን ጥሰት በስፋት የሚታይ በመሆኑ ቀጣይ በትኩረት መስራት ይጠበቃል፡፡

በአጠቃላይየከተሞችን ፕላን ዝግጅትና ትግበራ በህብረተሰቡ ተሳትፎና ባለቤትነት፣ በተሟላ የህግ ማዕቀፍና የአሰራር ሥርዓት እንዲሁም በጠንካራ ዲሲፕሊን ለመምራት ጥረት የተደረገ ሲሆንአሁንበዞኑ ከሚገኙ 99 ከተሞች ውስጥ97 (95.5%) ከተሞች ከፈርጃቸው ጋር የሚጣጣም የእድገት ፕላን በማዘጋጀት በፕላን እንዲመሩ ተደርጓል፡፡ ባለፉት 10 አመታት በዞኑ ከሚገኙ 99 ከተሞች ውስጥ 52 ከተሞች የአስተዳደር ወሰናቸውን ያካለሉ ሲሆን 71 ከተሞች በመሬት ላይ ቋሚ የወሰን ምልክቶችን ያስቀመጡ እና በካርታ ላይ ያመላከቱ ናቸው፡፡ እንዲሁም በከተሞች የአስተዳደር ወሰን ክልል ውስጥ የሚገኝ 1050 ሄ/ር ክፍት ቦታ እና 370 ሄ/ር በጊዜዊነት የተሰጠ ቦታ ቆጥሮና መዝግቦ ለመያዝ ታቅዶ 1775.717855(100%) ሄ/ር ክፍት ቦታ እና 174.076839(47%) ሄ/ርበጊዜዊነት የተሰጠ ቦታመቁጠርናመመዝገብተችሏል፡፡ በከተሞች ማስፋፊያና በመሃል ከተማ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚሆን 1600.685ሄ/ር በማዘጋጀት1670 ሄ/ር መሬት ለማስተላለፍታቅዶ 257.42(16%) ሄ/ርመሬት(51.52ሄ/ር ለጨረታ እና 205.89 ሄ/ር ለምደባ)የተዘጋጀ ሲሆን 1249.55764(74.82%) ሄ/ር

መሬት(48.26234ሄ/ር በጨረታ እና1201.2953 ሄ/ር በምደባ) ለተጠቃሚዎች ማስተላለፍ ተችሏል፡፡

## ውሃና ኢነርጂ ልማት

በመጀመሪያውና በሁለተኛውየዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በውሀና ኢነርጂ ልማት ዘርፍ በርካታ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ በተግባር ሂደትም ቀላል የማይባሉ ተግዳሮቶች አጋጥመዋል፡፡የመጀመሪያው (2003-2007 ዓ.ም) የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ዋናው አላማ ንጹህ መጠጥ ውሀ አቅርቦትን ለገጠሩ ነዋሪ እስከ 1.5ሜ ራድየስ ባለ ርቀት በግለሰብ 15 ሊትር በቀንና በከተማ ደግሞ እስ 0.5 ኪ/ሜትር ራድየስ ርቀት በግለሰብ 20ሊትር በቀን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ነበር፡፡በዚህም መሰረት የእቅዱ ግብ በ2007 ዓ.ም የመጠጥ ውሀ አቅርቦትን ሽፋን በገጠር እና በከተማ 98ና 100%¨ ማድረስ ነበር፡፡

የዕቅዱ መነሻ (የ2002 ዓ.ም) የሆነዉ መረጃ የሚያሳየዉ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ሽፋን በገጠር 58% በከተማ 77% እና በአጠቃላይ በዞን ደረጃ 61.6% ነበር፡፡ ይህም የሚያመላክተዉ የእቅዱ መነሻ የነበረዉ 2002 ዓ.ም ሽፋን በገጠርም ሆነ በከተማ ስሌቱ ሲሰራ የነበረው በተቋማት ስታንዳርድ እና ቁጥር ስለነበረ ይህ ስሌት በብሄራዊ የዋሽ ቆጠራ ስሌት መሰረት ሲሰራ ሽፋኑ ዝቅተኛ እንደነበር የሚያሳይ ይሆናል፡፡

በዕቅድ ዘመኑ ማለትም ከ2003-2007 ዓ.ም 6,922 አነስተኛ የመጠጥ ዉሃ ተቋማትን ለመገንባት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም የዋሽ ቆጠራ ሽፋኑን ዝቅ ስላደረገው በዕቅድ ዘመኑ ሊደረስበት የታቀደውን ሽፋን ለማምጣት ዕቅዱን መከለስ አስፈላጊ በመሆኑ በተከለሰው ዕቅድ መሰረት 11,263 አዳዲስ አነስተኛ የዉሃ ተቋማት ግንባታ ለማከናወን በታቀደው መሰረት 9,601 የውሃ ተቋማት ግንባታ የተከናወነ ሲሆን ይህ አፈጻጸም የሚያመለክተዉ በገጠር 97.89% መከናወኑን ነዉ፡፡

በአጠቃላይ በዞን በወቅቱከነበረው **2,864,132 የህዝብ ቁጥር** 1,484,089 ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ ሽፋኑ52% መድረሱን አመላክቷል፡፡ በተመሳሳይ፤ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን(2008-2012 ዓ.ም) 7,287 አዳዲስ አነስተኛ የገጠር ዉሃ ተቋማት ግንባታ ለማከናወን በታቀደው መሰረት 4,050 የውሃ ተቋማት ግንባታ ተከናውኗል፡፡

## 6. መልካም አስተዳደር ዘርፍ እንደ መነሻ

## ህዝብ ቅሬታ

በመልካም አስተዳደር ዘርፍ የህብረተሰቡን አቤቱታ እና ቅሬታዎች በመፍታት ረገድ ገና ሰፊ ስራ የሚተይቅ ተግባር ቢሆንም ባለፉት 10 አመታት በህዝብ ቅሬታ ሰሚ ዘርፍ የቀረቡ እና የተፈቱ አቤቱታዎችን በተመለከተ በድምሩ 98654 አቤቱታዎች ቀርበዉ 91746 አቤቱታዎችን በተገቢዉ መንገድ መፍታት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የመልካም አስተዳደር ተግባራትን በተመለከተ ባለፉት 10 አመታት 4849162 ሰወች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ለመስጠት ታቅዶ ለ5586113(115%) ማከናዎን ተችሏል፡፡

## ሰላምና ደህንነት

ዞኑ ከአጎራባች ክልል ከአፋር ከተለያዩ ዞኖች ጋር የሚዋሰን በመሆኑ መልካም ግንኙነት እንዲኖር በየደረጃው ያለው መዋቅርና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ለተከታታይ ዓመታት ጠንካራ ሥራዎች ተሰረተዋል፡፡ በተጎራባች ክልል ህዝቦች መካከል  በግጦሽ፣ በውሃ አጠቃቀም፣በመሬት ይገባኛል፣ በህገ ወጥ ሠፈራ፣ በስርቆት፣ ወንጀልና በመሳሰሉት የተከሰቱ አለመግባባቶችና ግጭቶችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የጋራ የልማት ትብብር ማዕቀፍን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በሃይማኖቶች መካከል መቻቻል እንዲኖርና ችግሮች ሲፈጠሩ በጋራ ለመፍታት የሚያስችል በየደረጃው ከቀበሌ ጀምሮ የሃይማኖት መሪዎች የተሳተፉበት የህዝብ መድረኮችን በመፍጠር 10000 ህዝብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርትና ስልጠና ተከታታይነት ባለው መልኩ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

በዞኑ ሠላማዊና አስተማማኝ የትራፊክ ደህንነት እንዲኖር ባለፈው ስትራቴጅ ዘመን የህብረተሰብ ግንዛቤ ፈጠራና የትራፊክ ህጐችን ለማስከበር ሰፊ እንቅስቃሴ ተደርጓል፡፡ በየአመቱ ከ10 ሚሊዮን በላይ የህብረሰብ ክፍሎች ትምህርት የመስጠትና ከ170 ሽ በላይ ደንብ ተላላፊዎችን በማረም በደንብና መመሪያው መሠረት የቅጣት እርምጃ መውሰድ ተችሏል፡፡

## የፍትህ ስርዓት

ባለፉት 10 አመታት በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ረገድ የመጀመርያው ተግባር የሆነው የወንጀል ድርጊት ከመፈጸሙ በፊት በወንጀል መከላከል ረገድ የንቃተ-ህግ ትምህርት በመስጠት ወንጀልና የወንጀል ስጋቶችን በመቀነስ የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት የመጠበቅ ስራ ሲሰራ የቆየ ሲሆን ህብረተሰቡ የወንጀል አስከፊነትን አውቆ ለመከላከል የራሱን ድርሻ እንዲወጣ

የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሲተገበር መቆየቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ወንጀሎች ሲፈጸሙ ወንጀል ፈጻሚዎችን በህግ ፊት አቅርቦ ራሳቸውንና ሌሎችን ሊያስተምር የሚችል ተመጣጣኝ ቅጣት የማስቀጣት ስራ ሲከናወን በመቆየቱ ምክንያት የዞኑ ሕብረተሰብ በፍትህ አስተዳደሩ ላይ ሊኖረው የሚገባውን አመኔታ በየጊዜው እንዲጨምር ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

አቃቤ ህግ የወንጀል መዛግብትን መርምሮ ውሳኔ ከመስጠት አንጻር ያለውን የማስቀጣት ምጣኔ አፈፃፀም ስንመለከት በ10ሩ ዓመት ውስጥ በቀጥታ ክስ 98% ለማድረስ ታቅዶ 98.37 %፣ በዐቃቤ ህግ ይግባ 95% ለማድረስ በዕቅድ ተይዞ በዐቃቤ ህግ ይግባኝ 85.33 % በፍርደኛ ይግባኝ 96.28%፣ መፈፀም ተችሏል፡፡የማቋረጥምጣኔን 1%ለማድረስ ታቅዶ አፈፃፀሙም 6.27 % ነው፡፡ የማስቀጣት ምጣኔ አፈፃፀሙ ጥሩ የሚባል ቢሆንም በየዓመቱ ከተያዘው ዕቅድ አንፃርመድረስ ያልተቻለ በመሆኑ ለመፈፀም የሚያስችልና ተደራሽ ዕቅድ አዘጋጅቶ መስራት ይኖርበታል፡፡ በአጠቃላይ በመንግስት እና ነፃ የህግ ድጋፍ ለሚሹ አካላት በፍርድ ቤት ስንከራከርባቸው ከነበሩ መዛግብት ውስጥ የማሸነፍ አቅም አፈፃፀም በጥቅል ስንመለከት በ10ኛው ዓመት መጨረሻ ላይ 97% ለማድረስ ታቅዶ በመዝገብ 85.9 % ሲሆን በገንዘብ መጠን 85.24 % ተከናውኗል፡፡ አቤቱታን በተመለከተ በ10 ዓመት ውስጥ ብዛት ያላቸውን አቤቱታወች የቀረቡ ሲሆን 100% ለማከናዎን ታቅዶ 100 % ለሚሆኑት ምላሽተስጥቷል፡፡ ሆኖም ዐቃቤያነ ህግ ትዕዛዝ በሰጡባቸው አቤቱታዎች እስከ መጨረሻው አፈጻጸማቸውን በመከታተል ረገድ ውስንነቶች ስለሚታዩ ወደፊት በትኩረት ሊሰራ ይገባዋል፡፡

## ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሐብት ልማት

በመልካም አስተዳደር ዘርፍ ከሚጠቀሱ ተግባራት መካከል አንዱ የሲቪል ሰርርቪስ ተግባራት ሲሆን የሲቪል ሰርቫንቱንም ሆነ በዘርፉ ያሉ የመለካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት እና የዘርፉን የሰዉ ሃይል ብቃት እና የመተግበር አቅም በየጊዜዉ ለማዳበር በዘርፉ የሚከናወኑ ተግባራትን በብቃት መወጣት ያስፈልጋል፤ በመሆኑም ባለፉት አስር አመታት ከተከናወኑ ተግበራት መካከል የተጠና ሰነድን ስንመለከት በመጀመሪያዉ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ጊዜ በ2007 ዓ.ም ብቻ 2 ሰነዶችን ለማጥናት ታቅዶ 2 ማጥናት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 100% ሲሆን በተመሳሳይ ከ2010-2012ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ባሉት አመታት 3 ሰነዶችን ለማጥናት ታቅዶ ክንዉን 3(100%) ማጥናት ተችሏል በዚህ ዘርፍ የተሰራዉ ስራ

አበረታች ቢሆንም በአንዳንድ አመታት የታየው የአፈጻጸም መቆራረጥ ለወደፊት ሊስተካከል የሚገባዉ ይሆናል፡፡

የዜጎችን እረካታ በመቶኛ ስንመለከት ከ2006-2007ዓ.ም በሁለቱ አመታት በአማካይ 87.2% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ ከ2008-2012ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በአማካይ ወደ 88.7% ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ ስራዊት የገነቡ ተቋማትን ስንመለከት ከ2006-2007ዓ.ም ባሉት ሁለት አመታት በአማካይ 80.75% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ ከ2008-2012ዓ.ም በነበሩት አመታት በአማካይ ወደ 76.67% ዝቅ ያለ በመሆኑ ለወደፊት ትኩረት የሚሻ ጉዳይ እንደሆነ ያሳያል፡፡ የተፈጠረ ግንባር ቀደም ባለሙያ እና አመራርን በተመለከተ ከ2006-2007ዓ.ም ባሉት ሁለት አመታት በአማካይ 75% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ ከ2008-2012ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በአማካይ ወደ 85.2% ከፍ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ የታዉ መሻሻል አበረታች ሲሆን ለወደፊት በዚሁ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ የስራ እድል የተፈጠረላቸዉ የመንግስት ሰራተኞችን ስንመለከት ከ2006-2007ዓ.ም ባሉት ሁለት አመታት በአማካይ 75% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ ከ2008-2012ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በአማካይ 98.7% ማሳካት የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘርፍ የታየዉ መሻሻል ዉጤታማ ነበር፡፡

## የመንግስት ኮሙኒኬሽን ስራችን

በዞናችን እንደ ኮሚዩኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ ባለፉት ሁለት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት (ከ2003-2012) በሰላም በልማትና በመልካም አስተዳደር ተግባራት፣ በዋና ዋና አገራዊ  እና ክልላዊ ጉዳዮች መግባባት የመፍጠር እንዲሁም የዞኑን ሁለንተናዊ ገፅታ የመገንባት ስራዎችን አብዛኞችን ማሳካት ተችሏል፡፡ **የቴክስት ዜና** ባለፉት 10 ዓመታት በዞን ወረዳና ከ/አስተዳደር ደረጃ 66,976 የቴክስት ዜናዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ እነዚህ ዜናዎች በዞኑ ላሉ ሚዲያዎች እንዲሁም የአካባቢ ሚዲያዎችን ጨምሮ በሌሎች ሜኒስትሪም (ሀገራ አቀፍ) ሚዲያዎች አየር ላይ የዋሉ ናቸው፡፡

**የምስል ዜና ዝግጅት** በተመሳሳይ ባለፉት 10 ዓመታት በዞን ወረዳና ከ/አስተዳደር ደረጃ 15,371 የምስል ዜናዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ እነዚህ ዜናዎች በዋናነት የአማራ ብዙሃን መገናኛ ድርጅትን ጨምሮ በሌሎች ሐገር አቀፍ ሚዲያዎች ተልከው አየር ላይ እንዲውሉ የተደረገ ሲሆን  ዜናዎች የአካባቢ ሚዲያዎች ጨምሮ በዋናነት በቲቪ

ፓርክ አማካኝነት ለአካባቢው ህብረተሰብ ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ **ለአካባቢ ማስተማሪያ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ዝግጅትን በተመለከተ፡-** ባለፉት 10 ዓመታት 1069 የቴሌቪዥንፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 110% ማከናወን ተችሏል፡፡ እነዚህም ፕሮግራሞች በአካባቢ ቲቪ ፓርክ አማካኝነት ለማስተማሪያነት እንዲጠቀሙባቸው ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡**የተዘጋጁ ዜናዎችን ሚኒ ሚዲያን ተጠቅሞ ማስተላለፍን በተመለከተ፡-** ባሳለፍነው የእቅድ ዘመናት በወረዳና ከ/አስተዳደር ደረጃ 21,753 ዜናዎችን ሚኒ ሚዲያን ተጠቅሞ ለማስተላለፍ ታቅዶ139% ማከናወን ተችሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተሰሩ ዜናዎችን ማህበራዊ ሚዲያን በዋናነት ፌስ ቡክን ተጠቅሞ ለህብረተሰቡ አወንታዊ መረጃ ተደራሽ ለማድረግ በተደረገው ጥረት ተቋሙ እስከ ወረዳ ባለው አደረጃጀት 26,979 መረጃዎችን ለማሰራጨት ታቅዶ ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

## 7. የነበሩ ጥቅል ተግዳሮቶች

### በኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ ፣

- ባለፉት 10 አመታት በግብርናው ዘርፍ ያጋጠሙን ችግሮች ዘርፈ ብዙ ቢሆም ዋና ዋና ዋናዎቹ ግን ወደ ዘመናዊ ሜካናይዜሽን የእርሻ ሥራ ለመግባት የቴክኖሎጅ አቅርቦት ችግር እና የግብአት እጥረቶች የዘርፋ ማነቆዎች ነበሩ፡፡

- ምርትና ምርታማነትን በተመለከተ ጥቅል ምርቱ ከአመት አመት እያደገ ቢመጣም ከህብረተሰቡ ፍላጎት አኳያ በቂ ባለመሆኑ የገበያ መረጋጋት ላይ በቂ ሚና መጫዎት ሳይችል ቆይቷል፡፡
- ባለፋት 10 አመታት የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ላይ በከፍተኛ የህብረተሰብ ተሣትፎ ተግባሩ ሲፈፀም መቆየቱ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በርካታ ለውጦች ማምጣት ቢቻልም የአረንጓደ ልማት እንድሁም በአፈርና እርጥበት እቀባ ዙሪያ የተሠሩ ሥራዎች ህብረተሠቡ በዘላቂነት ማሥቀጠል ላይ ውስን ችግሮች የሚታዩ በመሆኑ ለቀጣይ ለችግሩ መፍትሄ ማስቀመጥ አስፈላጊ ይሆናል፡፡
- በዞናችን በርካታ የውሃ ሃብት እንደመኖሩ መጠን የመስኖ እርሻ ሥራ አነቃቂ ተግበራቶች ያሉት ቢሆንም አሁንም ግን የዘርፋ ማነቆ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ የዚህ መሰረታዊ ችግር ደግሞ የአመለካከት ሽግግር ማምጣት አለመቻል ነው፡፡

- ኢትዮጵያ በእንስሣት ሀብታችን ከአፍሪካ ቀዳሚ ሀገር ብትሆንም ካለው የእነስሳት ሀብት አኳያ ከዘርፉ የተሻሻለ ምርት ሳይገኝ ቆይቷል፡፡ ለዚህ ደግሞ የመኖ አቅርቦት እጥረትና ከባህለዊ አሠራር የተላቀቀ አለመሆኑ ለዘርፉ ትልቅ ማነቆ ሆኖ ይታያል፡፡
- ከምግብ ዋስትናና አደጋ መከላከል ዘርፍ አኳያ በርካታ ተግባራት የተከናዎኑ ቢሆኑም ዘርፉ የቅድመ አደጋ ሥጋት ትንተና እና ትንበያ ስራ በሚፈለገው ልክ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ ሠፊ ችግሮች ገጥመውት ቆይቷል፡፡ ይህም በመሆኑ አርሶ አደሩ የአየር ንብረት መዛባት እና የዝናብ እጥረት በሚከሠትበት ጊዜ ዘርፉ በርካታ ችግሮች ገጥመውት እንደነበርና የ2008ዓ.ም ተፈጥሮ የነበረው ኢሊኖ ምርት በእጅጉ የቀነሰበትን በምሳሌነት ማየት በቂ ነው፡፡
- በሥራና ሥልጠና ዘርፍ ዋናውን ድርሻ የሚይዘው የስራ እድል ፈጠራ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ብዙ ተግባራት ቢከናወኑም በዞናችን ካለው ወጣቶች ቁጥር አንፃር የተፈጠረው የሥራ እድል በቂ አለመሆኑ በዘርፉ ዋናው ችግር የማህበረሠቡ የአመለካከት ችግር እንዳለ ሆኖ የመሠረተ ልማትና በቂ የፋይናንስ ብድር አቅርቦት አናሳ መሆን ዋና ማነቆ ሆኖ ዘልቋል፡፡
- ዞኑ በርካታ የቱሪስት ሀብቶች ያሉት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ቢሆንም ዘርፉ ካገጠሙት ችግሮች ውስጥ በቂ የመሠረተ ልማት እና የሆቴል አቅርቦት እጥረት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡
- በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመት ዘርፍ ከታዩ ማነቆዎች መካከል በአንድ በኩል ለኢንቨስትመንት የሚሆን መሬት ከሶስተኛ ወገን ነፃ አድርጎ ለባለሀብቶች ማስረከብ አለመቻልና በሌላ በኩል መሬት የተረከበው ኃይል በውሉ መሰረት ወደ ስራ ከመግባት ይልቅ አጥሮ ማስቀመጥ ከዚህም ሲያልፍ እሴት ሳይጨምር መሬት መቸብቸብ የተለመደ አሰራር እየሆነ መጥቷል፡፡

## በማህበራዊ ልማት ዘርፍ ፣

- በጤናው ዘርፍ በርካታ ተግባራቶች የተከናወኑ ቢሆንም ባለፋት አሥር አመታት በውጭ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት በቂ የመድሃኒት እና የህክምና ማቴሪያል እጥረት ተከሥቷል፡፡ በተመሣሣይ የማህበረሠብ አቀፍ የጤና ተደራሽነትና የጤና ትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ላይ ገና ብዙ መሠራት ይጠበቃል፡፡
- በትምህርት ዘርፍ የትምህርት ተደራሽነትና ሽፋን ላይ በቂ ሥራ ቢሠራም የትምህረት ጥራትን ከማረጋገጥ አኳያ ሠፊ ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

### መሠረተ-ልማት ዘርፍ ፣

- ከመንገድ ተደራሽነት አንፃር ወረዳን ከቀበሌ ለማገናኘት የተያዘው ግብ ጥሩ ሂደት ላይ ቢሆንም አሁንም የመንገድ ጥራትና አገልግሎት ከመስጠት አኳያ ውስንነት የታየበት ነው፡፡ በሌላ በኩል በቂ የበጀትና ማቴሪያል አቅርቦት ባለመኖሩ የህብረተሰቡን መሰረታዊ ጥያቄ አልተመለሰም፡፡ እየተገነቡ ያሉ ኘሮጀክቶችም በተያዘላቸው ጊዜ ባለመጠናቀቃቸው የማህበረሠቡ ሌላ የመልካም አስተዳደር ችግር ሆኖ ቀጥሏል፡፡
- የውሃ ተደራሽነት በተመለከተ የንፁህ መጠጥ ወሃ አቅርቦት ተግበራት የተሻለ በሆንም ርቀት ባለቸው ወረዳዎችና ቀበሌዎች የህብረተሠቡን ጥያቄ ያልተፈቱ ችግሮች ሆነው ተስተውለዋል፡፡
- የከተማ ልማት ዘርፍ ማህበረሠቡ ካለው የከተሜነት ፍላጎት አኳያ በርካታ ማህበረሠብ ከገጠር ወደ ከተማ በከፍተኛ ቁጥር እየጨመረ ነው፡፡ አሁን ያሉት ከተሞች ህዝቡን መሸከም የሚችሉ አለመሆናቸውና የመሰረተ ልማት አቅርቦቱ ካለው ፍላጎት ጋር ሲነፃፀር የማይጣጣሙ ናቸው፡፡

### መልካም አስተዳደር ፣

- ከህግ ማስከበር አንፃር ባለፋት 10 አመታት በርካታ ተግባራት የተፈፀሙ ቢሆንም በተለይ ከህገ-ወጥ ንግድና ሙስናን በመዋጋት ረገድ ውስንነት ታይቷል፡፡ ያለ እጅ መንሻ ጥራት ያለው አገልግሎት መስጥት አልተቻለም፡፡ በዚህ ምክንያት የተማረረ ህዝብና በመንግስት ላይ አመኔታ የሌለው እየሆነ መጥቷል፡፡

## 8. የ10 አመቱ እቅድ

### 8.1 የልማት እቅዱ መነሻ ሀሳቦች

### ዞናዊ የረጅም ጊዜ የልማት ራዕይ

የቀጣይ 10 ዓመት መሪ የልማት እቅዱ ዓላማዎች ፣ የትኩረት አቅጣጫዎችና ግቦች የተረጋጋ ኢኮኖሚ እንዲኖር ማድረግ፣ የኢኮኖሚው ዕድገት ቀጣይነትና ዘላቂነትን ማረጋገጥና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት ናቸው፡፡

## የቀጣይ አስር ዓመታት የልማት ዕቅዱ ዓላማዎች

- በቀጣይ አስር ዓመታት የክልሉ ኢኮኖሚው በአማካይ 10.4 በመቶ ለማሳደግ የተያዘውን ግብ ዞኑ የበኩሉን ድርሻ እንዲጫዎት ማድረግ ፣
- አነስተኛ የአምራች ዘርፋን ምርታማነትና የምርት ጥራት በማሻሻል ተወዳዳሪነትን ማጎልበትና መዋቅራዊ ሽግግር ማረጋገጥ ፣
- የህዝቡን የማስፈፀም አቅም በመገንባት የልማት ተሳታፊነት፣ ባለቤትነትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ፣
- በኢኮኖማ ያደገ ህብረተሰብ መፍጠር፣
- የቀጠናውን የአየር ንብረትና የአካባቢ ጥበቃን መሠረት በማድረግ ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ መሠረት መጣል ናቸው፡፡

## የልማት ዕቅዱ ምሰሶዎች (Strategic pillars)

- ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገትና የጋራ ብልፅግና ማረጋገጥ ፣
- የኢኮኖሚ ምርታማነትንና ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ ፣
- የቴክኖሎጂ አቅም መገንባት ፣
- የዘላቂ የእድገት እና የልማት ፋይናንስን ማረጋገጥ ፣
- የግሉን ዘርፍ የኢኮኖሚ እድገት መሪነት ማረጋገጥ ፣
- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት ፣
- የልማት ተጠቃሚነት እና ማህበራዊ አካተችነትን ማረጋገጥ፣
- የፍትህ ተደራሽነት እና ውጤታማ የህዝብ አገልግሎት ማስፈን ፣
- ዘላቂ የሰላም ግንባታ እና ጠንካራ መዋቅራዊ ትብብርን ማረጋገጥ ፣

## 8.2. የልማት መሪ እቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች

### 8.2.1. ጥራት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥ

በደ/ወሎ ከፍተኛ የሆነ የኑሮ ውድነት እና የሥራ አጥነት ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ እንዲሁም አምራች ዘርፎች በተሟላ መልኩ በሙሉ አቅም ተግባሮቻቸውን እንዳይፈፅሙ የውጭ ምንዛሪ እና የብድር አቅርቦት ማነቆ ሆኖ ይገኛል፡፡ ለዚህም መሠረታዊ ችግር የሆነው የምርታማነት ችግር እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ምርታማነትን ማረጋገጥ በመሪ እቅዱ ወሳኝ ጉዳይ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ለዚህም አቅርቦትን ወደሚያሳድጉ አምራች ዘርፎች በመሸጋገር በትኩረት

ይሠራል፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገት ጥራቱ በፍትሃዊነቱ፣ በቀጣይነቱ፣ በምርታማነቱ፣ በአጠቃላይ በመዋቅራዊ ለውጥ አረጋጋጭነቱ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል፡፡ በዞኑ በቀጣይ የሚመዘገበው የኢኮኖሚ እድገት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትንና ደህንነታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ለዘመናዊ ግብርና፣ አምራች ኢንዱስትሪ፣ ቱሪዝም፣ ማዕድንና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፎች ትኩረት ይሰጣል፡፡ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ለእድገት ምንጭ ዘርፎች ትኩረት በመስጠት የሚሠራ ይሆናል፡፡

በግብርናው ዘርፍ የሰብል ምርታማነትን መድረስ ይገባው ከነበረው የምርታማነት ድንበር የማድረስ ሥራ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን፣ የመካናይዝድ እርሻን እንዲሁም የመስኖ ልማትን ለማዘመን ትኩረት ይሠጣል፡፡ የእንስሳትን ምርታማነት የሚያሳድጉ የመኖ ልማት፣ የዝርያ ማሻሻልና የጤና ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

የግብርና እድገትን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለማረጋገጥ የመሬት አቅርቦትና አጠቃቀም ጉዳይ ወሳኝ ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ በመሆኑ መሬትን የላቀ ልማታዊ አስተዋጽኦ ለማበርከት በሚያስችል አኳኋን የመጠቀም ጉዳይ በትኩረት የሚሠራ ይሆናል፡፡ እንዲሁም የግብርና ልማትን ቀጣይነት ባለው መልኩ የማሳደግና ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የጥሬ እቃ አቅርቦት መሠረት ሊሆን የሚችለው ዞኑ ያለውን ተጨባጭ የልማት እድል በመለየት እነዚህን የልማት እድሎች አሟጦ ለመጠቀም በሚያስችል መንገድ ተለይቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

ሌላው የማዕድን ዘርፉ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ያለንን ሀብት አሟጠን ወደ ማምረት ካለማስገባት ጀምሮ በትክክል የአካባቢያችንን የማዕድን ሀብት በጥናት የመለየትና ባለሀብቶችን የመሳብ እንዲሁም ህገወጥነትን መልክ ማስያዝ አለመቻላችን ትልቅ ጉድለት ነው፡፡ በመሆኑም የዘርፉን ሁለንተናዊ አቅም በማሳደግ የጥናት ስራ በማካሄድ ወደ ተሟላ የማምረት ሂደት ውስጥ በማስገባት ከዘርፉ የሚገኘውን የላቀ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ በመሆኑም በአምራች ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ተግባራት ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚከናወኑ ሲሆን ለዚህም የግሉ ዘርፍ በዋነኛነት ተሳታፊ የሚሆንበትን ሁኔታዎች የማመቻቸትና ከውጭም ይሁን ከአገር ውስጥ ወደ አካባቢያችን የሚመጡ ኢንቨስተሮችን ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት በትኩረት ይሠራል፡፡

### 8.2.2. የሴቶችንና የወጣቶችን ተሳትፎ፣ ተጠቃሚነትና ብቃት ማሳደግ

የልማት መሪ ዕቅዱ ሊሳካ የሚችለው ያለንን የሰው ሀይል ወደ ልማት ማስገባት ሲቻል ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ወጣቶችና ሴቶች በልማቱ ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ የማይታለፍ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የወጣቶችንና ሴቶችን አቅም የመገንባት፣ አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ የማመቻቸት፣ የተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን የማስፋፋት እንዲሁም የሥራ እድሎችን መፍጠር የሚያስችሉ ተግባራት ይከናወናሉ፡

ዞኑ እያከናወነ ያለው የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገትና ድህነትን የማስወገድ እቅድ ተግባራዊ በማድረግ የፆታ እኩልነትን በማረጋገጥ የሴቶችና ወጣቶችን መብት እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ማስጠበቅ ቁልፍ የልማት ጉዳይ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

### 8.2.3. ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት

ሁሉን-አቀፍ ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማት መገንባት ወሳኝ ነው፡፡ በዓለም ደረጃ በተከሰቱ የአየር ንብረት ለውጦች ሳቢያ በህዝብና በንብረት ላይ በርካታ አደጋዎች እየተከሰቱ መምጣታቸው ይታወቃል፡፡ ይህንን ሁኔታ ለመቀየር እና የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችል የኢኮኖሚ ስትራተጂ በአገር ደረጃ ተቀርጾ ወደ ስራ በመገባት ላይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በዞናችን ተጨባጭ ሁኔታ በተፋሰስ ልማት በህዝባዊ ንቅናቄ ሰፊ ጥረት የተደረገና አጥጋቢ ውጤትም እየተመዘገበበት ያለ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በመሪ የልማት ዕቅዱ ዘመንም ይህ መልካም ጅምር በተለየ ትኩረት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በዚህም የተጀመሩ ተግባራትን በሁሉም የዞኑ አካባቢዎች ከማስፋት ባሻገር የተፋሰስ ልማት በተሰራባቸው አካባቢዎች ያሉ የተለያዩ ስትራክቸሮችን ማጠናከሪያ ተጨማሪ ስራዎችን በመስራት ዘላቂነት እንዲኖራቸው ማድረግና ጥቅም መስጠት ወደ ሚችሉበት ደረጃ ማሸጋገር፣ የደን ልማት ስራዎችን ማስፋትና ማጠናከር፣የኢነርጂ ቆጣቢ ምድጃዎችንና ባዮጋዝ ማብለያዎችን በስፋት ስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣ በገጠር የኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራምን ስራ ላይ ማዋል እና በአገር ደረጃ ከተቀረጹ ፕሮግራሞች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት በስፋት መፈጸም ይጠይቃል፡፡

### 8.2.4. የዞኑን አቅም መሠረት ያደረገ ቀልጣፋ ኢኮኖሚ መገንባት

በዞናችን የሚከናወኑ የልማት ሥራዎች የአካባቢን ፖቴንሻል መሠረት ባደረገ መልኩ እንዲሆን ይሠራል፡፡ ዘመናዊ የግብርና ልማት ሥራዎች በሰብልም ሆነ በእንስሳት ሃብት ልማት አቅሞች እንዲለዩ በማድረግ ያለውን ከባቢያዊ ፀጋ ወደ ላቀ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ በማሸጋገር ዞኑ ለክልሉ የኢኮኖሚ ለውጥ የሚኖረውን ሚና የማሳደግ እንዲሁም የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎች የአካባቢን ሀብት መሠረት በማድረግና ዞኑ የሚኖረውን ተነፃፃሪ ተጠቃሚነት እንዲሁም ጥሬ እቃንና የገበያ እድልን መሠረት በማድረግ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መግባት ያስፈልጋል፡፡

### 8.2.5. የመንግሰትን የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም በመገንባት እና የህዝቡን ተሳትፎ በማጐልበት ፍትህንና መልካምአስተዳደርን ማስፈን

የአንድን መንግስት ውጤታማነት ከሚወስኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ ተልዕኮውን በአግባቡ የሚፈፅም ተቋም የመኖር ወይም ያለመኖር ጉዳይ ነው፡፡ ውጤታማ ተቋም እንፍጠር ሲባል የመጀመሪያው ጉዳይ ለተቋማቱ ብቁ መሪ ፈጻሚ ባለሙያ መፍጠር ነው፡፡ ብቁ መሪና ተነሳሽነት  ያለው ባለሙያ ያለው ተቋም ውጤታማነቱ ከፍተኛ በመሆኑ በዞናችን ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

ሌላው ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማምጣትና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በሁሉም ደረጃ የሚገኘውን የማስፈፀም አቅምን ማሳደግ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ሲሆን  የማስፈፀም አቅም በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት የበቃ የሰው ኃይል እንዲፈጠር ማድረግ፣ በዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን የሚሰጡ አገልግሎቶች ደረጃቸውን የጠበቁ፣ ስታንዳርድ የወጣላቸውና ለአካባቢው ነዋሪ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ትኩረት የሚሰጣቸው ነጥቦች ናቸው፡፡

ለውጡ የአገልግሎት ቅልጥፍናን፣ የሥራ ውጤታማነትን፣ ተጠያቂነትንና ግልፀኝነትን ባጣመረ አኳኋን እንዲፈፀም ለማድረግ ይሠራል፡፡ ከዚህም አኳያ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ የተሠማራውን የሰው ኃይል ለማብቃት ልዩ ትኩረት ይሠጣል፡፡ የህግ የበላይነትን ለማስፈን የህግ አስከባሪ ተቋማትን በአመለካከት፣ በቁሳቁስና በሰለጠነ የሰው ሃይል የማጠናከርና የፍትህ አስተዳደር ስርዓቱን  አገልግሎት ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ በሚያሰችል መልኩ ማጠናከር ተገቢ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ የመንግስት ጉድለትን የሚሞላ ስርዓት መዘርጋት፣

ኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገትን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ስትራቴጂዎች፣ የህግ ማእቀፎች እንዲዘጋጁ ማድረግና ዘላቂነት ያለው የአሠራር ስርዓት መዘርጋት የሚሉት በትኩረት የሚሠሩ ይሆናል፡፡

## 9. የ10 ዓመቱ መሪ የልማት እቅድ የትኩረት መስኮች

ለዞኑ የኢኮኖሚ ዕድገት ኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግር መረጋገጥ እንዲሁም ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ ከመገንባት አንጻር ያላቸውን የጎላ ድርሻ መሠረት በማድረግ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ልዩ ትኩረት የሚደረግባቸው መስኮች ተለይተው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 9.1. ብዝሃ ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮች ልማት ላይ ማተኮር

እስካሁን ከነበረው በተለየ መልኩ በአንድ ዘርፍና የዕድገት ምንጭ ከማተኮር ይልቅ ወደ ብዝሃ-ዘርፍና ብዝሃ የገቢና የዕድገት ምንጭ ላይ ማተኮር የሚፈለገውን የኢኮኖሚ ዕድገትና መዋቅራዊ ሽግግር ከማምጣት አንጻር እንደ ወሳኝ ጉዳይ ታይቷል፡፡ እነዚህም ግብርናውን ማዘመን፣ ለአምራች ኢንዱስትሪው ትኩረት ሰጥቶ መሥራት፣ ማዕድን፣ ቱሪዝምና የከተማን ዕድገት መሠረት ያደረገ የአይሲቲ (ICT) ዘርፍ እንደ ተጨማሪ የዕድገት እና የሥራ ዕድል ምንጮች ተደርገው ተለይተዋል፡፡

### 9.2. የዘመናዊ ግብርና ልማት

የግብርና ዘርፍ በአብዛኛው በአነስተኛ አርሶ አደሮች የሚካሄድ ሲሆን ከ75 በመቶ በላይ የሚገመተው ህዝብ መተዳደሪያው የሆነና ከፍተኛ ድርሻው በሰብል ልማት የተያዘ ሲሆን ምርታማነቱን ሲታይ 22 ኩንታል በሄክታር ሲሆን ይህም ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የአርሶ አደሩን ገቢ በማሳደግ ረገድ እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የነበረው ፋይዳ እንዲሁም አስተዋጽኦ በጣም አናሳ ነው፡፡ ከዚህ ዘርፍ የሚጠበቅ ሚና ሲታይ በምግብ እህል አቅርቦት በራስ አቅም ከማሟላት ባለፈ ኢኮኖሚውን የማሳደግ፣ ለኢንዱስትሪው በግብዓትነት ጥሬ ዕቃዎችን የማቅረብ፣ ገበያ የመፍጠር እና የውጭ ምንዛሬ የማስገኘት፣ የስራ እድል የመፍጠር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም ዘርፉ በልማት መሪ ዕቅዱ ማነቆዎቹ ተፈተውለት ወደ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ እንዲሸጋገር ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም አርሶ አደሩ ፈጣን የሆነ የምርትና ምርታማነት ዕድገት በማምጣት የዘርፉ ዋና የዕድገት መሠረት ሆኖ እንዲቀጥል ማስቻል፣የመስኖ ልማትን ማስፋፋት፣አስፈላጊ የሆኑትን የግብርና ግብዓቶችንና ቴክኖሎጂዎችን በማምረትና በማቅረብ

የግብርናውን ዘርፍ መደገፍ በመሪ ዕቅዱ ትኩረት የሚደረግባቸው ዋንኞቹ የትኩረት መስኮች ናቸው፡፡

## 9.3. የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት

የኢኮኖሚ ሽግግርና ያለዘመናዊ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የማይታሰብ ሲሆን በተለይም እያደገ የመጣውን ህብረተሰብ ምርት ፍላጎት ለመሸፈን፣ የስራ ዕድል ለመፍጠር፣ ግብርናን ለማዘመንና በቴክኖሎጅ ተወዳዳሪ ለመሆን አዳጋች ይሆናል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የግብዓት አቅርቦት፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦት፣ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ እና የፋይናንስ አቅርቦት ችግሮች በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው፡፡

ስለሆነም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን እድገትና አቅምን ማሳደግ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

## 9.4. የማዕድን ሀብት ልማት

በዞኑ ውስጥ የሚገኘውን እምቅ የማዕድን ሀብት እንዴ ላይምስቶን፣ ጂፕሰም፣ድንጋይ ከሰል፣ ሲልካ ሳንድ፣ ኦፓል፣ነዳጅ እና ጃስፐር ያሉ የከበሩ ማዕድናትን በማልማት ጥቅም ላይ እንድውሉ ሰፊ ስራ ይጠይቃል፡፡ ይገኛሉ፡፡ ዘርፉ ምንም እንኳን በበርካታ ፈተናዎች የታጠረ የማዕድን ልማት ዘርፍ ቢሆንም በቀጣይ የልማት መሪ እቅዱ ዓመታት በሚደረግ ሰፊ ስራና ልዩ ትኩረት ከዘርፉ ከፍተኛ ፋይዳ ይጠብቃል፡፡

## 9.5. የቱሪዝም ልማት

የቱሪዝም ሀብት ለውጭ ምንዛሬ ግኝት፣ ለአገልግሎት ዘርፎች በተለይም ለሆቴል ኢንዱስትሪ እና ለትራንስፖርት አገልግሎቶች ልማት አስተዋጽኦው በጣም ከፍተኛ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ለሥራ ዕድል ፈጠራ ብሎም ድህነትን ለመቀነስ የሚጫወተው ሚና የጎላ ነው፡፡

ዞናችን ዓይነተ ብዙ የታሪክ፣ የባህልና የተፈጥሮ መዳረሻዎች (የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ሃብቶች) ያሉት አካባቢ ነው፡፡ ምንም እንኳን ዞናችን በርካታ የቱሪዝም ሃብቶች ቢኖሩትም ከዘርፉ የሚፈለገውን ያህል ጥቅም እያገኘ አይደለም፡፡ ስለሆነም በዘርፉ በእውቀት፣ በክህሎት እና በአደረጃጀት የተቃኘ አገልግሎት ስርዓት መዘርጋት ይገባል፡፡

## 9.6. የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት

ኢኮኖሚው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ እየተሰጠ ያለው ትኩረት አናሳ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህም አንፃር የሚያስፈልጉ የመሠረተ ልማት ዓይነቶችን በአግባቡ በመለየት ያሉትንና የተጀመሩትን ተቋማት የማጠናከርና የማስፋፋት ሥራ የሚሠራ ይሆናል፡፡

## 9.7. ዘላቂ የከተማ ልማት

በዞኑ የስነ ህዝብ ትንበያ መሰረት የክልሉ የህዝብ ብዛት እየጨመረ የሚገኝ እንደሆነ መረጃው ያመላክታል፡፡ በቀጣይ የመሪ እቅዱ ዓመታት በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚጨምርም ይገመታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከገጠር ወደ ከተማ ያለው ፍልሰት በየዓመቱ እየጨመረ የሚገኝ ሲሆን ከተሞችን በስርዓቱ ለመምራትና ህዝቡን ከከተማው ክፍለ ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለማድረግ በማያስችል መልኩ የስነህዝብ ሁኔታው እየተቀየረ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ባለፉት10 ዓመታት በገጠር በትምህርት መስፋፋት ምክንያት የከተማ ምጣኔ እየጨመረ ሄዷል፡፡ በመሆኑም ለመኖሪያ እና ለስራ ምቹ የሆኑ ዘላቂ ከተሞችን በዕቅድ መምራት ለነገ የማይባል ጉዳይ በመሆኑ የከተማ ልማት አንዱ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ዘርፍ ይሆናል፡ ፡ ሚዛናዊ የሆነ የከተማ-ገጠር ትስስርም እንዲኖር በትኩረት ተይዞ ይሰራል፡፡

በዞኑ የከተሞች ስሪት እና የአከታተም ሁኔታ በሥርዓት ያልተመራና በዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ስለሆነም ከተሞች ለአምራች ዘርፎች እድገት፣ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት፣ ለሥራ ስምሪትና ለነዋሪዎች ምቹ እንዲሆኑ በዘመናዊ የከተማ ዕቅድ የሚመራ የከተሞች አስተዳደር ሥርዓት ያስፈልጋል፡፡

## 9.8. መሠረተ ልማት

ዞኑ በመሠረተ ልማት መስፋፋት ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችን በመቅረፍ በዘርፉ የሚከናወኑ ኢንቨስትመንቶችን በከፍተኛ መጠን መጨመር፣ የኢኮኖሚ እድገት እንዲፋጠን በተለይ የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ በአግባቡ ለመምራት የተሟላ መሠረተ ልማት እንዲኖር ማድረግ በትኩረት ይሠራል፡፡ ለዚህም መሠረተ ልማቶችን የትራንስፖርት፣ የመገናኛና የሀይል አቅርቦትን በጥራትና በተወዳዳሪ ዋጋ ማቅረብ እንዲሁም ለመንገድ፣ ለኢነርጂ፣ ለመስኖ፣ ለመጠጥ ውሃ፣ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማቶች እንዲሁም ለማህበራዊ መሠረተ ልማቶች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በተለይ በመንገድ መሠረተ ልማት

ዙሪያ ዞኑ ከወረዳዎች ጋር እንድሁም የገጠር ቀበሌዎችን ደረጃቸውን በጠበቁና ክረምት ከበጋ በሚያገለግሉ መንገዶች ከዋና መንገድ ጋር የማገናኘት ሥራ አንዱ የትኩረት መስክ ነው፡፡

የዞኑን የውሃ ሽፋንን ማሳደግ፣ የመስኖ ግንባታዎችን ለማስፋፋት ይሠራል፡፡ የኮንስትራክሽን ዘርፉ የሰው ኃይልን በብዛት የሚጠቀም፣ ጤናማ ውድድር የሰፈነበትና የግሉ ዘርፍ ከፍተኛ ሚና የሚጫወትበት፣ ዘርፉ ከሙስና በፀዳ መልኩ በሥርዓት እንዲመራ ይደረጋል፡፡

## 9.9. የሰው ኃብት ልማትና የስነ ህዝብ ትሩፋት

ጥራት ያለው ትምህርት እና የጤና ስርዓትን መገንባት ለሰው ኃብት ልማቱ ድርሻው ከፍተኛ እንደሆነ አያጠያይቅም፡፡

የትምህርት ሽፋናችን እያደገ ያለ ቢሆንም የተወሰኑት ህጻናት በትምህርት ገበታ ላይ አይደሉም፡፡ በዚህ መሠረት ሁሉም በመዋዕለ ሕፃናት ደረጃና በ1ኛ ደረጃ ትምህርት የእድሜ ክልል የሚገኙ ህፃናት በሙሉ ትምህርት ቤት እንዲገቡ በማድረግ የትምህርት ሽፋንን የማሣደግ እንዲሁም ተገቢነትንና ፍትሀዊነትን የማስጠበቅ ሥራ በቀጣይም ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ ለትምህርት ጥራት ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በመሆኑም የትምህርት ተቋማትን የማስፋፋት፣ ለደረጃው የሚመጥኑ በቂ መምህራንን የማሟላት እንዲሁም የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ የሚቀንሱ ችግሮችን የማቃለል ተግባራት ማከናወን ይጠይቃል፡፡ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎች የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ለማስፋፋትና ለማጠናከር በሚያስችላቸው አግባብ እንዲሰለጥኑ ይደረጋል፡፡

በሌላ በኩልም የመሠረታዊ ጤና አገልግሎትን የማስፋፋትና የአገልግሎት ጥራትን የማስጠበቅ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የንፁህ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን እንዲሁም ስርዓተ-ምግብ የቀጣይ ዓመታትም የትኩረት መስኮች ናቸው፡፡ ማህበራዊ ተቋማትን ከማስፋፋት አንፃር ሁሉም የልማት ኃይሎች ከመንግስት ጋር በተቀናጀ አግባብ ርብርብ እንደሚያደርጉ ይጠበቃል፡፡

በመሆኑም መሰረታዊ የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ጣቢያዎችን በሁሉም የክልላችን አካባቢዎች ማስፋፋት፣ የጤና ተቋማቱን አገልግሎት የማሻሻልና ግብአቶችን የማሟላት ሥራም ትኩረት ተሰጥቶት የሚከናወን ይሆናል፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር የመሰረታዊ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት መሻሻልና በሽታን በመከላከሉ ስራ ላይ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ በትኩረት ይሠራል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ የሰው ኃይል ልማታችን የኢኮኖሚ ልማቱ ከሚጠይቀው አንፃር በጥራትም ሆነ በመጠን በማቅረብ በኩል ችግሮች ተስተውለውበታል፡፡ ስለሆነም በቀጣይ የመሪ እቅዱ ዓመታት የሰው ኃይል ልማት በወሳኝነት የሥራ ኃይሉ ጤናማ፣ የተማረና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም የሚችል እንዲሆን በማድረግ ይበልጥ ምርታማ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

## 9.10. ከስነ-ህዝብ ልማት

የአንድ ሀገር መሠረታዊ የሥነህዝብ ባህሪያት በአጠቃላይ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች እና በዜጎች ሁለንተናዊ የኑሮ ገፅታ ላይ ጉልህ ተፅእኖ አላቸው፡፡ በመሆኑም በመሪ የልማት ዕቅዱ ዘመን በዞኑ የህዝብ ዕድገት ምጣኔን ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በማጣጣም ከረጅም ጊዜ አኳያ ህዝብ የኑሮ ደረጃና አጠቃላይ ደህንነት ለማሻሻል የሥነሕዝብን መሠረታዊ ባህሪያት ከኢኮኖሚው አቅም ጋር ለማጣጣም የሚያስችል የሥነሕዝብ ባህሪያት ሁኔታ ተለዋዋጭነትን መሠረት በማድረግ የሚጠበቀውን ሁሉ መስራት ያስፈልጋል፡፡

## 9.11. ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ

ባለፉት ዓመታት የዞኑን ገቢ በማሳደግ ረገድ አበረታች ሥራዎች ሲሠሩ የቆዩ ቢሆንም ለልማት ከሚያስፈልገውን ወጪ ከማመንጨት አንጻር ሲመዘን የገቢ አሰባሰቡ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በቀጣይ የዕቅዱ ዓመታት የሚሰበሰብ ገቢን በእጅጉ የማሳደግና በራስ ገቢ ወጪን የመሸፈን አቅምን ማጎልበት ትኩረት የሚሠጠው ይሆናል፡፡ ለዚህም የታክስ አስተዳደሩን ማዘመንና የአገልግሎት አሠጣጡን ፈጣንና ቀልጣፋ የማድረግ፣ የህግ መዕቀፎችን መተግበር፣ ግንዛቤን የማሳደግ፣ በልማት ፋይናንስ የህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲጎለብት የማድረግ ሥራ እንዲሁም የታክስ ኦዲትን የማጠናከርና ተጠያቂነትን የማስፈን ሥራዎች በተጠናከረ መልኩ ይሠራሉ፡፡

# 10. የኢኮኖሚ ልማት አርፍ

## 10.1. ግብርና ልማት

### የግብርና ኤክስቴንሽን ኮምኒኬሽን ዘርፍ፤

**የዕቅዱዓላማ**

የተሻሻሉ አዳዲስ አሰራሮችን እና ቴክኖሎጅዎችን በማስተዋወቅ፣ በማስረፅ፣ፍላጎት በመፍጠርና የባህሪ ለውጥ በማምጣት የአርሶ አደሩን የአመራረት ዘዴ ዘመናዊ በማድረግ ገቢውን ማሳደግ።

**ስትራቴጅክ ግብ**

በሚቀጥሉት 10 አመታት ገበያ መር ተሳትፏዊ የኤክስቴንሽን አገልግሎትን በማጠናከርና የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን አርሶአደሮች 9,471,400ን ተጠቃሚ ማድረግ፤

**ግብ.1. የግብርናውን ዘርፍ ተወዳዳሪ ለማድረግ ተቋማዊ የመፈፀም አቅምን ማሳደግ**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

- በሁለተኛው ዕትዕ ዘመን መጨረሻ ካሉት 1076 ዲፕሎማ የቀበሌ ባለሙያዎችን 100% (1076) ወደ መጀመሪያ ዲግሪ ማሳደግ፤
- በ2ኛው የዕትዕ ዘመን  በግብርና ኮሌጆች 40 የነበረውን የደረጃ ማሳደግ 78 ለሚሆኑ የቀበሌ ግብርና ባለሙያዎችን በማሰልጠን ወደ ደረጃ  4 እና ዲግሪ ማሳደግ፣
- የመጀመሪያ ድግሪ ካላቸው 726 የቀበሌ ባለሙያዎች ውስጥ 200 ወደ ሁለተኛ ድግሪ ማሳደግ፤
- በሁለተኛው ዕትዕ ዘመን መጨረሻ 980 የነበረዉን በየደረጃዉ ያሉ የባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና የቀበሌ ባለሙያዎችን ቁጥር ወደ 1960 ማድረስ እና የወረዳ፣የዞን ባለሙያችን በየዓመቱ 160 ለሚሆኑት ባለሙያዎች ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ የሙያ ብቃት ምዘና እንዲወስዱ ማደረግ
- ለ2000 የቀበሌ ባለሙያዎች ተሳትፏዊ የግብርና ልማት ዕቅድ አዘገጃጀት ስልጠና መስጠት፤

- 220፣ የዞን እና የወረዳ ባለሙያዎች ቁጥር በድግግሞሽ 2000 ባለሙያዎችን አዳዲስ በሚወጡ ቴክኖሎጂዎችና አሠራሮች ዙሪያ አጫጭር ሥልጠና መስጠት፤
- በወቅታዊ የግብርና ልማት ተግባራት ግንዛቤ የተፈጠረላቸውን 479000 አርሶአደሮችን በየዓመቱ 505079 በማሳደግ በድግግሞሽ 5050790 ማድረስ፤
- በሁለተኛዉ ዕትዕ ዘመን መጨረሻ በስርዓተ ምግብ ዙሪያ በየቀበሌው በአማካይ 96 (በየዓመቱ 333,231 ለሚሆኑት አባወራ፣ እማወራና ባለትዳር ሴቶች) ስልጠና በመስጠት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 3,332,310 የሚሆኑ አርሶ አደሮች ተደራሽ ማድረግ፡፡
- በድግግሞሽ 22390 የአርሶአደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ኮሚቴዎችን ስልጠና መስጠት

**ግብ .2. የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

- በ2ኛው ዕትዕ ዘመን መጨረሻ የነበረውን 17086 የአባወራ እና እማወራ የልማት ቡድን ወደ 210090 ማሳደግ፣ የ1ለ5 አደረጃጀትን ደግሞ ከ83240 ወደ 922290 በማሳደግ በሁሉም የግብርና ልማት ተግባራቶች እንደ ሰራዊት እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ፤
- በ2ኛው ዕትዕ ዘመን መጨረሻ የነበረውን የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ቁጥር 1007238 ወደ 9471400 ማሳደግ
- በ2ኛው የዕትዕ መጨረሻ ዓመት 166576 የሙሉ ፓኬጅ አርሶአደሮችን ቁጥር በሚቀጥሉት አሥር ዓመት 3549985 ማድረስ፤
- በ2ኛው የዕትዕ ዘመን በአርሶአደር ማሰልጠኛ ተቋማት፣ በሞዴል አርሶአደሮች እና በተፋሰሶች ተሞክረው ውጤታማ የሆኑ 602 ምርጥ ተሞክሮዎችን የመቀመር እና ማስፋት ስራ ወደ 5230 ማሳደግ፤
- በ2ኛው ዕትዕ ዘመን መጨረሻ አመት 29225 የነበረውን የቤተሰብ ኃላፊዎች ቁጥር በየዓመቱ በአማካይ 34986 በማከናወን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 349886 (55%) የሚሆኑ አባወራዎች እና እማወራዎች የተመጣጠነ ስርዓተ ምግብ እንዲኖራቸው ማድረግ፤
- በ2ኛው ዕትዕ ዘመን መጨረሻ ዓመት የተከናወነውን 9843 የተለያዩ ሰርቶ ማሳያዎችን በየዓመቱ 15360 በማካሄድ በዕቅድ ዘመኑ 153609 ማድረስ

- በ2ኛዉ ዕትዕ ዘመን መጨረሻ 35000 የነበረውን የገበሬ በዓላትን ማዘጋጀት በዕቅድ ዘመኑ 177730 በማድረስ 23654275 አባወራዎች፣እማወራዎች፣ ባለትዳር ሴቶችና ወጣቶች እንዲጎበኟቸው ማድረግ፤
- በ2ኛው ዕትዕ ለ55728 ወጣቶች የተፈጠረውን የስራ ዕድል ፈጠራ በዘመኑ መጨረሻ 257293 ማድረስ
- የግል ባለሃብት 985(100%) የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ፤
- በግብርና ሃብት የፈጠሩ 4742 አርሶአደሮችን እሴት ወደ ሚጨምሩ ተግባራት ማሸጋገር፤
- በ2ኛዉ ዕትዕ ዘመን የተከናወነዉን 215 አዉደ ጥናት በዕቅድ ዘመኑ 880 ጊዜ በየሩብ ዓመቱ ፤በዞንና በወረዳ ደረጃ እንዲካሄድ ይደረጋል፤

**ግብ 3፡ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን መገንባትና ማጠናከር፡**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

- በ2ኛው ዕትዕ ዘመን ያለውን 348 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ግንባታ ቁጥር 280 በአዲስ በመገንባት ወደ 528 (100%) ማድረስ እና የባለሙያዎች የመኖሪያ ቤት ግንባታ ከ226 ቁጥር በአዲስ 830 በመገንባት በዕቅድ ዘመኑ ወደ 1056 ማድረስ፡፡
- በ2ኛው ዕትዕ ዘመን ቁሳቁስ የተሟላላቸውን 120 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ቁጥርን 408 በአዲስ በማሟላት በዕቅድ ዘመኑ ወደ 528(100%) ማድረስ፡፡
- በ2ኛው ዕትዕ ዘመን ሰርቶ ማሳያ መሬት የተሟላላቸው 110 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን ቁጥር 418በማሟላት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 528 ማድረስ፡፡
- በቀጣይ የዕቅድ ዘመን መሬት በተሟላላቸው 528 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት በተለያዩ የግብርና ዘርፎች በአዳዲስ አሰራሮች፣ ቴክኖሎጅዎችና የመካናይዜሽን አገልግሎት ሰርቶ ማሳያ ማካሄድ፡፡
- 528 የአርሶአደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የአየር ንብረትና የገበያ መረጃ እንዲሰጡ ማድረግ
- 528 የአርሶአደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ተጠቃሚ ማድረግ
- 422 (80%) የአርሶአደር ማሰልጠኛ ማዕከላት በራሳቸው የውስጥ ገቢ እንዲተዳደሩ ማድረግ

**ግብ 4፡የግብርና የልማት አካላት ግንኙነት ማካሄድ፡**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

- በ2ኛው የዕትዕ ዘመን መጨረሻ 718 የነበረውን የልማት አካላት ግንኙነት 1,740 ጊዜ ማካሄድ (በወረዳ 1,580፣ በዞን 150፣ መድረኮችን በማዘጋጀት በግብርና ልማት አካላት መካከል ያለውን ግንኙነት ማሻሻል፤
- በዞን ደረጃ የተለያዩ 4 ንዑስ የምክክር መድረኮች እንዲቋቋሙ ይደረጋል (ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ኤክስቴንሽን፤ ኤክስቴንሽን ምርምርና አርሶ አደር፤ ኤክስቴንሽን ምርምርና ባለሀብት፤ ስትራቴጂክ ኮሞዲቲ /ማሾ፣ ጥራጥሬ፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ማሽላ ወዘተ/
- በየደረጃው 1,740 የአርሶአደር ችግርና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድና ( በዞን 150፣ በወረዳ 1,580) ለልማት አካላት ማቅረብ፤
- በምርምር የሚወጡ አዳዲስ አሰራሮችና ቴክኖሎጅዎችን በቅድመ ኤክስቴንሽን ሰርቶ ማሳያ፣ በቅድመ ማስፋት፣ በገበሬ ምርምር ኤክስቴንሽን ቡድንበመጠቀም ተቀናጅቶ መስራት፤

**ግብ.5. የከተማግብርና፣ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች እንዲሁም የግል ባለሃብቶችን ድጋፍ ማጠናከር፤**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

- የአነስተኛ ከተሞች በግብርና ካላቸው ፋይዳ አንጻር የአደረጃጀትና የተጠሪነት ችግር ስላለባቸው በዕቅድ ዘመኑ በጥናት ክልሉ ምላሽ እድሰጥ መነጋገር፤
- በእርሻ ኢንቨስትመንት የተሰማሩ የግል ባለሃብቶች የሚከታተልና የሚደግፍ ባለሙያ በመዋቅር ባለመፈቀዱ በአሠራር ላይ ችግር የፈጠረ ስለሆነ አደረጃጀቱን በጥናት መልስ እድሰጥበት ከክልል ጋር መነጋገር፤
- የግል ባለሀብቶች የቀጠሯቸዉን ባለሙያዎች በተለያዩ የግብርና ልማት ፓኬጆች ስልጠና መስጠት፤
- የግብርና ኤክስቴንሽንን የሚደግፉ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞችን የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤

2. **የሰብል ልማት እና ጥበቃ የ10 አመት አቅድ** (2013-2022)

**የእቅዱዓላማ**

የሰብል ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ ለኢንዱስተትሪና ለውጪ ገበያ የሚውልምርት በመጠንና በጥራት ማምረት፤

**ስትራቴጅክ ግብ**

በ2011/2012 ምርት ዘመን ከዋናዋና ሰብሎች በመኸር የተገኘውን 9767838 ኩ/ል ምርት በ2021/2022 ምርት ዘመን ወደ 16140100 ኩ/ል ማድረስ ወይም 65% ማሳደግ እና የዋናዋና ሰብሎች አማካይ ምርታማነትን አሁን ካለበት 23 ኩ/ል በሄ/ርወደ 37 ኩ/ል በሄ/ር ማድረስ ወይም በ60% ማሳደግ፣ በ2011/12ምርት ዘመን በመኸር ከተመረተው የሰብል ምርትውስጥ ለገበያ የቀረበውን 12% በ2021/22 ወደ 30% ማሳደግ። ይህን ግብ ለማሳካት በአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች፣ መካከለኛና ሰፋፊ የባለሀብት እርሻዎች ይ በመኸርና በበልግ ለምግብነት፤ ለኢንዱስትሪና ለኤክስፖርት የሚሆኑ ሰብሎችን በሚፈለገው መጠንና ጥራት በማምረትምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፤

**ግብ.1. የምግብ ሰብሎችን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፤-** በ2011/2012 ምርት ዘመን ከምግብ ሰብሎች የተገኘውን 5162995 ኩ/ል ምርት በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 7997500 ኩ/ል (59.3%) ማሳደግ፣ የምግብ ሰብሎች አማካይ ምርታማነትን አሁን ካለበት 21 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 35 ኩ/ል በሄ/ር (66.7%) ማድረስ፣ በ2011/12 ምርት ዘመን በመኸር ከተመረተው የምግብ ሰብሎች ምርት ውስጥ ለገበያ የቀረበውን 10% በ2021/022 ወደ 30% ማሳደግ።

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

**በዋና ዋና የምግብ ሰብሎች፡-**

- **ጤፍ፤**-በ2011/12 ምርት ዘመን ምርታማነት ከነበረበት 19 ኩ/ል በሄ/ር በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 29 ኩ/ል በሄ/ር በማሳደግ ምርቱን ከመነሻው ዓመት ከነበረበት 1893388 ኩ/ል ወደ 2892025 ኩ/ል (53%) ማሳደግ፣
- **የምግብ ገብስ፤**-በ2011/12 ምርት ዘመን ምርታማነት ከነበረበት 24 ኩ/ል በሄ/ር በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 40 ኩ/ል በሄ/ር በማሳደግ ምርቱን ከመነሻው ዓመት ከነበረበት 674544 ሚ/ኩ/ል ወደ 1172040 ኩ/ል (73.7%) ማሳደግ፣

- **የዳጉሳ ሰብል፤**-በ2011/12 ምርት ዘመን ምርታማነት ከነበረበት 15 ኩ/ል በሄ/ር በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 25 ኩ/ል በሄ/ር በማሳደግ ምርቱን ወደ 35275 ኩ/ል ማድረስ፡
- **የበቆሎ ሰብል፤**- በ2011/12 ምርት ዘመን ምርታማነት ከነበረበት 27 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 45 ኩ/ል በሄ/ር በማሳደግ ምርቱን ከመነሻው ዓመት ከነበረበት 260901 ኩ/ል ወደ 434835 ኩ/ል(66.7%) ማድረስ፣
- **የማሽላ ሰብል፤**- በ2011/12 ምርት ዘመን ምርታማነት ከነበረበት 29 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 45 ኩ/ል በሄ/ር በማሳደግ ምርቱን ከመነሻው ዓመት ከነበረበት 1798087 ኩ/ል ወደ 2790135 ኩ/ል ማድረስ፣
- **የአተር ሰብል፤**- በ2011/12 ምርት ዘመን ምርታማነት ከነበረበት 17 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 28 ኩ/ል በሄ/ር በማሳደግ ምርቱን ከመነሻው ዓመት ከነበረበት 185402 ኩ/ል ወደ 305368 ኩ/ል(64.7%) ማድረስ፣
- **የምስር ሰብል፤**- በ2011/12 ምርት ዘመን ምርታማነት ከነበረበት 12 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 20.5 ኩ/ል በሄ/ር በማሳደግ ምርቱን ከመነሻው ዓመት ከነበረበት 185892 ኩ/ል ወደ 309820 /ኩ/ል(66.7%) ማድረስ፣

**ግብ 2. የኢንዱስትሪ ሰብሎች ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፤-**

በ2011/2012 ምርት ዘመን ከኢንዱስትሪ ሰብሎች የተገኘውን 3998115 ኩ/ል ምርት በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 6803500 ኩ/ል (70%) ማሳደግ፣ የኢንዱስትሪ ሰብሎች አማካይ ምርታማነትን አሁን ካለበት 27 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 43 ኩ/ል በሄ/ር (59%) ማድረስ። በ2011/12 ምርት ዘመን በመኽር ከተመረተው የኢንዱስትሪ ሰብሎች ምርት ውስጥ ለገበያ የቀረበውን 12 % በ2021/22 ወደ 40% ማሳደግ።

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

**በዋና ዋና የኢንዱስትሪ ሰብሎች፡-**

- **የዳቦ ስንዴ፤**- በ2011/12 ምርት ዘመን ምርታማነት ከነበረበት 27 ኩ/ል በሄ/ር በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 45 ኩ/ል በሄ/ር በማሳደግ ምርቱን ከመነሻው ዓመት ከነበረበት 3958470 ኩ/ል ወደ 6741000 ኩ/ል (70 %) ማሳደግ፣

- **የቢራ ገብስ፤**-በ2011/12 ምርት ዘመን ከነበረበት 24 ኩ/ል/ሄ/ር ምርታማነት በ2021/22 ምርት ዘመንወደ 35 ኩ/ል በሄ/ር በማሳደግ ምርቱን ምርቱን ከመነሻው ዓመት ከነበረበት 28680 ወደ 70000 ኩ/ል (144%) ማሳደግ ፣
- **የኑግ ሰብል፤**- በ2011/12 ምርት ዘመን ምርታማነት ከነበረበት 10 ኩ/ል በሄ/ር በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 15 ኩ/ል በሄ/ር በማሳደግ ምርቱን ከነበረበት 4090 ኩ/ል ወደ 10500 ኩ/ል (156 %) ማሳደግ፣

**ግብ3. የኤክስፖርት ሰብሎችን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፤-**

በ2011/2012 ምርት ዘመን በኤክስፖርት ሰብሎች የተገኘውን 735014 ኩ/ል ምርት በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 1339100 ኩ/ል (82%) ማሳደግ፣ የኤክስፖርት ሰብሎች አማካይ ምርታማነትን አሁን ካለበት 17 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 25 ኩ/ል በሄ/ር (47%) ማሳደግ ፡፡ በ2011/12 ምርት ዘመን በመኽር ከተመረተው የኤክስፖርት ሰብሎች ምርት ውስጥ ለገበያ የቀረበውን 32 % በ2021/22 ወደ 60% ማሳደግ፡፡

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

**በዋና ዋና የኤክስፖርት ሰብሎች፡-**

- **የሰሊጥ ሰብል፤**- በ2011/12 ምርት ዘመን ምርታማነት ከነበረበት 7 ኩ/ል በሄ/ር በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 13 ኩ/ል በሄ/ር በማሳደግ ምርቱን ከመነሻው ዓመት ከነበረበት 11809 ኩ/ል ወደ 32500 ኩ/ል (175 %) ማሳደግ፣
- **ቦሎቄ፤**-በ2011/12 ምርት ዘመን ምርታማነት ከነበረበት 16 ኩ/ል በሄ/ር በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 26 ኩ/ል በሄ/ር በማሳደግ ምርቱን ከመነሻው ዓመት ከነበረበት 137744 ኩ/ል ወደ 325000 ኩ/ል (136%) ማሳደግ፣
- **የባቄላ ሰብል፤**- በ2011/12 ምርት ዘመን ምርታማነት ከነበረበት 18 ኩ/ል በሄ/ር በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 25 ኩ/ል በሄ/ር በማሳደግ ምርቱን ከመነሻው ዓመት ከነበረበት 374094 ኩ/ል ወደ 577050 ኩ/ል (54%) ማሳደግ፣
- **ሽምብራ፤**-በ2011/12 ምርት ዘመን ምርታማነት ከነበረበት 17 ኩ/ል በሄ/ር በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 25 ኩ/ል በሄ/ር በማሳደግ ምርቱን ከመነሻው ዓመት ከነበረበት 149039 ኩ/ል ወደ 320250 ኩ/ል (78 %) ማሳደግ፣

- **የማሾ ሰብል፤-** በ2011/12 ምርት ዘመን ምርታማነት ከነበረበት 8 ኩ/ል በሄ/ር በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 15 ኩ/ል በሄ/ር በማሳደግ ምርቱን ከመነሻው ዓመት ከነበረበት 36088 ኩ/ል ወደ 84300 ኩ/ል (133 %) ማሳደግ፣

**ግብ 4.** በ2012 በጀት ዓመት ከዋና ዋና የበልግ ሰብሎች የተገኘውን 1077170 /ኩ/ል ምርት በ2021/2022 ምርት ዘመን ወደ 2379000 ኩ/ል (87.5%) በማሳደግ በዋና ዋና ሰብሎች አማካይ ምርታማነትን አሁን ካለበት 13 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 26 ኩ/ል በሄ/ር ማድረስ፣

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

- በ2012 ዓ.ም ከምግብ ሰብሎች የተገኘውን 1077170 ኩ/ል ምርት በ2022 ዓ.ም ወደ 2379000 ኩ/ል (121%) ማሳደግ፣ አማካይ ምርታማነትን አሁን ካለበት 13 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 26 ኩ/ል በሄ/ር ማድረስ።

- በ2012 ዓ.ም ከኢንዱስትሪ ሰብሎች የተገኘውን 67095 ኩ/ል ምርት በ2022 ዓ.ም ወደ 159600 ኩ/ል (138 %) ማሳደግ፣ የኢንዱስትሪ ሰብሎች አማካይ ምርታማነትን አሁን ካለበት 15 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 28 ኩ/ል በሄ/ር ማድረስ።

- በ2012 ዓ.ም በኤክስፖርት ሰብሎች የተገኘውን 59015 ኩ/ል ምርት በ2022 ወደ 185150 ኩ/ል ( 213%)ማሳደግ፣ የኤክስፖርት ሰብሎች አማካይ ምርታማነትን አሁን ካለበት 14 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 25 ኩ/ል በሄ/ር ማድረስ፣

**ግብ 5.**በ2011/2012 ምርት ዘመን በጠቅላላው ከለማው መሬት ውስጥ በዋና ዋና የኮሞዲቲ ሰብሎች በኩታ-ገጠም አሰራር 123269 ሄ/ር በማልማት የተገኘውን 3069662 ኩ/ል ምርት በ2021/2022 ምርት ዘመን 216956 ሄ/ር (ጠቅላላ ከሚለማው መሬት ውስጥ 50 % የሚሆነውን) በማልማት 8244328 ኩ/ል ምርት ማምረት፣

**ግብ 6.** የአፈር ለምነት ማሻሻያ ተግባራትን (አሲዳማ አፈርን በኖራ በማከም፤በኮምፖስት ዝግጅት፤ጥራጥሬ ሰብልን በህያው ማደበሪያ ማልማትና የኮትቻ አፈር ልማትን) አቀናጅቶ በመጠቀም የአፈር ለምነትን በማሻሻል ምርትና ምርታማነትን በላቀ ደረጃ ማሳደግ

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

- **የአሲዳማ አፈርን በኖራ ማከም፡-** በ2011/12 ምርትዘመን 210 ኩ/ልኖራ በመጠቀም የለማውን 7 ሄ/ር አሲዳማ አፈር በ2021/2022 ምርት ዘመን 14000 ኩ/ል ኖራ በመጠቀም የሚለማውን መሬት ወደ 700 **ሄ/ር** ማሳደግ፣
- **የኮምፖስት (መደበኛ፣ቨርሚ፣ባዮስለሪ ኮምፖስት) ዝግጅትና አጠቃቀም፡-** በ2011/12 ምርትዘመን 3077063 ሚ/ሜ/ኩብ ኮምፖስት ተዘጋጅቶ በ138497 ሄ/ር ጥቅም ላይ የዋለውን በ2021/2022 አንድ አባወራ/እማወራ 20 ሜ/ኩብ ኮምፖስት እንደሚያዘጋጅ ታሳቢ በማድረግ 8000000 ሚ/ሜ/ኩብ ማድረስ እቅድ ተይዟል፡፡በዚህም በአማካይ 233334 ሄ/ር መሬት ይሸፈናል፡፡
- **የህየው ማዳበሪያ አጠቃቀምን፡-** በ2011/2012 ምርትዘመን **6517** ሳቸት ህየወ ማዳበሪያ በመጠቀም የለማውን 1527 ሄ/ር መሬት በ2021/2022 ምርት ዘመንወደ **42000 ሳቸት** ህየወ ማዳበሪያ በማድረስ **10500 ሄ/ር** በማልማትየጥራጥሬሰብልምርታማነትንማሳደግ፣
- **የኮትቻ አፈር ልማትን ማሳደግ፡-**በ2011/12 ምርትዘመን በዞኑ በማጠንፈፍ የለማውን 64208 ሄክታር ኮትቻ አፈር በ2021/2022 ምርት ዘመን ወደ 66046 ሄ/ር ማሳደግ፣

ግብ7. የተሻሻሉ የሰብል አመራረት ስርዓትን በዳግም ሰብል ልማት፤አሰባጥሮ በመዝራት፤ በቅብብሎሽ በማልማትና በመስመር በመዝራት በትኩረት በመፈጸም በ2011/12 ምርት ዘመን አሰራሮችን በመተግበር የለማውን 5750 ሄ/ር መሬት በ2021/2022 ምርትዘመን 39750 ሄ/ር መሬት በማልማት ተጨማሪ ምርት ማምረት፣

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

- **ዳገም ሰብል ልማት፡-** በ2011/12 ምርትዘመን በዳግም ሰብል የለማውን 1520 ሄ/ር መሬት በ2021/2022 ምርትዘመን **3000** ሄ/ር መሬት በማልማት 45000 ኩ/ል ተጨማሪ ምርት ማምረት፡፡ ቀድሞ ደራሽ የሆኑ የስንዴ፤ የገብስና የባቄላ ዝርያዎችን በኮትቻ አፈር ላይ ትርፍ ውሃን አጠንፍፎ በመዝራትና በወቅቱ በመሰብሰብ በሚኖረው ቀሪ እርጥበት የጥራጥሬ ሰብሎችን (ሽምብራ፤ምስር ጓያ... ወዘተ) የማምረት ስራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የሚተገበር ይሆናል፡፡

- **ሰብልን አሰባጥሮ መዝራት፤-** በ2011/12 ምርትዘመን በሰብል ስብጥር የለማውን 2520 ሄ/ር መሬት በ2021/2022 ምርትዘመን 30000 ሄ/ር መሬት በማልማት 24000 ኩ/ል ተጨማሪ ምርት ይመረታል፡፡ሁለት ሰብሎችን በአንድ ማሳ ላይ ሙያዊ ምክረ-ሃሳበቡን ተከትሎ አሰባጥሮ መዝራት በማሳው ላይ አንድ ሰብል ብቻ በመዝራት ከሚገኘው ምርት ተጨማሪ ምርት ከማስገኘቱም ባሻገር የአፈር ለምነት በማሻሻል በኩል ጉልህ ድርሻ የአለው አሰራር ነው፡፡ በመሆኑም ተግባሩን መፈጸም የሚያስችል ለአርሶ አደሩ ተከታታይ ስልጠና በመስጠት አስፍቶ ለመስራት ጥረት ይደረጋል ፡፡
- **የሰብል ቅብብሎሽ ልማትን ማስፋፋት፡-** በ2011/12 ምርት ዘመን በቅብብሎሽ የለማውን 1710 ሄ/ር መሬት በ2021/2022 ምርት ዘመን 6750 ሄ/ር መሬት በማልማት 108000 ኩ/ል ተጨማሪ ምርት ማምረት፡፡
- **ሰብልን በመስመር መዝራት፡-** በ2011/12 ምርት ዘመን በመስመር የለማውን 126069 ሄ/ር መሬት በ2021/2022 ምርት ዘመን 312720 ሄ/ር (72% ከጠቅላላው መሬት) ማድረስ፡፡

**ግብ.8.** በተለያዩ የመስክና የጎተራ ተባዮች በቅድመና በድህረ-ምርት በአማካይ የሚደርሰውን 35% የምርት ብክነት በ2021/2022 ምርት ዘመን ወደ 15% ዝቅ በማድረግ የምርት ብክነትን ማዳን፡፡ በዞናችን ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ በየአመቱ በተለያዩ ሰብሎች ላይ ነባርና አዳዲስ ነፍሳት ተባይና በሽታዎች እንዲሁም ጥገኛና መጤ አረሞች በማስፋፋት ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህን ተባዮች በየወቅቱ አሰሳ በማካሄድ ምጣኔ-ሃብታዊ ጎጂ ደረጃ ሳይደረሱ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ መስራት ለሰብል ምርት እድገት ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም በመጭው አስር አመት እቅድ ዘመን በሰብል ላይ የሚከሰቱ ተባዮችን የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ መስራት ይኖርበታል፡፡

**ግብ.9** የግብርና ሜካናይዜሽን ተጠቃሚነት አሁን ካለበት 0.2% በ2021/2022 ምርት ዘመን ወደ 86782 (20%) በማሳደግ የሜካናይዜሽን አገልግሎትን ማስፋፋት፡፡ የኩታ ገጠም ልማት ተግባራዊ በሚደረግባቸው አካባቢዎች የቴክኖሎጂዎችን ፍላጎት በማሰባሰብ ለየአካባቢው ተስማሚ የሆኑትን በህብረት ስራ ማህበራት፤በግል ባለሃብቶች፤ወጣቶችን በማደራጀት እና በመንግስት ልማት ድርጅቶች በኩል እንዲቀርቡ ይደረጋል ፡፡

- በሰብል ልማት የሚሳተፉ የግል ባለሃብቶች ሙሉ በሙሉ የሜካናይዜሽን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ክትትልና ድገፍ ይደረጋል፡
- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለመካናይዜሽን የፈቀደውን ብድር አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን በትኩረት ይሰራል፡
- አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አካባቢዎች በትራክተር የሚታረሰው መሬት በአስር አመቱ እቅድ ዘመን መጨረሻ ዓመት ወደ 50000 ሄ/ር በማሳደግ 200000 አ/አደሮች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡
- ሰብልን በተሸሻሉ መሳሪያዎች እንዲሰበሰብ እና እንዲወቃ ከማድረግ አንጻር በኮምባየይን ሀርቨስተር 36782 ሄ/ር እንድሰበሰብ እና እንድወቃ ይደረጋል፡፡ በዚህም 210000 አ/ደሮች የቴክኖሎጅዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡

**ግብ 10. የሰብል ዘር ብዜት በዞናችን በእድገት እና ትራንስፎርሜሽን አቅዱ ተጀምሮ የተቋረጠ ተግባር ቢሆንም ከአስር አመቱ የመጀመሪያ አመት (2012/13) በመጀመር በ2021/2022 ምርት ዘመን 500 ሄ/ር መሬት ላይ በግልና በዘር አባዥ ዩኒዬኖች እንዲባዛ በማድረግ 20000 ኩ/ል ጥራቱን የጠበቀ የተመሰከረለት ዘር ለተጠቃሚው ማቅረብ ፡፡**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

- የመንግስት፣ የግል ዘር አምራች ድርጅቶችና ዩኒኖች በተወሰነ መልኩ ቅድመ መስራች እና በዋናነት መስራች ዘር ብዜትና አቅርቦትን በመኸርና መስኖ ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣
- የወጡ ዝርያዎች መሰረታዊ ባህሪያቸውን ሳይቀይሩ በአግባቡ ጠብቆ በማቆየት በየዓመቱ የዝርያ ዕድሳት እንዲሰራ ማድረግ፣ እና የመነሻ ዘር ፍላጎትን ሊያሟሉ የሚችሉበትን ተጠያቂ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣
- ሰፋፊ መሬት ያላቸው የግል ባለሀብቶች ወደ ዘር ማምረት ስራ እንዲገቡ ማድረግ፣

**ግብ 11. 2011/2012 ምርት ዘመን ለአግሮ ኢንዱስትሪ ለማቅረብ ከተመረተው 1022388 ኩ/ል የሰብል ምርት በ2021/2022 ምርት ዘመን 2044776 ኩ/ል ምርት በማምርተ ለአግሮ ኢንዱስትሪ ማቅረብ**

**ግብ.12. በ2021/2022 ምርት ዘመን ስንዴን በመስኖ በማምረት ምርትና ምርታማነት በማሳደግና ጥራቱን በማሻሻል 7000 ሄ/ር መሬት በማልማት በሄ/ር 40 ኩ/ል በማድረስ**

በጠቅላላው 280000 ኩ/ል የስንዴ ምርት በማምርት የዞናችንን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እና አገሪቱ ለስንዴ ግዥ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ ማስቀረትእንድሁም ስንዴን በግብዓትነት ለሚጠቀሙ የአገር ውስጥ አግሮኢንዱስትሪዎች ፍላጎት ማሟላት።

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

- 15400 ኩ/ል የአፈር ማዳበሪያ ጥቅም ላይ እንድውል ይደረጋል
- 10500 ኩል ምርጥ ዘር እና ደረጃ 2 እና 3 የአካባቢ ዘር ጥቅም ላይ ይውላል

**ግብ 13.** የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች አጠቃቀምን 2011/12 ምርት ዘመን በመኸር፣ በበልግና በመስኖ ሰብል ልማት ጥቅም ላይ የዋለውን 337297 ኩ/ል የአፈር ማዳበሪያ በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 619000 ኩ/ል (83.5%) ማሳደግ እንድሁም በ2011/12ምርት ዘመን በመኸርና በበልግ ጥቅም ላይ የዋለውን 14320 ኩ/ል ምርጥ ዘር በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 50000 ኩ/ል ማሳደግ፤

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

- በ2011/12ምርት ዘመን በመኸርና በበልግ ጥቅም ላይ የዋለውን 337297 ኩ/ል የአፈር ማዳበሪያ በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 619000 ኩ/ል (83.5%) ማሳደግ፤
- በ2011/12ምርት ዘመን በመኸርና በበልግ ጥቅም ላይ የዋለውን 14320 ኩ/ል ምርጥ ዘር በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 50000 ኩ/ል ማሳደግ፤
- በመስኖ ስንዴ ልማት የአፈር ማዳበሪያን አጠቃቀምን በ2022 ዓ.ም 15400 ኩ/ል በማድረስ ምርታማነትን ማሳዳግ፣
- በመኸር ሰብል ልማት በአንድ ሄ/ር መሬት ላይ ጥቅም ላይ ይውል የነበረውን 0.78 ኩ/ል የአፈር ማዳበሪያ በመጨረሻው የዕቅድ ዘመን ወደ 1.45 ኩ/ል ማድረስ፣
- የአሲዳማ አፈርን ምርታማነት ለማሳደግ በ2011/12 210 ኩ/ል ኖራ በመጠቀም የለማውን 7 ሄ/ር አሲዳማ መሬት መሬትን በኖራ በ2021/22 ምርት ዘመን 14000 ኩ/ል ኖራ ውህድ በመጠቀም 700 ሄ/ር መሬት ይታከማል ።
- የጥራጥሬ ሰብል ምርታማነትን በላቀ ደረጃ ለማሳደግ በ2011/12 መኸር ወቅት የህየወ ማዳበሪያ ከነበረበት 6517 ሳቸት በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 42000 ሳቸት ማድረስ፣
- የሰብል ጥበቃ ስራን ውጤታማ ለማድረግ የጸረ-ሰብል ተባይ ኬሚካል አጠቃቀምን በመቀነስ ባህላዊ መከላከልን ይበልጥ ማሳደግ ዋናው ተግባር ቢሆንም አሁን ካለው የኤክስቴንሽን

ስርጸት አኳያ በኬሚካል መጠቀምን የሚያስገድድ ሁኔታ ስላለ በ2011/12 መኸር፣ በልግና መስኖ ወቅት ጥቅም ላይ የዋለውን 8927 ኪ/ግ/ሊትር በየአመቱ በማሳደግ በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 34110 ኪ/ግ/ሊትር ማድረስ፤

ግብ 14. በተለያዩ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎች በ2011/12 ምርት ዘመን የተካሄደውን 2902 ሰርቶ ማሳያ በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 5804 (50%) በማሳደግ ማከናወን፣

ግብ15. በ2011/12 ምርት ዘመን ጥቅም ላይ የዋለውን 8927 ሊትር/ኪግ ኬሚካል በ2021/2022 ምርት ዘመን ወደ 34110 ሊትር /ኪግማድረስ፣

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- የኬሚካል አጠቃቀም እና መርጫ መሳሪያ አያያዝ ስልጠና ለባለሙያ እና አ/አደሮች ይሰጣል

## አትክልት ናፍራፍሬ መስኖ ውሃ አጠቃቀም ዘርፍ

**የእቅዱዓላማ**

ዉጤታማ አሰራሮች በማላመድና በማስተዋወቅ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እና ዘላቂ የሆነ የገበያ ትስስር ስርዓት እንዲዘረጋ በማድረግ አርሶአደሩን ብሎም ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ

ግብ1. የዞኑን የመስኖ ሽፋን በ2012 ዓ.ም ከነበረበት ነባር የመስኖ 22571 ሄ/ር የመሬት ሽፋንና የአዲስ መስኖ ሽፋንን በየዓመቱ በአማካይ 5 % በማሳደግ በቀጣይ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ 38670ሄ/ር የመሬት ሽፋን ማድረስ።

የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤

- በ2ኛ ዙርና ከዚያ በላይ መስኖ ልማት በ2012 ዓ.ም 7483.523 ሄ/ር ከነበረበት የመሬት ሽፋን በየአመቱ 5% በማሳደግ በ2022 ወደ 17437 ሄ/ር መሬት ሽፋን ማድረስ፡
- በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 3110668 ኩ/ል ምርት እና 104 ኩ/ል ሄ/ር ምርታማነት በየዓመቱ በአማካይ 5% ምርት እና 169.73% ምርታማነት በማሳደግ በ2022 ዓ.ም ወደ 5277061ኩ/ል ምርት ማድረስ፡

- የመስኖ ልማት ተጠቃሚ አ/አደሮች በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 128738 አ/አደር በየዓመቱ በአማካይ 5 % አዲስ የመስኖ ልማት ተጠቃሚ አ/አደሮችን ወደ ልማት በማስገባት በ2022 ዓ.ም ወደ 163000 ማድረስ፡
- በ2012 ዓ.ም በአንደኛና ሁለተኛ ዙር መስኖ ከነበረዉ 16665ኩ/ል ማዳበሪያ እና 0.07 ኩ/ል በሄ/ር የማዳበሪያ አጠቃቀም፣በየዓመቱ በአማካይ 5% ማሳደግና በ2022 የምርት ዘመን ወደ 72139ኩ/ል ማደበሪያ እና 1.8ኩ/ል ሄ/ር ማድረስ፡
- በ2012 ዓ.ም ከነበረዉ 97,058 ኩ/ል እና 0.41 ኩ/ል በሄ/ር ምርጥ ዘር አጠቃቀም በየዓመቱ በአማካይ 5 % ማሳደግና በ2022 የምርት ዘመን ወደ 40078ኩ/ል ምርጥ ዘር በመጠቀም 1 ኩ/ል በሄ/ር ማድረስ፡፡

ግብ.2. በ2012/13 የምርት ዘመን የተለያዩ የአትክልትና ቅመማቅመም ሰብሎችን ከነበረዉ10779ሄ/ር የመሬት ሽፋን 936736ኩ/ል ምርት እና 86ኩ/ል በሄ/ር ምርታማነት በ2021/22 የምርት ዘመን በየዓመቱ በአማካይ 5% የመሬት ሽፋን በማሳደግ ወደ 16377ሄ/ር እና 5% ምርታማነትን እና በየዓመቱ 5% ምርቱን በማሳደግ ወደ 866405 ኩ/ል ምርት ማድረስ፡፡እንዲሁም በ2011/12 ከነበረዉ 8787 የተሳታፊ አ/አደር ቁጥር በ2021/22 የምርት ዘመን በየዓመቱ 5% የተሳታፊ ቁጥርን በማሳደግ 172543 ማድረስ፡፡

ግብ 3. በሶስት የአትክልት ኮሞዲቲ ሰብሎች (ድንች፣የፈረንጅ ቀይሽንኩርት፣ካሮትና) በ2012 በጀት አመት በክላስተር ልማት ከነበረበት 813 ሄ/ር የመሬት ሽፋንና 161287ኩ/ል ምርት በየዓመቱ 5% የመሬት ሽፋንና 5% ምርቱን በማሳደግ በ2022 ዓ.ም 1723ሄ/ር ሽፋንና 380250ኩ/ል ምርት ማምረት፡፡

የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤

- የቀይ ሽንኩርት ልማት፡- ክላስተርን መሰረት ያደረገ የቀይ ሽንኩርት ልማት በ2012 ዓ.ም ከነበረዉ 429ሄ/ር የመሬት 72360ኩ/ል ምርት በየዓመቱ በአማካይ 10% ምርታማነትን በማሳደግ በ2022 ዓ/ም ወደ713ሄ/ር እና 178250ኩ/ል ምርት ማምረት፡፡ የተጠቃሚ አርሶአደሮችን ቁጥርንም ከ1190 ወደ 2852 ማድረስ፡፡
- የድንች ልማት፡-ክላስተርን መሰረት ያደረገ የድንች ልማት በ2012 ዓ.ም ከነበረዉ 334 ሄ/ር የመሬት ሽፋን እና 64627ኩ/ል ምርት በየዓመቱ በአማካይ 5% የመሬት ሽፋንንና

5% ምርትን በማሳደግ በ2022 ዓ/ም ወደ 699ሄ/ር እና 139800ኩ/ል ምርት ማድረስ፡፡ የተጠቃሚ አርሶአደሮችን ቁጥርንም ከ1394 ወደ 3495 ማድረስ፡፡

- የካሮት ልማት፡-ክላስተርን መሰረት ያደረገ የካሮት ልማት በ2012ዓ.ም ከነበረዉ 174ሄ/ር የመሬት ሽፋን እና 24300ኩ/ል ምርትበየዓመቱበአማካይ5% የመሬት ሽፋንንና 5% የምርት መጠንን በማሳደግ በ2022 ዓ/ም ወደ 311ሄ/ር እና 62200ኩ/ል ምርት ማድረስ፡፡የተጠቃሚ አርሶ አደሮችን ቁጥርንም ከ829 ወደ1244 ማድረስ፡፡

**ግብ4.** የዞኑን የቡና ልማት በ2012 ዓ.ም ከነበረዉ 416237 ከተዘጋጀዉ እና 312783 ከተተከለዉ ችግኝ በ2022 ዓ.ም በየ ዓመቱ በአማካይ 5% በማሳደግ ወደ 775665 በማዘጋጀት 697883 የቡና ችግኝ መትከል፡፡ በ2012 ዓ.ም ከነበረዉ 102ሄ/ር በየዓመቱ በአማካይ 5% የመሬት ሽፋንን በማሳደግ በ2022 ዓ/ም 413ሄ/ር መሬት ማድረስ፡፡ የተሳታፊ አ/አደሮችን በ2012 ዓ.ም ከነበረበት14302 በ2022 ዓ.ም ወደ 28728 ማሳደግ፡፡

**ግብ.5.** የክልሉን የዞኑን የቆላ ፍራፍሬ ልማት በ2012 ዓ.ም ከነበረዉ 409399 ከተዘጋጀዉ እና 283808 ከተተከለዉ ችግኝ በየዓመቱ በአማካይ 5% ችግኝ ዝግጅት እና 5% ችግኝ ተከላ በማሳደግ ወደ 930797 ችግኝ ዝግጅት እና 775665 ችግኝ ተከላን በ2022 ዓ.ም ማድረስ:: በ2012 ዓ.ም ከነበረዉ የቆላ ፍራፍሬ 160ሄ/ር የመሬት ሽፋንን በየዓመቱ በአማካይ 5% በማሳደግ ወደ 419ሄ/ር በ2022 ዓ.ም ማድረስ :: የተሳታፊ አ/አደሮችን ቁጥርም በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 17353 በየዓመቱ በአማካይ (5%) በማሳደግ በ2022 ዓ.ም ወደ 19669 ማድረስ፡፡

**ግብ 6.** የዞኑን የደጋ ፍራፍሬ ልማት በ2012 ዓ.ም ከነበረዉ 67842 ከተዘጋጀዉ እና 27393 ከተተከለዉ ችግኝ በየዓመቱ በአማካይ 5% ችግኝ ዝግጅት እና 5% ችግኝ ተከላ በማሳደግ ወደ 310266 ዝግጅት እና 217187 ተከላን በ2022 ዓ.ም ማድረስ:: በ2012 ዓ.ም ከነበረዉ የደጋ ፍራፍሬ የመሬት ሽፋን 23.6ሄ/ር፣ 590ኩ/ል ምርትና 25 ኩ/ል/ ሄ/ር ምርታማነትን በየዓመቱ በአማካይ 10% በማሳደግ 50 ኩ/ል/ሄ/ር ማድረስና5% የመሬት ሽፋንን በማሳደግ 117 ሄ/ር እና 5850ኩ/ል ምርት በ2022 ዓ.ም በማድረስ:: የተሳታፊ አ/አደሮችን ቁጥርም በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 1547 በየዓመቱ በአማካይ 5% በማሳደግ ወደ 4589 በ2022 ዓ.ም ማድረስ፡፡

## የግብዓት አቅርቦት

**ዓላማ:-**

የአካባቢን ፓቴንሽያል መሰረት ያደረገ የግብርና ግብዓቶችን በወቅቱ፤በጥራትእና በሚፈለገዉ አይነት ለተጠቃሚዉ አርሶ አደር በማቅረብ እና በማሰራጨት ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ እና የአርሶ አደሩን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል ፤

ግብ፡-በትራንስፎርሜሽን ዘመኑ መጨረሻ ማለትም በ2012/13 ምርት ዘመን በመ<ር የተሰራጨዉን 401444 ኩ/ል በ217556ኩ/ል በመጨመር በቀጣዩ 10 አመታት መጨረሻ 619000 ኩ/ል ማድረስ እና ምርጥ ዘርን ደግሞ በ2012/13 ምርት ዘመን የተሰራጨዉን 9189 ኩ/ል የተለያዩ የሰብል ምርጥ ዘሮችን በ10 አመቱ 50000ኩ/ል ማድረስ፣

**ዝርዝር ግቦች**

በትራንስፎርሜሽን ዘመኑ መጨረሻ የደረስንበትን የአፈር ማዳበሪያ በሚፈለገው መጠን ፣ ጊዜ እና የጥራት ደረጃ ከወደብ እስከ መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት ያለውን የአቅርቦት ስርዓት በማሳለጥ 401444 ኩ/ል የአፈር ማዳበሪያ በ217556 ኩ/ል በመጨመር በቀጣዮቹ 10 አመታት 619000 ኩ/ል የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ በወቅቱ አቅርቦ በማሰራጨት

ግብ ፡- 2 በአሳለፍነዉ የትራንስፎርሜሽ ዘመን የተሰራጨዉን 9189 ኩ/ል የተለያዩ ሰብል ምርጥ ዘሮችን 10 አመቱ 50000ኩንታል ምርጥ ዘር በጥራት እና በወቅቱ በማቅረብ ለአርሶ አደሩ እንዲሰራጭ ማድረግ ፣

ግብ ፡-3 የአፈር ለምነትን የሚያሻሽሉ የግብርና ግብዓቶችን በወቅቱ ፣ በጥራት እና በሚፈለገው መጠን ማቅረብ

- ኖራ በ2013/14 ምርት ዘመን ከ7086 ኩ/ል ኖራ ለአርሶ አደሩ በማሰራጨት ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ ፣
- በ2012/2013 ምርት ዘመን 16000 ሳቸት ህያዉ ማዳበሪያ **ለአርሶ አደሩ በማሳራጨት ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ ፣**

ግብ፡ 4. በተለያዩ ሰብሎች ላይ የሚደርሰውን የሰብል በሽታ እና ነፍሳተ ተባይ ለመከላከል ጸረ አረም 1959 ሊትር፤ጸረ በሽታ 2223 ሊ/ር እና ጸረ ተባይ 13979.5 ሊ/ር የተለያዩ ኬሚካሎችን በማቅረብ ለአ/አደሩ ማሰራጨት ፣

ግብ፡5. በተለያዩ ጊዚያት የተሰጡና ወደፊትም የሚሰጡ ብድሮችን ከዩንየኖች እና ወረዳዎች ጋር እንዲናበቡ ማድረግ በሙሉ መግባባት ተመስርቶ ዕዳ መቁረጥ እና ለየምርት ዘመኑ ለተለያዩ የግ/ግብዓቶች መግዣ የሚሆን ብድር ማቅረብ ፣

ግብ 6. ቴክኖሎጅወችን ማቅረብና ማሰራጨት

6.1 ጅኦሜምብሬን ማቅረብና መሰራጨት

በትራንስፎርሜሽን መጨረሻዉ 504 የሠራጨነዉን በ10 አመቱ ዉስጥ 5247 ማሰራጨት ሞተር ፓምፕ አሁን ከደረስንበት122 ያሰራጨነዉን በ10 አመቱ 1378 ማሰራጨት አይባር ቢቢኤም አሁን ከደረስንበት የተሰራጨ ባይኖርም በቀጣይ 670 ማሰራጨት እና ሌሎችንም ቴክኖሎጅወች በአግባቡ እናሰራጫ

## ተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃ

**ዓላማ፡- የተቀናጀ ተፋሰስ ልማትና ጥበቃ በመተግበር፤ የተፈጥሮ ሃብት መራቆትን በመቀነስ፣ ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል ህብረተሰቡን በዘላቂነት ተጠቃሚ ማድረግ፡፡**

**ግብ1.** የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ከሚሰራበት ቀሪ መሬት ዉስጥ 848485 ሄ/ር (100%) መሸፈን፤

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

- እስካሁን የተ/ሀብት ልማትና ጥበቃ ከተሰራባቸዉ 2982 ንኡስ ተፋሰሶች ዉስጥ 709 በመጀመሪያ ደረጃ የፊዚካል ስራ ከሞላ ጎደል በማገባደድ የተመረቁ ሲሆን ለቀሪዎቹ 2273 የተቀናጀ የክለሳ እቅድ በማዘጋጀትና በአዲስ 633 ተፋሰሶች በማጥናት በድምሩ 3615 ተፋሰሶች ላይ የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት መርህን መሰረት ያደረገ የአፈርና ውሀ ጥበቃ ስራ ይሰራል፣
- በዚህም የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ የሚጠይቀው 845485 ሄ/ር መሬት በአዲስ የአፈርና ውሀ ጥበቃ ስራወች እና የከልሎ ማገገምና ማልማት ስራወች ይሸፈናል፡፡ ግብ.2. የተ/ሀብት ስራ በተሰራባቸዉና በሚሰራባቸዉ 3615 ተፋሰሶች 0.36 ሚሊዮን ህብረተሰብ በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ማድረግ፣

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- ለ3615 ተፋሰሶች በራሳቸው ህገ ደንብ እንዲተዳደሩ በማድረግ የተጠቃሚዎች ማህበር እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ ለዚህም፡-

ግብ 3. በ218908 **ሄ/ርመሬትላይየጥምርደንእርሻፓኬጆችንተግባራዊማድረግ፤**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤**

- የረድፍ እርሻ 3585 ሄ/ር
- የማሳ ውስጥ ዛፍ ተከላና እንክብካቤ 10755ሄ/ር
- በማሳ ደንበርና በመንገድ ዳር ዛፍ ተከላ ማካሄድ 11472 ኪ/ሜ
- ጓሮ ዙሪያ ተከላ 21510 ሄ/ር እንዲሸፈን ይደረጋል፡፡

**ግብ4. የዞኑን ደንሽፋንአሁንካለዉ 13.24 % በየአመቱ በ1% በማሳደግ 23.24% ማድረስ፣**

የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤

- ይህተጨማሪ የደን ሽፋን በባለቤትነት ደረጃ ሲተነተንም
- ችግኝጣቢያዎችን በማስፋፋትእናያሉትን በማጠናከር 2313 ሚሊዮን ደረጃቸውንየጠበቁችግኞችማዘጋጀትና በመትከል የችግኝ የመፅደቅ መጠኑን አሁን ካለዉ አማካኝ 73% ወደ 85% የማሳደግ ስራ ይሰራል፣

## 10.2. እንስሳትና አሳ ሃብት

### የወተት ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ፡

**አላማ 1.** ከዳልጋ ከብት እና ከፍየል የሚመረተውን የወተት ምርት በ2012 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 146142 ቶን በ2022 በጀት ዓመት ዓመታዊ የማምረት ዓቅም ወደ 865870 ቶን ሊትር የማድረስ ግብ ተይዟል፡፡ በዚህም አግባብ የዞኑን አማካኝ አመታዊ የነፍስ ወከፍ የወተት ፍጆታ በ2012 መጨረሻ ከደረሰበት 19 ሊትር በ2022 ወደ 26 ሊትር በነፍስ ወከፍ ለማድረስ ኢላማ ያደረገ ነው፡፡ ይህን ግብ ለማሳካት በ2012 በቀን እየተመረተ ያለውን አማካኝ የወተት ምርታማነት ከአንድ የሀገር በቀል የወተት ላም ዝርያ 1.194 **ሊትር** ወደ 2 ሊትር በቤተሰብ ወተት ከብት እርባታ የተሻሻሉ ላሞችን ከ6 ሊትር በ2022 ወደ 8 ሊትር፣ የአነስተኛ ስፔሻላይዝድ ወተት ከብት እርባታ በ2012 ከተደረሰበት 8 ሊትር በ2022 መጨረሻ 12 ሊትርና በመካከለኛ ስፔሻላይዝድ ወተት ከብት እርባታ ላሞችን በ2012 የተደረሰበትን 11 ሊትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 14 የቀን ወተት ምርት ለማድረስ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ለገበያ የሚቀርብ ወተት መጠን በተመለከተ በ2022 መጨረሻ ከሚመረተው አጠቃላይ ወተት ምርት 54% ያህሉ ለገበያ እንደሚቀርብ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

### አላማዉን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

የወተት ከብቶች አያያዝ፣አመጋገብና ዝርያ የማሻሻል ሥራን አጠናክሮ በማስቀጠል አሁን ከሚታለቡ ጠቅላላ 388026 ላሞች-የሚታለበውን 146142 ቶን ሊትር ወተት በ2022 የላሞቹን 473781 በማድረስ በ2022 865870 ቶን ወተት ማምረት። ይህንም ተግባራዊ ለማድረግ የአካባቢ ዝርያ ላሞች በ5% በመቀነስ 47063 ቶን የወተት ምርት ማምረት እና በ2012 የሚታለቡ የተሻሻሉ ዝርያ 41786 ላሞችን በ20% በማሳደግ በ2022 ከ56324 የሚታለቡ ላሞች 395207 ቶን ወተት ማምረት ይሆናል።

የስፔሻላይዝ የወተት ከብት እርባታ ቁጥር እና ምርታማነት በማሳደግ አሁን ካለው 202 የአነስተኛ እና መካከለኛ ስፔሻላይዝድ የወተት ከብቶች እርባታ ዩኒት የሚገኘውን 4482.29 ቶን የወተት ምርት በ2022 ከ434 አነስተኛ ስፔሻላይዝድ የወተት ከብት እርባታ ዩኒት 14,023 ቶን የወተት ምርት ማምረት።

የሚታለቡ የሀገረሰብ ላሞችን የአለባ ቀን አሁን ያለውን የአለባ ቀን የሀገረሰብ ላሞች180 ቀን፣ የተሻሻለ ዝርያ ላሞች 210 ቀን በ2022 የአካባቢ ላሞች 210 ቀን፣የተሻሻሉ ላሞች 270 ቀን እንዲሆን በማድረግ የወተት ምርቱን ማሳደግ

### *ሥጋ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ*

አላማ 2. የእንስሳት ማድለብ ስራችን በማዘመን እና የገበያ ትስስሩን በማሳለጥ ከዳልጋ ከብት፣ ከበግ፣ ከፍየል በ2012 የተደረሰበትን ዓመታዊ የስጋ ምርት 48,898 ቶን በ2022 መጨረሻ 108,323 ቶን የስጋ ምርት በማሳደግ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ የስጋ ፍጆታ አሁን ካለበት 8 ኪ/ግ በ2022 12 ኪ/ግ በማድረስ ሀብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ፣
የእንስት ማድለብ ስራችን ሳይንሳዊ አሰራርን እንዲከተል በማድረግ በ2012 መጨረሻ የተደረሰበትን ከአንድ ዳልጋ ከብት 148.5 ኪ.ግ፣ከበግ 14 ኪ.ግ፣ ከፍየል 13 ኪ.ግ እና ከዶሮ1.5 ኪ.ግ አማካኝ የስጋ ምርታማነት በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ ከዳልጋ ከብት 157 ኪ.ግ፣ከበግ-15 ኪ.ግ፣ከፍየል 14 ኪ.ግ፣ ከደሮ 1.8 ኪ.ግ በማሳደግ እንዲሁም ከሚመረተው ዓሳ 35% ስጋ በማምረት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

**አላማዉን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

በ2012 የተደረሰበትን -ከዳልጋ ከብት 28925 ቶን፣ከበግ 10301 ቶን ከፍየል 6737 ቶን፣ከደሮ 2836 ቶን እና ከዓሣ 98 ቶን የስጋ ምርት በ2022 መጨረሻ ከዳልጋ ከብት 67368 ቶን፣ ከበግ 21489 ቶን ከፍየል 12103 ቶን፣ከደሮ 7034 ቶን እና ከዓሣ 226 ቶን እንዲመረት

ማድረግ፡፡ ስለሆነም አርቢው ህብረተሰብ የስጋ ምርትን ለማሳደግ የሚያስችል የሚደልቡ እንስሳት/ በሬ፣ወድን ጥጃ ፍየል፣ በግ /ፍላጎታቸዉን መሰረት ያደረግ እና አዋጭነትን ታሳቢ ያደረገ የተቀነባበረና ምጥን መኖን አመጋገብ ስርዓት እንዲከተሉ ይደረጋል፡፡

ምንም እንኳ እስከ አሁን በአነስተኛ ስፔሻላይዝድ የምርት ሂደት ይህ ነው የሚባልባይኖርም በ2022 መጨረሻ ከ46 አነስተኛ ስፔሻላይዝድ ማድለብ ዘርፍ 358 ቶን፣ ከ16 መካከለኛ ስፔሻላይዝድ ማድለብ ዘርፍ ደግሞ 76.9 ቶን ሥጋ ለማምረት ታስቧል

በከተሞች 15 ስፔሻላይዝ የስጋ ዶሮች አምራቾች በዘርፉ እንዲገቡ የአሰራርና ስልቶች መቀየስ

## የዶሮ ሀብት ልማት ስራችን በማዘመን የእንቁላል ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ

አላማ 3. በ2012 መጨረሻ ከተደረሰበት 92 ሚሊዮን በ2022 መጨረሻ 325 ሚሊዩን እንቁላል እና በ2012 ከተደረሰበት ከ*2836* ቶን በ2022 መጨረሻ *7034* ቶን የዶሮ ሥጋ በማድረስ የአምራቹን ተጠቃሚነት ማረጋጋጥ፣ ስነ-አመጋገብን ማሻሻልና በገበያ የሚመራ ኢንዱስትሪ ማድረግ፡፡
በ2012 መጨረሻ የተደረሰበትን የአንድ ዶሮ አማካኝ አመታዊ እንቁላል ምርታማነት ከአካባቢ ዝርያ 64 እና ከተሸሻለ ደሮ ዝርያ 214 እንቁላል በ2022 መጨረሻ ከአካባቢ ዶሮ 65 እና ከተሸሻለ ዶሮ 270 እንቁላል ማድረስ

### የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- በ2012 ዓ.ም መጨረሻ የነበረውን 590516 የተሻሻለ ዶሮ ጫጩት ስርጭት በ25% በማሳደግ በ2022 መጨረሻ ዓመታዊ የማስራጨት አቅም 738145 ኮሜርሻል የአንድ ቀን የዶሮ ጫጩት በማሰራጨት በ2012 መጨረሻ የተደረሰበትን የእንቁላል ምርት ከአካባቢ ደሮ ዝርያ 37.8 ሚሊዩን እና ከተሸሻለ ደሮ ዝርያ 53.72 ሚሊዩን እንቁላል ምርት በ2022 መጨረሻ ከአካባቢ ደሮ 88 ሚሊዩን እና ከተሸሻለ ደሮ 237 ሚሊዩን እንቁላል ምርት እንዲመረት በማድረግ የህብረተሰቡን የእንቁላል ፍላጎት ማሟላት
- የዶሮ መኖ አዘገጃጀት፣ አቅርቦት፣ አጠቃም፣ የዶሮ አያያዝ እና እንክብካቤ እና የዶሮ ጤና (ቅድመ መከላከል እና ባዮሴኩሪቲ) ስራችን ተደራሽነት እና ጥራት በማሻሻል ያለውን የዶሮ ሞት መቀነስ እና ምርታማነትን ማሳደግ፣

- አሁን ያሉትን 9 ዝቅተኛ ስፔሻላይዝድ የዶሮ እርባታ ዩኒት እና የተደረሰበትን 1.29 ሚሊየን የእንቁላል ምርት በ2022 ወደ105 ዝቅተኛ ስፔሻላይዝድ ዶሮ እርባታ በማሳደግ የሚመረተውን የዶሮ እንቁላል 15.05 ሚሊየን ማድረስ

## የማርና ሰም ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ

*ግብ 4. በ2012* በጀት ዓመት መጨረሻ ከተደረሰበት 1524.8 ቶን የማር ምርት እና 27.14 ቶን የሰም ምርት በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ *4371 እና 45* ቶን በቅደም ተከተል ማድረስ፣

በ2012 መጨረሻ ከአንድ ቀፎ እየተገኘ ያለውን አማካኝ አመታዊ የማር ምርታማነት ከባህላዊ ቀፎ *8.08* ኪ.ግ ኪግ፣ ከሽግግር ቀፎ 26.7 ኪ.ግ እና ከዘመናዊ ቀፎ *26.2* ኪ.ግ በ2022 መጨረሻ ከባህላዊ ቀፎ *9* ኪ.ግ፣ ከሽግግር *28* ኪ.ግ እና ከዘመናዊ ቀፎ *30* ኪሎ ግራም ማድረስ፣

ከማርና ሰም ምርት በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ገበያ ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጡ የንብ ውጤቶች (እንደ ፕሮፖሊስ፣ የንብ ወተት፣ የንብ መርዝ የመሳሰሉት) ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት እና ለስራው የሚያስፈልጉ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን የክልሉን ድጋፍ ጭምር በመጠቀምና በማሟላት አምርቶ ለገበያ በማቅረብ ከንብ ሀብታችን የሚገኘውን የገቢ አማራጭ ማስፋት

### በንብ ሀብት ልማት የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- የሽግግር ቀፎ አዘገጃጀት፣አያያዝ እና አጠቃቀም ላይ ያለውን የአመለካከት እና የክህሎት ችግር በመፍታት 6545 ኢትዮ ርብራብ የሽግግር ቀፎ ከአካባቢ ቁሳቁስ መስራት
- በ2012 የተደረሰበትን ዓመታዊ በህብረ-ንብ የተሞላ*14467* ዘመናዊ እና *7541* ሽግግር ቀፎ በ15% በየዓመቱ በዓማካኝ በማሳደግ በ2022 በህብረ-ንብ የተሞላ ዘመናዊ ቀፎ ዓማታዊ አቅም *58527-* እና የሽግግር ቀፎ *30507* በማድረስ አሁን ያለውን 116461 በህብረንብ የተሞላ ባህላዊ ቀፎ በየዓመቱ በማሻሻልና በመቀነስ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ
- የእናት ንብ ማባዛት /ህብረንብ ከፊላ ስራዎችን በተጠናከረ መንገድ በጥራት በመፈጸም በየአመቱ *በ15%* በማሳደግ በ2022 መጨረሻ *18622* አዲስ ኮሎኒ ማግኘ፣

- ጥራት ያለው የማር ምርት ለማምረት የሚያስችሉ በምርምርና ጥናት የተደገፉ የንብ ቀሰም እጽዋት ዝርያወችን በማላመድ 800 ሄ/ር መሬት በማልማት እና በማስፋፋት ደረጃውን የጠበቀ የማር ምርት ለማምረት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣

## ዓሣ ሀብት ምርታማነትን ማሳደግ፡

**አላማ 5.** በዞኑ ከሚገኙ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ የውኃ አካላት በ2012 መጨረሻ የተመረተውን 98 ቶን የዓሣ ስጋ 2022 መጨረሻ ዓመታዊ የማምረት አቅም ወደ 2399 ቶን የዓሣ ስጋ በማሳደግ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ። ለዚህም በ2012 የተመረተውን ከሀይቆች 132.3 ቶን ከወንዞች 88 ቶን ከግድቦች 0.2 ቶን የዓሣ ምርት በ2022 መጨረሻ ከሃይቆች 2078 ቶን ከወንዞች 205 ቶን፣ ከግድቦች 110 እና ከአኳካልቸር (ከነባር እና አዲስ ኩሬወች) 6 ቶን በድምሩ 2399 የዓሣ ምርት በማምረት ነባር እና አዲስ የዓሳ አስጋሪ ማህበራትን እና ቡድኖችን ተጠቃሚ ማድረግ፣

**ግቡን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በዞኑ ተገንብተዉ የዓሣ ጫጩት ያልተጨመረባቸዉን ግድቦች የዓሳ ጫጩት በመጨመርና በቀጣይ 10 ዓመት ከሚገነቡት ግድቦች ዉስጥ ለዓሣ እርባታ አመች የሆኑትን በመለየት 1000 የዓሳ ጫጩት በመጨመር የዘርፉን ምርታመነት ለማሳደግ መስራት።
- የመስኖ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ባሉበት አካበቢዎች ከሌሎቸ የግብርና ልማት እንቅስቃሴዎች ጋር በማቀናጀት በአ/አደር ቤተሰብ ደረጃ 40 የዓሳ ኩሬ እንዲያዘጋጁ በማድረግ 1000 የዓሳ ጫጩት መጨመር
- ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት የተደራጁ ማህበራትን፣ ኢንተርፐራይዞችን እና ባለሀብቶችን የሙያ ድጋፍ በማድረግ የገበያ ትስስሩን ማሳለጥ፣

## የቆዳና ሌጦ ምርትን ማሳደግ፡

- **ግብ 6.** በ2012 ያለውን 1093594 የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅርቦት በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ 1947250 ማድረስ ።

**ግቡን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት**

- በ2012 የተደረሰበትን ዓመታዊ የቆዳና ሌጦ ምርት 1093594 (የዳልጋ ከብት ቆዳ 159938 የበግ ሌጦ 584476 የፍየል ሌጦ 349180 ምርት) በ2022 መጨረሻ የዳልጋ

ከብት ቆዳ 306491 የበግ ለየጦ 1023262 እና የፍየል ሌጦ 617497 በድምሩ 1947250 ጥሬ የቆዳናሌጦ ምርት ደረጃውን ጠብቆ እንዲመረት ማድረግ

- በዘርፉ የተሰማሩ ነጋዴዎችን እና የቆዳና ሌጦ ማደራጃ ቤት ሰራተኞችን በማሰልጠን ከእርድ በፊት፣በእርድ ወቅት እና ከእርድ በኋላ የሚደርሰውን የቆዳና ሌጦ የጥራት መጓደል እና የምርት ብክነት በ75% በመቀነስ ለገበያ የሚቀርበውን ምርት ማሳደግ፣

## የእንስሳት ኤክስቴንሽን አግልገሎትን ማስፋፋት ፡

በሚቀጥሉት አስር አመታት አርሶ አደሩን በኤክስቴንሽን ፓኬጅ ተሳታፊ በማድረግ በ2012 ዓ/ም ከነበረው 118035 በ2022 ወደ 362470 ማድረስ፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት አስር ዓመታት የኤክስቴንሽን አገልግሎት ውጤት የሚለካው በዕውቀቱ፣ በክህሎቱና በአመለካከቱ ተለውጦ ቴክኖሎጂዎችን በመቀበልና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚተገብር አርብቶ አደር ሲፈጠር ይሆናል፡፡ ከእነዚህ የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች ውስጥ በ2022 መጨረሻ 80 በመቶ አርሶአደሮች ሙሉ የእንስሳት ፓኬጅ የሚተገብሩና የተሻሻሉ ቴክኖሎጅንና አሰራር ተጠቃሚ ማደርግ

## በዘርፉ የስራ እድል የተፈጠረላቸዉ ወጣቶች ቁጥርማሳደግ፡

በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከተደረሰበት 11967 ወጣቶች በ2022 መጨረሻ 96663 ለሚሆኑ ወጣቶች በዘርፉ የስራ እድል በመፍጠር የወጣቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እና በዘርፉ የቴክኒወሎጅ ሽግግር በማምጣት አሰራሩን ማዘመን፡፡

## እንስሳት መኖ አቅርቦት ማሳደግና እና አጠቃቀም ማሻሻል

በእንስሳቱ የሚፈለገውን ድርቆ መኖ ፍላጎትና አቅርቦት ልዩነት ለማጥበብና በበቂ ሁኔታ ለማሟላት በየዓመቱ ተጨማሪ 10% በጥራት በማምረት የድርቆ መኖ አቅርቦትን በ2012 ከተደረሰበት 3.95 ሚ/ቶን በ2022 መጨረሻ የሚገኘውን ድርቆ መኖ 4.13 ሚ/ቶን ማድረስ፣ ይህን ማሟላት የሚቻለዉ አሁን እየተመረተ ያለውን ድርቆ መኖ ከግጦሽ መሬት ከ 1.9 ሚሊየን ቶን፣ ከተሻሻሉ መኖ ልማት 0.32 ሚ/ቶ፣ ከሰብል ተረፈ ምርት 1.63 ሚ/ቶ፣ ከአግሮ ኢንደስተሪ ተረፈ ምርት 0.1 ሚ/ቶን ድርቆ መኖ በ2022 መጨረሻ ከግጦሽ 2.01፣ ከተሻሻለ መኖ 0.32 ሚ./ቶ፣ ከሰብል ተረፈ ምርት 1.65 ሚ/ቶን እና ከአግሮ ኢንደስትሪ ተረፈ ምርት 0.1 ሚ/ቶን ድርቆ መኖ ፣በጥራት በማዘጋጀት እንስሳት በየታ፣እንደ እድሚያቸው፣

እንደሚሰጡት የምርት ዓይነት እና መጠን ለይቶ በመመገብ የመኖ አጠቃቃሙን በማሻሻል የእንስሳቱን ምርታማነት ለማሳደግ የሚሰራ ይሆናል፡፡

## እንስሳት ዝርያ ማሻሻል እና ጥበቃ ማጠናከር

1. **የዳልጋ ከብት ዝርያ ማሻሻል** ፡ በ2012 ከተደረሰበት የተሻሻሉ የዳልጋ ከብቶች ቁጥር 95567 በእጥፍ በማሳደግ በ2022 መጨረሻ 191134 ለማድረስ ግብ ተቀምጧል፡፡ በ2012 ከተደረሰበት የተፈጥሮ ድራት ድቀላን ከ11945, የሆርሞን ድራት ድቀላ 3787 እና በኮርማ ድቀላን 19030 በድምሩ 34740 ዓመታዊ የድቀላ አገልግሎት በየዓመቱ 7% በማሳደግ እና የተደረሰበትን 18163 የተሻሻለ ጥጃ ውልደት በ2022 መጨረሻ በተፈጥሮ ድራት 48719 ፣ በሆርሞን ድራት 9947 እና በተሻሻለ ኮርማ 45459 በድምሩ ዓመታዊ የማዳቀል አቅም 104125 ማድረስና በዚህም በ2022 ዓ.ም መጨረሻ 31843 ጥጆች በማስወለድ የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፡፡

## የእንስሳት ጤና አገልግሎት ተደራሽነትና ጥራት ማሳደግ

የማህበረሰብ እንስሳት ጤና ግንዛቤ ማሳደግ፡ የማህበረሰብ እንስሳት ጤና ግንዛቤ በአርቢዉ ህብረተሰብና ባለድረሻ አካላት (100%) ማድረስ፡፡ ይህን ግብ እዉን ለማድረግ የእንስሳት በሽታን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ለእንስሳት አርቢው ህብረተሰብ እንዲሁም ባለድርሻ አካለት በተለያዩ የእንስሳት ጤና ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ማስጨበጥ ቅድሚያ የሚሰጠው ቁልፍ ተግባር እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ 10 አመታት በበሽታ መከሰቻ ወቅቶች እና የክትባት ካላንደር ላይ ከእንስሳት ወደ ሰው እንዲሁም ከሰው ወደ እንስሳት የሚተላለፉ በሽታዎች ምንነትና መከላከያ ዘዴዎችቻው እንዲሁም በህገ-ወጥ የእንስሳት እርድና መድኃኒት ዝውውር ላይ የግንዛቤ ማዳበሪያ ትምህርት ለአርሶ አደሮች፤ በዘርፉ ለተሰማሩ የግል ባለሀብቶች፤ ማህበራት እና ሙያዊ ድጋፍ ለሚያደርጉ አካላት የተለያዩ የኤክስቴንሽን ሲስተም ፤ ሚዲያዎች፡ በራሪ ወረቀቶች ወዘተ በመጠቀም የማስገንዘብ ስራ ይካሄዳል፡፡በዚህም አሁን የሚገኘውን በእንስሳት እርባታ ዘርፍ ከተሰማራው የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደሮች ቁጥር በየአመቱ 10 በመቶ በማሰልጠን በ2022 የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎችን ሙሉ በሙሉ ተደራሽ ለማድረግ ይሠራል፡፡

### በእንስሳት ሕክምና የማህበረሰብ ጤና አገልግሎትን ማጠናከር (veterinary public health)፡

**የዳልጋ ከብት ጥጆች፣ የበግና ፍየል ግልገሎች እና የዶሮ ጫጩት ሞት መጠንን መቀነስ፡**

በተለያዩ ጥናቶች የተቀመጠዉን የዳልጋ ከብት ጥጆች ሞትን አሁን ካለበት 12% ወደ 5%፣ የበግና ፍየል ግልገሎች ሞትን አሁን ካለበት 19% ወደ 5%፣ የዶሮ ጫጩት ሞትን አሁን ካለበት 57% ወደ 15% መቀነስ፣

*የእንስሳት ጤና ህክምና እና ክሊኒክ አገልግሎት ሽፋንና ጥራት ማሳደግ፡*

የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሽፋን በ2012 ከነበረበት ~~ከ84%~~ በ2022 ዓ.ም ወደ 100% ማሳደግ በማሳደግ በመጠንና በጥራት የተሟላ አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ይህን ግብ ለማሳካት በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ጥራቱን የጠበቀና ዘመናዊ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሽፋንና ተደራሽነትን በበቂ ደረጃ ለማሳደግ የተጀመሩ ስራዎች ተጠናክሮ ይቀጥላሉ፡፡

በወረዳዎች በሚገኙ ቀበሌወች በሙሉ1 ጤና ኬላ በመገንባት የክሊኒክ አገልግሎት ሽፋን አሁን ካለበት 84% ወደ 100% የሚደረስ ይሆናል፡፡ የተገነቡና የሚገነቡ የእንስሳት ጤና ክሊኒኮች እና ጤና ኬላወች አስፈላጊውን የሰለጠነ የሰው ሀይል፣ቁሳቁስ እና በቂ በጀት እንዲሟላ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ለማሻሻል አሰፈላጊዉን ሀብት በመንግስትና በህብረተሰብ ተሳትፎ በመመደብ የክሊኒኮችን ደረጃ 20% ሲ፣60% ቢ እና 20% ኤ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

**የንብ ማነቢያ ምርት ማቀነባበሪያ ግብዓት አቅርቦት ማሳደግ፡**

የሽግግር ቀፎ አቅርቦት በ2012 ከተደረሰበት 3218 በ2022 መጨረሻ 3218 የሽግግር ቀፎ የአርሶአደሩን ሰርቶ የመጠቀም አቅም በማሳደግ እንዲቀርብ 23025 ማድረግ፡፡

## 10.3. አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና

**ግብ 1፡ትክክለኛ የፕሮግራም ደንበኛ ቤተሰቦችን መለየት**

**ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ደንበኛ ልየታ (Client Selection)**

በፕሮግራሙ የልየታ ወቅት ይስተዋል የነበረው ሙሉ ቤተሰቦችን ያላማካተት እና ለሁሉም የማዳረስ ችግር በቀጣይ እንደሚፈታ እና ሙሉ ቤተሰቦችን የማካተት ስራ እንደሚሠራ ይታሰባል፡፡ የልማታዊ ሴፍቲኔት የፕሮግራም ደንበኞች ልየታ ፍትሃዊ፤ አሳታፊ እና

ግልፀኝነት አሠራር የሠፈነበት የደንበኛ ልየታ መርህን ይከተላል፡፡ ስለሆነም ለተለያዩ የፕሮግራሙ ድጋፎች ተጠቃሚነት የልየታ ስራ በማነኛውም የማህበረሰብ አባል ላይ መገለል እና መድልዖ እንዳያስከትሉ በጥንቃቄ ይሠራሉ፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍም የቅድሚያ ማስጠንቀቂያን ተከታታይ መረጃዎች፣ ከስነምግብ ችግር ጋር በተያያዘ ደግሞ የጤና ተቋማት መረጃዎችን መሠረት በማድረግ የሚሰራ ይሆናል፡፡

**የልማታዊ ሴፍቲኔት ተመራቂ ልየታ** (Targeting for Graduation)

የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የመጨረሻ ግብ የምግብ ዋስትና መታጣት ችግር ላለባቸው የፕሮግራሙ ደንበኞች የተለያዩ ድጋፎች በማቅረብ በምግብ እራሳቸውን እንዲችሉ እና አነስተኛ አደጋዎችን መቋቋም እንዲችሉ በማድረግ ከልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም እንዲመረቁ ማድረግ ይሆናል፡፡

ፕሮግራሙ የሚካሄድባቸዉ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ከፕሮግራሙ ደንበኞች ጋር፣ ከዞንና ከወረዳዎች ጋር በጋራ ታቅደው በፕሮግራሙ የተቀመጡ ስትራቴጅዎችና አቅጣጫዎችን በቅልጥፍና እና በዉጤታማነት በመፈፀም፣ በማህበረሰቡም ይሁን በቤተሰብ ደረጃ የሚሠሩ የገቢ ማስገኛ ተግባራት (የማህበረሰብና የቤተሰብ ጥሪት ግንባታ) ማቀድ እና መፈፀም፣ ብሎም ወደ ሚታሰበው የምረቃ ግብ ማድረሳቸውን በመከታተልና በመገመገም ችግር ካለም ለችግሮች

## ግብ ግብ .2. የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ደንበኞችን የምግብ ክፍተት እና የስነምግብ ችግር በመሙላት የጥሪት መመናመንን መከላከል

የተጠቃሚዎች የክፍያ ዓይነት በእህል ወይም በገንዘብ ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም የተጠቃሚዉን ቤተሰብ ፍላጎት፣ በመንግስት እና በለጋሽ ድርጅቶች የማቅረብ አቅም የሚወሰን ሆኖ የገንዘብ ክፍያ ቅድሚያ የሚሠጠው ይሆናል፡፡ የተጠቃሚዎችን የክፍያ መጠን በሚመለከት ለተጠቃሚዎች የሚከፈለው የቀን ምንዳ የአንድ ሰው በቀን የሚያስፈልገው አማካኝ የሀይል መጠን (2,100kCal per person per day) መሠረት ያደረገ ቢሆንም እንደ ሀገር 3 ኪ.ግ እህል (በወር 15 ኪ.ግ) ሲሆን ክፍያዉ በገንዘብ ሲሆን በቀን የሚከፈለው 3 ኪ.ግ. የምግብ እህል መግዛት የሚያስችል ይሆናል፡

**የትራንስፈር ተደራሽነት፣** የአለም አቀፍ ድንጋጌዎች የሰብዓዊ ድጋፎች አቅርቦት ተደራሽነት ከተጠቃሚዎች መኖሪያ ቤት ከ5 ኪሎ ሜትር እርቀት መብለጥ እንደሌለባቸው ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ከ90% በላይ የሚሆኑት ተጠቃሚዎች በአንድ ሰዓት የእግር ጉዞ እርቀት ክፍያቸውን ማግኘት እንዳለባቸው ይደነግጋሉ፡፡ እንዲሁም 90% የሚሆኑት የስነ ምግብ ችግር

ያለባቸው እና ለድጋፍ የተለዩ ቤተሰቦች ድጋፋቸውን ከአንድ ቀን ደርሶ መልስ የእግር ጉዞ ማግኘት እንዳለባቸው ያስቀምጣል፡፡

**የልማታዊሴፍቲኔትትራንስፈርወቅታዊነት**

የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች በምግብ እጥረት ምክንያት ምርታማ እሴቶቻቸዉን እንዳይሸጡ የተመደበላቸውን የቀን ምንዳ በፕሮግራም ማስፈፀሚያ ሠነዱ (PIM) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ በገንዘብ ከሆነ ክፍያዉ ወሩ ባለቀ በ20 ቀናት ዉስጥ፤ክፍያዉ በዓይነት ከሆነ ደግሞ ክፍያዉ ወሩ በተጠናቀቀ በ30 ቀን ዉስጥ ሙሉ በሙሉ ለተጠቃሚዎች ለማድረስ ይሠራል፡፡ ለዚህም ተፈጻሚነት ከፌደራል ሃብት አለቃቅ ጀምሮ ክፍያ ፈፃሚ ተቋማት እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉ በሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብና ቅንጅታዊ አሰራር የሚጠናከር ይሆናል፡፡

**ግብ 3. የተለያዩ የኤክስቴንሽን አገልግሎት እና የስራ መነሻ የሚሆን ሀብት (ብድር እና የነፃ ትራንስፈር) በመስጠት በቤተሰብደረጃእሴትመፍጠር (Household Asset building) ፤**

**የብድር አቅርቦት፡-** የብድርአቅርቦቱንቀጣይእናአስተማማኝለማድረግየተላያዩ አማራጮችን መጠቀም ግድ ይሆናል፡፡ እነዚህም ለብድር አገልግሎት የሚውል ገንዘብ ከፌደራል መንግስት እና ሌሎች ድጋፍ ሠጭ ድርጅቶች ተጨማሪ የተዘዋዋሪ ገንዘብ ለአነስተኛ የገንዘብ ተቋማት መስጠት፤ ከማህበረሰቡ በቁጠባ እና በእንሹራንስ መልክ ገንዘብ መሰብሰብ፤ ለብድር እየዋለ ያለውን ውዝፍ ብድር በማስመለስ እንደገና ለብድር እንደሚያገለግሉ ይታሰባል፡፡

**የኑሮማሻሻያነፃትራንስፈር አቅርቦት፤** ከጠቅላላው የፕሮግራም ደንበኞች 30% ለሚሆኑት ብድር ለሚፈሩየድሃድሃለሆኑየፕሮግራሙደንበኞችበተለያዩየገቢማስገኛአማራጮችተሠማርተውበቤተሰብ ደረጃ ተጨማሪ እሴትእንዲፈጥሩ ለማስቻልለመነሻየሚሆን በአንድ ቤተሰብ አንድ ዙር 400 የአሜሪካን ዶላር የኑሮማሻሻያትራንስፈር በነፃ ይሰጣቸዋል፡፡

## 10.4. ህብረት ስራ ማህበራት

ግብ 1፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት ብዛት አሁን ከተደረሰበት 617 በቀጣይ 10 ዓመት መሪ እቅድ 40 በመጨረሻ 657ማድረስ፣

**ግቡን ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራት**

- የተገልጋዮችን የኅብረት ሥራ ማህበራት ጥቅም ግንዛቤ ለማሳደግ እና ፍላጐት ለመፍጠር በየዓመቱ 1070 በ10 ዓመት 10700የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮች በቀበሌ ደረጃ ይካሄዳል፣
- በቀበሌ 150፣ በት/ቤት 200 የህብረት ሥራ ማህበራት ክለባት በማቋቋም እና በቀበሌ ደረጃ 537እና በት/ቤት ደረጃ 1200 የተቋቋሙ ነባር ክበባትን እንዲጠናከሩ ይደረጋል፤
- በየሶስት ዓመቱ ህጋዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት የምስክር ወረቀት እድሳት መስጠት፤

### የትኩረት አቅጣጫ 1፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላትን ተጠቃሚነት ማሳደግ

- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የአባላት ቁጥር አሁን ካለበት 674602 በቀጣይ 10 ዓመታት በየዓመቱ በ5% በማሳደግ የአባላትን ቁጥር ወደ 913689 ማሳደግ፤
- የሴት አባላትን ቁጥር አሁን ካለበት 25.8% ወደ 50% ማሳደግ እና የወጣት አባላትን ተሳትፎን አሁን ካለበት 29% ወደ 50% ማድረስ፤
- የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ካፒታል አሁን ካለበት 326047671 በየዓመቱ በ5% በማሳደግ ወደ 645284314 ማድረስ እንዲሁም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖችን ደግሞ አሁን ካለበት 7485000. በየዓመቱ በ10% በማሳደግ ወደ 95427169 ማድረስ፤
- ከጉድለት ነፃ የሆኑ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን አሁን ካለበት 39% ወደ 100% እንዲሁም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖችን ደግሞ ከ75% ወደ 100% ማሳደግ፤

### በየትኩረት መስክ-2፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት ተሳትፎና ድርሻ

የአገር ውስጥ የምርትና የአገልግሎት ግብይቱን የተሳለጠ እንዲሆን ለማድረግ የአምራች የኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያየ ምርት ከሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት በተመሳሳይ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የፍጆታ ምርቶች ፍላጎት ለማሟላት ከኢንዱስትሪ ምርት አምራቾች፣ አቀነባባሪዎች እና ከጅምላ አቅራቢዎች ጋር ውጤታማ የግብይት ትስስር እንዲፈጥሩ በማድረግ እና የግብይት ሰንሰለቱን በማሳጠር አምራቹና ሸማቹ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ማዕከል በማድረግ የህብረት ሥራ ማህበራትን የግብይት ተሳትፎ እና የግብይት ድርሻቸዉን ማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡

ከአገር ዉስጥ ግብይት በተጨማሪም የኅብረት ሥራ ማህበራት በውጪ ግብይት ያላቸውን ተሞክሮ በማስፋት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የግብርና ምርት በወቅቱና በብዛት ቀጣይነት

ባለው መልኩ በማሰባበሰብ እና በማከማቸት የዓለም ገበያ በማፈላለግ እና ጠንካራ የግብይት ትስስር በመፍጠር እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

በአጠቃላይ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የገበያ ድርሻ ለማሳደግ፤ የአባላትን ገቢ እንዲጨምርና ኑሮአቸውን እንዲሻሻል በቀጣይ 10 ዓመታት በየደረጃዉ ያሉ አካላት የትኩረት ማዕከል ተደርጎ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም የደቡብ ወሎ ዞን ህ/ስ/ማ/ማ/ተ/ጽ/ቤት የቀጣይ 10 ዓመታት ዋና ዋና የግብይት ግቦች እና ግቦችን ለማሳካት የሚከናዎኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-

**የትኩረት አቅጣጫ 3፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት የግብይት ተሳትፎ፤ ድርሻና የአባላት ተጠቃሚነት ማሳደግ፣**

**ግብ 1፡- የኅብረት ስራ ማኅበራት የሀገር ውስጥ የግብርና ምርት ግብይት ድርሻ አሁን ከነበረበት ከ5.06% ወደ 35% ማሳደግ፤**

**ግቦችን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት (Activities)**

- በምርት አቅራቢ እና ምርት ተቀባይ ተቋማት መካከል ጠንካራ የገበያ ትስስር እና ዘላቂነት ያለዉ እንዲሆን ማድረግ፣
- በቀጣይ 10 ዓመታት 9144812 ኩ/ል የተለያዩ የግብርና ምርቶችን በመሰብሰብ ለሀገር ዉስጥ ገበያ ማቅረብ፤
- የብዕርና አገዳ ሰብል የሚሰበሰብ መጠን ከ437913፣ የጥራጥሬ ሰብል የሚሰበሰብ መጠን ከ345517፣ የቅባት ሰብል የሚሰበሰብ መጠን 14588፣ የቅመማቅመም ሰብል የሚሰበሰብ መጠን 8021 ኩ/ል፤ የአት/እና ፍራ/ ምርት የሚሰበሰብ መጠን 108443 ኩ/ል በድምሩ 9144812 ኩ/ል ምርት በቀጣይ 10 ዓመታት እንዲሰበሰብ ይደረጋል፣
- የወተት ምርት የሚሰበሰብ መጠን 13856648 ሚ/ን ሊ/ር፣ የዓሳ ምርት የሚሰበሰብ መጠን 5715 እንዲሁም 1725 ኩ/ል የማር ምርት የሚሰበሰብ ይሆናል፣

**ግብ- 2፡- የግብርና ምርቶች የውጭ ግብይት ድርሻ በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት 5000 ኩ/ል ወደ 100000 ኩ/ል ማድረስ፤**

**ግቦችን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት (Activities)**

- የወጭ ምርት ተሳታፊ ዩኒየኖች ቁጥር በ2012 ዓም ከተደረሰበት 2 ወደ 3 ማሳደግ፣

- በውጭ ገበያ ተፈላጊና የላቀ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የግብርና ምርቶችን በመለየትና በመሰብሰብ ለዉጭ ገበያ እንዲቀርብ ማድረግ፣
- በአደራጅ ተቋማት፤በኅብረት ስራ ማኅበራትና በአጋር አካላት መካካል ወቅታዊ፤ታማኝነትና ተከታታይነት ያለው የውጭ የገበያ መረጃ ልውውጥ ማካሄድ፤

የትኩረት አቅጣጫ 4፡- በኅብረት ስራ ማኅበራት በኩል የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች፤ ቴክኖሎጅዎች፤ አገልግሎቶች፤ የኢንዱስትሪ/ፍጆታ ሸቀጦች አቅርቦት፣ ተሳትፎ እና የአባላት ተጠቃሚነት ማሳደግ፤

ግብ 1፡- የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት መጠን በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት ከ1387638 ኩ/ል
ወደ 6908368 ሚ/ኩ ማሳደግና ስርጭቱን ማሻሻል፤

ግብ 2፡- የምርጥ ዘር አቅርቦት መጠን በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት ከ40127 ኩ/ል ወደ 205584 ኩ/ል ማሳደግና ስርጭቱን ማሻሻል፤

ግብ 3፡- የምርጥ ዘር ብዜት ተሳትፎ በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት ከ2318 ኩ/ል ወደ 45,000 ኩ/ል ማሳደግ፤

ግብ 4፡- የቅድመ እና ድህረ ምርት ልዩ ልዩ ቴክኖሎጅዎችን አቅርቦት መጠን በ2012 ዓ.ም መጨረሻ
ከተደረሰበት ከ10 ወደ 21 ማሳደግ፤

ግብ 5፡- በግብርናና በሸማች ኅብረት ስራ ማኅበራት በራሳቸው ጥረት እና በመንግስት ድጎማ የሚቀርብላቸውን በአባላት ፍላጎት መሰረት የኢንዱስትሪ ምርቶች/ፍጆታ ሸቀጦች አቅርቦት መጠን ከ1794106244 ቢሊዮን ብር ወደ3705381904 ቢሊዮን ብር ማሳደግ፤

የትኩረት አቅጣጫ 3 ፡- የግብይት መሰረት ልማት ማስፋፋት፤ አሰራር ስርዓት መዘርጋት፤ አቅም መገንባት

ግብ 1 ፡- ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዝኖች ግንባታ ብዛት ከ279 ወደ 489 ማሳደግ፤ ምርት ማከፋፈያ ሱቆችን ቁጥር ከ248 ወደ 348 ማሳደግ፤ የሀገር ውስጥና የውጭ ገበያ መረጃ አመራር ስርዓት በዩኒዩኖች ዝርጋታ አሁን ካለበት 0 /ዜሮ/ ወደ 4 ማሳደግ፤ 4 የአሰራር መመሪያ፤ ሞዳሊቲና ማኑዋል ማዘጋጀትና ማሻሻል፤

ግብ 2፡- የኅብረት ስራ ግብይትን ለሚደግፉ 902 ባለሙያዎች፤ ግብይቱን የሚፈጽሙ 15,112 አመራር አካላት፤ 7,728 ቅጥር ሰራተኞች እና 9,230 ግለሰብ አባላት በግብይት ዘርፍ ያላቸው ዕውቀትና ክህሎት የመፈጸም አቅማቸውን ማሳደግ፤

ግቦችን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት (Activities)

- የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በንድፈ ሃሳብና በተግባር መስጠት፤
- ስልጠና ክትትል ማድረግ፤ ስልጠናዎች ምን ያህል እንደሰረጹና በተግባር ያመጡትን ለውጥ/ውጤታማነት በመስክ መገምገም፤

የትኩረት መስክ-5፡- የአግሮ ፕሮሰሲን ኢንዱስትሪዎችን ዉጤታማነት ማሳደግ እና ማስፋፋት

የኅብረት ሥራ ማህበራት በአባላት ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር አባላት ከምርታቸው የተሻለ የገበያ ዋጋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተለያዩ ዓይነት አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም እና ነባሮቹን ደግሞ በማጠናከር የአባላት ምርቶችን ላይ እሴት በመጨመር ለሀገር ዉስጥ እና ለዉጭ ገበያ እንዲያቀርቡ በትኩረት ይሰራል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በየደረጃው የሚደረገው የእሴት መጨመር ተግባር የጥራት ደረጃ፣ የዋጋ ተወዳዳሪ እና አዋጭነት፣ተቀባይነት፣ ቀጣይነት እና የተጠቃሚነት ደረጃ በማጥናት የእሴት ሰንሰለትን ተከትሎ ከቀላል እስከ ከፍተኛ ዕሴት መጨመር ተግባራት የሚሰራ ሆኖ በዋናነት በሰብል፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በእንስሳት እና እንስሳት ተዋጽኦ ምርቶች ማቀነባበር ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

በቀጣይ 10 ዓመታት የአግሮ ፕሮሰሲን ኢንዱስትሪዎችን ዉጤታማነት ለማሳደግ እና ለማስፋፋት የተጣሉ ዋና ዋና ግቦችና ግቦቹን ለማሳካት የሚከናዎኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-

ግብ 1፡- የተለያዩ የግብርና ምርቶችን የሚያቀነባብሩ አግሮ ፕሮሰሲንግ ፋብሪካዎችን በ2012 ከደረሰበት 0 /ዞሮ/ ፋብሪካዎች ወደ 2 ፋብሪካዎች ማሳደግ፤

ግቦችን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት (Activities)

- በቀጣይ 10 ዓመታት 2 የሚሆኑ የተለያዩ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎችን ማቋቋም፣

- ለማቀናበሪያ ፋብሪካዎች የግብርና ጥሬ ምርቶች በማሰባሰብና ተጨማሪ ግብዓቶችን ከሌሎች አቅራቢዎች ለማሟላት የገበያ ትስስር መፍጠር፤ በኮንትራት ማስመረትና ግዥ በመፈጸም ሂደት መደገፍና መከታተል፤

## የትኩረት መስክ-4፡- የኅብረት ሥራ ማኅበራት ቁጠባና ኢንቨስትመንት

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን ባልተዳረሰባቸው የገጠርና የከተማ የኅብረተሰብ ክፍሎች አዳዲስ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትን በማደራጀት እንዲሁም በነባር የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት በማጠናከር የአባላትን ቁጥር በማሳደግ፣ የካፒታል መጠን በመሻሻል፣ የአባለትን የቁጠባ ባህል በማዳበር ከፍተኛ ቁጠባ በመሰብሰብ የአባላትን የብድር ፍላጎት መሠረት በማድረግ የብድር አገልግሎቶችን በማስፋፋት የአባላትን ገቢ የሚያሳድጉ እና የሥራ እድል የሚፈጥሩ ኢንቨስትመንቶችን የማስፋፋት ሥራ ትኩረት ተሰጥቶ የሚከናዎን ቁልፍ ጉዳይ ይሆናል። የኅብረት ሥራ ማኅበራት ቁጠባና ኢንቨስትመንት ለማስፋፊት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀርፀዋል፡-

ግብ 1፡- የመሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራትን ቁጥር አሁን ካለበት 577 ወደ 598 እንዲሁም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒየኖችን ቁጥር አሁን የተደረሰበትን 4 አጠናክሮ መቀጠል

ግብ 2፡- የመሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት የአባላትን ቁጥር አሁን ካለበት 179122 ወደ 403522 ማሳደግ፣

ግብ 3፡- በመሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት የሴቶችን የአባልነት ሽፋን አሁን ካለበት 32.5% ወደ 50% ማድረስ፣

ግብ 4፡- የኅብረት ስራ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒዬኖች የአባላትን ቁጥር አሁን የተደረሰበት 4 አጠናክሮ መቀጠል

ግብ 5፡- የመሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት ካፒታል አሁን ካለበት ብር 86933330 ወደ ብር 137948460 ማድረስ፣

ግብ 6፡- ህብረት ስራ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒዬኖችን ካፒታል አሁን ካለበት 38029764 ወደ 1722408246 ማሳደግ፣

ግብ 7፡- የመሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት መደበኛ ቁጠባ አሁን ካለበት

ብር 179180908 ወደ ብር 366626900 ማሳደግ፣

ግብ 8፡- የህብረት ስራ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒዬኖች መደበኛ ቁጠባ አሁን ካለበት ብር 486692525 ወደ 145347870 ብር ማሳደግ

ግብ 9፡- የመሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት ብድር ስርጭት አሁን ካለበት

ብር 590608220 ወደ ብር 1847910620 ማሳደግ፣

ግብ 10፡- የኀብረት ስራ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒዬኖች ብድር ስርጭት አሁን ካለበት

ብር 567346210 ወደ ብር 1959152510 ማድረስ፣

ግብ 11፡- የህይወት መድን አገልግሎት የሚሰጡ የኀብረት ሥራ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒዬኖች 4 በማጠናከር አገልግሎታቸውን እንድያሰፉ ማድረግ፣

## የትኩረት መስክ-5፡- የኀብረት ሥራ ማህበራት ህግና ህጋዊነት እና ጤናማነት

የኀብረት ሥራ ማህበራት መርሆዎቻቸውንና እሴቶቻቸውን ጠብቀው በመሥራት የአባላትን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሚችሉበት ቁመና እንዲኖራቸው እና ህግን አክብረው መስራታቸውን ኢንስፔክት በማድረግ የታዩ የአሰራር ግድፈቶች ላይ የእርምት እርምጃ የመውሰድ ተግባር ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡

የኀብረት ሥራ ማህበራት ወቅታዊ የፋይናንስ አቋማቸው ተረጋግጦ በአባላቱ እንዲሁም በሌላ ወገን ተቀባይነት እንዲኖራቸው ለማስቻል የኀበርት ሥራ ማኀበራት ኦዲት አገልግሎት ሽፋን እንዲያድገና ጥራቱ የተጠበቀ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

የኀብረት ሥራ ማህበራት ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በተቀመጠው መመዘኛ መሥፈርት መሠረት ተመዝነው በሚያገኙት የአፈፃፀም ብቃት ደረጃቸውን በመለየት ለአቅም ግንባታና ለሌሎች ድጋፍ አሰጣጥ ዝግጁ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

ግብ 1፡- የኀብረት ሥራ ማህበራትን የኢንስፔክሽን ሽፋን በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት ከ83 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፣

ግብ 2- የኀብረት ሥራ ማህበራትን የጉድለት አመላለስ በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት ከ 18.3 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ

**ግብ 2፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የኦዲት አገልግሎት ሽፋን ኦዲት መደረግ ካለባቸው ህብረት ሥራ ማህበራት በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 56.2 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ**

**ግብ 3፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ የአገልግሎት ሽፋን በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 0% ወደ 100% ማሳደግ፣**

**ግቡን ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- ሁሉንም የኅብት ሥራ ማህበራትን የብቃት ደረጃ በመለየት የምስክር ወረቀት መስጠት፣
- በብቃት ደረጃ ምዘና መሠረት ከደረጃ በታች የሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራትን በመለየት ድጋፍ እንዲየገኙ ማድረግ፣

## 10.5. መሬት

**ግብ 3፡- የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርትፍኬት መስጠት አሁን ካለበት 98555 ይዞታ እና 479026 ማሳ ወደ 724070 ይዞታና 4403262 ማሳ በማድረስ የይዞታና የመጠቀም መብት ዋስትና ማረጋገጥ፣**

- በእቅድ ዘመኑ ለ 625515 ባለይዞታዎች 3924236 የማሳ ካርታ በማዘጋጀት በሁሉም የይዞታ ዓይነቶች የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ይሰጣል፣

**ግብ 5፡- በኮምፒውተር ሳይመዘገቡ የቀሩትን የሁሉንም የመሬት ባለይዞታዎች የመሬት መረጃ 100% ወደ ISLA (InformationSystem for Land Administration) Software በማስገባትየመሬትመረጃ ደህንነትና የአሰራርቅልጥፍናስርዓት ይሻሻላል፡፡**

- ሳይመዘገቡ የቀሩ ሁሉንም (348248 )የመሬት ባለይዞታዎች የመሬት መረጃ 100% ወደ ኮምፒውተር የመመዝገብ ስራ ይሰራል፣

**ግብ 6፡- የሚቀርቡትን ሁሉንም የመሬት ይዞታ ልውውጦች በማረጋገጥና በማጽደቅ በአናሎግ እና በ NRLAIS (National Rural Lanad Administration Information System) የመረጃ ሥርዓት በመመዝገብ የመሬት ግብይት ስርዓትንቀልጣፋነት ማሳደግ**

- የሚቀርቡትን ( ስጦታ 27734፣ ያለኑዛዜ ውርስ 105327፣ ኪራይ 14377) የመሬት ይዞታ ለውጦችን በማረጋገጥና በማጽደቅ በአናሎግ የመረጃ ሥርዓት የመመዝገብ ስራ ይሰራል፣

- በ20 ወረዳዎች የሚቀርቡትን 11446 የመሬት ይዞታ ልውውጦችን በማረጋገጥና በማጽደቅ በ NRLAIS(National Rural Lanad Administration Information System) የመረጃ ሥርዓት የመመዝገብ ስራ ይሰራል፣

**ግብ 7፡- ከመሬት ጋር የተያያዙ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት የመሬት ግጭቶችን መቀነስ፣**

- በዕቅድ ዘመኑ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት
- የተወረሩ 8168 ሄ/ር የወል መሬቶችን የማስመለስ፤
- በተሳሳተ ማስረጃ ከይዞታቸው የተፈናቀሉ 984 ተጋላጭ የህ/ሰብ ክፍሎች መረጃቸውን በማጣራት የይዞታ መሬታቸው እንዲመለስላቸው ይደረጋል፤
- በገጠር መሬትየይዞታና የመጠቀም መብት የሌላቸው 14340 ግለሰቦችን በመለየት 3698 ሄ/ር መሬት ወደ መሬት ባንክ የማስገባት ስራ ይሰራል፣
- ለ109792 ወጣቶችና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች በቡድንም ሆነ በጋራ መሬት በመስጠት ለስራ እድል መፍጠሪያ አገልግሎት እንዲውል የማድረግ ስራ በስፋት ይሰራል፡፡

**ግብ 8.በመሬት በማምረት አቅም ደረጃ ለ243,467 ባለይዞታዎች የመሬት አጠቃቀም እቅድ አዘጋጅቶ ርክክብ በማድረግ አሁን ካለው 480,600 ባለይዞታዎች ወደ 724,067 ባለይዞታ ማሳደግ**

መሬት የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለተጠቃሚው እንዲሰጥ እና አካባቢው የተጠበቀ መሬት ለመጭው ትውልድ ለማስተላላፍ እያንዳንዱ ማሳ በመሬት የማምረት አቅም ማጥናት፣ በጥናት መመራት እና መጠቀም ግድ ይላል፡፡

የእያንዳንዱ ማሳ የተለያዩ የመልማት አቅም ስላለው ለተጠናለት እና ለተወሰነለት ዓላማ ብቻ መዋል አለበት፡፡ ባለፉት አስር ዓመታት ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የክልሉ/የዞኑ ቀበሌዎችን በማጥናት ማቀድ ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት ለ243,467 ባለይዞታዎች፣ ለ403,702 ማሳዎች እና ለ119 ቀበሌዎች የመሬት አጠቃቀም በማጥናት ዕቀድ ይታቀዳል፡፡ ተጠንቶ የታቀደውን የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ለ243,467 ባለይዞታዎች፣ ለ403,702 ማሳዎች እና ለ119 ቀበሌዎች ርክክብ ይደረጋል፡፡ ርክክብ የተደረገውን የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ወደ ተግባር ለማስገባት ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ ይገባል፡፡ በመጭው አስር ዓመታትም ርክክብ ከተደረገላቸው እና ተጠንቶ ርክክብ የሚደረግላቸውን ለ264753 ባለይዞታዎች፣ ለ2402787 ማሳዎች እና ለ166

ቀበሌዎች ክትትል እና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ለ27598 ባለይዞታዎች፣ ለ66980 ማሳዎች እና ለ83 ቀበሌዎች በርክክቡ መሰረት ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

ግብ-9.*ግብ-4 በተሰማሚነት ደረጃ የተጠኑ የልማት ኮሪደሮች ከ 4 ወደ 6 ማሳደግ*

በተስማሚነት ደረጃ መሬትን ማጥናት ሁለተኛው እና ከመሬት የማምረት አቅም ቀጥሎ እየተጠቀምንበት ያለው መሬትን የምንገመግምበት ስልት ነው፡፡ ይህ ስልት የትኛው መሬት ለየትኛው የሰብል ዓይነት ይስማማል በሚል የሚለይ ሲሆን በእያንዳንዱ ዘርፍ እውቀት፣ ጊዜ፣ ጉልበት እና ከፍተኛ የሆነ መዋዕለ ነዋይ የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡ ባሳለፍነው አስር ዓመታት በቢሮው በዕቅድ ተይዘው ሳይጠኑ የቀሩትን መካከለኛው አማራ የልማት ቀጠና እና ደቡብ ምዕራብ የልማት ቀጠና 1፡20,000 ልኬት በማስጠናት ለፈፃሚ አካላት የማስረከብ ስራ ይሰራል፡፡

ግብ-11.*የዞኑን መሬት በYield Evaluation አቅም በመስረት ለተጠቃሚዉ ማረከብ*

በክልላችን እስካሁን መሬትን በማምረት አቅም እና በተስማሚነት ደረጃ ስራን በማጠናከር ጎን በጎን ይልድ ኤስቲሜሽን የአሰራር ሂደትን በመጠቀም በሞዴል ለመስራት 143 ቀበሌዎች፣ 715 ባለይዞታዎች እና 2,145 ማሳዎች በመስራት ለማስረከብ ታቅዷል ፡፡

**ግብ-14.የኢንቨስትመንትመሬቶች በመሬት አጠቃቀም እንዲመሩ በማድረግ የመሬት ምርታማነትን ማሳደግ**

በ11 ወረዳዎች የሚገኙ 1280.5 ሄ/ር ነባር እና አዲስ የኢንቨስትመንት መሬቶች በመሬት አጠቃቀም ጥናቱ መሰረት እንዲመሩ በማደረግ ተመጋጋቢ እና እርስ በርሳቸዉ ክላስተር ሆነዉ እንዲመሩ ማመላከት ስራ ይሰራል፡፡

**ግብ 15. በተበታተነ ሁኔታ የሚኖረውን አርሶ አደር በቀበሌ ማእከል ለማሰባሰብ በ1696 ቀበሌዎች ሽንሽና በማካሄድ ሽፋኑን ከ 1,620 የቀበሌ ማዕከላት ግንባታ ወደ 3316ቀበሌዎች ማእከላት ግንባታ ማሳደግ፤**

**ዋና ዋና ተግባራት**

እስካሁን ፕላን ያልተሰራላቸውን የ48 ቀበሌዎች ፕላን የማዘጋጀት ስራ ይሰራል፣

በ158 የቀበሌ ማእከላት 45,710 የቤት መስሪያ ቦታዎችን በ1,248.5 ሄ/ር መሬት ላይ በፕላናቸው መሰረት ይሸነሸናሉ፣

- 45,710 ግለሰቦች (ለመኖሪያ 35,300፣ ለተቋማት 1,260፣ ለስራ እድል ፈጠራ ለኢንተርፕራይዞች/ለንግድ/ 9,150) 1,248.5 ሄ/ር ቦታ ይረከባሉ፣
- ለ45,710 ግንባታዎች (ለመኖሪያ35,300፣ ለተቋማት 1,260፣ ለንግድ 9,150) ሳይት ፕላን ይሰጣል፣
- ለ22,855 ግንባታዎች (ለመኖሪያ 17,650 ለተቋማት 630፣ 4,575) የግንባታ ፕላን ይዘጋጃል፣
- ለ11,428 ግንባታዎች (ለመኖሪያ 8,825፣ ለተቋማት 315፣ ለንግድ 2,288) ቋሚ ካርታ ተዘጋጅቶ ይሰጣል፣
- 45,710 ግለሰቦች (ለመኖሪያ35,300፣ ለተቋማት 1,260፣ ለንግድ 9,150) በተረከቡት ቦታ ላይ ግንባታ ይጀምራሉ።
- ለ22,855 ግለሰቦች (ለመኖሪያ17,650፣ ለተቋማት 630 ፣ለንግድ 4,575) በተረከቡት ቦታ ላይ ግንባታቸውን እንዲያጠናቅቁ ይደረጋል፣
- የ920 ባለይዞታዎች ስመ ንብረት ዝውውር ይፈፀማል፣
- 11,428 ግለሰቦች (ለመኖሪያ 8,825፣ለተቋማት 315፣ ለንግድ 2,288) ወደ ገነቡት ቤት እንዲገቡ ይደረጋል፣
- ስታንዳረዱን ያሟሉ 70 የቀበሌ ማዕከላትን ወደ ታዳጊ ማዘጋጃ ቤት የማሳደግ ስራ ይሰራል፡

**ግብ 16. በ158 የቀበሌ ማእከላት የመሰረተ ልማት ስራዎች እንዲከናወኑ በማስተባበር ሽፋኑን ከ18 ቀበሌዎች ወደ 180 ቀበሌዎች ማሳደግ**

በቀጣይ አስር ዓመታት ከ2 ሺህ በላይ ነዋሪ ያላቸው ቀበሌ ማዕከላት ደረጃውን የጠበቀ የተቀናጀ መሠረተ-ልማትና አገልግሎት አቅርቦትን ለማሳደግ፡-

- የመንገድ ሽፋንን ተደራሽ ማድረግ በ 189 ቀበሌዎች ግንባታ እንዲከናወን የማስተባበር ስራ ይሰራል፣
- የውሃና ፍሳሽ ሽፋንን ለማስፋፋት በ336 ቀበሌዎች ድጋፍ ማድረግ፣
- የኃይል አቅርቦት ሽፊንን ለማሳደግ በ378 ቀበሌዎች እንዲዳረስ ከአጋር አካት ጋር በትብብር ይሰራል፣
- እንዲሁም አገራዊ የመሠረተ ልማት ቅንጅት ማስተር ፕላንና ማስፈጸሚያ ስታንዳርዶች ማዘጋጀትና የመሠረተልማት መረጃ የማደረጀት ስራ ይሰራል፣

- በተጨማሪም እያንዳንዱ የመሠረተ-ልማት አውታር ባለቤትና ገንቢ ባለድርሻዎች ግቡን ለማሳካት እንዲችሉ መግባቢያ ስምምነት መፈራረም፣ በእቅድ አካተው ተቀናጅተው እንዲሰሩ አስገዳጅ የህግ ማእቀፎች፤ አደረጃጀትና አሰራር ስርዓት መዘርጋት ስራ ይሰራል፡

**ግብ 17. በልማት ምክንያት ለሚፈናቀሉ 78844 ባለይዞታዎች 55,179 ሚሊየን ብር ካሳ በመክፈል ዘላቂ ልማትን መደገፍ፡-**

በክልላችንም ሆነ እንደሀገር ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ እንዲስፋፋና እንዲያድግ ለማድረግ ዋናዉ እንደግብዓት ሆኖ የሚጠቀሰዉ መሬት ነዉ፡፡ ይህንን መሬት እንዳይባክን፤በቁጠባና ህብረተሰቡን በሚጠቅም መንገድ መምራት በሚያስቻልበት ሁኔታ ለማስተዳደር ጥረት ይደረጋል፡፡ ስለሆነም በቀጣይ አሰር ዓመታት ዉስጥ፡-

- የገጠር መሬት ይዞታ ለላቀ የሕዝብ ጥቅም ሲባል ለሚወሰድባቸዉ 78,844 የልማት ተነሽዎች 39.422 ሄ/ር መሬት በህግ በተቀመጠዉ አግባብ የንብረት ቆጠራና የመሬት ልኬታ ከተደረገና መተማመን ላይ ከተደረስ በኋላ ብር 55,179 ካሳ እንዲፈከላቸዉ ይደረጋል፡፡

**ግብ.18. ለ 7,242 የልማት ተነሽዎች ትክ ቦታ ማዘጋጀት እና መስጠት**

በልማት ምክንያት ከይዞታቸዉ ለሚነሱና በከተማ ዉስጥ ለሚገኙ የገጠር ቀበሌ ነዋሪዎች በትክነት ሊሰጥ የሚችል ቦታ የያዘ ስፍራ የሚመለከታቸዉን ከተማ ቀጣይ ዕድገት ታሰቢ በማድረግ በጥናት ላይ ተመስርቶ ይሰጣል፡፡በትክነት ስለሚመረጠዉ ስፍራ በቅድሚያ የጋራ ዉይይት እየተካሄደ እንዲሰፍሩ ይደረጋል፡፡ የይዞታቸዉ መሬት ለሚወሰደባቸዉለ 7513 ባለይዞታዎች የመሬቱ የቦታ አቀማመጥ፤ ስፋት እና የማምረት ደረጃ ተመጣጣኝ ከሆነ ትክ የእርሻ መሬት ይሰጣቸዋል፡፡ከዚህምበተጨማሪ በልማት ምክንያት ለተፈናቀሉ 7884 ባለይዞታዎች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲቀርብላቸው ድጋፍ ይደረጋል፤እንዲሁም 7884 የልማት ተነሽዎች የደረሰባችን ጉዳት ማሻሻል እንዲችል በመረጡት የስራ ዘርፍ እንዲሰማሩ ለማድግ የመስሪያ ቦታ ይጋጅላቸዋል፡፡

**ግብ-19.ተፈናቃዮች ባላቸው የካፒታል አቅም መሰረት በተለያዩ የስራ ዘርፎች እንዲሳተፉ ድጋፍ በማድረግ መልሰው እንዲቋቋሙማድረግ፤**

የጉዳት መጠናቸዉ 20% እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ለ15,769 የልማት ተነሽዎችን በሚሰጣቸዉ ካሳና በሚደረግላቸዉ የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ለሁሉም የልማት ተነሽዎች

ለሚያመርቱት ምርትና ለሚሰጡት አገልግሎት የገበያ ትስስር ይደረግላቸዋል፤ከእነዚህ የልማት ተነሽዎች መካከል 3,154 (20 %) የብድር ትስስር ይፈጠርላቸዋል፡፡

ለሁሉም የልማት ተነሽዎችና በልማት ምክንያት አካላዊ፤ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የደረሰባቸዉን በየጊዘዉ ሙያዊ ድጋፍ ማለትም የሚመርጡትን የስራ ዕድል በማስፋት፤ የቢዘዝነስ ፕላን በማዘጋጀት የተለያዩ ግብዓቶችን እንዲያገኙ በማድረግ በየዕለቱ ክትትልና ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

**ግብ-2000 ሄ/ር የኢንቨስትመንት መሬት በመለየት በባለሀብቶች አሁን የሚለማውን መሬት ከ ከ1280.5ሄ/ር ወደ 3280.5 ሄክታር ከፍ በማድረግ ምርታማነትን ማሳደግ፤**

በገጠር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት በሚደረገው ጥረትም በተለያየ የግብርና ዓይነቶች ውስን ባለሀብቶች በኢቨስትመንት የያዙትን ትንሽ መሬት በማልማት ላይ ይገኛሉ ፡፡ስለሆነም በግብርና የተሰማሩ ባለሀብቶች ከእርሻ ወደ አግሮ ፕሮሴሲንግ እንዲሸጋገሩ ማገዝ አስፈላጊ ሲሆን፤ባለሀብቶች ምርታማነትን በማሳደግ የክልሉን ልማት ይበልጥ ድርሻቸው እንዲሰፋ ለማድረግ፡-

- 2000 ሄ/ር የኢንቨስትመንት መሬት በጥናት ይለያል፤
- የተለየውን መሬት ለ20 ለባለሀብቶች በውድድር በማስተላለፍ አዲስ ውል እንዲይዙ ይደረጋል፣
- የውል ዘመናቸውን ለሚያጠናቀቁ 8 ባለሀብቶች ውል የማደስ ስራ ይሰራል፣
- በኢንቨስትመንት ለማልማት ውል የወሰዱትን የ 47 ባለሀብቶች መረጃ በሀርድና በሶፍት ኮፒ ተደራጂቶ ይያዛል፣
- በየዓመቱ የሁሉም የግብርና ኢንቨስትመንት ባለሀብቶች የልማት አፈፃፀም ግምገማ በማካሄድ ፕሮፋይል ይዘጋጃል፤
- በውላቸው መሰረት ያላለሙ ባለሃብቶችን በመመሪያው መሰረት በየደረጃው በማስወሰን ውል ማቋረጥና መሬቱን ወደ መሬት ባንክ ማስገባት ስራ ይሰራል፡

**ግብ 23.ግብርና ሆነ ከግብርና ነክ ውጭ የተሰማሩና የሚሰማሩ የ 21 ባለሃብቶችን የማሳ ካርታ ማዘጋጀት መስጠት፣**

- አዲስ ውል ለሚወስዱ ለ13 ባለሃብቶች የማሳ ካርታ ማዘጋጀትና መስጠት፣
- ውል ለሚታደስላቸውለ8 ባለሃብቶች የማሳ ካርታ ማዘጋጀትና መስጠት፣

## 10.6. ስራና ስልጠና

### 1.የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ምስረታ

**አላማ:- በተፈጠረ ሰፊ የሥራ ዕድል የክልሉን ህዝብ የነፍስ ወከፍ ገቢና የክልሉን ጠቅላላ ገቢ (GDP) በማሳደግ ልማታዊና ተወዳዳሪ ኢንተርፕራይዞችን በብዛት በማፍራት ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ የድርሻችንን መወጣት፣**

**ጥቅል ግብ፣**

በክልሉ ያለውን የገበያ ክፍተት መነሻ በማድረግ አዲስ እና ነባር ኢንተርፕራይዞችን (ጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን) በማቋቋምና በመደገፍ፣ በመንግስት ትልልቅ ፕሮጀክቶችና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች እና በመንግስት መ/ቤቶች፣የልማት ድርጅቶችና የውጭ አገር የስራ ትስስር ቅጥር በከተሞች ለ508,111 ሥራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ዘርፉ የሥራ አጥነቱን ምጣኔ በየአመቱ በ0.84 በመቀነስ 10 ዓመት መጨረሻ በ12.14 በመቶ ስራ አጥነትን በመቀነስ የስራ ዐጥት ምጣኔውን ከ19.7 ወደ 7.56 እንዲሁም በገጠር ለ948,311 ስራ ፈላጊ ዜጎች የስራ ዕድል በመፍጠር የስራ አጥነቱን ምጣኔ በ10 አመት መጨረሻ ወደ በ6.67 በመቶ ለማድረስ በጥቅሉ በከተማ 47,729 በገጠር 89,078 በድምሩ 136,807 ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋም በሂደቱ የዜጎችን የነፍስ ወከፍ ገቢ የማሻሻልና ፍትሀዊ ተጠቃሚነትን የማሳደግ ሥራ ይሰራል፡፡

ከሚፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥም 80%ቱን ዘላቂነት ያለውና ቋሚ እንዲሆን የማድረግ፣ የሴቶች ተጠቃሚነትና ተሳትፎን 50%፣ የወጣቶች ተጠቃሚነትና ተሳትፎ 80% የማድረስ እና በሥራ ፈላጊነት የሚመዘገቡትን አካል ጉዳተኞችንና ስደት ተመላሾችን 100% ተጠቃሚ ለማድረግ ይሰራል፡፡

**ዝርዝር ግቦች፡-**

ግብ1.በሁሉም ገጠርና ከተማ ያለውን የገበያ ክፈተት መነሻ በማድረግ በግብርና ዘርፍ(እንስሳትንና አሳ ሃብት ልማትን ሳይጨምር) በከተማ 12196 በገጠር 22761 በድምሩ 34,957 አዲስ ኢንተርፕራይዝ በማቋቋም ከተማ 60,974 ገጠር 113,797 በድምሩ ለ174,771 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በዚው ዘርፍ በከተማና ገጠር ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን በማጠናከር

በድምሩ ለ87,385 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፡፡

ዋና ዋና ተግባራት

- የስራ እድል መፍጠሪያ ፀጋዎችን መለየትና መጠቀም
- የሥራ ፈላጊዎችን መረጃ በትምህርት ደረጃ፣በእድሜና በፆታ ለይቶ መሰብሰብ፣ ማደራጀትና መተንተን
- የስራ እድል ለመፍጠር የሚያግዝ የፕሮጀክት ፕሮፋይል ማዘጋጀት
- ሥራ ፈላጊዎች ስለሥራ ዕድል ፈጠራ ግንዛቤ መፍጠር ሰነድ ማዘጋጀትና ሥልጠና መስጠት
- ሥራ ፈላጊዎች ቅድመ ብድር ቁጠባ እንዲቆጥቡ ማበረታታት፣
- በፍላጎት ላይ የተመሠረተ የአደረጃጀት ሥራ መሥራት፣
- አዋጭ የንግድ ስራ እቅድ (Business plan) እንዲዘጋጅ በማድረግ

ግብ2. በሁሉም ገጠርና ከተማ ያለውን የገበያ ክፈተት መነሻ በማድረግ በእንስሳትና አሣ ሃብት ልማት ዘርፍ በከተማ 5285 በገጠር 9864 በድምሩ 15,149 አዲስ ኢንተርፕራይዝ በማቋቋም ከተማ 26,420 ገጠር 49,313 በድምሩ ለ75,733 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በዚው ዘርፍ ጥቃቅን፣አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን በማጠናከር በድምሩ ለ37,867 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን

ግብ3. በሁሉም ገጠርና ከተማ ያለውን የገበያ ክፈተት መነሻ በማድረግ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በከተማ 5,588 በገጠር 10,431 በድምሩ 16,019 አዲስ ኢንተርፕራይዝ በማቋቋም ከተማ 22,357 ገጠር 41,725 በድምሩ ለ64,082 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በዚው ዘርፍ ጥቃቅን፣አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን በማጠናከር በከተማ 11,178 በገጠር 20,863 በድምሩ ለ32,041 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፡፡

ግብ4. በሁሉም ገጠርና ከተማ ያለውን የገበያ ክፈተት መነሻ በማድረግ በኮንስትራክሽን ዘርፍ በከተማ 6,504 በገጠር 12,137 በድምሩ 18,641 አዲስ ኢንተርፕራይዝ በማቋቋም ከተማ 32,521 ገጠር 60,692 በድምሩ ለ93,213 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በዚው ዘርፍ ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን በማጠናከር በከተማ 16,260 በገጠር 30,346 በድምሩ ለ46,606 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፡፡

ግብ5. በሁሉም ገጠርና ከተማ ያለውን የገበያ ክፈተት መነሻ በማድረግ በማዕድን ሃብት ልማት ዘርፍ በከተማ 3,250 በገጠር 6,070 በድምሩ 9,320 አዲስ ኢንተርፕራይዝ በማቋቋም ከተማ 16,260 ገጠር 30,346 በድምሩ ለ46,606 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በዚው ዘርፍ ጥቃቅን፣አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን በማጠናከር በከተማ 8,130 በገጠር 15,173 በድምሩ ለ23,303 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፡፡

ግብ6. በሁሉም ገጠርና ከተማ ያለውን የገበያ ክፈተት መነሻ በማድረግ በአገልግሎት ዘርፍ በከተማ 10,162 በገጠር 18,968 በድምሩ 29,130 አዲስ ኢንተርፕራይዝ በማቋቋም ከተማ 30,486 ገጠር 56,901 በድምሩ ለ87,387 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በዚው ዘርፍ ጥቃቅን፣አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን በማጠናከር በከተማ 15,243 በገጠር 28,449 በድምሩ ለ43,692 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር በማድረግ

ግብ7. በሁሉም ገጠርና ከተማ ያለውን የገበያ ክፈተት መነሻ በማድረግ በንግድ ዘርፍ በከተማ 4,744 በገጠር 8,851 በድምሩ 13,595 አዲስ ኢንተርፕራይዝ በማቋቋም ከተማ 14,227 ገጠር 26,553 በድምሩ ለ40,780 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በዚው ዘርፍ ጥቃቅን፣አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን በማጠናከር በከተማ 7,114 በገጠር 13,276 በድምሩ ለ20,390 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፡፡

ግብ8. በሁሉም ገጠርና ከተማ ባሉት ትልልቅ የመንግስት ፕሮጀክቶች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር የስራ ትስስር በመፍጠር በከተማ 162,598 በገጠር 303,459

በድምሩ ለ466,057 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፡

ግብ9. በሁሉም ገጠርና ከተማ ባሉት የመንግስት መ/ቤቶች፣የመንግስት የልማት ድረጅቶች እና ከውጭ አገራት ጋር የስራ ትስስር በቅጥር በመፍጠር በከተማ 40,648 በገጠር 75,864 በድምሩ ለ116,512 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል እንዲፈጠር በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፡፡

## 2.የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር

ዓላማ- ለክልላችንና ለአገራችን ኢንዱስትሪ ዕድገት መሠረት የሚጥሉ በአለም ገበያ ተወዳዳሪ ምርትና አገልግሎት የሚያቀርቡ፣ ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እድገትና ለቴክኖሎጅ አቅም ፈጠራ ትኩረት የሚሰጡ ልማታዊ አስተሳሰብ ያጎለበቱ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች እንዲስፋፉ የሚያስችል ጠንካራ ድጋፍ መስጠት፡፡

ጥቅል ግብ፡- ውጤታማ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ በመስጠት በገበያ ተወዳዳሪ ኢንተርፐራይዞችን በማፍራት ለኢንዱስትሪው መሰረት መጣል፡፡

ዝርዝር ግቦች፡-

ግብ-1. በእድገት ተኮር ዘርፎች ክፍተትንና የእድገት ደረጃን መሠረት ያደረገ ለ20,699 ነባርና አዲስ ኢንተርፐራይዞች (ለ63,559 አንቀሳቃሾች) የተሟላ የኢንዱትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት 10,334 አንቀሳቃሾችን አስመዝኖ በማብቃት ምርታማነትንና ጥራትን ማሻሻል፡፡

ዋና ዋና ተግባራት

- የጥ/አ/ኢንተርፐራይዞችን መረጃ በዘርፍ፣በስራ መስክ፣ በእድገት ደረጃና በትርጓሜ ለይቶ መያዝ፤የሚደግፉ አሰልጣኞችን መመደብና ወደ ስራ ማስገባት፣
- ሳይንሳዊ ዘዴን በመጠቀም የኢንተርፐራይዙን ክፍተት መለየት፣ ክፍተትን መሰረት ያደረገ የማሰልጠኛ ሰነድ ማዘጋጀትና ስልጠና በመስጠት በማስመዘን ማብቃት በዚህም፣
- በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለ7,782 (19,402 አንቀሳቃሾችን) ነባርና 1,130 (3,390 አንቀሳቃሾችን) አዲስ ኢንተርፐራይዞችን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት

- በኮንስትራክሽን ዘርፍ ለ3,374 (19,004 አንቀሳቃሾችን) ነባርና 640 (1,920 አንቀሳቃሾችን) አዲስ ኢንተርፕራይዞችን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት
- በግብርና ዘርፍ ለ2,713 (8,519 አንቀሳቃሾችን) ነባርና 490 (1,470 አንቀሳቃሾችን) አዲስ ኢንተርፕራይዞችን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት

**ግብ-2 ፍላጎትንና ክፍተትን መሠረት ያደረጉ 19 የእሴት ሰንሰለት ትንተና በመስራት 725 ፕሮቶታይፖችን በመኮረጅና በማሸጋገር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርታማነትና የምርት ጥራት ማሳደግ፡፡**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- 725 አዋጭ ቴክኖሎጅዎችን በአይነት መለየት፤
- በአይነት 725 ቴክኖሎጅዎችን ሙሉ ዶክሜንት እና ማንዋሎች ይዘጋጃሉ፤
- በአይነት 725 ፕሮቶታይፖችን ማዘጋጀት፤
- አንድ ቴክኖሎጅ በብዛት በ5 የማባዛትና በድምሩ 7,250 ቴክኖሎጅዎችን ለተጠቃሚዎች የማድረስ
- በቴክኖሎጅ ሽግግር ብር 60,196,874 ሃብት ማፍራት፣
- በቴክኖሎጂ መቅዳት (ፍብረካ) ላይ 9,920 ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ማብቃት፣
- 7,250 የጥቃቅንና አንስተኛ ኢንተርፕራይዞችን (22,326 አንቀሳቃሾችን) የቴክኖሎጅ ተጠቃሚ ማድረግ፣

**ግብ-3፡- ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ከሚሰጣቸው ኢንተርፕራይዞች መካከል በትኩረት ዘርፍ የተሰማሩ 1,220 ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን በመፍጠር፣ የ565 ኢንተርፕራይዞችን ተሞክሮ በመቀመርና ከተቀመሩት ውስጥ የ305 ኢንተርፕራይዞችን ተሞክሮ ለ10,208 ኢንተርፕራይዞች በማስፋት፣ 8,277 ኢንተርፕራይዞች ከደረጃ ደረጃ እንዲሸጋገሩ በማድረግ ተጠቃሚነታቸዉን ማሳደግ፡፡**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- ከጥቃቅን ጀማሪ ወደ ጥቃቅን ታደጊ 2,897 ይሸጋገራሉ፣
- ከጥቃቅን ታደጊ ወደ ጥቃቅን መብቃት 2,615 ይሸጋገራሉ፣
- ከጥቃቅን መብቃት ወደ አነስተኛ ጀማሪ 1,256 ይሸጋገራሉ፣

- ከአነስተኛ ጀማሪ ወደ አነስተኛ ታዳጊ 790 ይሸጋገራሉ፣
- ከአነስተኛ ታዳጊ ወደ አነስተኛ መብቃት 464 ይሸጋገራሉ፣
- ወደ ታደጊ መካከለኛ ደረጃ 255 ኢንተርፕራይዞች ይሸጋገራሉ፣

**ግብ-6፡- ኢንተርፕራይዞች ምርትና ምርታማነታቸውን የሚያሳድግና ጥራት ያለው ምርት ማምረት እንዲችሉ በማኑፋክቸሪንግ የተሰማሩ 740 ነባር ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ውጤታማነታቸውን ማሳደግ፡፡**

## 3. ውጤት ተኮር ትምህርና ሥልጠና

**ግብ-1 አመታዊ የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የመደበኛ የሰልጣኝ ቅበላ በ2012 በ1፡12፡ 10 ጥምርታ ከነበረበት 11,450 በ2022 ዓ.ም 112,730 በማሳደግ ጠቅላላ ቅበላዉን በዕቅድ ዘመኑ 112,730 ሰልጣኞችን በማፍራት የኢንዱስትሪዉን የሰለጠነ የሰዉ ሃይል ፍላጎት ማሟላት፡፡**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- በደረጃ 1 እና 2 35,174 (ነባር 20,276) ሰልጣኞችን ተቀብሎ ማሰልጠን፣
- በደረጃ 3 እና 4 73,916 (ነባር 56,036) ሰልጣኞችን ተቀብሎ ማሰልጠን፣
- በደረጃ-5 3,641 (ነባር 2,155) ሰልጣኞችን ተቀብሎ ማሰልጠን፣
- 100% ሰልጣኞች በደረጃ ደረጃ ሽግግር ምዘና እንዲያልፉ ማድረግ፣
- የሴት ሰልጣኞችን ተሳትፎ 55% ማስጠበቅ፣
- የአካል ጉዳተኛ ሰልጣኞችን ተሳትፎ በማሳደግ 100% ተጠቃሚ ማድረግ፣
- መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን ሰልጣኞችን በ2012 ዓ.ም ከተደረሰበት 88% ወደ 100% በማሳደግ በምዘና ብቁ ማድረግ፣
- የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን ድጋፍና ክትትል በማድረግ በ2012 ዓ.ም ከተደረሰበት 80.15% ወደ 100% በማሳደግ ስራ ማስያዝ፣
- ተከታታይ የሆነ የተቋም ውስጥ የሰልጣኞች ምዘና ማካሄድ፣
- በኮሌጅ የሚሰጡ ሁሉም የቴክኒክና ሙያ ስልጠናዎች ተግባር ተኮር ፕሮጀክት መሰረት ያደረገ ስልጠና መስጠት፣
- የማሰልጠኛ ወርክ ሾፖች በካይዘንን በተገቢው ሁኔታ የተደራጁ እንዲሆኑ ማድረግ፣

- የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች፣ ሌሎች ኮሌጆችን የሚደግፉበት ስርአትን መተግበር፣

ግብ-3 ገበያ ባላቸው ሙያዎች መደበኛ ባልሆነ አጫጭር ሥልጠና በዕቅድ ዘመኑ ከነበረበት 104,374 ወደ 1,455,927 ቁጥሩን በማድረስ ስራ የሚፈጠርላቸውን ዜጎች የሥራ ፈጠራ አመለካከታቸውንና ክህሎታቸውን ማሳደግ ።

ግብ-4 የኢንዱስትሪ ውስጥ አሰልጣኝ በ2012 ከነበረበት 672 በ2022 ዓ.ም 11,394 ማድረስና የአሰልጣኝ ሰልጣኝ ጥምርታን በማስጠበቅ የስልጠና ጥራትንና ተደራሽነት ማሳደግ፡፡

ዋና ዋና ተግባራት

- የA ደረጃ አሰልጣኞች የ B ደረጃ አሰልጣኞችና የC ደርጃ አሰልጣኞችን በክህሎት፣ በእውቀትና በአመለካከት እንዲያበቁ ማድረግ፣
- የሲ ደረጃ አሰልጣኞችን 6,602 ማድረስ፣
- የB ደረጃ አሰልጣኞችን 4,101 ማድረስ፣
- የA ደረጃ አሰልጣኞችን 691 ማድረስ፣

ግብ-7 ኢንዱስትሪውንና የባለድርሻ አካላትን በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ትግበራ ያላቸዉን ተሳትፎ ማሳደግ፡፡

ዋና ዋና ተግባራት

- 20,788 የትብብር ስልጠና የሚሰጡ ኢንተርፕራይዞችንና ኢንዱስትሪዎችን ማፍራት፣
- የትብብር ስልጠና ሽፋን 100% የሚያስጠብቁ ስራዎችን ማጠናከር፣
- የኩባንያ ውስጥ ስልጠና የሚሰጡ ኢንደስትሪዎችን 2720 ማድረስ፣
- ከመሪ የትኩረት ዘርፍ መስሪያቤቶች ጋር በጋራ እቅድ መስራት፣

## 4. የማሰልጠኛ ተቋማት ብቃት ማረጋገጫ

አላማ- ለክልላችንና ለአገራችን ልማት መፋጠን ተገቢውን ድርሻ የሚጫወት በቴክኒክ እውቀት፣ክህሎትና አመለካከት ብቁ የሆነ የሰው ኃይል በብዛት ማፍራትና ወደ ስራ የሚሰማሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

ጥቅል ግብ፡- የግል ኮሌጆችን ተሳትፎ ከፍ በማድረግ በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነና ብቃቱ የተረጋገጠ የሰው ሃይል ለኢንዱስትሪው ማቅረብ፡፡

ዝርዝር ግቦች፡-

ግብ-1 የግል እና መንግታዊ ያልሆኑ ኮሌጆች የመደበኛ ሰልጣኝ ቅበላ በ2012 ከነበረበት 1,232 በ2022 ዓ/ም በ2,298 በማሳደግ ጠቅላላ ቅበላዉን በዕቅድ ዘመኑ 2,298 ሰልጣኞችን በማፍራት የኢንዱስትሪዉን የሰለጠነ የሰዉ ሃይል ፈላጎት ማሳደግ፡፡

ዋና ዋና ተግባራት

- በደረጃ 1 እና 2 አዲስ 2,436 ሰልጣኞችን ተቀብሎ ማሰልጠን፣
- በደረጃ 3 እና 4 አዲስ 1,066፣ ነባር 1,232 በጠቅላላ 2,298 ሰልጣኞችን ተቀብሎ ማሰልጠን፣
- 100% ስልጠና አጠናቃቂዎች በምዘና እንዲበቁ ማድረግ፣
- 100% ሰልጣኞች በደረጃ ደረጃ ሽግግር ምዘና እንዲያልፉ ማድረግ
- የሴት ሰልጣኞችን ተሳትፎ 65% ማስጠበቅ፣
- የአካል ጉዳተኛ ሰልጣኞችን ተሳትፎ በማሳደግ 100% ማድረስ፣
- መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ምሩቃንን ሰልጣኞችን በ2012 ዓ.ም ከተደረሰበት 23.6% ወደ 100% በማሳደግ በምዘና ብቁ ማድረግ፣
- የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን ድጋፍና ክትትል በማድረግ በ2012 ዓ.ም ከተደረሰበት 39% ወደ 84% በማሳደግ ስራ ማስያዝ፣

ግብ-2 ገበያ ባላቸው ሙያዎች መደበኛ ባልሆነ አጫጭር ሥልጠና የሚሰጡ ተቋማትን እንዲጠናከሩ ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ በዕቅድ ዘመኑ ከነበረበት 1,518 ወደ 2,275 ቁጥሩን በማድረስ የኢንዱስትሪውን የሰለጠነ የሰው ሀይል እጥረት መቀነስ ፡፡

ግብ-3 በግልና እና መንግስታዊ ባልሆኑ ኮሌጆች የአሰልጣኝ ልማት ስራችንን በመጠንና በጥራት በማሳደግና በማሻሻል የግል ቴ/ሙ/ኮሌጅ አሰልጣኞችን በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 36 በ2022 ዓ/ም ወደ 50 በማድረስና የአሰልጣኝ ሰልጣኝ ጥምርታን በማስጠበቅ የስልጠና ጥራትንና ተደራሽነት ማሳደግ፡፡

ግብ-4 ኢንዱስትሪውንና የባለድርሻ አካላትን በግል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ትግበራ ያላቸዉን ተሳትፎ ማሳደግ፡፡

ዋና ዋና ተግባራት

- የትብብር ስልጠና ሽፋንን በ2012 ከነበረበት 84% 2022 100% ማሳደግ፣
- የትብብር ሰልጠና መስጫ ድርጅቶችን መለየት እና ለስልጠና እንዲውሉ ውል መያዝ፣

ግብ -5፡- መደበኛ ስልጠና እና አጫጭር ስልጠና የሚሰጡ የመንግስት የግል እና መንግስታዊ ያልሆኑ ቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆች መንግስት ያወጣቸውን አዋጆች ደንቦች እና መመሪያዎች መሰረት ተከትለው ስልጠና እንዲሰጡ በማድረግ የስልጠና ጥራትን ማረጋገጥ፡፡

## የገበያ ልማት ግብይት

ዓላማ፡- በቀጣይ 10 አመታት በፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት፣ በገበያ፣ ብድርና ኦዲት ፈላጊዎችና በህብረተሰቡ ዘንድ የሚታዩ የአመለካከት፣ የክህሎትና የግብዓት፣ የአሠራር፣ የክትትልና ድጋፍ ክፍተቶችን በመለየትና በመፍታት የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

ጥቅል ግብ፡- የኢንተርፕራይዞችን የገበያ ክፍተት በመለየት እርስ በርሳቸው፣ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችና ከውጭ አገር ከሚገኙ የገበያ ዕድሎች በማስተሳሰር ተጠቃሚ ማድረግ፡፡

ዝርዝር ግቦች፡-

ግብ1. በቀጣይ 10 ዓመታት የጥቃቅንና ከማኑፋክቸሪንግ ዉጭ የሆኑ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችና ተቋማት እንዲሁም ኢንተርፕራይዞችን በጎንዮሽ እርስ በእርስ በምርት እና በግብዓት በአውት-ሶርሲንግ እና በሰብ-ኮንትራት የግብይት ስርዓቶች 36,000 ኢንተርፕራይዞችንና 108,000 አንቀሳቃሽን የብር 2,700,000,000 የገበያ ትስስር በመፍጠር የኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚነት ማሳደግ፡፡

ዋና ዋና ተግባራት

- የጥቃቅንና ከማኑፋክቸሪንግ ዉጭ የሆኑ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች፣ ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች፣ ከመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኢንተርፕራይዞችን በምርትና ግብዓት እርስ በርስ ትስስር እንዲሁም በግልና በተቋማት በሚፈጠር የገበያ ትስስር ለ34,000 ኢንተርፕራይዞችን (104,400 አንቀሳቃሽን) የብር 2,610,000,000 የገበያ ትስስር ይፈጠራል፡፡
- 120 የንግድ ትርዒትና ኤግዚቪሽኖችን በማዘጋጀት በኢምፖርየም በማስገባትና በሰንበት ገበያዎች 3,600 ኢንተርፕራይዞችን (10,800 ተጠቃሚዎችን) በማሳተፍ 1,850,000

ሰዎችን በማስነብኘት በሚፈጠረው የገበያ ትስስር ብር 18,000,000 በማስገኘት ተጠቃሚ ማድረግ፡፡

- የአካባቢ የገበያ አማራጮችን በመረጃ ላይ ተመስርቶ በመለየት ያለውን የገበያ እድል አሟጦ በመጠቀም ኢንተርፕራይዞቻችንን በሀገር ውስጥ ገበያ ተጠቃሚ ለማድረግ በስፋት መስራት
- በጨርቃጨርቅና አልባሳት፣ የቆዳና እደ ጥበብ ውጤቶች የተለያዩ ምርት ናሙናዎችን በመሰባሰብና ለገዥ ድርጅቶች በማሳየት የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ ማድረግ
- የእድገት ተኮር ዘርፎች በጥናት ላይ ተመስርቶ በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ከተቋማትና እርስ በርስ በግብይት ስርአቶች መሰረት የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ምቹ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚነት ማሳደግ፤
- በጨርቃጨርቅና ልብስ ስፌት፣ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢ/ዞችን ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በተለዩ የምርት አይነቶች ማስተሳሰር፤

**ግብ2. የውጭ አገር የገበያ ትስስር በመፍጠር በቀጣይ 10 ዓመት 35 ኢንተርፕራዞች ወደ ዉጭ ገበያ በማስገባት 5,000,000 USD በማግኘት በምርት ጥራትና መጠን ተወዳዳሪነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፡፡**

**ግብ 3. በሶስቱ የትኩረት ዘርፎች ለተሰማሩ 30,000 ኢንተርፕራይዞች የቅድመ ኦዲት እና ለ22,200 ኢንተርፕራይዞች የኦዲት አገልግሎት በመስጠት የእንተርፕራይዞችን ትርፋማነትና ተጠቃሚነት ማሳደግ፡፡**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- ለ30,000 ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ አያያዝ መስመር እንዲዘረጉ ድጋፍ ያደርጋል፣
- ለ22,200 ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ አያያዝ መስመር እንዲዘረጉ ድጋፍ ያደርጋል፣
- ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ አያያዝ መስመር እንዲዘረጉ ድጋፍ ይደረጋል
- የሂሳብ መስመር የዘረጉትን ኢ/ዞች የተተነተነ መረጃን መሰረት በማድረግ የአሰራር ስርአት ይቀየሳል
- የኢ/ዞች አሰራርና የሂሳብ አያያዙ ሁኔታ ወደፊት የተሻሉ እንዲሆኑ ይደገፋሉ
- የጥቃቅን ኢ/ዞችን ናሙና በመውሰድ የኦዲት አገልግሎት እንዲያገኙ ድጋፍ ይደረጋል

**ግብ 4. ከአበዳሪ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ለ42,000 አዳዲስ እና ነባር ኢንተርፕራይዞች የብር 2,940,000,000 የብድር አገልግሎት በማቅረብ በዘመኑ መመለስ ያለበት ብድር 100%**

እንዲመለስ እና የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል እና ግንዛቤ በማሳደግ የብድሩ 80 በመቶ ከህብረተሰቡና ከትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በሚሰበሰብ ቁጠባ እንዲሸፈን ይደረጋል፡፡

**ዋና ዋና ተግባራት**

- ለስራ ዕድል ፈጠራና ስራን ለማስፋፋት የሚያግዝ ለብደር አገልግሎት የሚዉል ብር 2,352,000,000 ከቁጠባ እንዲሰባሰብ ይደረጋል፣
- ለ42,000 አዳዲስ እና ነባር ኢንተርፕራይዞች የብር 2,940,000,000 የብድር አገልግሎት ይቀርባል፣
- የብድርና ቁጠባ አገልግሎት አሰጣጥ አጠቃቀምና አመላለስ ስራዎችን በተመለከተ የማስፈጸሚያ እቅዱን በማዘጋጀት ለአፈጻጸሙ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፤
- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢ/ዞች የብድር አሰጣጥና አመላለስ ስርአት ቀልጣፋ ለማድረግ የሚረዱ ሞዴል የአሰራር ማኑዋሎችን በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ይደረጋል፤
- ለዘርፉ ባለሙያዎች የስልጠና ሰነድ ይዘጋጃል፣ ስልጠናም ይሰጣል፤
- የቁጠባና የብድር አጠቃቀም ባህልን ለማሳደግ የሚያስችል የህዝብ ግንኙነት ስርአት ተግባራዊ እንዲሆን ይሰራል፤

## 6.የግንባታና ግብዓት አቅርቦት

**ዓላማ፡-** በዘርፉ በዝቅተኛና መካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ ባለሙያዎችን የሚያፈሩ እና አንቀሳቃሾችን አዳዲስ አዋጭ ቴክኖሎጂዎችን በማስታጠቅ በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያደርጉ የማሰልጠኛ ኮሌጆችን በመገንባት በክልላችንና በሃገራችን ስራ አጥነትንና ድህነትን መቀነስ ነው፡፡

**ጥቅል ግቦች፡-** በክልሉ ውስጥ የቴ/ሙ/ኮሌጆችን ተደራሽነት ማስፋት፣ለኮሌጆችና ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ግብዓት ማቅረብ፡፡

**ዝርዝር ግቦች፡-**

**ግብ-1፡-** የማሰልጠኛ ኮሌጆችን አሁን ካለበት 13 ወደ 24 ማሳደግ፣ የፖሊቴክኒክ ኮሌጆችን ከ3 ወደ 6 በማሳደግ ጥራትንና ተደራሽነትን ማረጋገጥ

**ዋና ዋና ተግባራት**

- ኮሌጅ በሌለባቸው ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች 11 አዲስ የቴ/ሙ/ኮሌጆችን መገንባት፣ 10,800 ሰልጣኞች እንዲሰለጥኑ ማድረግ፣
- የኮሌጆች ይዞታ የሚሆን 146 ሄክታር መሬት እንዲዘጋጅ ማድረግ፣
- ለአዳዲስ ኮሌጆች መገንቢያ ከመንግስት (50%) የሚያስፈልግ ብር 182,000,000 ገንዘብ ማስመደብ፣
- ለአዳዲስ ኮሌጆች መገንቢያ ከህዝብና ከየአካባቢው ወረዳ (50%) የሚያስፈልግ ብር 182,000,000 ገንዘብ ማስመደብ፣
- በነባር የቴ/ሙያ ኮሌጆች ቀሪ ወርክሾፖችን 10 መገንባት ከመንግስት በብር 154,000,000 ከህዝብ 154,500,000 እንዲመደብ በማመቻቸት ሰልጣኞች እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
- በዞኑ የሚገኙ ሁሉም የቴክኒክና ሙያ ስልጠና መስጫዎች ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆችና ኮሌጆች ለደረጃቸው የሚመጥን የስልጠና ግብአት እንዲሟላላቸው ይደረጋል፣
- ቀደም ብለው ለተገነቡትና አዲስ ለሚገነቡት የቴ/ሙ/ኮሌጆች መሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው /መንገድ፣ውሀ፣መብራት/ ማድረግ፣

ግብ-2፡- 33 ነባር የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን በስታንዳርዱ መሠረት በ144 የሰው ሀይልና በማቴሪያል በማጠናከር እና በየ2.5 ኪ.ሜ ለ15,000 ህዝብና ለ500 ኢንተር ፕራይዞች አገልግሎት መስጠት የሚችሉ 49 አዳዲስ የአንድ አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ተከፍተውና 343 ባለሙያዎች ተቀጥረውላቸው ቀልጣፋና የተሟላ አገልግሎት ለህብረተሰቡ እንዲሰጡ በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጡንና ተደራሽነቱን ማሳደግ፡፡

**ግብ-3፡- በገጠርና በከተማ አሁን ያሉትን 2601 ሼዶች ቁጥር ወደ 6,680 በማሳደግና መሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው አድርጎ ለኢንተርፕራይዞች በማስተላለፍ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፡፡**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- በከተማ 1500 ሼዶች በገጠር 5,180 በድምሩ 6,680 ሼዶች በመገንባት በከተማ 7,500 ኢንተርፕራይዞች (37,500 አንቀሳቃሾች)፣ በገጠር 25,900 ኢንተርፕራይዞች

(129,500 አንቀሳቃሾች)፣ በጠቅላላው በገጠርና በከተማ 45,800 ኢንተርፕራይዞች (183,222 አንቀሳቃሾች) ተጠቃሚ ማድረግ፣

- ለሼዶች መገንቢያ የሚሆን በከተማ ብር 274,500,000 በገጠር ብር 947,940,000 በድምሩ ብር 1,222,440,000 ከወረዳ/ከተማ አስተዳደሮችና ከህዝቡ (50%) እንዲሰባሰብ ይደረጋል፣
- በ10 ዓመት ውስጥ 10 ጥገና የሚያስፈልጋቸው ሼዶች ይጠገናሉ፣

**ግብ-4፡- ለኢንተርፕራይዞች የማምረቻና መሸጫ ቦታ 1,830 ሄክታር የለማ መሬት ለሼድ መገንቢያ፣ለከተማና ገጠር ግብርና፣ ለአሸዋ፣ ለድንጋናይ ለጠጠር ማምረቻ አዘጋጅቶ በማስተላለፍ ተጠቃሚነታቸውን ከፍ ማድረግ፡፡**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- በከተማ 200 ሄክታር ለ10,000 ኢንተርፕራይዞች (40,000 አንቀሳቃሾች)፣ በገጠር 1,630 ሄክታር ለ35,800 ኢንተርፕራይዞች (143,230 አንቀሳቃሾች) በማመቻቸት ተጠቃሚ ማድረግ፣

## 10.7. ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት

**ዓላማ.1. በየደረጃው የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን በመገንባት የኢንቨስትመንቱን እድገት ማረጋገጥና ቅንጅታዊ አሰራሮችን በማጠናከር የተቋሙን ተልዕኮ ማሳካት፣**

**ግብ.1. የአጋር አካላትን ቅንጅታዊ አሰራር ውጤታማነትን ማሳደግ፣**

**ዝርዝር ተግባር**

- አምራች ኢንዱስትሪዎችን ከምርምርና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር ትስስር በመፍጠር የኢንዱስትሪዎችን ውጤታማነት የማጠናከር ስራ መስራት፣
- የመሰረተ-ልማት አቅራቢ ተቋማት ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችና ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የመሰረተ ልማት ፍላጎትን እንዲያሟሉ መስራት፣
- ለአምራች ኢንዱስትሪው ግብአት የሚያመርቱና የሚያቀርቡ ተቋማት ጥራት ያለው ግብአት በብዛት ማቅረብ እንዲችሉ መስራት፣

- የፋይናንስ ተቋማት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችንና የአምራች ኢንዱስትሪዎችን አቅም መሰረት ያደረገ የብድር አገልግሎት ግልጽና ቀልጣፋ በሆነ መልክ እንዲያቀርቡ መስራት፣
- መሬትን የሚያስተዳድሩ ተቋማት ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችና ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የመስሪያ ቦታ ከ3ኛ ወገን ነጻ በማድረግ እንዲያቀርቡ መስራት፣
- የፍትህና የጸጥታ አካላት ጋር በዞናችን አንጻራዊ ሰላም እንዲሰፍንና ህገወጥ አሰራሮች እንዲታረሙ ተባብሮ መስራት

ግብ.2. የተገልጋዮችን እርካታ አሁን ካለበት 69.53% በ2022 ዓ.ም ወደ 95% ማሳደግ፣

ዝርዝር ተግባር

- ተቋሙን 100% በካይዘን ፍልስፍና የተቃኘ በማድረግ ጽዱ፣ማራኪና ቀልጣፍ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ ፣
- ተቋሙ 100% ከሙስና የፀዳ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣
- ምቹና ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት የሚያግዙ ማኗሎችን እንዳስፈላጊነቱ 100% ማዘጋጀት፣

ግብ.3. የሃብት አጠቃቀምንና ውጤታማነትን በ2022 ዓ.ም 100% ማድረስ፣

ዝርዝር ተግባር

- 20 ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ተጨማሪ ሃብት በገንዘብም ሆነ በአይነት እንዲገኝ ማድረግ፣
- የተመደበን የመንግስት መደበኛ በጀት በተቀመጠው እቅድ መሠረት 100% ተፈፃሚ ማድረግ፣
- በሚገኘው ገቢ እና በተመደበው የመንግስት በጀት ተቋሙን 100% በሎጅስቲክስ እንዲሟላ ማድረግ፣

**ዓላማ 2፡ ዞኑን ተወዳዳሪ እና የተሻለ የኢንቨስትመንት መዳረሻ በማድረግ፣ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በማስፋፋትና በሙሉ አቅማቸው ምርት እንዲያመርቱ/ አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ ዘርፉ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረውን ድርሻ በማሳደግ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ፣**

**ግብ.1. የዞኑን ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት የሚያግዙ ፀጋዎችን በጥናት የመለየቱን ስራ በ2022 ዓ.ም 100 % ማድረስ፡፡**

**ዝርዝር ተግባር**

- የዞኑን እምቅ ሃብት በዩኒቨርስቲ 2 ጊዜ በማስጠናት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የስራ መስኮች መለየት እና መረጃዎችን ወቅታዊ ማድረግ
- የዞኑን የትኩረት መስኮች መሰረት በማድረግ በጥናት ሶስት የልማት ቀጠናዎችን መለየት
- በዞኑ በጥናት የተለዩትን የልማት ቀጠናዎች ለኢንቨስትመንት ዝግጁ ማድረግ፣
- የዞኑን የኢንቨስትመንት አማራጮች ተወዳዳሪነትና ተመራጭነትን የሚያሳይ ሁለት ሰነድ ማዘጋጀት፣

**ግብ.2. ውጤታማ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽንን በመተግበር የኢኮኖሚ እድገት ሊያመጡ በሚችሉ ዘርፎች ላይ የሚሰማሩ ባለሃብቶችን ቁጥር አሁን ካለበት 1066 በ2022 ወደ 4313 ማሳደግ፣**

**ዝርዝር ተግባር**

- በዞኑ ቀዳሚ በሆኑ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ እንዲሰማሩ በማስተዋወቅ 3896 ባለሀባቶችን መለየት፣
- ለተለዩት ቀዳሚ ዘርፎች የሚስማሙ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን በመጠቀም ለ3896 ባለሃብቶች የማሰተዋወቅ ስራ መስራት፣
- የኢንቨስትመንት ዘርፎችን መሰረት በማድረግ የማስተዋወቅ ስራ ከተሰራላቸው ባለሃብቶ ውስጥ 80% መመልመል ፣
- የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማውጣት የሚመጡ ባለሀባቶችን 100% ፈቃድ መስጠት፣
- የእሴት ሰንሰለት ክፍተት የተለየላቸውን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ክፍተቱን ሊሞሉ የሚችሉ ባለሃብቶችን በየዘርፉ የማስተዋወቅ ስራ በመስራት መሳብ፣

**ግብ.3. ከአምራች ኢንዱስትሪው ውጭ ያሉ ፈቃድ ያወጡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በመደገፍና በመከታተል ወደ ምርት ማምረት/አገልግሎት መስጠት የሚገቡትን አሁን ካለበት 49.5% በ2022 ዓ.ም ወደ 70% ማድረስ ፣**

**ዝርዝር ተግባር**

- የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ዝርዝር መረጃ /ፕሮፋይል/ 100% ማዘጋጀት፣
- የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መሬትና ሌሎች መሰረተ ልማቶች 100% እንዲሟላላቸው ድጋፍና ክትትል ማድረግ ፤
- መሬት ወስደው እና ተከታታይ ድጋፍ ተገርጎላቸው ወደ ስራ ያልገቡ ፕሮጀክቶችን መሬት 100% እንዲመለስ ማድረግ፣
- የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የፋይናንስ አገልግሎት 100% ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የማበረታቻ አገልግሎት 100% ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- ከጉምሩክ ቀረጽ ነጻ የተፈቀዱ ማበረታቻዎች 100% ለታለመለት ዓላማ መዋላቸውን ማረጋገጥ፤
- ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ውጭ ያሉ ድጋፍና ክትትል የተደረገላቸው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን 100% ወደ አፈጻጸም እንዲገቡ ማድረግ፣
- ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ውጭ ያሉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ለ20193 ዜጎች የስራ እድል እንዲፈጥሩ ማድረግ፣

**ግብ.4. የዞኑን ኢንቨስትመንት ለማስፋፋትና ለማበረታታት የመልካም ገፅታ ግንባታ ተግባር በ2022 ዓ.ም ወደ 100% ማሳደግ፡**

**ዝርዝር ተግባር**

- ለመልካም ገጽታ ግንባታ የሚረዱ 100% በሚዲያ ማስተዋወቅ
- ለመልካም ገጽታ ግንባታ የሚረዱ 10 አውዶችን ማዘጋጀት
- ወቅታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለሚመለከታቸው አካላት 100% የግንዛቤ መስጫ መድረኮችን ማዘጋጀት፣
- የዞኑን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለሚመለከታቸው አካላት ለ10 ጊዜ ያህል በመስክ የማስጎብኘት ስራ መስራት፣

**ዓላማ 3፡ ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውል የመሬት እና ሌሎች መሰረተ-ልማት አቅርቦትን በማሟላት የተሻለ የእሴት ጭማሪ ያላቸውን የኢንዱስትሪ ምርቶች በብዛት፣ በጥራትና በዓይነት በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት የሚችሉ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በማደራጀት እንዲስፋፉ እና ውጤታማ እንዲሆኑ ማስቻል ፤**

ግብ.1. ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውል 100% መሰረተ ልማት የተሟላለት የመሬት አቅርቦትን አሁን ካለበት 403.54 ሄክታር መሬት በ2022 ዓ.ም በ1473.886 ሄ/ር መሬት ማሳደግ፣

**ዝርዝር ተግባራት**

- ለክላስተር ማዕከል እና ለሁለገብ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚውል በሳይት ፕላንና በካርታ የተመላከተ መሬት 100% ማዘጋጀት
- ለተቀናጀ የክልል ሁለገብ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚውል በሳይት ፕላን እና በካርታ የተመላከተ መሬት 100% ማዘጋጀት፣
- ለኢንዱስትሪ ሽድና ለሌሎች የኢንዱስትሪ ቀጠናዎች የሚውል በሳይት ፕላን እና ካርታ የተመላከተ መሬት 100% ማዘጋጀት፣
- ለሁሉም የኢንዱስትሪ ቀጠናዎች ለተዘጋጀው መሬት 100% ካሳ ተክፍሎ ከሶስተኛ ወገን የፀዳ እንዲሆን ማድረግ፣
- ለኢንዱስትሪ አገልግሎት እንዲውል ለተዘጋጀ መሬት 100% የመሰረተ ልማት/መንገድ፣ ውሃ፣ቴሌ፣መብራት፣የውሃ ማፋሰሻዎች፣ድልድይ/ እንዲሟላ ማድረግ፣

ግብ.2. የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን በመገምገም፣በመከታተልና በመደገፍ በ2022 ዓ.ም የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ቁጥር አሁን ካለበት 514 በ2022 ዓ.ም ወደ 8275 ማድረስ፡፡

**ዝርዝር ተግባር**

- ተገምግመው ያለፉ ፕሮጀክቶችን መሰረተ-ልማት የተሟላለት የመስሪያ ቦታ/መሬት 100% እንዲያገኙ ማድረግ፣
- መሬት የተሰጣቸው ሁሉም ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ መሰረት የግንባታ አፈጻጸማቸውንና ሌሎች ተግባራትን በመከታተልና በመደገፍ ወደ ማምረት እንዲገቡ ማድረግ፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን በመደገፍ የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- መሬት ወስደው እና ተከታታይ ድጋፍ ተገርጎላቸው ወደ ስራ ያልገቡ ፕሮጀክቶችን ግምት በመስራት መሬቱን 100% ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ማድረግ፣

ግብ.3. ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የተሟላ ድጋፍ በማድረግ በ2022 ዓ.ም 100% ዘላቂነታቸውን ማረጋገጥ፣

**ዝርዝር ተግባር**

- የግብአት እና የምርት ገበያ ችግር ያለባቸውን አምራች ኢንዱስትሪዎች ትስስር በመፍጠር 100% ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- የፋይናንስ ችግር ያለባቸውን አምራች ኢንዱስትሪዎች 100% ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- አምራች ኢንዱስትሪዎች የመሰረተ-ልማት ችግር 100% መፍታት፣
- የሁሉንም የአምራች ኢንዳስትሪዎች የማምረት አቅም ሳይንሳዊ በሆነ አሰራር በመለካት አሁን ካለበት 74% በ2022 ዓ.ም ወደ 85% እንዲደርስ ማድረግ፣
- አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርታቸውን በብዛት አምርተው ወደ ውጩ በመላክ አሁን ከሚያስገኙት 177,916,833.00 ዶላር በ2022 ዓ.ም 283,553,611 ዶላር ገቢ እንዲያስገኙ ማድረግ፣

**ዓላማ 4፡ የማዕድን ዘርፉ ኢንቨስትመንት ማስፋፋት ፤**

**ግብ.1. የአገር ዉስጥ የማዕድን ስራዎች ኢንቨስትመንትን አሁን ካለበት 6 የከፍተኛ ደረጃ ኮንስትራክሽን ማዕድን ማውጣት በ2022 20 የከፍተኛ ደረጃ ኮንስትራክሽን ማዕድን ማውጣት ማድረስ**

**ዝርዝር ተግባር፡**

- በዞኑ ውስጥ ያሉ የኮንስትራክሽን ግብዓት የሚሆኑ የቁፋሮ ቦታዎችን 100% መለየት
- የተለዩ የኮንስትራክሽን ግብዓት የሚሆኑ የቁፋሮ ቦታዎችን ለ480 ባለሀብቶች የማስተዋወቅ ስራ መስራት
- የኮንስትራክሽን ግብዓት የሚሆኑ የቁፋሮ ቦታዎች ላይ የሚሰማሩ ባለሀብቶችን መለየትና ምቹ ሀኔታ መፍጠር

**ግብ.2 የአነስተኛና የባህላዊ ደረጃ የግንባታ ማዕድናት ማምረት ስራ ባለፈቃድ ኢንተርፕራይዞችን አሁን ካሉበት 797 በ2022 ወደ 5497 ማድረስ**

**ዝርዝር ተግባር፡**

- በዞኑ ውስጥ ያለንን ጸጋ በመለት መረጃ መያዝ
- የተደራጁ ኢንተርፕራይዞችን መረጃ ከሙያና ቴክኒክ መቀበል

- ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች በባህላዊ ደረጃ ፈቃድ መስጠት
- ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች በአነስተኛ ደረጃ የኮንስትራክሽን ፈቃድ መስጠት

ግብ.3. በባህላዊ ዘዴ ኦፓል የሚያመርቱ 32 ኢንተርፕራይዞችን በ2022 100% ወደ ልዩ አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስራ ማሸጋገር

ዝርዝር ተግባር፡

- ለ32ቱም የባህላዊ ኦፓል አምራች ኢንተርፕራይዞች ወደ ልዩ አነስተኛ ለመሸጋገር የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ላይ ግንዛቤ መፍጠር
- ተከታታይ ድጋፍና ክትትል ስራ መስራት
- 32ቱንም ኢንተርፕራይዞች ወደ ልዩ አነስተኛ ማሸጋገር

ዓላማ 5፡ የማዕድን ሥራዎችና ግብይት ህግ ተገዥነትን ማሻሻል፤

ግብ 1. የማዕድን ስራዎች ክትትልና ቁጥጥር ድጋፍ ሰጭ ግብረ ሃይሎችን በ2022 100% ማቋቋና ወደ ስራ ማስገባት

ተግባር፡

- የማዕድን ስራዎች ክትትልና ቁጥጥር ድጋፍ ሰጭ ግብረ ሃይሎችን ማቋቋሚያ ሰነድ ላይ ግነዛቤ መፍጠር፣
- የማዕድን ስራዎች ክትትልና ቁጥጥር ድጋፍ ሰጭ ግብረ ሃይሎች የጋራ ዕቅድ ማዘጋጀት፣
- የዕቅዱን አፈጻጸም መከታተልና ግብረ መልስ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ግብረ መልስ መስጠት

ዓላማ 6፡- ከዘርፋ የሚገኘውን የሀገር ውስጥ ገቢ ማሳደግ፣

ግብ$_1$፡- ከሮያሊቲ፣ ከመሬት ኪራይ፣ ከፈቃድና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚሰበሰበውን ብር ከ27,141,917 ወደ 47,700,000 ማሳደግ፣

ዝርዝር ተግባር

- ከማዕድን ፈቃድ መስጠት የሚሰበሰብ ገቢን 100% መሰብሰብ፣
- ከቁርጥ ዋጋ መሰብሰብ ያለበትን ገቢ 100% መሰብሰብ፣

- ህገወጥ የማዕድን ምርትና ዝውውርን 100% ማስቆም፣
- ከባለፈቃዶች መሰብሰብ ያለበትን ሮያሊቲ 100% በወቅቱ መሰብሰብ፣

**ዓላማ 7፡- ለውጭ ገበያ የሚቀርቡን ጥሬና እሴት የተጨመረባቸው የከበሩ ማዕድናት ምርትና ሽያጭ ማሳደግ፣**

**ግብ$_1$፡- ለውጭ ገበያ የሚቀርብን ጥሬና እሴት የተጨመረባቸው የከበሩ ማዕድናትን ምርት ከነበረበት 34,645.5 ኪ.ግራም ወደ 45,000 በማሳደግ ቀድሞ ከነበረው ሽያጭ ብር 26,443,109.5 ወደ 54,000,000 ማሳደግ፣**

**ዝርዝር ተግባር**

- ለውጭ ገበያ የሚቀርብን ጥሬና እሴት የተጨመረባቸው የከበሩ ማዕድናትን ምርት መጠን
- ለውጭ ገበያ የሚቀርብን ጥሬና እሴት የተጨመረባቸው የከበሩ ማዕድናትን ምርት ሽያጭ በብር
- ህገወጥ የከበሩ ማዕድናት (ኦፓል + አምበር) ምርትና ዝውውርን 100% ማስቆም፣
- ለባለፈቃዶች በማዕድን አዋጅና ደንብ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር 100% ህጋዊ የገበያ ስርዓት እንዲፈፅሙ ማድረግ፣
- የከበሩ ማዕድናት የግብይት ስርዓት 100% በግብይት አዋጁ መሠረት እንዲካሄድ ማድረግ፣
- የከበሩ ማዕድናት ግብይት በገበያ ማዕከሉ እንዲካሄድ ማድረግ፣

## *10.8 ንግድና ገበያ ልማት*

**ዓላማ 1. አደረጃጀትን ፣ አሰራርን ፣ የግብዓት አቅርቦትንና የአመለካከት ለውጥን በቀጣይነት በማሻሻል እውቀትና ክህሎትን በማጎልበት የተደራጀ የልማት ሠራዊቱን የመፈጸም ብቃቱን ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ፣**

ግብ 1- የተቋቋሙትን የሸማች ህ/ስራ ማህበራት መቶ ፐርሰንት ማጠናከር፤ የሸማቾች ሲቪክ ማህበራትን እንዲቋቋም ማድረስና የሴቶች ድርሻ 35% ማሳደግ፤

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፤**

- ማህበራት ያሉበትን ሁኔታ በጥናት በመለየት ግኝቱን መሰረት በማድረግ ችግሮቻቸውን መፍታት
- ሸማቾች ግንዛቢያቸው እንዲያድግ በጋራ እንዲመክሩና የጋራ ተልዕኮ ለመስጠት እንዲሁም የሸማቾች መብቶች ጥቅሞች እንዲከበሩ አኩሪ ተግባር የፈጸሙ አካላትን ለማጠናከር የሸማቾች ቀን በማክበር እውቅና መስጠት፣
- በዘርፉም ሆነ በማህበራቱ የሚታየውን የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ድርጊት በተቀናጀ ሁኔታ ትግል ማድረግ እንዲችሉ በስልጠናና በግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት

ግብ 2- የሸማቾች ህ/ስ/ማህበራት በምግብ ሸቀጦች ግብይት 10% የሚሆነውን የገበያ ድርሻቸውን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 40% ማድረስ፣

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፤**

- ከአጋር አካላት ጋር በመቀናጀት የንግድ ክህሎት ስልጠናና ግንዛቤ ማስጨበጫ ማንዋል በማዘጋጀት ስልጠና በመስጠት የአመለካከት፣ የእውቀትና የክህሎት አቅማቸውን ማጠናከር
- የሸማች ህብረት ስራ ማህበራትን የቦታ፣ የማቴሪያልና የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያገኙ ማመቻቸት
- በቴክኖሎጂ የተደገፈ መደበኛ የገበያ መረጃ እንዲደርሳቸውና ከሁለገብ ዩኔዮኖችና ከማምረቻ ድርጅቶች ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው መደገፍ

ግብ 3. ሴቶች፣ በመ/ቤቱና በልዩልዩ አደረጃጀቶች ውስጥ 30% አመራርና 50 % አባል እንዲሆኑ አልሞ በመንቀሳቀስ የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤ በተቋሙ የኤችአይቪ ኤድስ ተጋላጭነትንና የአካል ጉዳት አድሎን 0% ማድረስ፣

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- ሴቶች በንግድና ግብይት ልማቱ እንቅስቃሴ የጎላ ሚና እንዲኖራቸው ተቋማዊ ልዩ የአሰራር ማቀፍ ማዘጋጀት፣

**ዓላማ 2. ዘመናዊ የግብይት ስርዓት መዘርጋት እና ቀልጣፋና የላቀ የገበያ ማስፋፊያና ትስስር ስርዓት በመገንባት የውጪ ምንዛሪ ግኝታችንን ማሳደግ፣**

**ግብ-1** በ2012 መጨረሻ ለአገር ዉስጥ ገበያ ቀርቦ የነበረዉን የግብርና ምርት በ35% ጭማሪ በማሳደግ ለአገር ውስጥ ገበያ እንዲቀርብ በመስራት የአምራቹን፣ የነጋዴዉን እና የሸማቹን ተጠቃሚነት ማሳደግ እና የአምራች ፋብሪካዎችን የጥሬ ምርት ፍላጎት ማርካት፣

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-**

- ከሁሉም ከተማዎችና ወረዳወች ወቅቱን የጠበቀና ጥራት ያለው የገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀት፣ እና በመተንተን በልዩ ልዩ መገናኛ ዘዴዎች የማሰራጨት ስራ መስራት፣
- የዞኑን የሰሊጥና ነጭ ቦለቄ ግብይት ክትትል በማጠናከር በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ያለዉን የአቅርቦት መጠን ማሳደግ

**ግብ-2** በመስኖ አዉታሮች በ2012 ለሃገር ዉስጥ ገበያ የቀረበዉ አትክልትና ፍራፍሬ እና ቅመማ ቅመም ምርት በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ ላይ በ20% በማሳደግ ምርቱን ለሃገር ዉስጥ ገበያ ማቅረብ

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-**

- የገበያ ዕድሎችንና ክፍተቶችን በመለየት ለአምራቹና ለንግዱ ህብረተሰብ በተለያዩ መድረኮች የግንዛቤ ፈጠራ ስራ መስራት፣
- በዘመናዊ መልኩ የለማዉን የገበያ መረጃ ቋት አገልግሎት በማጠናክር የመስኖ ምርት አምራቾች፣ ነጋዴዎችና ሸማቾች ከአገልግሎቱ የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ብቁ ማድረግ፣

**ግብ- 3፡-** ለአገር ዉስጥ ገበያ የሚቀርበዉን የቁም እንስሳት ፣ የእንስሳት ተዋጽኦ (ማርና የማር ዉጤቶች፣ የእንስሳት መኖ፣ ዓሣ ፣ ደሮና ዕንቁላል የግብይትና የአገልግሎት አሰጣጥና አሰራርን በማሻሻል ይቀርብ ከነበረዉ ምርት በዕትድ ዘመን መጨረሻ ምርቱን በማድረስ) ከንዑስ ክፍለ ኢኮኖሚዉ የሚገኘዉን ገቢ ማሳደግ፣

**በዘርፉ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-**

- ለአገር ዉስጥ ገበያ የቁም እንስሳት በመሸኛ መላክ በ2012 መጨረሻ ተሸኝቶ ከነበረው በቁጥር 186675 ወደ 295570 ከፍ የማድረግ ስራ ይሰራል፤
- ቆዳና ሌጦ ምርትን ወደ ፋብሪካዎች በመሸኛ መላክ በ2012 መጨረሻ ተሸኝቶ ከነበረው በቁጥር 391779 ወደ 636774 ለማድረስ ይሰራል፤

- በ2012 መጨረሻ ኤክስፖርት ተደርጎ የነበረውን 3000 የቁም እንሰሳት ቁጥር 5082 በማድረስ በ2012 ተገኝቶ ከነበረው 150000 ዶላር ወደ 419060 ዶላር በማድረስ የውጭ ምንዛሬን መጠን ማሳደግን ያጠቃልላል፡፡

ግብ 4 ዘመናዊ የግብይት ስርዓት በመዘርጋት፤ የግብይት መሰረተ ልማት በማስፋፋት፤ ቀልጣፋና የላቀ የትስስር ስርዓት በመገንባት የውጪ ምንዛሪ ግኝትን የማሳደግ፣

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- በ2012 መጨረሻ ለአገር ዉስጥ ገበያ ቀርቦ የነበረው የሰብል ምርት 955011ሚሊዮን ኩ/ል በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 3610090 ሚሊዮን ኩ/ል በማድረስ የአምራቹን፣ የነጋዴዉን እና የሸማቹን ተጠቃሚነት ማሳደግ እና የአምራች ፋብሪካዎችን የጥሬ ምርት ፍላጎት የማርካት ስራ ይሰራል፣

**ዓላማ 3 ጠንካራ የንግድ ሪጉላቶሪ ስርአት በመዘርጋት የህጋዊ ነጋዴዎንና የሸማቹን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ**

ግብ 1. በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ መጀመሪያ በጀት ዓመት የነበረውን 46860 የነጋዴ ቁጥር በየአመቱ በማሳደግ የነጋዴውን ቁጥር 160353 በማድረስ የሴቶችን ተሳትፎ ከ30% ወደ 50% ማድረስ፣

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፣**

- በንግድ ምዝገባና ፈቃድ ህጉ፣ አዋጅና ደንብ የተለያዩ አንቀፅች ላይ ያሉ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ እንዲሁም ዕድሳት አገልግሎት አስጣጥ ወቅት የንግዱን ማህብረሰብ የሚያስቸግሩ የአሰራር ስርዓቶች ችግሮችን መፍታት፣
- የነጋዴና የንግድ ስራ ፈቃድ ቁጥር ለማሳደግ ችግር ሆነው የሚስተዋሉ የአሠራር ችግሮች እንደ ችግራቸው ክብደት እየተፈተሹ ማሻሻያ እንዲደረግባቸው ለውሳኔ አስጣጥ የሚረዱ የመረጃ ግብዓቶች ለውሳኔ ሰጪ አካላት ማቅረብ ፤

ግብ 2 - የንግድ ውድድር ስርዓትንና የሸማቹን መብቶች በማስከበር የሸማቹን ማህበረሰብ የመደራደርና የገበያ ተጠቃሚነት ከሚገመተው 650% ወደ 90% ማሳደግ፤

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፤**

- የምርትና አገልግሎት ጥራትና ደረጃ እንዲወጣና በአስገዳጅ ደረጃ የተወሰኑትም እንዲተገበሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መስራት፣

- ለሸማቹ ጤናና ደህንነት ጉዳት የሚያስከትሉ ምርቶችና አገልግሎቶች ለገበያ እንዳይቀርቡ መከታተልና መቆጣጠር እንዲሁም ለሸማቹ ምክርና መረጃ መስጠት

ግብ 3- በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ የተደረሰበትን 50% ህጋዊ የንግድ ሽፋን በስትራቴጅክ ዕቅዱ መጨረሻ ወደ 70% ማድረስ (ስሌቱን A /A+B+C) በማድረግ ይሰላል፡፡

- ህጎችንና አሰራሮችን መሰረት አድርጎ ህገ-ወጥ ንግድን ለመከላከል በሚያስችል መልኩ የንግድ አሰራር ደንቦች፣ የስራ ማንዋሎችና መመሪያዎችን ማዘጋጀትና እዲፀድቁ መከታተል፤
- በየድርጅቱ በሚደረጉ የበርከበር ጉብኝት ግንዛቤ ማስጨበጥ፤ ክትትልና ቁጥጥር ስራን በመፈፀም ህገ-ወጥነትን ማስተካከል፤
- በተገኙ ህገ-ወጥ የንግድ ተግባራት አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እና ህጋዊ ርምጃዎችን በመውሰድ እንዲስተካከሉ ማድረግ፡፡

**ዓላማ 4. የዘርፉን አገልግሎት ለማሻሻል፣ ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ አሰራርና አጠቃቀምን ማሳደግና ማሻሻል፣**

ግብ1. በ2012 ዓ.ም መጨረሻ የነበረውን የንግድ ምዝገባ፣ የንግድ ፈቃድ መስጠትና መረጃዎች በኦን ላይን ወደ ኮምፒውተር የማስገባት አፈፃፀም መነሻ በማድረግ የኦን ላይን አገልግሎት 100% ተግባራዊ በማድረግ በኦን ላይንወደ ኮምፒዩተር የሚገባውን የንግድ መረጃ (100%) ማስቀጠል፣

የሚከናወኑ ተግባራት፣

- ሁሉም የአንድ ማዕከላት በሽቦ አልባ ቴክኖሎጂ የማገናኘት ሥራን መስራትና አገልግሎት እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መነጋገር፤
- ሲስተሙን /የሚያንቀሳቅሱ ማቴሪያሎች አሁን ያሉት ሥራ እንዳያቋርጡ የጥገና አገልግሎት መስጠትና የአዳዲሶች ግዥ እየፈፀሙ ተግባሩ እንዲቀጥል ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መነጋገር፤

ግብ 2 በ2012 መጨረሻ በወረዳ ኔት ወርክ የተሳሰሩና የዋጋ መረጃ አገልግሎት ይሰጡ የነበሩትን ወረዳና ከተማ አሰተዳደሮች የሉም ነገር ግን በቀጣይ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በሁሉም ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች የወረዳ ኔት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የመረጃ ልዉዉጡን ዘመናዊ ማድረግ፣

**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ፡-**

- ኢንፎረሜሽን ቴክኖሎጅ አቅርቦትና ተጠቃሚነትን ማሳደግና ማስፋፋት
- የመረጃ ስርጭትና አጠቃቀም ውጤታማነትን በአመት ሁለት ጊዜ በጥናት መለየት፣

## 10.9. ባህል ቱሪዝም

**ግብ 1. የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤን ማሳደግ፡-**

**ተግባራት**

- የቋሚ ቅርሶችን የጉዳት መጠን ልየታ ከ14 ወደ 187 ማድረስ፣
- የቋሚ ቅርሶችን ጥገና ከ6 ወደ 10 ማድረስ እንዲሁም 110 ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን መጠገን፣
- የይዞታ ማረጋገጫ ያገኙ ቋሚ ቅርሶችን ከ148 ወደ 300 ማድረስ፣
- የቋሚ ቅርስ ምዝገባ 30 እና ተንቀሳቃሽ 2000 በማከናወን የምዝገባ ሽፋን 100% በማጠናቀቅ ህጋዊ እዉቅና እንዲያገኙ ማስቻል፣
- ቁጥጥርና ክትትል የሚደረግላቸውን ቋሚ ቅርሶች ከ155 ወደ 255 እንዲሁም የተንቀሳቃሽ ቅርሶችን ደግሞ ከ9243 ወደ 11418 ማድረስ፣

**ግብ 2. የባህል እሴቶች ልማት ማሻሻል**

**ተግባራት**

- መጤ ባህሎችን፣ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን፣አመለካከቶችና አስራሮችን ለመቀነስ የሚፈጠሩ የግንዛቤ መድረኮችን ከ800 ወደ 1,900 ማድረስ እንዲሁም ግንዛቤ የሚፈጠርላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎችን ከ356,000 ወደ 600,000, ማድረስ፣ (የሴቶች 50%፣የህጻናት 10%፣የወጣቶች 60%፣የአዋቂዎች 30% ድርሻ ነው)
- ከዞን እስከ ወረዳ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ዙሪያ 150 የንቅናቄ ሳምንት በመፍጠር 16150 የህብረተሰብ ክፍሎችና ባለደርሻ አካላትን ማሳተፍ፣
- የዞኑን 5 ባህላዊ ተምሣሌቶች /icons/ በመለየት እንዲታወቁ ማድረግና ዕውቅና መስጠት፣
- 10 የሕዝብ ቤተመጻሕፍትን በቴክኖሎጅ፣ በቁሳቁስና በአደረጃጀት ማጠናከር፣
- 50,000 መጻሕፍትን በድጋፍና በግዥ በማሰባሰብ ለህዝብ ቤተመጻሕፍት ተደራሽ ማድረግ፣

ግብ 3. የባህል ኢንዱስትሪ ፈጠራን ማሳደግ፣

ተግባራት

- በባህል ኢንዱስትሪ ለተሰማሩ ተቋማት በክልሉ እና ከክልሉ ውጭ የሚፈጠርላቸውን የገበያ ትስስርን ከ10 ወደ 20 ማድረስ በዚህም 120 አባላትን ማሳተፍ፣
- በዞኑ ተቋቁመው የሚሰሩ የኪነ-ጥበብ ማህበራትና የባህል ቡድኖች ውስጥ 50% የሚሆኑትን ወደ ኢንተርፕራይዝ ማሸጋገር፣
- የሚካሄዱ የሥነጽሑፍ እና የቅኔ ምሽቶችን ከ456 ወደ 819 እና የሚታደሙ የህብረተሰብ ክፍሎችን ከ89,564 ወደ 199,971 ማሳደግ፣ (የሴቶች 50%፣የህጻናት 10%፣የወጣቶች 60%፣የአዋቂዎች 30% ድርሻ ነው)
- በአማተር ኪነ-ጥበብ ከያኒያን፣በስነ-ጽሑፍ፣በቲያትር፣በሙዚቃ፣በባህል ሙዚቃ መሣሪያ አጨዋወት፣ በስዕልና ቅርጻቅርጽ ሙያ 1,200 ለሚሆኑ ተሳታፊዎች ስልጠና መስጠት፣

ግብ 4. የቱሪዝም መሰረተ ልማት አቅርቦት ማስፋፋት፣

ተግባራት

- የመሰረተ-ልማት አውታር የሚሰራላቸውን የመስህብ ሀብቶች ከ6 ወደ 68 በማድረስ የመንገድ ዝርጋታውን ከ 156 ኪ.ሜ ወደ 894 ኪሎ.ሜትር፣ 27 የመስህብ ሃብቶች ንጹህ መጠጥ ዉሃ አቅርቦት ፣ 21 የመጸዳጃ ቤት /Toilet/ እና የመታጠቢያ ቤት (ሻዎር) መገልገያዎች ፣ ለ21 መስህብ ሀብቶች የመብራት መሰረተ-ልማት አቅርቦት እንዲሰራ ማስተባበር፣
- በነባርና አዲስ መዳረሻዎች 15 የቱሪስት እረፍት ማድረጊያ መጠሊያዎችን /break stop shelters/ መገንባት፣
- የገጸ-ምድር ማስዋብ /landscape leveling/ የተሰራላቸውን የመስህብ ሃብቶች 16 ማድረስ፣
- በ4 ሀይቆች ዳር ለዳር፣በ3 ጥብቅ ስፍራዎች እና 2 ብሄራዊ ፓርኮች የ150 ኪ.ሜትር የዉስጥ ለዉስጥ እግረኛ መንገድ /walk way/እንዲኖራቸዉ ማድረግ፣

ግብ 5. የቱሪዝም ምርትና ገበያ ልማት ተደራሽነት ማሳደግ፣

ተግባራት

- አዲስ የሚለሙ የተፈጥሮ ቱሪዝም ምርቶችን ለማስፋፋት በዞኑ የሚገኙ 2 የፍል-ዉሃ ምርቶችን፣ 3 ጥብቅ ደኖችን፣ 2 የለሙ ተራራዎችን፣ 1 ወንዝ፣ 4 ሀይቆችን፣ 4

ዋሻዎችን፣ 1 ሸለቆ፣ 5 ፏፏቴዎችን፣ 2 ብሄራዊ ፓርኮችን፣ 2 ልዩ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ ያላቸዉ ስፍራዎች፣ በማልማት ወደ ቱሪዝም ገበያ ማስገባት፣

- አዲስ የሚለሙ ባህላዊ ቱሪዝም ምርቶችን ለማስፋፋት በዞኑ 3 የስነ-ቅርስ ቁፋሮ/አርኪዮሎጂ/ስፍራዎችን፣ 3 ጦርነት የተካሄድባቸዉ ጥንታዊ ስፍራዎች /የጦርነት አዉድማዎች/፣ 10 ጥንታዊ ገዳማት፣ አብያተ ክርስቲያናትና መስጅዶችን፣ 2 የገበያ ስፍራዎችን፣ 3 ሀይማኖታዊ የጠበል ስፍራዎችን፣ 3 ጥንታዊ አብያተ መንግስታት፣ 10 ባህላዊና ሀይማኖታዊ ሁነቶችን፣ 10 አዲስ ታሪካዊ ቲም-ፓርኮችን በማልማት ወደ ቱሪዝም ገበያ ማስገባት፣
- 2 በዉሃማ አካላት፣1 በአየር ላይ እና 1 በምድር/መሬት/ ላይ የጀብድ ቱሪዝም ለማስፋፋት የሚያስችሉ በድምሩ 3 አዳዲስ የቱሪዝም ትግበራዎችን /tourism activities/ በማልማት ለቱሪዝም ገበያ ማቅረብ፣
- የመዳረሻዎች ወይም የመስህብ ሀብቶች የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ በትብብር የሚሰሩ ፕሮግራሞችን በአገር ውስጥ ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ከ320 ወደ 510፣ በሬዲዮ ከ396 ወደ 510 ማሳደግ፣
- ለማስተዋወቅ የሚሰሩ ዘጋቢ ፊልሞችን በአይነት 10 በማድረስ በቅጅ ብዛት 5,725 ማድረስ፣

**ግብ6. የሀገር ዉስጥ ቱሪዝም ልማት ማስፋፋት፣**

**ተግባራት**

- በቱሪዝም ማህበራዊ፣ባህላዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ጠቀሜታዎች ዙሪያ 230 መድረኮችን በማዘጋጀት ለ6,900 (50% የሴቶች ድርሻ) የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት መስጠት፣

**ግብ7. ከቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘዉን ገቢ ማሳደግ፣**

**ተግባራት**

- ከዉጭ አገር ቱሪስት ፍሰት የሚገኘዉን ገቢ በየአመቱ 20 በመቶ በማሳደግ ከ15,324 ወደ 53,301,573 ማድረስ፣
- ከሀገር ዉስጥ ቱሪስት ፍሰት የሚገኘዉን ገቢ በየአመቱ 20 በመቶ በማሳደግ ከ2,256,140,162 ወደ 7,552,428,388 ማድረስ፣

## የትኩረት መስክ4. የላቀ የአገልግሎት አሰጣጥ

### ግብ 9. የሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎቶችን መጠን፣አይነት እና ደረጃ ማሻሻል

ኢላማዎች፡-

- ለሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎቶች የሚሰጠውን የሙያ ድጋፍና ክትትል ከ30,218 ተቋም ወደ 32,700 ማድረስ፣
- በየአመቱ ግንባታቸውን አጠናቀው ወደ አገልግሎት የሚገቡ የሆቴልና ቱሪዝም ኢንቨስትመንቶች ብዛት ከ18 ወደ 80 ማድረስ፣
- ምርትና አገልግሎታቸውን ያሻሻሉ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ከ3,527 ወደ 12,525 ማድረስ ወይም ከ27% ወደ 73% ማድረስ፣
- የኮከብ ደረጃ የተሰጣቸውን አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ከ1 ወደ 5 ማድረስ፣

# 11. ማህበራዊ ልማት ዘርፍ

## 11.1. ትምህርት

ግብ 1. በብቃት ላይ የተመሰረተ፣ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ክህሎትን ና ሀገር በቀል እውቀትን መሰረት ያደረገ የተለያዩ ፍላጎቶች የሚያስተናግድ ስርአተ ትምህርት መቅረጽ፣

- በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የመመህራን ማስተማሪያ መጻህፍት ጥምርታ 1፤1 ማድረስ
- በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪዎች የመጻህፍት ጥምርታ ከነበረዉ 1፤2 ወደ 1፤1 ማድረስ
- በልዩ ፍላጎት ትምህርት የተማሪዎች የመጻህፍት ጥምርታ 1፤1 ማድረስ
- በ6ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ተመዝነው 50 % እና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች ብዛት (በመቶኛ) ከ0 ወደ 100%

ግብ 2. ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና የብሄራዊ ፈተናን አዲስ ከሚዘጋጀው ስርአተ ትምህርት አኳያ አጣጥሞና አሻሽሎ መተግበር

- በ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ተመዝነው 50 % እና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች ብዛት በመቶኛ (መነሻው የ2011 ዓ/ም ውጤት ነው) ከ44.04% ወደ 85% ከፍ ማድረግ
- በ12ኛ ክፍል ሀገራዊ ፈተና ተመዝነውወደ ከፍተኛ ትም/ያለፉ ተማሪዎች ብዛት በመቶኛ (መነሻው የ2011 ዓ/ም ውጤት ነው) ከ65.51% ወደ 80% ከፍ ማድረግ

ግብ. 3. የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ስርአተ ትምህርት አሻሽሎ በማዘጋጀት መተግበር

- በጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ስርአተ ትምህርት የሰለጠኑ ጎልማሶች ብዛት በመቶኛ ከ41% ወደ 100% ከፍ ማድረግ

ግብ 4. የትምህርት ተደራሽነትን ማሻሻል፣

- ጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነት ከ31.6% ወደ 100 % ክፍ ማድረግ
- ጥቅል የ1ኛ ክፍል ቅበላን ከ63.2% ወደ 100% ክፍ ማድረግ
- ንጥር የ1ኛ ክፍል ቅበላን ከ56.9% ወደ 100% ከፍ ማድረግ
- ጥቅል ከ1ኛ-8ኛ ክፍል ከ70% ወደ 93.26% ከፍ ማድረግ
- ንጥር ከ1ኛ-8ኛ ክፍል ከ66.53% ወደ 87.9% ከፍ ማድረግ
- ጥቅል ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ከ27.58% ወደ 75% ከፍ ማድረግ
- ንጥር ከ9ኛ-12ኛ ክፍል 24.35% ወደ 75% ከፍ ማድረግ

ግብ 5. የትምህርትን ፍትሀዊነትና አካታችነት ማረጋገጥ፣

- የቅድመ አንደኛ ትምህርት በጥቅል የትምህርት ተሣትፎ የስርአተ ጾታ ምጥጥን 1.00 ማድረስ
- ከ1-8ኛ ክፍል በጥቅል የትምህርት ተሣትፎ የስርአተ ጾታ ምጥጥን ከ0.95 ወደ 1.00 ከፍ ማድረግ
- ከ9-12ኛ ክፍል በጥቅል የትምህርት ተሣትፎ የስርአተ ጾታ ምጥጥን ከ1.27 ወደ 1.22 ከፍ ማድረግ

ግብ 6. ሳይንስና ቴክኖሎጂን ለመተግበር የሚያስችል የትምህርት ቤት መሰረተ ልማት እና የትምህርት ግብዓት አቅምን ማሻሻል፣

- በየደረጃው ለተግባራዊ ስራ የተዘጋጁና የተሟሉ የሳይንስ የቤተ መኩራዎች ብዛት (በመቶኛ)የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ከ78.5% ወደ 100% ከፍ ማድረግ
- በየደረጃው ለተግባራዊ ስራ የተዘጋጁና የተሟሉ የሳይንስ የቤተ መኩራዎች ብዛት (በመቶኛ)የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከ53.7% ወደ 100% ከፍ ማድረግ

ግብ.7. የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ማሻሻል፣

- በትምህርት ኢንስፔክሽን ደረጃ 3 የደረሱ ትምህርት ቤቶች ብዛት በመቶኛ የቅድመ አንደኛ በመቶኛ ወደ 96% ከፍ ማድረግ
- በትምህርት ኢንስፔክሽን ደረጃ 3 የደረሱ ትምህርት ቤቶች ብዛት በመቶኛ የአንደኛ ደረጃ በመቶኛ ከ17.4% ወደ 96% ከፍ ማድረግ

- በትምህርት ኢንስፔክሽን ደረጃ 3 የደረሱ ትምህርት ቤቶች ብዛት በመቶኛ የሁለተኛ ደረጃ በመቶኛ ከ20% ወደ 81.2% ከፍ ማድረግ
- በትምህርት ኢንስፔክሽን ደረጃ 4 የደረሱ ትምህርት ቤቶች ብዛትበመቶኛ የቅድመ አንደኛ በመቶኛ 4% ማድረስ
- በትምህርት ኢንስፔክሽን ደረጃ 4 የደረሱ ትምህርት ቤቶች ብዛትበመቶኛ የአንደኛ ደረጃ በመቶኛ 9.4% ማድረስ
- በትምህርት ኢንስፔክሽን ደረጃ 4 የደረሱ ትምህርት ቤቶች ብዛትበመቶኛ የአንደኛ ደረጃ በመቶኛ 18.8% ማድረስ

ግብ 8. መምህራንንና በሙያ ፈቃድ ምዘና ብቃታቸውን ማረጋገጥ፡፡

- የሙያ ፈቃድ የብቃት ምዘና ወስደው ከአጥጋቢ ውጤት በታች ያመጡና ዳግም የሙያ ፈቃድ ምዘና የወሰዱ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን በመቶኛ፤ 100% ማድረግ

**ግብ 9. የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት መርሀ ግብሮችን ተደራሽነት ማሳደግ፣**

- የአንደኛ ዓመት የጎልማሶች ትምህርት ተሣታፊዎች በመቶኛ ከ20.6% ወደ 70% ከፍ ማድረግ
- የሁለተኛ ዓመት የጎልማሶች ትምህርት ተሣታፊዎችበመቶኛ ከ22.9% ወደ 60% ከፍ ማድረግ

## *11.2. ጤና ልማት*

**ግብ 1፡- የእናቶችን ጤና መሻሻል**

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- የእናቶች ሞት ምጣኔ በህይወት ከወለዱ 1,000,000 እናቶች መካከል ከ401 ወደ 135 ማውረድ
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ሥርጭት መጣኔ በመቶኛ (CPR) ከ50 ወደ 58 ማድረስ
- የድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ሽፋን ከ70 ወደ 98 ማድረስ

**ግብ 2፡- የህፃናትን ጤና መሻሻል**

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- ከ5 ዓመት በታች ያሉ የህፃናት ሞት ምጣኔ ከ1000 በህይወት ከሚወለዱ ህጻናት መካከል ከ69 ወደ 30 ማውረድ
- ዕድሜያቸው ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ የህፃናት ሞት ምጣኔ ከ58 ወደ 22 ማውረድ

- የጨቅላ ህፃናት ሞት ምጣኔ ከ1000 በህይወት ከሚወለዱ ህጻናት መካከል ከ46 ወደ 16 ማውረድ

**ግብ 3፡-የክትባት አገልግሎት ሽፋንን ማሻሻል**

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- የሶስተኛ ዙር የፔንታቫለንት ክትባት ያገኙ ሕፃናት ሽፋን በመቶኛ ከ93 ወደ 99 ማሣደግ
- ሙሉ በሙሉ ክትባት ያገኙ ህጻናት ሽፋን በመቶኛ ከ89 ወደ 98 ማሳደግ
- የሁለተኛን ዙር የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት (MCV2) ያገኙ ሕፃናት ሽፋን ከ59 ወደ 98 ማሣደግ

**ግብ 4፡- የህጻናት ስርዓተ ምግብን በማሻሻል በህጻናት ላይ የሚታየውን መቀንጨር መቀነስ**

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- ከ5 ዓመት በታች ያሉ የህፃናት መቀንጨር ከ1000 ህጻናት መካከል በመቶኛ ከ41 ወደ 11 መቀነስ
- ከ5 ዓመት በታች ያሉ የህፃናት መቀጨጭ በመቶኛ ከ8 ወደ 2 ማውረድ

**ግብ 5፡-የተላላፊ በሽታዎች መቆጣጠር እና መከላከልን ማሻሻል**

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- የፀረ ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መድኃኒት ህክምና ሽፋን በመቶኛ ከ68 ወደ 95 ማሣደግ
- የሁሉም አይነት የቲቢ በሽታ ልየታ ሽፋን በመቶኛ ከ51 ወደ 93 ማሣደግ
- መድሃኒት የተላመደ ቲቢ ህሙማን ከበሽታው የመዳን መጠን ከ80 ወደ 95 ማድረስ
- በወባ አዲስ የመያዝ ምጣኔ ከ1000 ሰዎች መካከል ከ33 ወደ 0 ዝቅ ማድረግ

**ግብ 6፡- የተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እና ጠንቆቻቸው መከላከል መሻሻል**

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ያለ ዕድሜ የሚከሰት የሞት ምጣኔ ከ18 ወደ 10 ዝቅ ማድረግ
- የማህፀን ካንሰር ቅድመ ምርመራ ያደረጉ ከ30-49 ዓመት የሆኑ ሴቶች ድርሻ ከ3.3 ወደ 80 ማሣደግ
- በአዋቂዎች የሚከሰት የደም ግፊት በሽታን የመቆጣጠር ሽፋን በመቶኛ ከ51 ወደ 90 ማሣደግ

- በአዋቂዎች የሚከሰት የስኳር በሽታን የመቆጣጠር ሽፋን በመቶኛ ከ41 ወደ 88 ማሣደግ

ግብ 7፡- የጤና አገልግሎት አቅርቦት ጥራት መሻሻል

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- የተመላላሽ ህክምና አገልግሎት ምጣኔ ከ1.7 ወደ 3.7 ማሣደግ
- የአልጋ መያዝ መጠን በመቶኛ ከ44 ወደ 85 ማሣደግ

ግብ 8፡-ጤና ኤክስቴንሽንና የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤን ማሻሻል

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- የድንገተኛና መሰረታዊ ቀዶ ጥገና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ጣቢያዎችና የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ሽፋን በመቶኛ ከ8 ወደ 33 ማሣደግ
- ከፍተኛ አፈጻጸም ያላቸው የመጀመሪያ ደረጃ የጤና እንክብካቤ መስጫ ተቋማትን (PHCUs) ሽፋን በመቶኛ ከ8 ወደ 80 ማሣደግ
- አጠቃላይ የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ኬላዎች ሽፋን በመቶኛ ከ0 ወደ 25 ማሣደግ
- በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ መመሪያን (EPHCG) ተግባራዊ ያደረጉ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና እንክብካቤ አሃዶች ከ25 ወደ 100 ማሳደግ

ግብ 9፡- የህክምና ግብኣቶች አቅርቦትን ማሻሻል

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- የመሰረታዊ መድኃኒቶች አቅርቦት በጤና ተቋማት በየደረጃቸው በመቶኛ ከ64 ወደ 95 ማሣደግ
- በአቅራቢ ድርጅቶች የህክምና ግብዓት አቅርቦት ምጣኔ (Drug/Pharmaceutical supply refill rate) ከ45 ወደ 95 ማሣደግ

ግብ 10፡- የጤና ቁጥጥር ስርዓትን መሻሻል

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- ጥራታቸው ያልተጠበቀና ህገወጥ መድኃኒት በገበያ ላይ ስርጭት ሽፋን በመቶኛ ከ8.6 ወደ 5 ማውረድ
- ደየህክምና ግብኣቶች አቅርቦትን ማሻሻልህንነታቸው ያልተጠበቀና ህገወጥ ምግብ በገበያ ላይ ስርጭት ሽፋን በመቶኛ ከ40 ወደ 5 ማውረድ

## ግብ 11፦ የጤና መሰረተ ልማት ጥራትን ማሻሻል

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- የጤና ኬላ ለህዝብ ጥምርታ ከ5844 ወደ 4000 ማሻሻል
- የጤና ጣቢያ ለህዝብ ጥምርታ ከ23334 ወደ 20000 ማሻሻል
- የተሻሻለ የውኃ አቅርቦት ያላቸው ጤና ተቋማት (ጤና ኬላን ጨምሮ) በመቶኛ ከ20 ወደ 95 ማሣደግ
- የኤሌትሪክ አቅርቦት ያላቸው ጤና ተቋማት (ጤና ኬላን ጨምሮ) በመቶኛ ከ25 ወደ 90 ማሣደግ
- መሰረታዊ የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት ያላቸው ጤና ተቋማት (ጤና ኬላን ጨምሮ) ሽፋን በመቶኛ ከ12 ወደ 100 ማሣደግ
- የተሻሻለ የመጸደጃ ያላቸው ጤና ተቋማት (ጤና ኬላን ጨምሮ) ሽፋን በመቶኛ ከ54.3 ወደ 100 ማሣደግ
- የጤና ተቋማትን ደረጃ ስታንዳርድ ያሟሉ ጤና ተቋማት ሽፋን በመቶኛ ከ0 ወደ 100 ማሣደግ

## ግብ 12፦ የአካባቢ ንጽሕና አጠባበቅ መሻሻል

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- ሁሉም አይነት መፀዳጃ ቤት ያላቸው አባወራዎች/እማወራዎች ሽፋን በመቶኛ ከ81 ወደ 100 ማሣደግ
- ዘወትር በወሳኝ ጊዜያት እጃቸውን በአግባቡ የሚታጠቡ ቤተሰቦች ሽፋን በመቶኛ ከ40 ወደ 100 ማሣደግ
- የሞዴል ቀበሌዎች ቁጥር ከ100 ወደ 500 ማሣደግ
- የሞዴል አባወራ/እማወራ ሽፋን በመቶኛ ከ66 ወደ 95 ማሣደግ

## ግብ 13፦ የጤና የመረጃ ስርዓት መሻሻል

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- የመረጃ ጥራት ማረጋገጫ መስፈርትን ያሟሉ ጤና ተቋማት ሽፋን (dat verification factor within 10% range for selected indicators) በመቶኛ ከ88 ወደ 95 ማድረስ
- የውልደት ማሳወቅ ሽፋን(በተቋም ከተወለዱ ህጻናት) በመቶኛ ከ92 ወደ 100 ማሻደግ
- የሞት ማሳወቅ ሽፋን(በተቋም ውስጥ ሞት) በመቶኛ ከ70 ወደ 100 ማሳደግ

- በስታንዳርዱ መሰረት በቁጥጥር ስር የዋለ የጤና ወረርሽኝ ከ56 ወደ 100
- የጤና አደጋዎች ደህንነት ኢንዴክስ ከ0.63 ወደ 0.9 ማሣደግ

**ግብ 14፡-የጤና አገልግሎቱን ለመደገፍ የተሰባሰበ እና የተመደበ ፋይናንስ ማሣደግ**

የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- ከአቅም በላይ የሆነ የጤና ወጪ ክስተት በመቶኛ ከ2.1 ወደ 1.5 መቀነስ
- ለጤና አገልግሎት ከኪስ የሚያወጣ ወጪ ሽፋን (out of Pocket Expenditure) በመቶኛ ከ31 ወደ 20 ማውረድ
- የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት ሽፋን (ቤተሰቦች) በመቶኛ ከ67.7 ወደ 100 ማድረስ
- በማህበራዊ የጤና መድህን (SHI) የታቀፉ ሰራተኞች ሽፋን በመቶኛ ከ0 ወደ 100 ማሣደግ

## 11.3. ሴቶች ህጻናት

**ዓላማ፡-** በ2022 የህፃናት ማህበራዊ ተጠቃሚነት፣ተሣትፎና ጥበቃን በማጎልበት የህፃናትን መብትና ደህንነት ማረጋገጥ

**ግብ1፡ የህፃናትን ሁለንተናዊ ዕድገት ማጎልበት፤**

**ውጤት 1፡ በመልካም ባህሪ የታነፁ ህፃናት**

በህጻናት መብት፣ ደህንነትና አያያዝ፣ በአወንታዊ ስነምግባር አጠባበቅ፣ በወላጅነት ክህሎት፣ የህይወት ክህሎትና በህጻናት ጥበቃ ዙሪያ ለ8300 (ወ 4150 ሴ 4150) ህጻናት፤ለ509,829 (ወ 257623 ሴ 252206) የህብረተሰብ ክፍሎች እና 944 (ወ 546 ሴ 398) ባለሙያዎች ግንዛቤ ይፈጠራል፡፡

**ውጤት 2፡ ጤናቸው የተጠበቀ ህፃናት**

- ለ 487,028 የሴቶች የልማት ቡድኖች አባላት በህጻናት ንጽህና አጠባበቅ፣ጡት በማጥባት፣በህጻናት አመጋገብ፣በህጻናት መቀንጨርና መቀጨጭ በማወስገድ ዙሪያ (በተሻለ የስርዓተምግብ አያያዝና አጠቃቀም ላይ) ግንዛቤይፈጠራል፡፡
- የተጠናከረ የመንግስት የጤና ተቋማትን የመከታተል፣መደገፍናማብቃትስራይሰራል፡፡

**ግብ 2፡ የህፃናትን ጥበቃ ማጎልበት፤**

**ውጤት 1፡ ድጋፍና እንክብካቤ የተደረገላቸው ህፃናት**

- ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸውን ህፃናት መረጃ የመሰብሰብና ተገቢነቱን የማረጋገጥ፤
- 327,600 ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በአማራጭ የህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ፕሮግራሞች ላይ ግንዛቤ መፍጠር፤
- 2216 ህጻናትን ማህበረሰብ አቀፍ በሆኑ እና በተለያዩ የህጻናት ድጋፍና እንክብካቤ አማራጮችተጠቃሚእንዲሆኑይደረጋል፣

**ውጤት 2፡ የቀነሰ የህፃናት ተጋላጭነት**

- በዞን ደረጃ ከ1 ወደ 5 እና በወረዳ ከ24 ወደ 40 የህጻናት ማቆያ ማዕከላት በማቋቋም ስራ እንዲጀምሩ ይሰራል፡፡
- ተስማሚ የህፃናት ችሎቶችን ከ6 ወደ 24 ማሳደግ፣
    - ያለድሜጋብቻ፤የሴትልጅ ግርዛት፣ህገወጥ ዝውውር በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንሱ ማድረግ እንድሁም ህፃናት በህግ አባትን የማወቅ መብታቸው 100% እንዲረጋገጥላቸው ማድረግ

**ግብ 3፡ የህፃናትን ተሳትፎ ማጎልበት፤**

**ውጤት1፡ የህፃናት ሀሳብ መከበር**

የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት፡-

- ህፃናት በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ፣ በአካባቢ፣ በትምህርት ቤቶች እንዲሁም በክልል ደረጃ እነሱን በሚመለከታቸው ጉዳዮች ሀሳባቸውን የመስጠትና የመደመጥ መብቶቻቸውን በማረጋገጥ የህፃናትን ተሣትፎ ለማጎልበት የሚያስችሉ የግንዛቤና ንቅናቄ ሥራዎች፣የተሳትፎ መድረኮችን የማሳደግና የአቅም ግንባታ ሥራዎች ተጠናክረው ይሰራሉ፡፡
- በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክርቤቶች 3 የህጻናት ፓርላማን አባላትን በመወከል 1803 ህጻናትን ማሳተፍና ድምፃቸውን እንዲያሰሙ ይሰራል፡፡

**ውጤት 2 ፡ መብትና ግዴታቸውን ያወቁ ህፃናት፣**

- ለ378,926 ህጻናትን በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር፣
- በመደራጀት ጥቅም እና አስፈላጊነት ዙሪያ ግንዛቤ ከመፍጠላቸው ህጻናት ውስጥ 378,926 ማደራጀት ይህም ግንዛቤ ከተፈጠረላቸው ውስጥ 80 በመቶውን በተለያዩ የህጻናት አደረጃጀቶች እንዲደራጁይደረጋል፡፡

- 1803 ህጻናት በህጻናት ፓርላማ በንቃት እንዲሳተፉ ይሰራል፡፡
- በወረዳየሚገኙበሙያ 617 የህጻናትፓርላማን፣ 617 በቁሳቁስና 617 በገንዘብ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ይጠናከራሉ፡፡

**ግብ 4፡ የሴቶች፣ ህፃናት፣ አረጋውያና አ/ጉዳተኞች መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማስጠበቅ**

**ዝርዝር ግቦች**

- የሴቶች አካላዊ ጥቃት መጣኔንን ወደ 5% መቀነስ፣
- የህፃናት ያለዕድሜ ጋብቻ መጣኔ ወደ 0 መቀነስ
- የሴት ልጅ ግርዛት መጣኔ 0 ማድረስ፣
- የጥቃት ሰለባዎች ድጋፍ አገልግሎቶችን ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶችን ድርሻ 100 % ማድረስ፣
- በመደራጀት መብትና ጥቅማቸውን ያስጠበቁ ሴቶችን ድርሻ 70% ማድረስ፣
- ለሴቶች ተሳትፎ አዎንታዊ አመለካከት ያለው ህብረተሰብ በመቶኛ ወደ 80 ፐረሰንት ማድረስ

**ግብ 5፡ የሴቶች፣ ህፃናት፣አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣**

**ዝርዝር ግቦች**

- ከጠቅላላ ሴት የመንግስት ሰራተኞች የከፍተኛ ትምህርት ዕድል ተጠቃሚ የሆኑ ሴት የመንግስት ሰራተኞችድርሻ በመቶኛ አሁን ካለበት ወደ 50 % ማሳደግ፣
- የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶችን ከ 3056ሺ ወደ 80ሺ ማሳደግ፣
- በቁጠባ የተሳተፉ ሴቶችን ቁጥር ከ32947 ሚሊዮን ወደ 329470 ማድረስ፣
- የሴቶች የቁጠባ መጠን ብር ከ 128ሚ ወደ 1280 ማሳደግ፣
- የቀነሰ የሴቶች የስራ አጥነት ምጣኔ (Rate of women unemployment rate) ወደ 12.4% ዝቅ ማድረግ
- በጥቃቅንና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ የሴቶች የባለቤትነት ድርሻ ወደ 50 % ማሳደግ፣
- በህብረት ስራ ማህበራት በአባልነት የታቀፉ ሴቶችን ቁጥር ከ32947 ወደ 329470 ማሳደግ፣

- የገጠር መሬት ባለቤትነት የተረጋገጠላቸው ሴቶችን ቁጥር ወደ 100 % ማሳደግ፣
- በጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶችን ቁጥር ከ 1508 ወደ 15080 ማሳደግ፣
- የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች መጣኔን ወደ 100% ማድረስ፣

**ግብ 6. የአካል ጉዳተኞች፣ የአረጋዊያን እና የኢኮኖሚያዊና የማህበራዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የኢኮኖሚያዊና የማህበራዊ ተካታችነት፣ ተሳታፊነት፣ ተደራሽነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ፤**

**ዝርዝር ግቦች**

- ማህረሰብን መሠረት አድርገው የተዋቀሩ አደረጃጀቶች፣ ሲቪክ ማህበራት እና የንግዱ ማህረሰብ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋዊያን እና ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ላደረጉ ዜጎች የድጋፍ እና የእንክብካቤ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ በማድረግ ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣

- ተከታታይነት ያላቸው በየዓመቱ 578 ቀበሌዎች ላይ የሥልጠናና የግንዛቤ ማሳደጊያ መድረኮችን በመፍጠርና በመጠቀም ህብረተሰቡና የሚመለከታቸው አካላት ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋዊያን እና ለኢኮኖሚያዊና የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያድርጉትን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍና እንክብካቤ ሽፋን ማሳደግ፣

- የህብረተሰቡንና የአስፈጻሚ አካላትን ግንዛቤ በማሳደግ የኢኮኖሚያዊ እና የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን 90%ማሻሻል፣

## 11.4. ወጣትና ስፖርት

### ግብ 1. የስፖርት መሠረተ ልማቶችን ማስፋፋት

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችና የማሰልጠኛ ማዕከላት ተደራሽነት ፣ ህጋዊነት እና የጥራት ደረጃ በሚፈለገው ደረጃ አለመድረሱን ተከትሎ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እና የማሰልጠኛ ማዕከላት ከሕብረተሰቡ ቁጥር አንፃር ቁጥራቸውን በማመጣጠን ፣ በማሳደግ እና በአዋጅ ቁጥር 729/2004 መሠረት አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግላቸው በማድረግ ከዚህ ቀደም

በዕቅድ ተይዞ ተግባራዊ ያልተደረገውን በቀበሌ ሁለት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲኖሩ ማስቻልና ሁሉም አገልግሎት የሚሰጡበትንና ለስልጠናና ውድድሮች ምቹ የሚሆኑበትን ሁኔታ መፍጠር እንዲሁም በወረዳ ደረጃ አንድ ደረጃውን የጠበቀ 3ኛ ደረጃ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ የሚገነቡበት እና የሚስፋፉበት ስልት ስራ ላይ የሚውል ይሆናል፣

### ግብ 2. የሕብረተሰብ ስፖርት ተሳትፎን ማጎልበት፡-

ዞናችን ከክልሉ ካሉት ዞኖች ውስጥ ሰፊና ትልቅ እንደመሆኑ መጠን በርካታ የህረተሰብ ክፍሎች ይኖሩበታል፡፡ እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች የመጠቃት ዕድሉ መቀነስና ማጥፋት ሴክተሩ ከአጋር አካላት ጋር በትብብር ከሚሰራቸው ተግባራት አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰባችንን ጤናማ ፣ ንቁ እና አምራች ዜጎች ለማድረግ በቀጣይ አስር ዓመታት ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ስፖርት እንቅስቃሴ ፕሮግራሞችን እና ኩነቶችን ስራ ላይ በማዋል የነቃ ማህበረሰብ መፍጠር ቁልፍ ጉዳይ ይሆናል፡፡

### ግብ 3. የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞችን ማጠናከር

በሃገር አቀፍ ፣ ክልል አቀፍ እና ዞን አቀፍ የስፖርት ውድድር መድረኮች ዞናችንን የሚወክሉ ተተኪ ስፖርተኞችን በተፈጥሮ ብቃት ላይ በተመሠረተ ሳይንሳዊ የስፖርት ስልጠናዎች ማፍራት እና የስፖርት ሳይንስ ባለሙያዎችን ወጥ በሆነ የስልጠና ስርዓት በማብቃት በቀጣይ አስር ዓመታት በስፖርቱ ዘርፍ አሸናፊና በክልል ደረጃ በሚደረጉ የታዳጊ ወጣቶች ስልጠና የምዘና ውድድር ፣ የመላ አማራ ጨዋታ ፣ የከፍተኛ ሊግና የብሔራዊ ሊግ ውድድሮች ፣ የአማራ ሊግ ውድድሮች ፣ የባህል ስፖርት ውድድሮች እና የሻምፒዮን ሺፕ ውድድሮች ወዘተ ቀጣይነታቸውን ማረጋገጥ ጥራታቸውንና ደረጃቸውን የማሳደግ ተግባራት ትኩረት የሚሰጣቸው ሲሆን በውድድሮቹም የአንደኛ ደረጃን ማግኘት ትኩረት የሚሠጠው ጉዳይ ይሆናል፣

### ግብ 4. የግል ዘርፉን ተሳትፎ ማጎልበት

ስፖርትን ቀስ በቀስ ከመንግስት ድጎማ ለማላቀቅ በሚደረገው ጥረት ጉልህ ሚና ሊጫወት የሚችለውን የግሉን ዘርፍ በስፋት ለማሳተፍ የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎችና ስትራቴጂዎች ተቀርፀው ተግባር ላይ የሚውሉ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ዘርፍ እንደ ዞን የሚገነቡ ሆቴሎችና የሚገነቡ ፋብሪካዎች ውስጥ የመዋኛ ገንዳ እና የሜዳ ቴንስ እንዲሁም ሌሎች

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲኖራቸው በማድግ የግሉን ዘርፍ እንደ አንድ አጋዥ መሳሪያ እንጠቀምበታለን፡፡

ግብ 5. ስፖርትን ለማህበራዊ ልማትና ለሀገር ብልፅግና ማዋል

ስፖርትን ለልማት ለማዋል የሚያስችል አደረጃጀትና ስርዓት በመፍጠር ፣ ስፖርትን በዘላቂነት ችግሮችን በመፍታት ስፖርት ለማህበራዊ ልማትና ለአገር ብልጽግና ፣ ህዝቦችን ለማቀራረብ ፣ ለገጽታ ግንባታ እና ለቱሪዝም ዕድገት ፣ እንዲሁም ከአጎራባች ዞን ፣ ክልል እና ሃገር ህዝቦች ጋር አንድነትን ለማምጣት መሳሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል፡፡

## 12. መሰረተ ልማት ዘርፍ

### 12.1. መንገድ

ዓላማ 1፡ የመንገድ መሠረተ ልማት ፍትሃዊና ተደራሽነትን ማድረግ፤

ግቦች፤

- የዞኑንን አጠቃላይ የመንገድ ሽፋን አሁን ካለበት ከ3694.03 ኪ.ሜ በ2022 ወደ 4694.03 ኪ.ሜ ማሳደግ፤
- እስከ 2022 ዓም ድረስ 147.1 ኪሎ ሜትር የነባር መንገዶች ደረጃ ማሻሻል፤
- እስከ 2022 ዓም ድረስ 500 ኪ/ሜ የዩራፕ መንገድ መልሶ ግንባታ ማካሄድ
- በመንገድ ተደራሽነት ከቀበሌ ቀበሌ፤ከወረዳና ከዋና መንገድ ማገናኘት የቀበሌ ሽፋን አሁን ካለበት 433 በ2022 ዓ/ም 524 ማድረስ
- የመደበኛ እና የወቅታዊ ጥገና ሽፋን አሁን ከነበረው 354.452 ኪ.ሜ በ2022 ወደ 506.11 ኪ.ሜ ማሳደግ፤
- በዩራፕ መደበኛና ወቅታዊ ጥገና ሽፋን አሁን ካለበት 552 ኪ/ሜ በ2022 ዓም ወደ 7000 ኪ/ሜ ማሳደግ
- የዞኑ ጠጠር መንገድ ግንባታ አሁን ካለበት 34.8 ኪ.ሜ በ2022 ዓ/ም ወደ 540.8 ኪ.ሜ ማድረስ ፤

- የURRAP መንገድ ግንባታ አሁን ካለበት 1966 ኪ.ሜ በ2022 ዓ/ም ወደ 2966 ኪ.ሜ ማድረስ፤
- በዩራፕ ከ2004 እስከ 2009 ዓ/ም የታለፉትን 58 ድልድዮች ሰርቶ ማጠናቀቅና አዲስ 58 ድልድዮችን መገንባት

## 12.2. ዉሃና ኢነርጂ ልማት

**ንጹህ መጠጥ ዉሃ አቅርቦት**

**ግብ .1**

☞ በገጠር በመሪ ዕቅድ ዘመን ስታንዳርድ መሠረት [በ1.0 ኪ/ሜ ርቀት 25 ሊትር በቀን በሰው ለአነስተኛ ተቋማትና በ0.5 ኪ/ሜ ርቀት 25 ሊትር በቀን በሰው በባለመስመር ተቋም] በ2012 ከደረሰበት 64.8% የንጹህ መጠጥ ዉሃ ሽፋን በመነሳት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ሽፋኑን 100% ማድረስና የተጠቃሚውን ቁጥር በ2012 ከተደረሰበት 1735517 ህዝብ ወደ 2811223 ማሳደግ፤

**ዝርዝር ተግባራት**

**1.የአነስተኛ የገጠር የውሀ መገኛ ጥናት ፤ዲዛይን እና ግንባታ**

- 3284 የማህበረሰብ የአነስተኛ የገጠር የውሀ መገኛ ጥናት ፤ዲዛይን እና ግንባታሥራዎችን በወረዳ አቅም መገንባት፡፡
- 1098 እጅ ጉድጓድ፤1459 ምንጭ በቦታው፤664 ምንጭ ከአነስተኛ መስመር ጋር /RPS/፣14 የግለሰብ ገመድ ፓምፕ፤12 የማህበረሰብ ገመድ ፓምፕ፤32 ማስፋፊያ

**2.አርፒኤስ እና አነስተኛ የገጠር ከተሞች የውሃ ተቋማት ግንባታ**

በአጠቃላይ በተለያዩ የበጀት ድጋፍ 48 አርፒኤስ፤ 50 መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ እና 10 ጥልቅ ጉድጓድ የጥናት፤ ድዛይንና ግንባታን በማጠናቀቅ የንጹህ መጠጥ ዉሃ ተጠቃሚ ማድረግ፡፤

**ግብ-2**

በከተማ በመሪ እቅድ ዘመን ስታንዳርድ መሠረት [በ0.25 ኪ.ሜ ርቀት ከ30-80 ሊትር በቀን በሰው እንደየከተማ ምድባቸው] በ2012 ከደረሰበት 65% የንጹህ መጠጥ ዉሃ ሽፋን በመነሳት

በእቅድ ዘመኑ የከተማ ንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን 100% ማድረስና የተጠቃሚዉን ቁጥር በ2012 ከተደረሰበት 247780 ወደ 591874 ማሳደግ፤

**ዝርዝር ተግባራት**

- በክልል ካፒታል በጀት የሚገነቡ 10ነባር ፕሮጀክት (ሳይንት አጂባር፤እዋ እና አሳታዊ፤ ከላላ ጥራንጥር ፤በደዶ ሀይቅ ሀይቅ፣ ጃማ ደጎሎ፤ አጂባር አምባ ማሪያም፤ኩታበር ከተማ፤አምባሰል ማርዬና ውጫሌ)ግንባታማጠናቀቅ፤
- የግንባታ ስራቸዉ ተጠናቆ በመብራት አለማግኘት ችግር ስራ ያልጀመሩ ፕሮጀክቶችን በእቅድ ዘመኑ እንድያገኙ ማድረግ /ደላንታ ወረዳ ወገልጤና ፤ደሴ ዙሪያ ወረዳ ሃራ ወበሎና ጠባሲት፤ ቃሉ ወረዳ ጂዳ፤መቅደላ ወረዳ ማሻ፤ቦረና ወረዳ ደንሳ ከረባ ፤/
- ከ2012 ዓም በፊት እስከ ድዛይን መጠናቀቅ የደረሱ ጥልቅ ጉድጓድ ፕሮጀክቶች ብዛት 11 ናቸዉ። በእቅድ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ወደ ተግባር እንዲገቡ ማድረግ። /አልቡኮ ወረዳ ሰኞ፤ ቃሉ ወረዳ አዳሜ ቱሉ እ ናሃርቡ፤ ለጋምቦ ወረዳ ጢንጫ፤ ከላላ ወረዳ ቲርቲራና ሻፊ፤ መሃል ሳይንት ወረዳ ደንሳ እና ያለጌታ፤ወረኢሉ ወረዳ ሰኞ፤ለገሂዳ ወረዳ ወይን አምባ ከተማና ሲባ/።

**ግብ 3፡-** በሁሉም የዞኑ ወረዳዎችና ከተሞች የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ተደራሽነትን ለማሻሻል አሳታፊ፤ አዋጭ እና ተቀባይነት ያለው 180 የጥናትና ዲዛይን ዶክመንት ሠርቶ ለትግበራ ዝግጁ ማድረግ፤

**ዝርዝርተግባራት**

- 120 የገጠር መጠጥ ዉሃ ፕሮጀክቶች/RPS/ ጥናትና ዲዛይን ዶክመንት ተገምግሞና ተዘጋጅቶ ለትግበራ ዝግጁ ማድረግ፤
- 60 የከተማ መጠጥ ዉሃ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ዶክመንት ተገምግሞና ተዘጋጅቶ ለትግበራ ዝግጁ ማድረግ፤

**ግብ 4፡-** በዕቅድ ዘመኑ የገጠርና የከተማ የንፁህ መጠጥ ውሃ ፍላጎትን ለማሟላት 120-/ጥ/ጉድጓድ 120 መ/ጥ/ጉድጓድ ጥናትና ቁፋሮ ስራ ማከናወን፤

- የ120 ጥልቅ ጉድጓድ ውሃ መገኛ ጥናት ማካሄድ
- የ 120 መለሰተኛ ጥልቅ ጉድጓድ ውሃ ማስቆፈር።

ዝርዝር ተግባራት

- የ120 ጥልቅ ጉድጓድ ውሃ መገኛጥናት ማካሄድና ለትግበራ ዝግጁማድረግ፡፤
- የ120 መለሰተኛ ጥልቅ ጉድጓድ የውሃ መገኛ ጥናት ማካሄድና የጨረታ ሰነድ ማዘጋጀት፡
- የ 120 ጥልቅ ዉሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ፓምፕቴስት ስራ ማጠናቀቅ፤

## የኦፕሬሽንና ጥገና ተቋማት አስተዳደር

**ግብ 1፡- የውሃ ተቋማትን የብልሽት መጠን አሁን ካለበት ከ10.96% ወደ 6.56% መቀነስ፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

- 10,908 የውሃ ተቋማትን ቀላል፣ መካከለኛና ከባድ ጥገና ማካሄድ፣
- ለጥገና 6,119,666 ብር ጥሬ ገንዘብ፤14,623,770 ብር የሚገመት የቁሳቁስ መዋጮ እና 15,269,800 ብር የሚገመት የጉልበት ተሳትፎ በድምሩ 36,013,236 ብር ከተጠቃሚዉ ህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲኖር ማስቻል፤

**ግብ 3፡- በከተማ ያለዉን የውሃ ብክነትን አሁን ካለበት 7.7 % ወደ 4.77% በመቀነስ ንጽህናውን የጠበቀ የመጠጥውሃ ለህብረተሰቡ ማዳረስ፤**

**ዝርዝር ተግባራት**

- በ 15ከተሞች የውሃ ብክነት መንስኤዎችን በመለየት መፍትሄ መስጠት፤
- በ 20 የዉሃ ተቋማት በስታንድረዱ መሰረት ተከልለው እንዲታጠሩ እና የይዞታ ደብተር እንዲኖራቸዉ ማድረግ፤
- በ 42 የዉሀ አገልግሎቶች የደንበኞች ፎረም ማቋቋም

**ግብ 4፡- የዉሀ ጥራት ቁጥጥር ስራዎችን በማከናወን ንጽህናውን የጠበቀ የመጠጥ ውሃ ለህብረተሰቡ ማዳረስ፤**

**ዝርዝር ተግባራት**

- 127,000 ተቋማት ላይ ድግግሞሽን ጨምሮ የሳኒቴሽን ቅኝትናማከም ስራ ማድረግ

ግብ 5፡- የከተማ ዉሃ አገልግሎቶች ተገቢዉን የዉሃ ታሪፍ እንዲያወጡ ድጋፍ በማድረግ 49,776,973 ሚሊዮን ብር የኢንቨስትመንት ወጪ እንዲመልሱ ማድረግ፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

- 20የዉሃ ተቋማት ተግቢውን ታሪፍ እንዲያወጡ ድጋፍ ማድረግ፤
- 9 የከተማ ውሃ አገልግሎቶችን የቢዝነስ ፕላን ዝግጅት ላይ የሞያ ድጋፍ ማድረግ፤
- 23 ነባር ውሃ አገልግሎቶችን ደረጃ ማሳደግ፤

ግብ 6፡- ዘመናዊ የመስኖ አውታር ለመስራት ከታስበው 2000 ሄ/ር መሬት የሚያለሙ አነሰተኛና መካከለኛ የመስኖ ተቋሞችን ለይቶ

ግብ 7 ፡- 4000 ሄ/ር መሬት የሚያለሙ አነስተኛና መካከለኛ የመስኖ ተቋሞችን ግንባታ በጥራትና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መንገድ በማጠናቀቅ በዘመናዊ የመስኖ ተቋማት የሚለማውን መሬት ስፋት ማሳደግ፤

**ዝርዝርተግባራት**

- ግንባታቸው የተጀመረ 9 ነባር የመስኖ ፕሮጀክት ማጠናቀቅ
- ከ20 አዳዲስ የመስኖ ፕሮጀክት ግንባታ 15 ማጠናቀቅ፤ቀሪዎቹን በአማካይ 60% ማድረስ

ግብ 8፡- የተሻሻሉ ኃይል ቆጣቢ ምድጃዎች ስርጭት ሽፋን ከ56 ወደ100% ማድረስ፣

ዝርዝር ተግባራት

- 390,500 የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎች ምርትና ስርጭት ማከናወን (ምርጥ 215285፣ጎንዜ 58950፣ፈጠነች(በሞልድ የተሰራች) 39000፣ላቀች(ላይነር) 49130፣ምርጫ (ብርኬት) 8070፣ሮኬት ምድጃ(ትክክል) 19565)

ግብ 9፡- በቤተሰብ ደረጃ የባዮጋዝ ማመንጫ ፕላንቶችን ተጠቃሚነት ቁጥር 1750 ወደ 7400 ማድረስ እንዲሁም ፍላጎት ያላቸውን ተቋማትና የንግድ ድርጅቶች የባዮጋዝ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ቁጥር ወደ 15 ማድረስ፣

**ዝርዝር ተግባራት**

- 5665 የቤተሰብ ባዮ.ጋዝ ማመንጫ ፕላንቶችን ማስገንባት
- ለ15 ተቋማትና የንግድ ድርጅቶች የባዮ.ጋዝ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ማድረግ

**ግብ 10፡- በገጠር መንደሮችና ከተሞች ከተለያዩ አማራጭ ኢነርጂ ሀይል በማቅረብ (ከፀሃይሃይል) 215950 አባዉራ/እማዉራና 40 ተቋማትን ተጠቃሚ ማድረግ፤**

**ዝርዝርተግባራት**

- 97645 (Solar home system) ለተጠቃሚ አባዉራ/እማዉራ ማቅረብ እና መትከል፣
- 135,950 የሶላር ማሾዎች (Solar Lanterns) ለተጠቃሚ አባዉራ/እማዉራ ማቅረብ እና መትከል፤

**ግብ 10፤ በገጠር መንደሮችና ከተሞች 56200 የኤሌክትሪክ ምጣድና ምድጃዎች ምርትና ስርጭት በማቅረብ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ፤**

**ዝርዝርተግባራት**

- 35000 የኤሌክትሪክ ምድጃዎች ምርት ማቅረብ እና ማሰራጨት፣
- 21,200 የኤሌክትሪክ ምጣድ ምርት በማቅረብ ለተጠቃሚ አባዉራ/እማዉራ ማሰራጨት፤

## 12.3. ከተማና መሰረተ ልማት

**ግብ 1. የክትመት ምጣኔን ማሳደግ፣**

- የገጠር የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ህጋዊ የከተማነት ዕውቅና መስጠት ከ55 ወደ 85 ማድረስ
- ከታዳጊ ወደ ንዑስ ማዘጋጃ የተሸጋገሩ ከተሞች ከ19 ወደ 39 ማሳደግ
- ከመሪ ማዘጋጃ ቤት ወደ አነስተኛ ከተማ አስተዳደር የተሸጋገሩ ከ9 ወደ 19 ማድረስ
- ከአነስተኛ ከተማ ወደ መካከለኛ ከተማ አስተዳደርነት የተሸጋገሩ ከ1 ወደ 10 ማድረስ

**ግብ 2. የከተሞችን የገቢ አቅም ማሳደግ**

- የሚሰበሰበውን ገቢ ከ 113ሚሊዮን ወደ 228 ሚሊዮን ማሳደግ
- በጉድለት የተገኘ ገቢ ማስመለስ ምጣኔን ከ25% ወደ 100% ማድረስ

**ግብ 3. የህብረተሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ**

- አሁን ካለበት 42% የህብረተሰብ ተሳትፎ ወደ 60 ማሳደግ

**ግብ 4. የመሬት ሃብት አጠቃቀምን ውጤታማነት ማሻሻል፣**

- ሁሉም ከተሞች በግልፅ የሚታወቅ የአስተዳደር ወሰን እንዲኖራቸው አሁን ካለንበት 99 ወደ 129 ማድረስ
- መሰረተ ልማት ተሟልቶለት ለምደባ የተዘጋጀ መሬት ከ205.8ሄ/ር ወደ 411.6ሄ/ር ማድረስ
- መሰረተ ልማት ተሟልቶለት ለጨረታ የተዘጋጀ መሬት መጠን ከ51.5ሄ/ር ወደ 103 ማድረስ
- ቦታ ያገኙ የቤት ስራ ማህበራት ብዛት ከ846 ወደ 1816 ማድረስ
- ቦታ ወስደው ጥቅም ላይ ባለመዋሉ የተነጠቀ መሬት 41.97ሄ/ር ወደ 83.94 ማድረስ

**ግብ 5. ዘመናዊና ውጤታማ የከተማ መሬት ይዞታ አስተዳደር ሥርዓት ማጎልበት፣**

- ለግል የተሟላ ሰነድ የሌላቸውና ሰነድ አልባ ባለይዞታዎች ሰነድ መስጠት ከ94.7% ወደ 100 ማድረስ
- በከተሞች ፕላን ወሰን ውስጥ እየተስፋፋ የሚገኘውን ህገ ወጥ ይዞታ ስርዓት በማስያዝ የመሬት ወረራን 100% መከላከል

**ግብ 6. የከተሞች ፕላን አፈፃፀምን ማሻሻል**

- ፕላን የተዘጋጀላቸው ከተሞች ከ99 ወደ 194 ማድረስ
- በከተሞች የፕላን መንገድ ከሶስተኛ ወገን ነጻ እንዲሆን እና የመንገድ ወሰኖችን ማስከበር ከ804ኪ.ሜ ወደ 1608 ኪ. ሜ ማድረስ

**ግብ 7. የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓትን ማሻሻል**

- በከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አጓጓዝ ሽፋን 80 በመቶ ማድረስ
- የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ሳይት /ቦታ/በስታንዳርድ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ያዘጋጁ ከተሞች ከ 1 ወደ 9 ማሳደግ
- የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአትን ለማሻሻል የተዘጋጁ ህጎች፣ስታንዳርዶችና የአሰራር ማኑዋሎች በአግባቡ የተገበሩ ከተሞች ከ75 ወደ 99 ማድረስ
- በዓይነት የተለየና የተጓጓዘ ደረቅ ቆሻሻ ከ108696ሜ3 ወደ 217,657 ማድረስ

**ግብ 8. በከተሞች አረንጓዴ ልማትን ማስፋፋት**

- የአረንጓዴ ቦታዎች በበቂ ሁኔታ በፕላኑ የተመላከተባቸው ከተሞች ከ54 ወደ 99 ማድረስ
- በፕላኑ መሰረት ለአረንጓዴ ቦታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያዘጋጁ ከተሞች ከ73 ወደ 99 ማድረስ
- አዲስና ነባር ችግኝ ጣቢያዎች በስታንዳርድና ዲዛይን መሰረት ያለሙ ከተሞች ከ27 ወደ 54 ማድረስ
- የመንገድ ዳርቻ፣ አካፋይና አደባባዮችን በዲዛይንና በስታንዳርዱ መሰረት ያለሙ ከተሞች ከ5 ወደ 21 ከፍ ማድረግ
- በከተሞች በስታንዳርድና ዲዛይን መሰረት እንዲለሙ የተደረጉ አዲስና ነባር ፓርኮች ከ5 ወደ 15 ማድረስ

**ግብ 9. የመኖሪያ ቤት ልማትን ማሻሻል**

- **በማህበራት የተገነቡ ቤቶች ከ 6851 ወደ 13,701 ማድረስ**

**ግብ 10. የከተሞችን መሰረተ ልማት ማስፋፋት**

- **የመሰረተ ልማት ሃብት ቆጠራና መረጃ አያያዝ 100% ማከናወን**
- **ኔጠኛ መንገድ ግንባታ ከ14ኪ.ሜ ወደ 28 ኪ.ሜ ማሳደግ**
- **ጠጠር መንገድ ግንባታ ከ310ኪ.ሜ ወደ 620ኪሜ ማሳደግ**
- **የጎርፍ መውረጃ ዘመናዊ ካናል ግንባታ ከ65ኪ.ሜ ወደ 130ኪ.ሜ ማሳደግ**
- **የሸድ ግንባታዎች ከ903 ወደ 1803 ማሳደግ**
- **የቄራ ግንባታ ከ6 ወደ 43 ማሳደግ**

# 13. መልካም አስተዳደር ዘርፍ

## 13.1. ሲቪል ሰርቪስ

**ግብ 1፡- የመንግስት ተቋማትን ውጤታማነት በአደረጃጀትና በአሰራር ማጎልበት፤**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- የመንግስት ተቋማት የውስጥ አደረጃጀት ቀልጣፋና በውጤት ላይ ያተኮረ፣ ለተገልጋዩ ተደራሽ የሆነና የልማት ስራውን የሚያፋጥን እንዲሆን የሚያስችሉ ሥራዎችን ማከናወን፣

- ተቋማት በየጊዜው የሚያቀርቡትን የአደረጃጀት ማሻሻያ ጥያቄ በጥናት ላይ ተመስርቶ ውሳኔ ሲሰጥ ተግባራዊ ማድረግ፣
- በሲቪል ሰርቪስ ተቋማት ከምደባ ሥርዓት ወደ ነጥብ የስራ ምዘና ዘዴ የተደረገውን ለውጥ መሠረት በማድረግ የተዘጋጁትን መመሪያዎች መተግበር፣
- አዳዲስ የህግ ማዕቀፎች እዲዘጋጁ ፣ ነባሮችን የማሻሻልና በአንድ ሰነድ የማደራጀት ሥራዎች እንዲጠናቀቁ ግብአት መስጠት፣

**ግብ 2፡- የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ሥርዓቱን ማሻሻል**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- በሲቪል ሰርቪሱ አሠራር ዙሪያ በሚታዩ ክፍተቶች ላይ በመመስረት ሥልጠና መስጠት፣
- ወጣት ምሩቃን በትምህርት ዝግጅታቸው፣ በሥነ-ምግባራቸውና በብቃታቸው እየተመለመሉ ወደ ሲቪል ሰርቪሱ እንዲቀላቀሉ ማድረግ፣
- ዞናዊ የሰው ሃብት ልማት ሥራዎች በዕቅድ እንዲመሩ ማድረግ፣

**ግብ 3፡- የሠራተኞችን ዕቅድ አፈፃፀም ምዘና ሥርዓት ማሻሻል**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- የሠራተኞች ሥራ አፈፃፀም ምዘና ተዘጋጅቶ በወረደ ስታንዳርድ መሰረት ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣
- ተቋማት የሠራተኞችን ስራ አፈጻጸም ሚዛናዊና ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ እንዲተገብሩ መከታተል፣ መደገፍ፣
- በምዘና ሥርዓቱ ላይ ጥናት ማካሄድ፣
- የሥራ አፈፃፀም ምዘና ትግበራ በቀጣይነት የመንግስት የአፈጻጸም አመራር ማዕቀፍ እንዲሆን ግብዓት መስጠት መስራት፣

**ግብ 4፡- የተገልጋዮችን እርካታ ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- የመንግስት ተቋማት አሰራርና ውሳኔ አሰጣጥ ለዜጎች ግልጽ እንዲሆንና ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ ማድረግ፤
- በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ለሚነሱ ቅሬታዎች ወቅታዊና ፍትሃዊ ውሳኔ መስጠት፣
- በአመለካከት፣ በዕውቀት፣ በክህሎት፣ በአሰራርና በአደረጃጀት እንዲሁም በግብአት አቅርቦት ዙሪያ ያሉ ማነቆዎችን እየፈቱ መሄድ፣
- የዜጎች ቻርተርን በተሟላ ሁኔታ በመተግበር በተቋሙ የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር የበለጠ እንዲጎለብት የሚያስችሉ ስራዎችን ማጠናከር፣

**ግብ 3፡- የተግባቦት ሥርዓቱን ማሳደግ፤**

**የሚከናወኑ ተግባራት፤**

- ፈፃሚዎች፣ ባለድርሻ እና የህዝብ ክንፍ አካላት በየዓመቱ በተቋማዊ ዕቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም ግምገማ ወቅት ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- የተቋሙ አመራሮችና ሰራተኞች ለውጡን ተቀብለው የተግባቦት ሥራዎችን እንዲተገብሩና እንዲያስተዋውቁ ማድረግ፣

**ግብ 4፡- የለውጥ መሣሪያዎችን ውጤታማነት ማሳደግ**

- በለውጥ ሥራዎች ጽንሰ-ሐሳብና አተገባበር ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር፣
- የካይዘን ፍልስፍና፣ የዜጎች ቻርተር፣ ተሞክሮ መቀመር ማስፋትና ሌሎች የለውጥ መሣሪያዎችን መተግበር፣

**ግብ 5. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ**

- ወረቀት አልባ ግንኙነትን ማጠናከርና በተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት (Integrated Civil Service Management Information System) ዙሪያ የተጀመሩ ተግባራትን ማስቀጠል፤

## 13.2. ዐቃቤ ህግ

**ግብ 1፡- ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሠራርን ማሣደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- በዞንና በወረዳ ያለውን የፍትህ ስርዓት አስተባባሪ ኮሚቴ፣ የፍትህና የፖሊስ የጋራ ኮሚቴ፣ የኦዲት ግኝቶች ስትሪንግ ኮሚቴ፣ የሰብዓዊ መብትየድርጊት መርሀ ግብርኮሚቴ፣ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ተከላካይ ግብረ ኃይል እና ሌሎች የክላስተር አደረጃጀቶች

ተልዕኳቸውን ማሣካት በሚችሉበት ደረጃ ላይ መሆናቸውን በአመት 4 ጊዜ ክትትል ማድረግ፤

**ግብ 2፡- የሙስና እና የብልሹ አሰራር አመለካከትና ተግባራትን ለመታገል ግልፅነትና ተጠያቂነትን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- የሙስና እና የብልሹ አሰራር ምንነት ይዘትና አደጋዎች በተመለከተ ለመምሪያው ሰራተኞች በአመት 1 ጊዜ የግንዛቤ ማሣደጊያ ስልጠና መስጠት፤
- የህግና ፍትህ ኢንስፔክሽን /Legal Auditing/ ስራበአመት 4 ጊዜ በማካሄድ በግኙቱ መሠረት ስህተቶችን ማረም፤

**ግብ 3፡- በፍትህ አስተዳደሩ ውስጥ የህብረተሰቡን የተደራጀ ተሣትፎና ባለቤትነት ማሣደግ፤**

**የሚከናወኑዝርዝር ተግባራት**

- ህዝቡ መብቱንና ግዴታውን አውቆ ህግ በማክብርና ማስከበር ወንጀልን በመከላከል በኩል የዜግነት ግዴታውን እንዲወጣ በበጀት ዓመቱ ከተሠጠው የንቃተ ህግ ትምህርት ቁጥር 512,401 መሠረት በማድረግ  በ 10 አመቱ 100% የሚሆነውን በዞን 39,596 በወረዳዎች 7,902,625 በድምሩ 7,942,221  በድግግሞሽ የህብረተሰብ ክፍል የንቃተ ህግ ትምህርት መስጠት፤
- ህዝብ በዐቃቤ ህግ መ/ቤትአገልግሎት ያለውን እርካታና አመኔታ ቢያንስ በዓመት1 ጊዜ የእርካታ ደረጃ ጥናት ማካሄድ፤

**ግብ 4፡- በወንጀል የቀጥታ ክስ መዝገቦች የዓ/ህግ ተከራክሮ የማስቀጣት አቅም ከ 93.05 % ወደ 97% ማሣደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝርተግባራት**

- ዐቃብያነ ህግ ወደ ችሎት ከመግባታቸው  ከአንድ ቀን በፊት መዝገብ ደርሷቸውአጥንተው ወደ ችሎት መግባት95%፣
- እጅ ከፍንጅ ወንጀሎችን በተፋጠነ ፍርድ አሰጣጥ ስርዓት /RTD/ እንዲቀርብ በማድረግ በጊዜ ማግኘት /የሚጠፉን/ ማስረጃ መቀነስ 95%፡፡
- በወንጀል ከተጠረጠሩ ሰዎች በምርመራ ምክንያት በኤግዚቢትነት የተያዙ ንብረቶች አፋጣኝ ውሳኔ 95% ማሰጠት፤
- በሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን፣ በአካል ጉደተኞችና ሌሎች ልዩ ትኩረት በሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች  የወንጀል መዝገባት የማስቀጣት  ምጣኔን 100% ማሳደግ፤

**ግብ 5፡-የዐቃቤ ህግ ይግባኝ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነት ከ 85.33% ወደ 95% ማሣደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝርተግባራት**

- በይግባኝ የሚቀርቡ ውስብስብ እና ከባድ የወንጀል ጉዳዮችን ቅሬታ በጋራ በፓናል በማየት አሣማኝ የህግና የፍሬ ነገር ጉዳዮች በማንሣት የተሣሣተ የስር ፍ/ቤት ውሣኔን 95% ማስለወጥ፡፡
- በሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ዓ/ህግ ይግባኝ የጠየቀባቸው መዝገቦች አፈጻጸም ውጤታማነትን 95% ማሳደግ፤

**ግብ-6 የወንጀል አቤቱታ አቀባበል ውሣኔ አሰጣጥ እና የአቤቱታ ተፈፃሚነት 91.36 % ወደ 98%ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝርተግባራት**

- በወንጀሎች ቅጣት የሚያስከትሉ ድርጊቶች የተፈፀሙ ለመሆኑ በቂ ጥርጣሬ በመኖሩ ወይም ጥቆማ በቀረበ ጊዜ ተገቢው ምርመራ ተጣርቶና በበቂ ማስረጃ ተደግፎ እንዲቀርብ ማድረግ፤
- የወንጀል አቤቱታዎችን እንደ አግባብነቱ በተዘጋጀው የአቤቱታ መቀበያ ፎርማት መሠረት በስልክ፣ በአካል ወይም በፋክስ መዝግቦ መቀበል፣
- የቀረበው አቤቱታ ወዲያውኑ በጽ/መ/አስ/ር ባለሙያ ተመዝግቦና ፋይል ተከፍቶለት ውሣኔ የመስጠት ስልጣን ለአለው ባለሙያ መቅረቡን ማረጋገጥ፣

**ግብ 8፡- በፍትሐብሄር ጉዳዮች የቅድመ መከላከል ስራን በማጠናከር የመንግስትና የህዝብን ሀብትና ንብረት ከብክነት መከላከል በመዝገብ 70% በገንዘብ 69% የነበረውን ወደ 95% ማሳደግ፤**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- የህግ ባለሙያ ከሌላቸው ተቋማት ውጭ ሁሉንም የመንግስት ተቋማት እንደ ጉዳያቸው ፍሰት ደረጃ በህግ ጉዳዮች ድጋፍ የሚያደርግላቸው ዐቃቤ ህግ መድቦ 95% መከታተል፡፡
- በተገልጋዩች የሚቀርብን የረቂቅ ውል ምርመራ እና የውል ሰነድ ዝግጅት በ5 ቀን ውስጥ በማዘጋጀት ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት፣
- የመንግስት መ/ቤቶችንና ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የልማት ድርጅቶችን የህግ ምክርና ድጋፍን ጥያቄዎችን ተቀብሎ በጥናት ላይ ተመስርቶ ምላሽ በመስጠት 100% ማከናዎን፣

- አገልግሎት ፈላጊዎች የሚያቀርቧቸውን ውሎች በአግባቡ መርምሮ ህጋዊ መሠረት እንዲይዙ በማድረግ በውል አያያዝ ክፍተት ምክንያት የሚደርሱ ጉዳቶችን 100% መቀነስ፣
- ለሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን እና በአካል ጉዳተኞችን በውል ዝግጅትና የህግ ምክር 100% ድጋፍ መስጠት፤

**ግብ 9፡- በፍትሐብሄር ከምንይዛቸው ጉዳዮች ውስጥ በድርድር መጨረስ በመዝገብ እና በገንዘብ 30% ማሳደግ፤**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- በየደረጃው ያሉት የመንግስት ተቋማት ኃላፊዎችና ጉዳዩ የሚመለታቸው ተወካዮች ጉዳዮችን በድርድር መጨረስ አስፈላጊነትና ፋይዳን ማስገንዘብ፣
- ከሣሽም ሆነ ተከሣሽ በሆንባቸው ጉዳዮች አግባብ ያለው ማስረጃ መሠብሰቡን ከአረጋገጥን በኂላ ክስ ወይም መልስ ከመቅረቡ በፊት ሁሉንም ጉዳዮች በድርድር ለመጨረስ ጥረት ማድረግ፣
- በድርድር ሒደት የተገኙ መልካም ውጤቶችን እና እንቅፋቶች በየዓመቱ የዳሰሣ ጥናት/ግምገማ ሰነድ በማዘጋጀት ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ማካሄድ፡፡
- ለሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን እና በአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ 30% በድርድር መጨረስ፤
- ለሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን እና በአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በድርድር ያለቁትን 90% ገቢ ማድረግ፤

**ግብ 10፡- በፍትሐብሄር ጉዳዮች በቀጥታ ክስና መልስ የዓ/ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ አቅም በመዝገብ 85.9% በገንዘብ 85.24 %ወደ 92% ማሣደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- ክስ በመሠረትንባቸው የፍትሐብሄር ጉዳዮች መዛግብት ከሣምንት በፊት ለችሎት ዓ/ህግ ደርሶት በቂ ዝግጅት በማድረግ 95% ውጤታማ የችሎት ክርክር ማድረግ፣
- ዐቃቤ ህግ ጉዳያቸውን የሚይዝላቸው አካላት በሚከሰሱበት ጊዜ መብታቸውን በሚያስጠብቅ መልኩ የችሎት ክትትልና ክርክር በማድረግ በነፃ እንዲሰናበቱ ማድረግ፣
- በሁሉም የችሎት መዛግብት በክርክር የተነሱ ጭብጦች ከፍ/ቤቱ የተሰጡ ውሣኔዎችና ትዕዛዞች በአግባቡ መመዝገባቸውን 95% ማድረስ፣

- አላግባብ በተሸነፍንባቸው ጉዳዮች የይግባኝ መጠየቂያ ጊዜው ከማለፉ በፊት የይግባኝ ቅሬታ በማቅረብ እና አግባብ ያለው መቃወሚያ በማዘጋጀት በመከራከር የመንግስትን እና የህዝብን መብትና ጥቅም ማስከበር፣

**ግብ 11፡-ይግባኝ መዝገቦች የዓቃቤ ህግ የክርክር ውጤታማነት በመዝገብ 54.48% በገንዘብ 60.1 % ወደ 70% ማሣደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ በተሰጣቸው ጉዳዮች በወቅቱ ይግባኝ በመጠየቅ ውሣኔው እንዲታረም ማድረግ፣
- በይግባኝ የሚቀርቡ ቅሬታዎች በጋራ በፓናል በማየት አሣማኝ የህግና የፍሬ ነገር ጉዳዮች በማንሣት የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ማስለወጥ፡፡
- ዐቃብያነ ህግ ወደ ችሎት ከመግባታቸው ከ5 ቀን በፊት መዝገብ ደርሷቸውአጥንተው ወደ ችሎት መግባት 95%፣

**ግብ 12፡- ይግባኝ መልስመዝገቦች የዓቃቤ ህግ የክርክር ውጤታማነት በመዝገብ 70.69 በገንዘብ 69 %ወደ 85% ማድረስ፣**

**የሚከናወኑዝርዝር ተግባራት**

- በይግባኝ መልሶችን በጋራ በፓናል በማየት አሣማኝ የህግና የፍሬ ነገር ጉዳዮች በማንሣት የስር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፀና ማድረግ፡፡
- በተከሣሽ በሚቀርቡ የይግባኝ መዝገቦች የቀረበውን መቃወሚያ ከስርዓ/ህግ ክስ እና የፍ/ቤት ውሣኔ እንዲሁም አግባብ ካለው ህግና ማስረጃ ጋር በማገናዘብ ተገቢውን መልስ ማቅረብ፣

**ግብ 13፡- ክስ ባቀረብንባቸው ጉዳዮች አስቀድሞ ንብረት ፈልጎ ማሳገድአሁን ካለበት በመዝገብ 49 % በገንዘብ 26 % ወደ በመዝገብ 85 % በገንዘብ 50% ማድረስ**

**የሚከናወኑዝርዝር ተግባራት**

- ክሱ እንደቀረበ የተከሳሽን ስም አደራሻ በመለየት ለክሱ ማስፈፀሚያ የሚያገለግል ንብረት አፈላልጎ በፍርድ ቤት ማሳገድ፤
- የሚታገደው ንብረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም ሌላ እስከ ፍርድ ማስፈፀሚያ ቀን ድረስ መቆየት የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ
- የተከሳሽ ንብረት ከታገደ በኋላ አልፎ አልፎ ድንገተኛ ማጣራት በማድረግ እግዱ መከበሩን ማረጋገጥና የፍ/ቤትን ትዕዛዝ በማያከብሩ አካላት ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፤

- ማስረጃ ከማሰባሰብ ጐን ለጐን ከጉዳዩ ጋር ተመጣጣኝ ንብረት በማፈላለግ የፍርድ አፈፃፀም ግብዓት እንዲሆን ማድረግ፣
- በሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፤ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ላይ ሃብትና ገንዘብን በመዝገብ 85% በገንዘብ 50% ማሳገድ፤

**ግብ 14፡-ጠበቆች በአመለካከት በክህሎት እና ሥነ-ምግባር ዳብረው ለፍትህ ስርዓትአጋዥ እንዲሆኑ ማድረግ**

**የሚከናወኑዝርዝር ተግባራት**

- የጥብቅና ፈቃድ በደንቡ መሠረት በየዓመቱ መታደሱን 100% ማረጋገጥ፣
- ከጠበቆች ማህበር ጋር በመቀናጀት የጠበቆች ክህሎት እና ሙያዊ ስነ-ምግባር የሚገነባበት ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ፡፡
- ደንበኞች በጠበቆች ላይ የሚያቀርቡትን ቅሬታ በአግባቡ አጣርቶ ህጋዊ ውሣኔ በመስጠት ለሚመለከተው በማስተላለፍ የተጠያቂነት አሠራርን ማረጋገጥ፣

**ግብ 15፡- በህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከልና ምላሽ መስጠት ላይ የሚሰሩ አደረጃቶችን ማጠናከር፣**

**የሚከናወኑዝርዝር ተግባራት**

- በህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ለተጠቁ የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ከሚሰጡ ተቋማት ጋር በመተባበር መስራት፤
- ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ስደተኞችን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገርን አስመልክቶ ችግር ያለባቸውን ቦታዎች እና ምክንያቶችን በአመት 1 ጊዜ ጥናት ማካሄድ፤

**ግብ 3፡-በፍርድም ሆነ በጊዜ ቀጠሮ በማረሚያ ቤቶች የሚገኙና በፖሊስ ጣቢያዎች በህግ ቁጥጥር ስር ውለው የሚገኙ ሰዎች ሰብዓዊ መብቶቻቸው በአግባቡ መከበሩንማረጋገጥ፣**

**የሚከናወኑዝርዝር ተግባራት**

- በማረሚያቤት፣በማረፊያቤትና በጊዜያዊ የእስረኞች መጠለያ የሚገኙ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ከኤችአይቪ ኤድስ ጋር የሚኖሩ እንዲሁም ከእናቶቻቸው ጋር የገቡ ህፃናት በህግ የተጠበቁላቸው መብቶች ሳይጓደሉ መከበራቸውን ማረጋገጥ፤

- ፖሊስ ጣቢያ ወይም ማረፊያ ቤቶችን በዞን በወር 2 ጊዜ በወረዳ በሳምንት 5 ቀን በመጐብኘት በህግ ጥላ ስር የዋሉ ሰዎች በህግ የተፈቀደላቸው መብቶች መከበሩን ማረጋገጥ፤

## 13.3.ህዝብ ቅሬታ

**ዓላማ**.1 አስተዳደራዊ ፍትህ ፈልገዉ ለሚቀርቡ አቤቱታዎችን ፈጣንና ፍትሃዊ ውሳኔ እንዲሰጥ፤

ግብ.1.የቀረቡ ቅሬታዎችን እና አቤቱታዎችን ተቀብሎ ፍትሃዊ ዉሳኔ በመስጠት የተገልጋዮችን እርካታ 85.68 % ወደ 95.68 % ማሻሻል፤

**ዝርዝር ተግባራት**

ተግባር .1. ከተገልጋዮች የሚቀረቡ ቅሬታዎችን በመቀበል መፈታትና በስታንዳርዱ መሰረት ፈጣን ዉሳኔ መስጠት፤

- በተለያዩ መንገዶች ለሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች የሚሰጡ ውሳኔዎችን ተቀብሎ ተፈፃሚ እንዲሆኑ መከታተል፤
- ደረጃዉን ጠብቀዉ በአካል የሚመጡ ባለጉዳዮችን ማመልከቻ መፃፍ ወይም ማስፃፍሳያስፈልጋቸው 100% በተዘጋጅው የቅሬታ/ አቤቱታ መቀበያ ቅጽ ተቀብሎ ማስተናገድ
- ደረጃዉን ጠብቀዉ እና የቡድን ለቀረቡ አቤቱታዎች 100 % የጹሁፍ ዉሳኔ መስጠት ፤

**ተግባር.2 በይድረስ ለመንግስት (Hello Government) አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ፤**

- የይደረስ ለመንግስት የስልክ አገልግሎት ተግባራዊ በማድረግአቤቱታዎች መልስ እንያገኙ ማድረግ፤
- በአጭር የጽሁፍ መልዕክት (SMS) በነፃ የሚያቀርብበት፤ ምላሹንም እዚያው ባለበት ሆኖ የሚያገኝበት ይድረስ ለመንግስት /HELLO GOVERNMENT /C2G/ ስርዓት በመዘርጋት የቅሬታ አቀራረብ ስርዓቱን ማሳደግ፤

**ተግባር 3. የሚሰጡ ዉሳኔዎችን ለዉሳኔ ጥራት በእቅድ መምራት፤**

- የመስክ ምርመራ የሚያስፈልጋቸዉን አቤቱታዎችን በመስክ እቅድ አዘጋጅቶ በጋራ ገምግሞ መስራት
- የመስክ ምርመራ እቅድ የተዘጋጀላቸዉ የመስክ ምርመራ በማድረግ የመስክ መልስ የምርመራ ሪፖርት አዘጋጅቶ እየገገመገሙ እንዲሰራ ማስቻል፤

ግብ.2 ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸዉን ለይቶ የመደገፍ ተግባር ተደራሽ ማሳደግ ፤

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1. ልዩ ድጋፍ ለሚፈልጉ የህብረተሰብ ክፍሎች በአገልግሎት ሂደት ቅድሚያ በመስጠት ማስተናገድ፤**

- በአካል ጉዳተኞች፤ በህፃናት፤ በሴቶች፤ በአረጋዊያን፣ በጎዳ ተዳዳሪዎች፣ ከኤች አይቪ ቫይረስ ጋር በሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ለይቶ ቅድሚያ ሰጥቶ 100% ተገቢዉን ድጋፍ ማድረግ፤

**ተግባር 2. ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸዉን በየዓመታቱ ቀድሞ በጥናት ለይቶ አስተዳደራዊ በደል የሚየደረሰባቸዉን በእቅድ ይዞ ተከታትሎ ከሚመለከተዉ ጋር ተቀናጅቶ በትኩረት በመያዝ እንዲፈታላቸዉ ማድረግ ::**

- በደንቡ መሰረት የማናያቸው ቢሆኑም እንኳ ሴቶች፤ ህፃናት፤ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ላይ የደረሱ አስተዳደራዊ በደሎችን ከቀረቡ 100% አጣርቶ መፍትሄ እንዲያገኙ ለሚመለከተው አካል አስፈላጊውን የውሳኔ የድጋፍ/የመፍትሄ/ አስተያየት በማቅረብ መስራት፤

**ዓለማ 2. የአስተዳደራዊ በደል ክስተቶችንመከላከልና ተጠያቂነትን ማጠናከር፤**

**ተግባር.3. ደንበኞች በአገልግሎት አሰጡጡ ላይ በመዝገብና በሳጥን የተሰጡ አውንታዊ ወይም አሉታዊ አስተያቶችን ተንትኖ ለስራ ክፍሉ በማቅረብ ገምግሞ ግብረመልስ መስጠት ፣**

## 13.5. ሰለምና ደህንነት

**ዓላማ :- በዞኑ አስተማማኝ ሠላምና የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ በ2022 ዜጎች ያለምን የፀጥታ ስጋት በልማትና በዲሞክረሲ ግንባታ ሥራዎች ላይ ተሳትፎቸው እንዲያድግና ፍጹም ስላማዊ ዞን እንዲሆን ማድረግ፡፡**

**ግብ 1:- የሰላም ባህል በመገንባት በዞኑ ውስጥና ከአጎራባች ክልልና ወረዳዎች መካከል ሊፈጠር የሚችለውን የግጭት ክስተት አሁን ካለበት 96.6% የመፍታት አቅም ወደ 100% ማሳደግ:**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- ግጭት ለመከላከል የሚያስችሉ በሠ/እሴትና ታያያዥ ጉዳዩች ዙሪያ ለተለያዩ

አደረጃጀቶች የሰላም አደረጃጀቶች አባላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠትና ማጠናከር፤

- የሰ/ምክር ቤቶችን/ማጠናከር ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ መከታተል፡
- በዞኑ ባሉ አዋሳኝ ክልል ፣ ዞንና ወረዳዎች የአመራር ለአመራር ግንኙነት በማድረግና ኮንፈረንስ በማካሄድ የሚፈጠሩ ግጭቶችን መቀነስና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት፡

**ግብ 2፡- በዞኑ በሃይማኖቶች መካከል በሰላም አብሮ የመኖር እሴትን በመገንባት የሃይማኖትን ጽንፈኝነት 95% መቀነስ፡፡**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- በየደረጃው የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ በማቋቋምና ነባር የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤን በማጠናከር፡፡
- ከመተዳደሪያ ደንባቸው ውጭ ሲንቀሳቀሱ የተገኙ የሐይማኖት ድርጅቶችና ማህበራትላ ይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ፣

**ግብ 3፡- የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት ተደራሺ በማድረግ የወንጀል ክስተቶች መቀነስ፡ ፡**

- የቀበሌ ኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ሽፋን አሁን ካለበት 67.99 ወደ 100 % ማደረስ፡፡
- የኮሚኒየቲ ፖሊሲንግ አፈፃፀም የጥራት ደረጃ አሁን ካለበት ከፍተኛ 38.6%፣ መካከለኛ 60.01%፣ ዝቅተኛ1.3% ወደ ከፍተኛ 90% እና መካከለኛ 10%ማድረስ፡
- ህገወጥ ኮንትሮባንድና የጦር መሣሪያ ዝውውርን አሁን ካለበት 90% መቆጣጠር፣

**ግብ 4፡- የወንጀል ምርመራ ስራችንን ተደራሽነት ፣ ጥራትና ቅልጥፍና በማሻሻል 95% ውጤታማ ማድረግ ፣**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- በሁሉም ወረዳ የፎረንሲክ ምርመራን በማስጀመር የወንጀል ምርመራ አገልግሎቱን 95% ተደራሽ ማድረግ ፣
- ዘመኑ ያፈራውን የቴክኖሎጅ ውጤቶች ውስጥ ዘመናዊ የወንጀል ምርመራ መቅረፀ ድምፅ መሳሪያዎችን በሁሉም ወረዳ እንዲሟሉ በማድረግ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የማጣራት አቅማችንን 95% ማሳደግ ፣

**ግብ 5፡- የመንገድ ትራፊክ ደህንነት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና ተደራሽነትን በማሳደግ በህይወትና ንብረት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት 40% መቀነስ፡**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- በዘመናዊ የቁጥጥር ማቴሪያሎች በመታገዝ በ2022 ዓ.ም በቁጥጥር ችግር የማደርሰ የትራፊክ አደጋዎች በ92% መቀነስ ፣
- ሞት የሚያስከትል አደጋን በ40% በትራፊክ አደጋ የሚሞቱ ሰዎችን በ50% መቀነስ፣
- በስትራቴጅክ እቅድ ዘመኑ መጨረሻ በእግረኞች በግንዛቤ እጥረት የሚያደርስ የትራፊክ አደጋ በ75% መቀነስ ፣

**ግብ.6፡-የመንግስትና የግል ታጣቂውን ወንጀል የመከላከል አቅም ማሳደግ፤**

**ግቡን ለማሳካት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለ11,139 የመንግስት ታጣቂዎች በተቋሙ ዓመታዊ ዕቅድ ትውውቅ እንዲሳተፉና ግልጸኝነት እንዲፈጠርላቸው ማድረግ፤
- ለ44,323 የግል ታጣቂዎች በተቋሙ ዓመታዊ ዕቅድ ትውውቅ እንዲሳተፉና ግልጸኝነት እንዲፈጠርላቸው ማድረግ፤

## 13.5. መንግስት ኮሙኒኬሽን

**ግብ 1. ስለ ዞናችን ሁለንተናዊ የገጽታ ግንባታና የጋራ መግባባት ዙሪያ የመረጃ አቅርቦትና ጥራትን ማሻሻል፣**

**ማስፈጸሚያ ስሌቶች፡**

ተግባር 1. በየዓመቱ ሁነቶችን በመፍጠር በሚገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለህዝቡ አስተማሪ የሆኑ 2944 **መልዕክቶችን** አዘጋጅቶ ለህብረተሰቡ ማስተላለፍ

ተግባር 2. የሚዲያ ሽፋን ለሚያስፈልጋቸው ዋና ዋና የዞኑ መንግስታዊ ጉዳዮች ለሚዲያ አካላት በተደራጀ ሁኔታ 2944 **የሚዲያ** ዘገባ ስራ ይሰራል፡፡

**ግብ 2፡- የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች አካታችነትን ማጎልበት**

**ማስፈጸሚያ ስሌቶች፡**

ተግባር 1. በዘርፉ የሚወጡ ዕቅዶች የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች (የሥርዓተ ፆታ፣ የወጣቶች፣ የኤ.ች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ የአረጋውያን፣ የህጻናት፣የስነ ህዝብ፣ የአካል ጉዳተኞች እና የአካባቢ ደህንነት ጉዳዮች) 100% ያካተቱ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል

ተግባር 2. የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች ከአፈጻጸም ሪፖርቶች ተሳታፊነትናተጠቃሚነታቸው በየሚመለከታቸው እቅድ አፈጻጸም ውስጥ መካተቱን በመከታተል በየሩብ ዓመቱ ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡ የሴቶች፣የወጣቶችና የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነት በዘርፉ በሚከናወኑ የአቅም ግንባታ ስራዎች (ሥልጠና እና ትምህርት)

ተግባር 3. በተዋረድ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመግታት፣ መከላከልና መቆጣጠርን መሰረት በማድረግ በየዓመቱ 1 ጊዜ የስራ ላይ ውይይት ማድረግ እና በተቋሙ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፈንድ ተጠቃሚ ለሆኑ ህፃናትም ድጋፍ ማድረግ፡፡

ተግባር 4. የወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ወጣቶችን በልማታዊ ቅኝት አስተሳሰባቸውን ለመቅረጽ የስራ ባህላቸውን ለማዳበር የተሳኩ ስራዎችን በማስተዋወቅ ጤናማና አምራች ወጣት ትውልድ በመቅረጽ ሚናቸውን እንዲወጡ ሊያደርጉ የሚችሉጉዳዮችን በኤሌክትሮኒክስና በህትመት ሚዲያ እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡ (በበራሪ ወረቀት፣ በማስተማሪያ ፕሮግራምና በዘገባ)

ተግባር 5. ዓለም አቀፍ ዓመታዊ የበዓላት ቀናቸውን አስመልክቶ (የሴቶች ቀን፣የአካል ጉዳተኞች ፣የኤ.ች.አይ.ቪ/ኤድስ፣የአረጋውያን ና የስነ ህዝብ ቀን.....) ምክንያት በማድረግ የምስልና የቴክስት ዜና ፣ መልእክት የመቅረጽ፣በበራሪ ወረቀት፣ ተሞክሮ መቀመር፣ ዘገባ መስራት እና ሌሎችንበማዘጋጀት ማስተላለፍ፣

ተግባር 7. በበጀት ዓመቱ የወጣቶችን የልማትና የእድገት ፓኬጅ አፈጻጸሞችን በተመለከተ የማስተዋወቅ ስራ ይሰራል፡፡ (በበራሪ ወረቀት፣ በማስተማሪያ ፕሮግራምና በዘገባ)

ተግባር 8 በወጣቶች ዘርፍ ወቅታዊና ጥራት ያለው መረጃ እንዲያገኙ የሚቻልበትን አግባብ እንዲፈጠር ይሰራል፡፡

ተግባር 9. በወጣቶች ዙሪያ በህብረተሰቡ ዘንድ ያለውን የተዛባ አመለካከት ለመቀየር የሚያስችሉ የግንዛቤ ስራዎችን በተለያዩ የህትመት ውጤቶችን በመጠቀም ይሰራል፡፡

ተግባር 10. ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር በወጣቶች በተለይም በሴቶች ላይ እያደረሰ ያለውን ችግር ለመከላከል የተለያዩ መድረኮችን/ ፓናሎችን/ ማዘጋጀት

ተግባር 11. በስነ ህዝብ ልማት ላይ (የስነ ህዝብና ልማት ትስስር፣ በቤተሰብ ምጣኔ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም፣በስነ ህዝብ መልካም አጋጣሚ እና ከገጠር

ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰት ዙሪያ) ያተኮረ **በማህበረሰብ ሬድዮና በሌሎች ህትመቶች ግንዛቤ የማስያዝ ስራ ይሰራል፡፡**

ተግባር 12. በቀጣይ 10 ዓመታት መንግሥት በአገር ደረጃ የሚያወጣቸውን ሁሉንም ያታ ተኮርና ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን መሰረት ያደረጉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች እንዲሁም ልዩ ልዩ አዋጆችና አለም አቀፍ ስምምነቶች በሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች አማካኝነት የአካባቢ ሚዲያዎች እንዲሁም በተለያዩ የሚዲያ አውትሮች ለሕብረተሰቡ ማድረስ፡፡

## *13. የመንግስት ወጭ አስተዳደር*

### 13.1. ገንዘብ መምሪያ

ዓላማ 1፦ የልማት ሀብት አቅርቦትን ማሳደግ

ግብ 1፦ የዞኑን ገቢ ማሳደግ

ግብ 2፦ የመንግስት፣የበየነ መንግስታት እና የሲቪክ ማህበራት ግንኙነትን ማጠናከር

ግብ 3፦ የቻናል አንድ የቻናል 2፣የቻናል 3 እና ሌሎች የውጭ ሀብት ግኝቶችን ውጤታማ የአሠራር ሥርዓት ማሻሻል

ዓላማ 3፦የሀብት አመዳደብ ውጤታማነት ማሻሻል

ግብ 1፦ የበጀት ማከፋፈያ ቀመር ማሻሻል/እንድሻሻል ማድረግ/ግብዓት የሚሆን መረጃ መስጠት

ግብ 2፦ የበየነ መንግስታትና ሲቪክ ማህበራትን ሀብት አጠቃቀም የክትትልና ግምገማ ሥራዓት ማጠናቀር

ዓላማ 4፦የመንግስት ፋይናንስ፣ግዥና ንብረት አስተዳደርን ማሻሻል

ግብ 1፦ የበጀት አስተዳደር ወደ ዘመናዊ የአሠራር ሥራዓት ማሻሻል

ግብ 2፦ የክፍያ፣ጥሬ ገንዘብና የሂሳብ አያያዝ ወደ ዘመናዊ አሠራር ሥራዓት ማሻሻል

ግብ 3፦ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥራዓት ማሻሻል

ግብ 4፡- የውስጥ ኦዲት አሠራር ወደ ዘመናዊ አሠራር ሥራዓት ማሻሻል

**ዓላማ 5፡-የክትትል፣የግምገማ፣የድጋፍ አሰጣጥና የተጠያቂነት አሠራር ማሻሻል**

ግብ 1- ከዞን እስከ ወረዳ ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ሥራዓት መዘርጋት

ግብ 2፡- የግምገማ ስራዓት በማጠናከር የተጠያቂነት አሰራር ማጕልበት

## 13.ገቢ አሰባሰብ

**ግብ 1፡- በባህሪና በስጋት የተለዩ የደረጃ ሀ እና ለ ግብር ከፋዮችን ግንዘቤያቸውን በማሳደግ የህግ ተገዥነታቸውን በ2012 ዓ.ም ከነበረው 54% ወደ 74% ማድረስ፣**

**ዋና ዋና ተግባራት፣**

- ግብር ከፋዩን በዘርፍና በባህሪያቸው በመለየት ራሱን የቻለ የማስተማሪያ ክፍልና ጊዜ እንዲሁም ማስተማሪያ ሰነድና አስተማሪ በመመደብ ማስተማርና 24% ህግ የማያከብሩትን ወደ 10% ማውረድ፣
- ህጋዊና ህገወጡን እየቀላቀለ የሚሄደውን ግብር ከፋይ የተሸለ ግብር ከፋይ እንዲሆን አልሞ መስራት፣

**ግብ 2. የደረጃ "ሀ" እና "ለ" የሂሳብ መዝገብ አቅራቢዎች ቁጥርን በ2012 ከነበረው 1027 (85%) በ2022 ወደ 1705 (95%) ማሳደግ፣**

**ዋና ዋና ተግባራት፡-**

- 1705 ግብር ከፋዮችን በሂሳብ አያያዝ መርህ ላይ ስልጠናና ትምህርት በመስጠት ግንዛቤያቸውን ማሳደግ፣

**ግብ 3፡- በጣት አሻራ የተደገፈ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መያዝ የሚገባቸውን ግብር ከፋዮች አሁን ካለው 97% በአስር አመቱ 100% ማድረስ**

**ዋና ዋና ተግባራት፡-**

- አዳዲስ ወደ ስርዓቱ ለሚገቡ 5,805 የንግድ ትርፍ ግብር ከፋዮች በጣት አሻራ የተደገፈ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርን መስጠት፣

- አዳዲስ ወደ ስርዓቱ ለሚገቡ ለ1000 የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎች የቫት ሰርተፍኬት አትሞ መስጠት፤
- ከንግድ ስርዓቱ ለሚወጡ ግብር ከፋዩች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርና የቫት ሰርተፍኬት ሙሉ በሙሉ እንዲመለስ/እንዲዘጋ ማድረግ፤

**ግብ 4፦ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ ግብር ከፋዮችን ቁጥር በ2012 ዓ.ም 563 በአስር አመቱ መጨረሻ ወደ 1705 እንዲያድግ ማድረግ፣**

**ዋናዋና ተግባራት፦**

- የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መጠቀም የሚገባቸውን 1705 ግብር ከፋዮች በዘርፍ በደረጃ በመለየት፣ ማደራጀትና ቅደም ተከተል በመስጠት መሳሪያውን እንዲገዙ ማድረግ፣

**ግብ 5፦ ለምርመራ የሚቀርቡ የታክስ ወንጀሎችን በብቃት በማጥራት ሽፋኑን በ2012 ከነበረው 100% በ2022 ወደ100%ማድረስናጥራቱን በ2012 ከነበረው 95% በ2022 ዓ.ም 98% ማድረስ፤**

**ዋና ዋናተግባራት፦**

- ለምርመራ የሚቀርቡ ክስና ጥቆማዎች መዝገቦችን ወንጀል መሆናቸውን 100% ማረጋገጥና ምርመራ እንዲጣራ ማድረግ፣

**ግብ 6፦ የታክስ ኦዲት ጥራት የማረጋገጥ ተግባር የሚከናውንባቸው ሂሳብ መዝገቦችን በመምረጫ መስፈርቱ መሠረት በመለየት በ2012 የተመረመረውን ሂሳብ መዝገቦች በ2022 ወደ 600 ሂሳብ መዝገቦች ማሳደግ፣**

**ዋና ዋና ተግባራት፦**

- የኦዲት ጥራትን ለማረጋገጥ በኦዲተሮች የተመረመሩ 600 ሂሳብ መዝገቦችን በመምርጫ መስፈርቱ መሠረት በስጋት ደረጃ መለየት፣

**ግብ 7፦ የዞኑን መደበኛ ገቢ አሁን ካለበት ብር 1,604,681,064 በአስር አመቱ ወደ ብር 4,604,681,064 ማድረስ፤**

**ዋና ዋና ተግባራት፦**

- ከአርሶአደሩ የገጠር መሬት መጠቀሚያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር እንዲሁም ከእርሻ ሥራ ባለሀብቶች መሰብሰብ የሚገባውን ብር 44,410,076 ገቢ በመሰብሰብ ከጠቅላላ ገቢው 0.96% ድርሻ እንዲኖረው ማድረግ፤
- ከተጨማሪ እሴት ታክስ 702,781,881 ብር ገቢ መሰብሰብና ከጠቅላላ ገቢው 15.2% ድርሻ እንዲኖረው ማድረግ፣
- ከተርን ኦቨር ታክስ 843,505,291 ብር በመሰብሰብ ከጠቅላላው ገቢ 18.5% ድርሻ እንዲኖረው ማድረግ፤

**ግብ 8፡- የዞኑን የከተማ አገልግሎት ገቢ አሁን ከአለበት 156,465,688 በአስር አመቱ መጨረሻ ወደ 562,460,835 ብር ማድረስ፣**

**ዋና ዋና ተግባራት፡-**

- ከማዘጋጃ ቤታዊ (ከከተሞች ህንጻ እና ቀሚ ንብረት ክፍያ) አሁን ያለውን 1,352,207 ብር በአስር አመት እቅድ ዘመኑ መጨረሻ 6,335,358 ሚሊዮን ብር በመሰብሰብ ከጠቅላላ ድርሻው 13.4% እንዲኖር ማድረግ፣
- ከማዘጋጃ ቤት ንብረቶች ኪራይ ገቢ አሁን ያለውን 6,070,939 ሚሊዮን ብር በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ 25,713,946 ብር በመሰብሰብ ከጠቅላላ ድርሻው 4.5% እንዲኖር ማድረግ፣
- ከኢንቨስትመንት (ከሊዝ) የቅድሚያ እና ዓመታዊ ክፍያ አሁን ያለውን 24,985,797 ብር በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ 43,516,479 ብር በመሰብሰብ ከጠቅላላ ድርሻው 7 % እንዲኖር ማድረግ፣
- ከማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ክፍያ የሚሰበሰበውን ገቢ አሁን ያለውን 45,532,623 ብር በ2022 224,068,073 ብር በመሰብሰብ ከጠቅላላ ድርሻው 39.8% እንዲኖር ማድረግ፣

## 14. የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

የ10 ዓመት የልማት ዕቅዱን በተሟላና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ መከታተልና መገምገም በየጊዜው የሚከሰቱ ተግዳሮቶችን በፍጥነት ለመለየትና አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት ከማስቻሉም በላይ በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን ይረዳል፡፡ በዚህ ረገድ በሀገር ደረጃ በተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች እንደታየው ባለፉት የዕቅድ ዘመናት ተግባራዊ ሲደረግ የነበረው የክትትልና ግምገማ አሠራር በሀገሪቱ ለተመዘገበው ልማት የራሱ አስተዋጽዖ ቢኖረውም በርካታ ድክመቶችም ነበሩበት፡፡ ከድክመቶች መካከል የዕቅድ ክትትልና ግምገማ ቅንጅት ደካማ መሆን፣ በተለያዩ ደረጃዎች የክትትልና ግምገማ አቅም ውስን መሆን፣ በክትትልና ግምገማ ዙሪያ የተዛባ አመለካከት መኖር፣ የክትትልና ግምገማ አሠራሩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አለመሆን፣ ከስኬት (outcome) ይልቅ ሂደትና ውጤት (process and output) ላይ ማተኮር እንዲሁም በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ግልጽነትና ተጠያቂነት በሚፈለገው ደረጃ ላይ ያለመድረስ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ውጤታማ የሆነ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ውጤቶችና ስኬቶች የሚለኩበት ግልጽና መለካት የሚችሉ ቁልፍ አመልካቾች (key performance indicators) ያስፈልጉታል፡፡ ይሄንንም ለማሳካት የፕላንና ልማት ከሁሉም አስፈፃሚ አካላት ጋር ውይይት በማድረግና እያንዳንዱ አስፈፃሚ አካል የራሱን ዘርፍ ቁልፍ አመልካቾች እንዲለይ በማድረግ ዞናዊ ቁልፍ የውጤት አመልካቾች አዘጋጅቷል፡፡ በመሆኑም የ10 ዓመት የልማት ዕቅዱ ውጤቶችና ስኬቶች የሚለኩት በእነዚህ አመልካቾች መሠረት ይሆናል፡፡

**የዕቅድ ትግበራ ዘመን አጋማሽ ግምገማ** (mid-term review)፦ ሌላው የክትትልና ግምገማ ዘዴ በዕቅድ ዘመኑ አጋማሽ ላይ የሚደረግ ግምገማ ነው፡፡ ዓላማውም በልማት ዕቅዱ የተቀመጡ መሠረታዊ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ዋና ዋና ግቦችና የማስፈጸም ኢላማዎች ምን ያህል እየተሳኩ እንደሆነ በዝርዝር ለመፈተሽና ለማረጋገጥ፣ አስፈላጊ ማስተካከያዎች ካሉም በአስተማማኝ መረጃዎች ላይ የተመሠረቱ የእርምት እርምጃዎችን ለመውሰድና በቀሪው የዕቅድ ዘመን የተሻለ አፈጻጸም ለማስመዝገብ እንዲረዳ ነው፡፡ በመሆኑም የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የመካከለኛ ዘመን ግምገማ የሚከናወን ይሆናል፡፡

**የዕቅድ ትግበራ ዘመን ማጠናቀቂያ ግምገማ** (final evaluation)፦ የዕቅድ ዘመን ማጠናቀቂያ ግምገማ በልማት ዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት ላይ የሚከናወን ግምገማ ሲሆን፣ ዓላማውም የልማት ዕቅዱ ግቦችና ኢላማዎች በዕቅዱ በተቀመጡ መሠረታዊ አቅጣጫዎችና የማስፈፀሚያ ስልቶች መሠረት መፈፀማቸውንና የዕቅዱ ዓላማዎች መሳካታቸውን ማረጋገጥ፣ መልካም ተሞክሮዎችንና

የአፈጻጸም ጉድለቶች ካሉ ከነምክንያቶቻቸው በመለየት በቂ ትንተናና ግምገማ ማካሄድና በቀጣይ መወሰድ ያለባቸውን አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የሚጠቁም ምክረ ሀሳብ ማቅረብ ነው፡፡

## 15. የክትትልና ግምገማ ማስፈጸሚያ ስልቶች

የክትትልና ግምገማ አሠራር፣ አደረጃጀትና የሰው ኃይል አቅም ማጠናከር፦ የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ፣ አሠራርና አደረጃጀቶችን አስመልክቶ በተለያዩ የመንግሥት አስተዳደር ዕርከኖችና የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት ሰፊ ክፍተቶች ይታይባቸዋል፡፡ በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ዘመን እነዚህን ክፍተቶች በማስወገድ የልማት ዕቅዱን አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ በጠንካራ አሠራርና አደረጃጀት እንዲሁም በአስፈላጊ የሰው ኃይል በመደገፍ የሚጠበቀውን ዓላማ ለማሳካት ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡ በልማት ሂደት ውስጥ አሠራርና አደረጃጀት ብቻቸውን የማስፈጸም አቅም ሊሆኑ አይችሉም፡፡ አሠራርና አደረጃጀት ጠንካራ የማስፈጸም አቅም ሊሆኑ የሚችሉት በተሟላ የሰው ኃይል ሲደገፉ ብቻ ነው፡፡ በልማት ሂደት ውስጥ ወሳኙ አቅም የተማረና የሠለጠነ የሰው ኃይል ነው፡፡ በመሆኑም ይህን የልማት ዕቅድ ውጤታማ ለማድረግና በሀገራችን የተጀመረውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ማህበራዊና የአካባቢ ልማት ለማስቀጠል፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ የዜጎችን የልማት እኩል ተሳታፊነትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው አግባብ የክትትልና ግምገማ የማስፈፀሚያ ስልቶች ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር በተለያዩ የመንግሥት የአስተዳደር እርከኖች በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ተመድበው የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ተግባራትን የሚያከናውኑ ባለሙያዎች ቀጣይነት ባላቸው የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎች እንዲታነፁ በማድረግ የሰው ኃይል አቅም በየደረጃው እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡

**በዓመታዊ ዕቅድና በጀት የተደገፈ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ፦** የልማት ዕቅዱን በተሟላ ሁኔታ በመከታተል፣ በመገምገምና በመደገፍ ውጤታማነቱን ማረጋገጥ በሁሉም የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት በባለቤትነት ተይዞ መፈጸም ያለበት ትልቅ ኃላፊነት ነው፡፡ በዚህም መሠረት የልማት ዕቅዱን የክትትልና ግምገማ ሜትሪክስ መሠረት ያደረገ፣ ቁልፍ የውጤት መስኮችን፣ ኢላማዎችንና ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾችን በግልጽ ለይቶ ያስቀመጠና በበጀት የተደገፈ ዓመታዊ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ዕቅድ ማዘጋጀት ይህንንም ተፈፃሚ ማድረግ ከእያንዳንዱ የመንግሥት አስፈፃሚ አካል የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

**በመስክ ጉብኝትና ምልከታ የታገዘ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ፦** የመስክ ጉብኝት ክትትልና ግምገማ ማለት የዕቅድ አፈጻጸም ደረጃን ለማረጋገጥ በተመረጡ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዙሪያ የሚዘጋጅ ጉብኝት ሆኖ ዓላማው በየጊዜው ከሚዘጋጁ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች በተጨማሪ በመስክ ምልከታ የአፈጻጸም ልዩነቶችን በማረጋገጥና የአፈጻጸም ክፍተቶች ካሉም የማስተካከያ እርምጃዎች በወቅቱ እንዲወሰዱ ማስቻል ነው፡፡ ይህም በዓመታዊ ዕቅድና የአፈጻጸም መርሐ ግብር የሚከናወን ይሆናል፡፡ የመስክ ጉብኝቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ከማመንጨት በተጨማሪ በአንድ የመረጃ ምንጭ ወይም በሪፖርት ላይ ከመወሰን ይልቅ የመረጃ ምንጮችን ማስፋትና የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመስክ ከተገኘው መረጃ ጋር ለማመሳካር (triangulation) ጠቃሚ በመሆኑ ነው፡፡

**ዓመታዊ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሪፖርቱን በባለድርሻ አካላት ማስገምገም፦** ይህ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈንና ለማጠናከር እንዲሁም በህብረተሰቡ ዘንድ የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር ከማድረግ አንጻር ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

**ለክትትልና ግምገማ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት መገንባት፦** የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት በሕግ ከተሰጧቸው ኃላፊነቶች ጋር በተገናኘ ለልማት ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ የሚያግዙ መረጃዎችን ያመነጫሉ፡፡ የእነዚህ መረጃዎች አያያዝ፣ አደረጃጀትና ሥርጭት ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓትን የተከተለና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ ሊሆን ይገባል፡፡ ነገር ግን ከተወሰኑ የመንግሥት አስፈፃሚ ተቋማት በስተቀር የአብዛኛዎቹ አሠራሮች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዙ አይደሉም፡፡ በመሆኑም የአስፈፃሚ አካላት የልማት ዕቅድ አፈጻጸም የክትትልና ግምገማ አቅም በዘመናዊ መልኩ የተደራጀና የተቀናጀ የመረጃ ማኔጅመንት ሥርዓት ሊጠናከር ይገባል፡፡ በተጨማሪም መረጃዎቹን ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ማኔጅመንት ሥርዓት (management information system) በመዘርጋትና ሶፍትዌሮችን በማልማት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡ የዘርፍ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች የልማት ዕቅድና የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ የመረጃ ቋቶች ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የመረጃ ቋት ጋር የሚተሳሰሩበትን ሥርዓት በመፍጠር የመረጃ ፍሰትን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከልማት አጋሮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ሪፖርት አቀራረብ (performance tracking and reporting) በቴክኖሎጂና ሶፍትዌር እንዲደገፍ ይደረጋል፡፡

**የዕቅድ አፈጻጸም ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማጎልበት፦** የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ዓላማ የመንግሥት አስፈፃሚ አካላትን የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ማሻሻልና በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህም በዕቅድ አፈጻጸም የሚታዩ ድክመቶች መንስዔያቸው ምን እንደሆነ ከመለየት ጀምሮ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማመላከትንና ተግባራዊ መሆናቸውን መከታተልን ይጠይቃል፡፡ ከላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአስፈፃሚ አካላት የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ደካማነት ከተቋሞቹ የበላይ ኃላፊዎች የሥነ ምግባር ችግር፣ የባለቤትነትና የቁርጠኝነት ጉድለት፣ የሕዝብ ጥቅምን ያለማስቀደምና የአቅም ማነስ ችግር ጋር የተያያዘ ከሆነ በየደረጃው የተቀመጡ የልማት ግቦችና ኢላማዎችን ለማሳካት የሚደረገውን የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ድጋፍ ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የሕዝብ ጥቅም አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል፡፡ ተገልጋዩ ሕዝብም በመንግሥት ላይ ያለው እምነት እየተሸረሸረ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡ ይህም በሂደት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ሊያስከትል ይችላል፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ማህበራዊ ቀውሶች ሁሉ በዋናነት የተጠያቂነት ሥርዓቱ ደካማ ከመሆኑ የተነሳ የሚመነጩ ናቸው፡፡ በመሆኑም የአስፈፃሚ ተቋማትንና ተቋማቱን የሚመሩ የበላይ ኃላፊዎችን የሥራ አፈጻጸም በተሟላ ሁኔታ በየጊዜው በመገምገምና የአፈጻጸም ደረጃ በመስጠት ተጠያቂ የሚሆኑበት ሥርዓት የሚዘረጋ ሲሆን፣ ይህንንም ለዜጎች ለማሳወቅና ይፋ ለማድረግ ከሚዲያዎች ጋር የሚሰራ ይሆናል፡፡